# የኢትዮጵያ የኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጂ

**(ረቂቅ)**

**ኅዳር 2010**

**አዲስ አበባ**

**መውጫ**


መቅድም (Executive summery) .......... v

መግቢያ .......... 1

የዓለም አቀፍ የኅብረት ሥራ ነባራዊ ሁኔታ .......... 2

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ነባራዊ ሁኔታ፡- .......... 9

ክፍል አንድ፡- የኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጂ መሠረታዊ ዓላማዎች፣ መርሆዎችና አስፈላጊነት .......... 16

1.1. ኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጂው ዓላማ .......... 16

1.2. ኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጂ መርሆዎች (guiding principles) .......... 17

1.3. ለስትራቴጂው መነሻ ምክንያቶች .......... 19

1.4. ኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጂ አስፈላጊነት .......... 19

1.5. ኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጂው ተፈፃሚነት ወሰን .......... 21

1.6. ኅብረት ሥራ ሴክተር ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች ፣ .......... 22

1.7. የኅብረት ሥራ ትርጉም፣ መርሆ፣ ዕሴቶች፣ .......... 22

ክፍል ሁለት፡- የኅብረት ሥራ ሴክተር ነባራዊ ሁኔታዎች .......... 24

2.1. የነባራዊ ሁኔታዎች ትንተና .......... 24

2.2. የኅብረት ሥራ ሴክተር ውስጣዊና ውጫዊ ትንተና (ጥ.ድ.መ.ሰ)፡ .......... 24

ክፍል ሦስት፡-የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀትና አወቃቀር የምንከተለው ስትራቴጂ .......... 29

አምድ1፡- በአገራችን የሶሺዮ-ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት .......... 30

አምድ 2፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሥራ ግንኙነት ማጠናከር፣ .......... 48

አምድ 3፡- ጠንከራ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ሊግ መፍጠር፣ .......... 53

ክፍል አራት፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የማጠናከር፣ መፈፀምና የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራቴጂ .......... 57

አምድ 4፡- የአገራችን የልማት አቅጣጫና የኅብረት ሥራ ማህበራት ትኩረት .......... 58

አምድ 5፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ጠንካራ አመራርና አስተዳደር ስርዓት መገንባት የአባላትን ባለቤትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣ .......... 62

አምድ 6፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የአሰራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን ማጠናከር፣ .......... 73

አምድ 7፡- የኅብረት ሥራ ምርታማነት ማሳደግ ኤክስቴንሽን ስርፀትና የኢንዱስትሪ ግንኙነትን ማስፋፋት፣ .......... 76

አምድ 8 ፡- የኅብረት ሥራ ሴክተር የትምህርት፣ የሥልጠና እና የጥናትና ምርምር ሥርዓት፣ .......... 82

አምድ 9፡- በኅብረት ሥራ አቅም ግንባታ የኅብረት ሥራ ማህበራት እና የሌሎች አካላት ሚና፡- .......... 89

ክፍል አምስት፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ግብይት ስርዓትን ማጠናከር......94

ዓምድ 10፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብዓት ግብይትን ማጠናከር፣......95

ዓምድ 11፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሀገር ውስጥ ግብይትን ማጠናከር፣......98

ዓምድ 12፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የውጭ ግብይት ማጠናከር......108

ዓምድ 13፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የገበያ ጥናት እና መረጃን ማጠናከር......113

ዓምድ 14፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት ምርቶችና አገልግሎት ላይ ዕሴት መጨመር፤......115

ዓምድ 15፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት የሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥን ማጠናከር፡-......119

ዓምድ 16፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት ምርት እና አገልግሎት ግብይት የቅብብሎሽ ሰንሰለት ማሳጠር፤......122

አምድ 17፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን መሠረተ ልማት ማስፋፋት፣......125

ዓምድ 18፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት የስራ እድል ፈጣራን ማጠናከር፣......127

ክፍል ስድስት፡-የኅብረት ሥራ የመረጃ ስርዓትን የማጠናከር ስትራቴጅ......130

ዓምድ 19፡- የኅብረት ሥራ የመረጃ ስርዓትን ማጠናከር......130

ክፍል ሰባት፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ፋይናንስ ስርዓት እና ተደራሽነትን ማጠናከር......134

የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት እና አስተዳደርን ማጠናከር፣......134

አምድ 20፡- የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትና አስተዳደር ፣......136

ዓምድ 21፡- ኅብረት ሥራ ባንክ እና ኢንሹራንስ አደረጃጀትና አስተዳደር ኅብረት ሥራ ባንክ አደረጃጀትና አስተዳደር፡-......145

አምድ 22፡- የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የቁጥጥር እና አሰራር ስርዓት......151

አምድ 23፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አቅም ማጠናከር......158

አምድ 24፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የሀብት አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል፣......170

ክፍል ስምንት፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ሬጉላቶር፣ ኦዲት እና ኢንስፔክሽን......176

ዓምድ 25፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ሬጉላቶር ማጠናከር......176

ክፍል ዘጠኝ፡- የኅብረት ሥራ ሴክተር እና ሌሎች አካላት ድጋፍና ሚና፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ማህበራዊ አስታወጽዖ እና ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ተሳትፎ......186

የስትራቴጂው የማስፈጸሚያ ስልቶች እና ክትትልና ግምገማ ስርዓት......194

1. የማስፈጸሚያ ስልቶች፡-......194

2. ክትትልና ግምገማ ስርዓት፡-......197

ማጣቀሻዎች......198

# ሰንጠረዦች

ሰንጠረዥ 1፡ ውስጣዊ ሁኔታዎች ትንተና ........................................ 25
ሰንጠረዥ 2፡ ውጫዊ ሁኔታዎች ........................................ 27
ሰንጠረዥ 3፡ የዕምበባ ሓያ የገጠር ገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃላ/የተ የኅብረት ሥራ ማህበር በሞደልነት የተወሰደ (BENCH MARK) ........................................ 64
ሰንጠረዥ 4፡ ጨርጨር ኦዳ ቡልቱም ኃ.የተ ሁለገብ የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ዩኒዬን በሞደልነት የተወሰደ (BENCH MARK) ........................................ 77
ሰንጠረዥ 5፡ የወረርባ ኃ. የተ መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በሞደልነት የተወሰደ (BENCH MARK) ........................................ 137
ሰንጠረዥ 6፡ ሦሥር ኃ.የተወ. የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን በሞደልነት የተወሰደ (BENCH MARK) ........................................ 161
ሰንጠረዥ 7፡ ኢጋር የሸማቾች መሠረታዊ እና ምዕራብ የሸማቾች የኅብረት ሥራ ዩኒየን በሞደልነት የተወሰደ (BENCH MARK) ........................................ 101
ሰንጠረዥ 8፡ የኦሮሚያ የቡና አብቃይ እና የፀሐይ ኃላ.የተ ሁለገብ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ዩኒየን በሞደልነት የተወሰዱ (BENCH MARK) ........................................ 110
ሰንጠረዥ 9፡ ወደራ እና ራያ ዋከና ኃ.የተ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበር ዩኒየን በሞደልነት የተወሰዱ (BENCH MARK) ........................................ 116
ሰንጠረዥ 10፡ የነጻነት ፋና የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ ኅብረት ሥራ ዩኒየን በሞደልነት የተወሰዱ (BENCH MARK) ........................................ 128
ሰንጠረዥ 11፡ የፌሮና አከባቢው መሠረታዊ እና የኦሮሚያ የቡና አብቃይ ኃ.የተ ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒዬን ተሞክሮ በሞደልነት የተወሰዱ (BENCH MARK)........................................ **ERROR! BOOKMARK NOT DEFINED.**

DRAFT

## ቻርቶች

የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የክልል ስርጭት........ 9
የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት........ 10
አጠቃላይ አገራዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት በጾታ በሚከተለው ግራፍ ላይ ቀርቧል፡-........ 10
የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ካፒታል መጠን........ 10
የመሠረታዊ እና ዩኒዬን ኅብረት ሥራ ማህበራት ካፒታል........ 11
የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች እና አባላት ብዛት........ 12
የምርት ማሳደጊያ ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት........ 12
የአገር ውስጥ እና የውጭ የሰብል ምርት ግብይት........ 13
በግብርና ምርት ላይ እሴት ጭማሪ........ 14
የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የካፒታል፣ ቁጠባና ብድር ሁኔታ........ 15

# መቅድም (Executive summery)

አገራችን የምትከተለው የኢኮኖሚ ስርዓት ግብርና መር ኢንዱስትሪ እንደመሆኑ መጠን ባሳለፍናቸው ዓመታት ግብርና የሀገራችን ኢኮኖሚ ዋልታ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ባለፉት 13 ዓመታት የአገራችን ኢኮኖሚ በአማካይ በለሁለት አሃዝ እድገት እያስመዘገበ መጥቷል፡፡ የኢኮኖሚ እድገቱ በአገሪቱ የተረጋጋ ማክሮ-ኢኮኖሚ እንዲፈጠርና የነፍስ ወከፍ ገቢ እንዲያድግ ከማስቻሉም በላይ የነበረውን የዋጋ ግሽበት በመቀነስ ወደ አንድ አሀዝ እንዲወርድ በማድረግ ለዜጎች የስራ ዕድል በመፈጠሩ የገቢ ምንጫቸው እንዲያድግና ድህነት እንድቀንስ አስችሏል፡፡ ለእነዚህ ስኬቶች መመዝገብ ዋናኛው የተቀየሱት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ውጤታማ በመሆናቸው ነው፡፡

የተመዘገበውን ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በማስቀጠል ድህነትንና ኋላቀርነትን በማስወገድ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ፣ ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት ሕብረተሰቡን ፊትሃዊ ተጠቃሚ ለማድረግ፣ በኢኮኖሚ ትስስር ውስጥ ያላውን ድርሻ ለማሳደግ እና ያለውን ፈጣን እድገት እና ጠንካራ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መገንባትን እውን ለማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጉልህ ድርሻ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚታይባቸው የክህሎት፣ የአመለካከትና የግብዓት ችግሮችን በመፍታት የመፈጸም እና የማስፈጸም አቅማቸውን በማሳደግ አመራራቸውን፣ አሠራራቸው እና የአገልግሎት አሰጣጣቸውን በማጠናከር የተቀመጠውን አቅጣጫ በአግባቡ መፈጸም እንዲችሉ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ በዚህም መሠረት በአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ባለቤትነት፣ ተቆጣጣሪነት እና ፍትሃዊ ኢኮኖሚያው እና ማህበራዊ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ የተጀመረውን መልክም ተሞክሮ አጠናክሮ በማስቀጠል ለአገር ኢኮኖሚ እድገት የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማስቻል ሁሉአቀፍ የኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጅ ማዘጋጀት ተገቢ ይሆናል፡፡

በመሆኑም የተቀመጡ አቅጣጫዎችን በአግባቡ ለመተግበር እንዲቻል በሚቀጥሉት 15 ዓመታት (ከ2011 እስከ 2025 ዓ.ም) ውስጥ በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚተገበሩ ዋና ዋና ጉዳዮችን በመለየት፣ ለተግባራዊነቱ እንቅፋት የሆኑ ዋና ዋና ማነቆ እና የሚፈታበትን አቅጣጫ ተመላክቷል፡፡

**የተለዩ አምዶች፣ የሚታዩ ዋና ዋና ማነቆዎች እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች፡-**

**አምድ1፡-** በአገራችን የማህበራዊ-ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች 1) የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጭነት ባለው መልኩ አለመደራጀት፣ 2) ኅብረት ሥራ ማህበራትን ያለ በቂ ግንዛቤና ፈቃደኝነት ማደራጀት እና በኅብረት ሥራ ማህበራት እና በአባላት መካከል የተጠናከረ ግንኙነት አለመኖር፣ 3) የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትና አመዘጋገብ አሰራር ወጥነት የሌለው መሆን 4) በሀገራችን

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁባቸው ግልጽና አዋጭ የሆኑ የስራ መስኮች በበቂ ሁኔታ መለየት አለመቻል፣ 5) ግልጽና ወጥ የሆነ የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ዓይነትና ስያሜ አለመኖር፣ 6) የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴ የሚመራ ጠንካራ አደረጃጀት አለመኖር እና 7) ለኅብረት ሥራ ማህበራት ግልፅ መብትና ግዴታ፣ተግባርና ሃላፊነት አለመኖር ናቸው፡፡

**አምድ 2፡-** የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሥራ ግንኙነት ማጠናከር በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች 1) የጋራ ተጠቃሚነትን ያረጋገጠና ግልጽ የሆነ ግንኙነት አለመኖር እና 2) በኅብረት ሥራ ማህበራት እና አባላት መካከል የተቀናጀ ግንኙነት አሰራር አለመኖር ናቸው፡፡

**አምድ 3፡- ጠንከራ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ሊግ መፍጠር** በተመለከተ የተለየ ማነቆ የሀገሪቱን ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚወክል የኅብረት ሥራ አካል አለመኖር ነው፡፡

**አምድ 4፡- የአገራችን የልማት አቅጣጫና የኅብረት ሥራ ማህበራት ትኩረት** በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች 1) የገጠርና የከተማ ኅብረት ሥራ ማህበራት የትስስር ስርዓት አለመጠናከር፣ 2) ኅብረት ሥራ ማህበራት የድህነት ቅነሳ እና የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ ወሳኝ ተቋማት ስለመሆናቸው በቂ ግንዛቤና አመለካከት አለመዳበር እና 3) የኅብረት ሥራ ማህበራትን በመከፈል ወይም በመዋሃድ መልሶ አለማጠናከር ናቸው፡፡

**አምድ 5፡-** የኅብረት ሥራ ማህበራት ጠንካራ አመራርና አስተዳደር ስርዓት መገንባት የአባላትን ባለቤትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች 1) ጠንካራ የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራርና አስተዳደር አለመኖር፣ 2) በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ጠንካራ የመልካም አስተዳደር አለመስፈን፣ 3) የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት፣ አመራር አካላትና ቅጥር ሠራተኞች የሚጠበቅባቸውን ግዴታ አለመወጣት፣ 4) የአባላት ባለቤትነት፣ ውሳኔ ሰጭነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት በሚፈለገው ደረጃ አለመረጋገጥ፣ 5) የኅብረት ስራ ማህበራት በተግባርና ባህሪያቸው ግንባር ቀደም በሆኑ አመራሮች አለመመራት እና 6) የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሮቻቸውን በሰለጠነ የሰው ኃይል አለመምራት ናቸው፡፡

**አምድ 6፡-** የኅብረት ሥራ ማህበራት የአሰራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን ማጠናከር በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች 1) ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት የሚመጥን የአሰራር ስርዓት እና አገልግሎት አሰጣጥ አለመጠናከር እና 2) በኅብረት ሥራ ማህበራት ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለይቶና ቀምሮ ማስፋት አለመቻል ናቸው፡፡

**አምድ 7፡-** የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን ስርፀትና የኢንዱስትሪ ግንኙነትን ማስፋፋት በተመለከተ የተለየው ማነቆ ጠንካራና ውጤታማ የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን ስርፀትና የኢንዱስትሪ ግንኙነት ስርዓት አለመኖር የሚል ነው፡፡

**አምድ 8፡-** የኅብረት ሥራ ሴክተር የትምህርት፣ የሥልጠና እና የጥናትና ምርምር ሥርዓት በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች 1) ጠንካራ የኅብረት ሥራ የትምህርትና ሥልጠና ስርዓተ ትምህርት እና አሰራር አለመኖር፣ 2) የተቀናጀ የኅብረት ሥራ የልህቀት ማዕከል አለመኖር፣ 3) የኅብረት ሥራ ሴክተር ግልፅ የጥናትና ምርምር አሰራር አለመኖር እና 4) የኅብረት ሥራ ሴክተር፣ የትምህርትና ስልጠና እና የጥናትና ምርምር ተቋማት ጠንካራ ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር ናቸው፡፡

**አምድ 9፡-** በኅብረት ሥራ አቅም ግንባታ የኅብረት ሥራ ማህበራት እና የሌሎች አካላት ሚና በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች መካከል 1) የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአቅም ግንባታ ትኩረት ሰጥቶ በአሰራር፣ በባለቤትነት እና በቅንጅት አለመስራት፣ 2) በመንግስት ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡ ስልጠናዎች አሰራር የተዘጋላቸው፣ ችግር ፈቺ እና ተደራሽ አለመሆን፣ 3) ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚመሩባቸው የአቅም ግንባታ አሰራር ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ አለመዘርጋት፣ 4) በአቅም ገንቢዎች ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡ ስልጠናዎች ቀጣይነት የሌላቸው፣ ራስን የማያስችሉ መሆን እና 5) በባለድርሻ አካላት የሚደረጉ የአቅም ግንባታ ስራዎች የተቀናጀና ችግር ፈቺ አለመሆን የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

**ዓምድ 10፡-** የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብዓት ግብይትን ማጠናከር በተመለከተ የተለየው ማነቆ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሚፈልጓቸውን ግብዓቶች በማቀድ በሚፈለገው መጠን፣ ጥራት፣ እና ጊዜ ማቅረብ አለመቻል ነው፡፡

**ዓምድ 11፡-** የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሀገር ውስጥ ግብይትን ማጠናከር በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች መካከል 1) የኅብረት ሥራ ማህበራት የሀገር ውስጥ የግብርና ምርት ግብይት የመጠን፣ የጥራት፣ ወቅታዊነት እና የአሰራር ችግር፣ 2) የኅብረት ሥራ ማህበራትን የምርት ግብይት ተግባር የሚያሳልጥ መሰረተ ልማት አለመጠናከር፣ 3) የኅብረት ሥራ ማህበራት ከግብርና ምርቶች ውጭ ባሉት ምርቶች ግብይት ላይ ያላቸው ተሳትፎ አናሳ መሆን እና 4) የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሚፈልጓቸውን የፍጆታ ምርቶችን በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት እና በጊዜ ማቅረብ አለመቻል ናቸው፡፡

**ዓምድ 12፡-** የኅብረት ሥራ ማህበራት የውጭ ግብይት ማጠናከር በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች መካከል 1) የኅብረት ሥራ ማህበራት በውጭ ገበያ የሚፈለጉ ምርቶችን በብዛት ፣ በጥራትና በወቅቱ ማቅረብ አለመቻል እና 2) የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችንና የፍጆታ ምርቶችን ከውጭ በጅምላ ለማስገባት የሚያስችል ግልጽ አሰራር አለመኖር ናቸው፡፡

**ዓምድ 13፡-** የኀብረት ሥራ ማህበራት የገበያ ጥናትን ማጠናከር በተመለከተ የተለየው ማነቆ የኀብረት ሥራ ማህበራት ጥናትን መሰረት ያደረገ ግብይት አለማካሄድ ነው፡፡

**ዓምድ 14፡-** በኀብረት ሥራ ማህበራት ምርቶችና አገልግሎት ላይ ዕሴት መጨመር በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች መካከል 1) የኀብረት ሥራ ማህበራት የእሴት መጨመር ተግባራትን በጥናት በመለየት በስፋት መግባት አለመቻል እና 2) የኀብረት ሥራ ማህበራት የሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት አለመስፋፋት ናቸው፡፡

ዓምድ 15፡- በኀብረት ሥራ ማህበራት የሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥን ለማጠናከር የተለየው ማነቆ የኀብረት ሥራ ማህበራት የሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት አለመስፋፋት ነው፡፡

**ዓምድ 16፡-** በኀብረት ሥራ ማህበራት ምርት እና አገልግሎት ግብይት የቅብብሎሽ ሰንሰለት ማሳጠር በተመለከተ የተለየው ማነቆ የኀብረት ሥራ ማህበራት የምርትና አገልግሎት ግብይት ቅብብሎሽ እሴት የማይጨምርና የተንዛዛ መሆን ነው፡፡

**አምድ 17፡-** የኀብረት ሥራ ማህበራትን መሠረተ ልማት ማስፋፋት በተመለከተ የተለየው ማነቆ የኀብረት ሥራ ማህበራት መሰረተ ልማት አለመስፋፋት እና ጠንካራ የመረጃ ስርዓት አለመዘርጋት የሚል ነው፡፡

**ዓምድ 18፡-** በኀብረት ሥራ ማህበራት የስራ እድል ፈጣራን ማጠናከር በተመለከተ የተለየው ማነቆ የኀብረት ሥራ ማህበራት በስራ እድል ፈጠራ ላይ ግልጽና በቂ ግንዛቤ አለመኖር ነው፡፡

**ዓምድ 19፡-** የኀብረት ሥራ የመረጃ ስርዓትን ማጠናከር በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች መካከል 1) የተቀናጀና ዘመናዊ የኀብረት ሥራ መረጃ ስርዓት አለመኖር እና 2) የተቀናጀ የኀብረት ሥራ ማህበራት የገበያ መረጃ ስርዓት አለመኖር ናቸው፡፡

**አምድ 20፡-** የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኀብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትና አስተዳደር በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች መካከል 1) የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኀብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ጠንካራና ወጥ አለመሆን፣ 2) የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኀብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎት አለመስፋፋት እና 3) የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኀብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አስተዳደር የሚያግዙ ዘመናዊ አሰራር ስርዓቶች አለመዘርጋት፣ የክህሎትና የእውቀት ችግር መኖር የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

**ዓምድ 21፡-** ኀብረት ሥራ ባንክ እና ኢንሹራንስ አደረጃጀትና አስተዳደር ኀብረት ሥራ ባንክ አደረጃጀትና አስተዳደር በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች መካከል 1) የኀብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ ችግር ሊፈታ የሚችል የኀብረት ሥራ ባንክ አለመደራጀት እና 2) የኀብረት ሥራ ኢንሹራንስ አለመደራጀት ናቸው፡፡

**አምድ 22፡-** የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የቁጥጥር እና አሰራር ስርዓት በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች መካከል 1) ጠንካራ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖር፣ 2) ጠንካራና ሊያሰራ የሚችል የፋይናንስ የአሠራር ሥርዓት አለመዘርጋት ናቸው፡፡

**አምድ 23፡-** የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አቅም ማጠናከር በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች መካከል 1) አማራጭ የውስጥ የፋይናንስ አቅም አሟጦ አለመጠቀም፣ 2) የቁጠባ ባህልን ለማሳደግ ጠንካራ የፋይናንስ ክህሎት ማበልጸጊያ ሥርዓት አለመገንባት፣ 3) የፋይናንስ አገልግሎቶች አለመስፋፋት፣ 4) የኅብረት ሥራ ማህበራትን የርስ በርስ የፋይናንስ ግብይት ትስስር አሠራር ሥርዓት አለመዘርጋት፣ 5) የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚያደርጉት የፋይናንስ ግብይት ትስስርና ግንኙነት የተጠናከረ አለመሆን፣ 6) መንግስትና አቅም ገንቢ አካላት ለኅብረት ሥራ ማህበራት በቂ የፋይናንስ ድጋፍ አለማድረግ እና 7) ለኅብረት ሥራ ማህበራትን ግብይት የሚያግዝ የፋይናንስ አቅርቦት አለመኖር ናቸው፡፡

**አምድ 24፡-** የኅብረት ሥራ ማህበራት የሀብት አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች መካከል 1) ኅብረት ሥራ ማህበራት የመጠባበቂያ ሂሳብ፣ የማይከፋፈሉ የወል ንብረቶች እና ተካባች ሂሳቦች አጠቃቀምና አስተዳደር አሰራር አለመዘርጋት፣ 2) የኅብረት ሥራ ፈንድ አደረጃጀት፣ አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዓት አለመዘርጋት፣ 3) ጠንካራ የኅብረት ሥራ ማህበራት የንብረት አያያዝ አስተዳደር ስርዓት አለመኖር እና 4) በኅብረት ሥራ ማህበራት የንብረት እና የሀብት ብክነት መኖር ናቸው፡፡

**ዓምድ 25፡-** የኅብረት ሥራ ማህበራት ሬጉላቶር ማጠናከር በተመለከተ የተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች መካከል 1) የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት ተደራሽ አለመሆን፣ 2) የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት ጥራት ችግር መኖር፣ 3) የኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥጥር ደካማ መሆን፣ 4) በኅብረት ሥራ ማህበራት የሀብት ብክነት መኖር እና 5) የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ ተደራሽ አለመሆን ናቸው፡፡

በተጨማሪም የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማህበራዊ አስተዋጽኦ እና ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ተሳትፎ ማሻሻል እና የኅብረት ሥራ ሴክተር እና ሌሎች አካላት የግንኙነት ሥርዓት ማጠናከርን በትኩረት ተተንትኗል፡፡

**ከስትራቴጅው የሚጠበቁ ዋና ዋና ውጤቶች መካከል፡-**

የተለዩ ማነቆዎችን በመፍታት በስትራቴጅው የተቀመጡ ዝርዝር ውጤቶችን ለማምጣት መንግስት፣ አቅም ገንቢዎች፣ ባለድርሻ አካላት እና የኅብረት ሥራ ማህበራት አስፈላጊውን ሃብት፣ እውቀት እና ክህሎት በማሰባሰብ እና በመቀናጀት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በዚህም መሠረት በ2025 ዓ.ም የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባለት እድገት በገጠር አርሶ/አርብቶ አደር 85 በመቶ እና በከተማ 75 በመቶ ይደረሳል፡፡ ካሉት የኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ 80 በመቶ የሚሆኑት ተጠናክረው በላቀ ደረጃ የሚፈለገውን አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በአገር አቀፍ ደረጃ የሚወክል አካል ተቋቁሞ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በመወከል አገር አቀፍ እና አለም ግንኙነቶችን በማድረግ ይደግፋል፡፡ በገጠር የሚገኙ የግብርና ኅብረት ሥራ ማህበራት የኅብረት ሥራ፣ የግብርና እና ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት 100 በመቶ ለአባለት ይሰጣሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ትምህርት፣ ስልጠና እና ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ 12 የልህቀት ማዕከላት ተገንብቶ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚያስፈልጋቸው መሠረተ ልማቶች ውስጥ 90 በመቶ ይሟላል፡፡

ከአጠቃላይ የአገርቱ ከሚሰበሰበው የቁጠባ መጠን ውስጥ በፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ 25 በመቶ ይሆናል፡፡ የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባለት የሚየቀርቡት የብድር አገልግሎት ድርሻ 90 በመቶ ይሆናል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአገር ውስጥ የግብርና ምርቶች ግብይት ድርሻ 70 በመቶ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ የውጭ ግብይት (ማለትም በቡና፣ በሰሊጥ፣ የቅባት እህሎች፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ እንስሳት እና እንስሳት ተዋጽኦ፣ ቅመማ ቅመም እና ሌሎች) ድርሻ 65 ከመቶ ይደርሳል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት ለገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶ 100 በመቶ እሴት የተጨመረበት ይሆናል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጠው የግብርና ሜካናይዘሽን አቅርቦት እና አገልግሎት 50 በመቶ ይሆናል፡፡ እንዲሁም ከቀላል እስከ ከባድ የኢንዱስትሪ ግንባታ ካሉት የግብርና ኅብረት ሥራ ማበህራት ውስጥ 60 በመቶ ገንብቶ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ በአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች 60 ትላልቅ የገበያ ማዕከላት ተገንብቶ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ በተጨማሪም በ80 ከተሞች የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት መረጃ ማዕከላት ተቋቁሞ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ በሚቀጥሉት 15 ዓመታት ውስጥ በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ ለ20 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት ሽፋን፣ የኢንስፔክሽን አገልግሎት ሽፋን እና የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ማረጋገጫ እውቅና የአገልግሎት አሰጣጥ 100 በመቶ እንዲሆንና የኅብረት ሥራ ማህበራት ሃብትና ንብረት ሙሉ

በሙሉ ከምዝበራ እና ብክነት የጸዳ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ በሚቀጥለው 15 ዓመታት ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ በአገር ኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት ውስጥ የላቀ ድርሻቸውን ይወጣሉ፡፡

**የማስፈጸሚያ ስልቶች፡**

ስትራቴጅውን ለማስፈጸም የኅብረት ሥራ ሴክተር ልማታዊ ኮሚዩኒኬሽን እና የሕዝብ ግንኙነት አሰራርን በማጠናከር፣ በየደረጃው የሚገኙ ቁልፍ ፈጻሚ፣ አስፈጻሚ እና ባለድርሻ አካላት የሚኖራቸው ተግባር እና ኃላፊነት በግልጽ ተመላክቷል፡፡ በስትራቴጅው የተለዩ ዋና ዋና የኅብረት ሥራ ሴክተር ማነቆዎችን ለመቅረፍ እና የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ እንዲቻል በየደረጃው የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት፣ ባለድርሻ አካላት፣ አቅም ገንቢዎች እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ተቀናጅተው እና ትኩረት ሰጥቶ ተግባርና ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ፡፡

የተቀመጡ ዝርዝር ስትራቴጅያዊ የመፍትሄ ሃሳቦች በአንድ ጊዜ የሚተገበሩ ሳይሆን በሚቀጥለው 15 ዓመታት ውስጥ በተቀመጠው መሰረት በየምዕራፉ ተከፋፍሎ የሚተገበር ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረት በየምዕራፎቹ የሚተገበሩ ዋና ዋና ተግባራት እርስ በርሳቸው የሚመጋገቡ በመሆናቸው ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት በየቅደም ተከተላቸው እንዲከናወኑ በማድረግ ይሆናል፡፡

የስትራቴጅውን አፈጻጸም በተመለከተ መንግስት፣ ባድርሻ አካላት፣ አቅም ገንቢዎች እና ኅብረት ሥራ ማህበራት በየጊዜው ተገናኝተው አፈጻጸሙን እየገመገሙ የሚታዩ ችግሮች በወቅቱ እንዲፈቱ አቅጣጫ በማስቀመጥ የሚተገበር ይሆናል፡፡ ለስትራቴጅው መሳለጥ አስፈላጊ የሆኑ የሕግ ማዕቀፎች፣ የተለያዩ አሰራሮች፣ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች እና ሌሎች የማስፈጸሚያ ስልቶች ተዘጋጅቶ ይተገበራሉ፡፡

# መግቢያ

አገራችን የምትከተለው የኢኮኖሚ ስርዓት ግብርና መር ኢንዱስትሪ እንደመሆኑ መጠን ባሳለፍናቸው ዓመታት ግብርና የሀገራችን ኢኮኖሚ ዋልታ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ባለፉት 13 ዓመታት የአገራችን ኢኮኖሚ በተከታታይ በአማካይ በለሁለት አሃዝ እድገት እያስመዘገበ መጥቷል፡፡ የኢኮኖሚ እድገቱ በአገሪቱ የተረጋጋ ማክሮ-ኢኮኖሚ እንዲፈጠርና የነፍስ ወከፍ ገቢ እንዲያድግ ከማስቻሉም በላይ የነበረውን የዋጋ ግሽበት በመቀነስ ወደ አንድ አሀዝ እንዲወርድ በማድረግ ለዜጎች የስራ ዕድል በመፈጠሩ የገቢ ምንጫቸው እንዲያድግና ድህነት እንድቀንስ አስችሏል፡፡ ለእነዚህ ስኬቶች መመዝገብ ዋናኛው የተቀየሱት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ውጤታማ በመሆናቸው ነው፡፡

በመሆኑም የተመዘገበውን ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በማስቀጠል ድህነትንና ኋላቀርነትን በማስወገድ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ፣ ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት ሕብረተሰቡን ፊትሃዊ ተጠቃሚ ለማድረግ፣ በኢኮኖሚ ትስስር ውስጥ ያላውን ድርሻ ለማሳደግ እና ያለውን ፈጣን እድገት እና ጠንካራ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መገንባት እውን ለማድረግ በቁርጠኝነት እየተሰራ ይገኛል፡፡

በአገራችን ለተመዘገበው የኢኮኖሚ እድገት የኅብረት ሥራ ማህበራት ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በአባላት ሙሉ ፍቃደኝነት በመደራጀት በገጠርና በከተማ የሚኖረውን ሕብረተሰብ ከኢኮኖሚ እድገቱ ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ትኩረታቸው መሆን የሚገባው በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖሩ የአባላት መሰረታዊ ችግር መፍታት ሲሆን በዋናነት ከተማና ገጠርን በማስተሳሰር የአኪኮኖሚ ትስስሩን ጤናማነትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ ብሎም የከተማና የገጠር የተቀናጀ የእደገት ትስስር እንዲኖር ያግዛሉ፡፡

በገጠር ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓት እና የግብርና ሜካናይዜሽን በማቅረብ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት፣ ሸማቹንና አምራቹን በማስተሳሰር ፍትሃዊና የተረጋጋ ገበያ እንዲኖር በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በአባላት ምርት ላይ እሴት በመጨመር፣ የእንዱስትሪ ውጤቶችና የፍጆታ እቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋና ጥራት በማቅረብ፣ የቁጠባ ባህልን በማጎልበት፣ የፋይናንስ አቅርቦት በማመቻቸትና በማቅረብ እንዲሁም ለአባላትና ለህብረተሰቡ የስራ እድል በመፍጠር በኢኮኖሚና በማህበራዊ ልማት ውስጥ ጉልህ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ናቸው፡፡

በከተሞች ያለውን የሕብረተሰቡን ፈጣን፣ ቀልጣፋና ፍትሃዊ አገልግሎት በተመጣጣኝ እንዲያገኙ ለማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራት ያላቸው ሚና የጎላ ነው፡፡ በመሆኑም የፍጆታ እቃዎችንና የእንዱስትሪ ምርቶችን በጥራት፣ በወቅቱ እና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ፣ የአባላትን የመኖሪያ ቤት ችሮችን ለመፍታት የሚያስፈልጉ ብድሮችን በማመቻቸት

ቢጋራ ቤቶችን እንዲገነቡ በማድረግ እና የአባላትን የቁጠባን ባህልን በማጎልበት ለኢንቨስትመንት አቅም በመሆን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡ አሁን በመተግበር ላይ ያለውን መሰረታዊ የኢኮኖሚ አላማ በቀጣይነት በአስተማማኝ ሁኔታ ለማሳካት የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚኖራቸው ሚና ጉልህ ነው፡፡

በመሆኑም በስትራቴጂው ትኩረት የሚደረግባቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ማነቆዎች መካከል ጠንካራ አደረጃጀትና አሰራር አለመኖር፤ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ውስንነት፣ የግብይት ድርሻቸው አነስተኛ መሆን፣ በእሴት መጨመር ተግባር ላይ በስፋት መግባት አለመቻል፣ የቁጠባ ባህል አለመዳበር፣ ለገጠር ትራንስፎርሜሽን እና ኢንዱስትሪ ልማት የሚያስፈልግ ፋይናንስ በሚፈለገው ደረጃ አለመኖር፣ መሰረተ ልማት አለመዘርጋትና አለመስፋፋት፣ የኦዲት እና የኢንስፔክሽን ጥራትና ተደራሽ አለመሆን፣ የአቅም ግንባታ ስራዎች ተደራሽ እና ችግር ፈቺ አለመሆን ችግሮች በስፋት ይታያሉ፡፡

ሆኖም የአገሪቱን የኅብረት ሥራ ማህበራት የወደፊት የእድገት አቅጣጫ የሚያሳይ ሁሉ አቀፍ የሆነ የኅብረት ሥራ ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በማዘጋጀት ተግባራዊ ባለመደረጉ ምክንያት እድገቱ በሚፈለገው ደረጃ እየተፋጠነ አይደለም፡፡ የኅብረት ሥራ ሴክተር አሁን ካለበት ወደ ላቀ ደረጃ የሚያሻግር፣ የአባላትና የዜጎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር በዘላቂነት የሚፈታ፣ አባላት በአገሪቱ ልማት ቀጥተኛ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚያደርግ፣ በራሱ የሚተማመን ዜጋ በማፍራት፣ ለሀገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ጉልህ ድርሻ እንዲያበረክቱ ጠንካራ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲኖሩ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የኅብረት ሥራ ማህበራት ስትራቴጂ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

## የዓለም አቀፍ የኅብረት ሥራ ነባራዊ ሁኔታ

የሰው ልጅ የጥንታዊ አኗኗር ዘይቤው በራሱ በኅብረት እንደሆነ ከታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለዘመናዊ ኅብረት ሥራ አጀማመርና ታሪካዊ አመጣጥ በመነሻነት የሚጠቀሰው በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በአውሮፓ የኢንዱስትሪው አብዮት በፈጠረው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ ምክንያት ነው፡፡

በአለም አቀፍ ደረጃ በአሁን ጊዜ አደረጃጀቱ ከሀገር ሀገር የሚለያይ ቢሆንም በአብዛኛው የመጀመሪያ ደረጃ (መሠረታዊ) ፣ የሁለተኛ ደረጃ እና ከፍተኛ ደረጃ (Apex) ኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት አርከኖች እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የአገራቱን ኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚወክል የኅብረት ሥራ ማህበራት ህብረት (ሊግ) በሀገር አቀፍ ደረጃ በማደራጀት የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴ (movement) ቀጣይነት እንዲኖረው በመደገፍ ላይ ይገኛሉ፡፡

በአሁን ወቅት የኅብረት ሥራ ማህበራት የተደራጁባቸው የስራ መስኮች በርካታ ቢሆንም በዋናነት በማምረት፣ በአግልግሎት እና በማምረትና የአገልግሎት ተግባርን አጣምረው የሚሰሩ ተብለው በመደራጀት ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህ መሰረት አግልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ ዋና ዋና የኅብረት ሥራ ማህበራት አይነቶች መካከል በግብርና፣ የወተትና

ወተት ተዋጾ፣ በመስኖ፣ ሸማቾች፣ ፋይናንስ፣ የቤቶች ልማት፣ የሰራተኞች እና ሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች ይገኛሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሮቻቸውን በአግባቡ እንዲፈጽሙ ለማስቻል በዋናነት በራሳቸው የውስጥ አቅምና በፈጠሩት አደረጃጀት፣ በአቅም ገንቢዎች እና በመንግስት የአቅም ግንባታ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ የበርካታ ሀገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው የኅብረት ሥራ ማህበራት በራሳቸው አደረጃጀት የሚመራና የሚተዳደር የኅብረት ሥራ የልህቀት ማዕከላትን በመቋቋም ለአባላት፣ ለአመራር አካላት፣ ለቅጥር ሰራተኞች እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት በሚያከናውኑት ተግባራት፣ በኅብረት ሥራ ጽንሰ ሐሳቦች እና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ክፍተትን መሰረት ያደረገ ቀጣይነት ያለው የአቅም ግንባታ ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በአለም ላይ በአሁኑ ጊዜ በ145 ሀገራት ውስጥ 1ቢሊዮን በላይ አባላት ያሏቸው ከ2.6 ሚሊዮን የተለያዩ አይነት ኅብረት ሥራ ማህበራት ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የአለም አቀፍ ኅብረት ሥራ ህብረት (ICA) አባል ከሆኑ 100 ሀገራት ውስጥ ከ700 ሚሊዮን በላይ ግለሰብ አባላት ያቀፉ እና ከ2.5 ቲሪሊዮን የአሜርካን ዶላር በላይ ካፒታል ያፈሩ 300 የኅብረት ሥራ ማህበራት ይገኛሉ፡፡ ምንጭ (ICA Fact and Figures, 2016)

ከዚህ ውስጥ 387 ቢሊየን የአሜርካ ዶላር የተገኘው የካፒታል እንቅስቃሴ ከኅብረት ሥራ ባንክና ገንዘብ ቁጠባና ብድር ሲሆን 1,020.8 ቢሊየን የአሜርካን ዶላር የሚሆነው ደግሞ የተገኛው ከኢንሹራንስና ከሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ነው፡፡

የኅብረት ሥራ ማህራት ለ250 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ሰዎችም ቋም የስራ እድል ፈጥረዋል፡፡ በአለም ላይ ከሚገኙ የበለጸጉ ሃያ ሀገሮች (G20) ከፈጠሩት የሥራ እድሎች ውስጥ በኅብረት ሥራ ማህበራት በኩል የተፈጠረው የሥራ እድል 12 ከመቶ ድርሻ አላው፡፡ ይህ ቁጥር በአለም ላይ የሚገኙ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ከፈጠሩት የስራ እድል በ20 በመቶ ብልጫ አለው፡፡ በተጨማሪም ኅብረት ሥራ ማህበራት ለስራ ምቹና አስተማማኝ የስራ እድሎች የሚፈጠሩባቸው ተቋም ናቸው፡፡ (Source: - ICA-facts and figers 2014)

### ከኅብረት ሥራ አደረጃጀት አንፃር

በተለያዩ የዓለም ሀገራት የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት በኅብረት ሥራ ማህበራት መርህ መሰረት የሚደራጅ ሆኖ የተለያዩ ስኬቶች ታይቷል፡፡ **በካናዳ** ከሚኖረው ሕዝብ 50 በመቶ ማለትም 18 ሚሊዮን የሚሆነው የኅብረት ሥራ ማህበራት አባል ነው፡፡ **ካናዳ** ውስጥ ኩቤክ በምትባለው ግዛት 70 በመቶ የሚሆነው ህዝብ የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ሲሆን በሳስካችዋን ግዛት 56 በመቶ የሚሆን ህዝብ የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ነው፡፡



DRAFT

**በማሌዢያ** 6.78 ሚሊዮን (27 በመቶ)፣ **በጣሊያን** 22.5 ሚሊዩን፣ **በኖርዌይ** ካለው 4.8 ሚሊዮን ህዝብ ውስጥ 2 ሚሊዮኑ የሚሆነው የኅብረተሰብ ክፍል የኅብረት ሥራ ማህበራት አባል ነው፡፡ **ኖርዌይ** አጠቃላይ አመታዊ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) 22 በመቶ ድርሻ አላቸው፡፡ **በአሜሪካ** 350 ሚሊዮን አባላትን ያፈሩ ከ40ሺ በላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ይገኛሉ፡፡ **በፊንላንድ** 72 በመቶ የሚሆነው ሕዝቧ የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ነው፡፡ 36 በመቶ የሚሆነው **የኡራጋይ** ሕዝብ የኅብረት ሥራ ማበር አባል ነው፡፡ 25 በመቶ የሚሆነው **የስንጋፖር** ሕዝብ የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ነው፡፡

በጃፓን ከ3ቱ 1፣ በኬንያ ከ5ቱ 1፣ በህንድ 236 ሚሊዮን፣ በቻይና 180 ሚሊዮን፣ በእንግሊዝ 9.8 ሚሊዮን፣ በብራዚል 5.6 ሚሊዮን፣ በአርጀንቲና 9.1 ሚሊዮን የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባል ሆነው ይገኛሉ፡፡ በሌሎች አገሮችም ኅብረት ሥራ ማህበር አባላት ቁጥር ከአገር አገር የሚለያይ ቢሆንም ቁጥሩ ቀላል አይደለም፡፡

(Source: - ICA-facts and figers 2014)

### የግብርና ኅብረት ሥራ አንፃር፡-

**በጃፓን** 91 በመቶ ከሚሆነው የጃፓን አርሶ አደር ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት 96 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ዋጋ የሚያወጣ ምርት ከአባላት ሰብስበው በከተሞች ውስጥ በተሰጣቸው የገበያ ማዕከላት ምርታቸውን ለከተማ ሸማች ህብረተሰብ ያቀርባሉ፡፡ **በህንድ ደቡባዊ** ግዛት በካርናቱካ ክልላዊ መንግሥት ዋና የንግድ ማዕከሉን ባንግሎር ከተማ ያደረገው የአትክልትና ፍራፍሬ ኅብረት ሥራ ማኅበር አምራቹና ሸማቹ ከ50 እስከ 70 ከመቶ የሚሆንውን ወጪዎችን በማስቀረት ከግል ነጋዴ ዋጋ ጋር ሲነጻጻር ከ15 እስከ 20 ከመቶ የተሻለ ዋጋ እንዲያገኝና የተፈጥሮ ምርት የሆነና ጥራቱን የጠበቀ ምርት ለገበያ ማቅረብ እንዲችል አድርጎታል፡፡

**በኒውዝላንድ** ከአገሪቱ አጠቃላይ (GDP) ውስጥ ከኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ 22 በመቶ ሲሆን 95 በመቶ የሚሆነው የአገሪቱ የወተትና የወተት ተዋጽኦ ምርት የሚሸፈነው በኅብረት ሥራ ማህበራት ነው፡፡ ሀገርቱ ወደ ውጪ ከሚትልከው የወተት ተዋጽኦ ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት 95 በመቶ፣ የሥጋ ምርት 50 በመቶ፣ የእርሻ መሳሪያዎች አቅርቦት 50 በመቶ እና የአፈር መዳበርያ 75 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ ይዘዋል፡፡ **በኡራጓይ** ኅብረት ሥራ ማህበራት በአገሪቱ አመታዊ ጥቅል ምርት (GDP) ላይ 3 በመቶ ድርሻ አላቸው፡፡ ወደ ውጭ ከሚላኩ ምርቶች ውስጥ 90 በመቶ የሚሆነውን የወተት ምርትና 60 በመቶ የስንዴ ምርት በኅብረት ሥራ ማህበራቱ በኩል 40 ለሚሆኑ አገራት በመላክ የውጪ ምንዛሬ ለአገራቸው እያስገኙ ይገኛሉ፡፡ **በፊንላንድ** ኅብረት ሥራ ማህበራት 96 በመቶ በወተት፣ 82 በመቶ በስጋ ግብይት ላይ የገበያ ድርሻ አላቸው፡፡

**ኬንያ** ከአጠቃላይ የሀገርቱ GDP ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ 45 በመቶ ሲሆን ከወተት ግብይት ውስጥ 95 በመቶ፣ የቡና ግብይት በ70 በመቶ እና የጥጥ ምርት ግብይት 95 በመቶው የሚሆነው የሚከናወነው በኅብረት ሥራ ማህበራት በኩል ነው፡፡

(Source: - ICA-facts and figers 2014)

### እሴት ከመጨመር አንፃር፡-

**በቻይና** ከአጠቃላይ የአግሮ ፕሮሰስንግ ወስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ 68 በመቶ ደርሷል፡፡ **በኖርዲክ** አገሮች ውስጥ ያሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት ካላቸው የእድገት ደረጃ አንጻር አብዛኞቹ ከአገራቸው ካለው ገበያ ውጭ በአካባቢው ባሉ አገሮች ገበያዎችን በመቆጣጠር ላይ ይገኛሉ፡፡ ለአብነት፡- **አየርላንድ**፣ ኖርዌይ፣ **የዴንማርክና የሲውዲን** የጋራ የወተት እና የወተት ተዋጽኦ የሚያቀነባብር ኅብረት ሥራ ማህበር ሲሆን ከ8000 በላይ የሚሆኑ አባላት እና ከ6.5 ቢሊዮን ዩሮ አመታዊ እንቅስቃሴ ያለው ኅብረት ሥራ ማህበር ነው፡፡ (Source: - ICA-facts and figers 2014)

### ከመሰረተ ልማት ግንባታና ቴክኖሎጂ አቅርቦት አንፃር፡

**በአሜሪካን** ውስጥ በገጠር ኤሌክትሪክ አቅርቦትና ስርጭት 920፣ በገጠር ቴሌፎን አቅርቦትና ስርጭት 255፣ በንጹህ ውሃ አቅርቦትና ስርጭት 3,350 በአጠቃላይ 4,525 የሚደርሱ በመሰረተ ልማት ግንባታ ላይ የተሰማሩ ኅብረት ሥራ ማህበራት ያሉ ሲሆን ሀብታቸው 119 ቢሊዮንና አመታዊ ገቢያቸው 96.4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲሁም 19.7 ሚሊዮን አባላትና እና 80,570 ሰራተኞች ቀጥረው ይገኛሉ፡፡ **በቦሊቭያ** በሳንታክሩዝ በዓለም ላይ ትልቁ የውኃ አቅርቦት የኅብረት ሥራ ማህበር የሚገኝ ሲሆን በመዲናይቱ ውስጥ በዘረጋው 183,000 በሚሆኑ አውታሮች አማካኝት የነዋሪውን 1/3 ማለትም 1.2 ሚሊየን የሚሆነውን ህዝብ የንፁህ ውኃ ተጠቃሚ ለማድረግ ችሏል፣

**በሕንድ** በብሄራዊ የመኖርያ ቤቶች የኅብረት ሥራ ፌዴሬሽን ሥር በተዋቀሩ 92,000 የመኖርያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት 6.5 ሚሊየን ቤቶችን በመገንባት 75% የሚሆነውን ድሃ የከተማ ነዋሪ (urban poor) የቤት ባለቤት ለማድረግ ተችሏል፣ **በባንግላዴሽ** በተቋቋሙ 70 የገጠር የኤሌክትሪክ የኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት 47,600 የሚሆኑ የገጠር መንደሮችን ለማገናኘትና ለ30 ሚሊየን ህዝብ ሽፋን ለመስጠት የተቻለ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ 170,000 ለሚሆኑ የመስኖ ውኃ ማከፋፈያ ጣቢያዎች ኃይል ለማቅረብ ተችሏል፡፡

**በእንግሊዝ** ውስጥ 3300 የውሀ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚገኙ ሲሆን በእነዚህ ማህበራት አማካኝነት የመጠጥ ውሃ፣ የመስኖ ውኀ፣ የእሳት አደጋ ማጥፊያ ውኃ ወዘተ… የሚሰራጭ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ፍሳሽ የማስወገድ አገልግሎትም እንደሚሰጡ ይጠቀሳል ፡፡ በእንግሊዝ ከሚኖረው ሕዝብ ውስጥ 15 ሚሊየን የሚሆነው በኅብረት ሥራ

የታቀፈ ነው፡፡ **በቱርክ-አንካራ** ከማዘጋጃ ቤቱ ጋር በተደረገ ስምምነት መሠረት 200,000 የዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ነዋሪዎች በኅብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው የመኖርያ ቤት ችግሮቻቸውን ለመፍታትና አካባቢያችን ለማልማት ችለዋል፡፡

(Source: - ICA-facts and figers 2014)

## ከሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት አንፃር፡-

**በዴንማርክ** ውስጥ ካሉ የችርቻሮ ሽያጭ ሱቆች መካካል 36.4 በመቶ የሚሆነውን በሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚንቀሳቀስ ነው፡፡ **በፊንላንድ** 75 በመቶ የሚሆኑት ቤተሰቦች የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበር አባላት በመሆናቸው የእሴት ሰንሰለት (valu chain) የሚደረግ የምግብ ትስስር የሚከናወነው በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት ሲሆን 44 በመቶ የእለታዊ የፍጆታ እቃዎች ሽያጭ ላይ የገበያ ድርሻ አላቸው፡፡ **በኒውዝላንድ** ከአጠቃላይ የፋርማስ የጅምላ አቅርቦት ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራ ድርሻ 75 በመቶ ስሆን በተመሳሳይ የሻቀጣ ሸቀጥ አቅርበት ድርሻ 62 በመቶ ነው፡፡

**በጃፓን** ያሉ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት አጠቃላይ አመታዊ እንቅስቃሴያቸው 34,048 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የደረሰ ሲሆን በአገሪቱ የምግብ ገበያ ድርሻ ውስጥ 5.9 በመቶ ድርሻ አላቸው፡፡ **በደቡብ ኮሪያ** የሚገኘው የሀንሳሊም የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበር 284,000 ተጠቃሚና 2,000 አምራች አባላትን ያቀፈ ከ328 በላይ ሰራተኞች ያሉትና 131 የሽያጭ ማዕከሎች አማካኝት አመታዊ ሽያጭ 160 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የደረሰ ኅብረት ሥራ ማህበር ሲሆን በተለይ ተፈጥሯዊ የግብርና ምርቶች ላይ አቶክሮ የሚሰራና በገበሬዎችና በተጠቃሚ መካከል ቀጥተኛ የግብይት ትስስር የፈጠረ ማህበር ነው፡፡ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ባዘጋጃቸው የሽያጭ ማእከሎች የከተማው ተጠቃሚ ኅብረተሰብና የገጠሩ አርሶ አደሮች በቀጥታ የሚገበያዩበት ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ የምርቶቹ ሽያጭ ዋጋ የሚወሰነው በተጠቃሚው እና በአምራቹ ምክክር ሲሆን 76 በመቶ የሚሆና የዋጋ ድርሻ በቀጥታ ለአምራቹ የሚሄድ ሲሆን ቀሪው 24 በመቶ ደግሞ ምርቱን ለተጠቃሚው ለማድረስ የወጡ ወጪዎች መሸፈኛ ነው፡፡

(ICA web site fact and figers እ.ኤ.አ በ2014)

## ከፋይናንስ አቅርቦት አንፃር፡-

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአጠቃላይ የፋይናንስ ተደራሽነት አንፃር አየር ላንድ 77%፣ በአሜሪካ 48.8%፣ ኢኳዶር 46.2%፣ ካናዳ 44.1%፣ ደቡብ ኮሪያ 16%፣ ታይላንድ 8.2%፣ ቶጎ 28.2%፣ ቤኒን 22.6%፣ሩዋንዳ 22.8%፣ ስሼልስ 21.2%፣ ኬኒያ 21.3%፣ሴኔጋል 23%፣ ኡጋንዳ 7.2%፣ ኢትዮጵያ 2.1% የሚጠቀሱ ናቸው። **በፊንላንድ** የኅብረት ሥራ ባንክ ቁጠባን በመሰብሰብ 35 በመቶ ድርሻ አለው። **ኬንያ** ከአጠቃላይ ቁጠባ ውስጥ 31 በመቶ የሚሆነውን የሚሸፍኑቱ የኅብረት ሥራ ማህበራት ናቸው።

በአጠቃላይ በአለም ላይ ካሉት የፋናንስ ኅብረት ስራ ማህበራት ውስጥ 9,978 የሚሆኑት ሃብታቸውም 2.9 ትሪሊዮን እና አመታዊ ገቢያቸውም 264.8 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሲሆን አማካይ የአገልግሎት ተደራሽነት ሽፋናቸውም 8.3 በመቶ ነው። ምንጭ፡ WOCCU,2015

### ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር፡-

**በፊንላንድ** በደን ልማት የተቋቋመ አንድ አገራዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በስሩ 129,000 አባላት ያሉት ሲሆን ከ17,500 የሚደርሱ ቅጥር ሰራተኞች ሲኖሩት በአገሪቷ ውስጥ በደን እና በእንጨት ምርት ውጤቶች ገበያ 36 በመቶ ድርሻ ይዞ ይገኛል። **በማሌዥያ** የደን ልማት የኅብረት ሥራ ማበራት ለአካባቢ ጥበቃ በአደረጉት አስተዋጽኦ መነሻነት ሙሉ የዓለም አቀፍ ግብይት እውቅና እንዲሰጣቸው በመደረጉ በእዚህ እድል ተጠቅመው የጣውላ ኤክስፖርት ገበያውን በበላይነት ለመቆጣጠር ችለዋል።

**በኮሎምቢያ**፣ **በብራዘል**፣ **በአርጀንቲና**፣ **በሜክሲኮ**፣ **በፊሊፒንስ** እና ሌሎች የአገለግሎት፣ የአረጀና የወደቁ ቁሳቁሶችን በመሰብሰብ ለመልሶ ጥቅም ለኢንዱስትሪ የሚያርቡትን በአገራችን በተለምዶ ቆራሊዮ /WASTE-PICKERS/ ተብለው የሚጠሩትን ሰዎች በኅብረት ሥራ ማህበር በማደራጀት የዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከመደረጉም በላይ ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለከተሞች ጽዳትና ውበት በሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በመንግሰትም ሆነ በአካባቢ ተቆርቋሪ አካላት በኩል ከፍተኛ አድናቆትና ድጋፍ እየተቸራቸው ይገኛል።

(ICA web site fact and figers እ.ኤ.አ በ2014)

### ከስራ ዕድል ፈጠራ አንፃር፡-

**በአሜሪካን** 40,000 የሚሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት ሲኖሯት 350 ሚሊዮን የሚሆኑ አባላት አሏት። ከአጠቃለይ ህዝቧ ወስጥ በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት ከ2 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ የስራ እድል ተፈጥረዋል። **በኮሎምቢያ** በተፈጠረው የኅብረት ሥራ ንቅናቄ 137,888 የሚሆኑ ስራ አጦችን በኅብረት ሥራ ማህበራት በኩል የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ሲሆን ለ559,118 ስራ አጥ ዜጎች በኅብረት ሥራ ማህበራት በመደራጀት የስራ እድል የተፈጠረላቸው ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 3.65 በመቶ ድርሻ ይዘው ይገኛል።

**በፈረንሳይ** ከ21 ሺ በላይ የሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከ1 ሚሊዮን በላይ ለሚጠጉ ሰዎች የስራ እድል የፈጠሩ ሲሆን ይህም በአጠቃላይ ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 3.5 በመቶ ድርሻ ይኖራል፡፡ **በፊንላንድ** ያሉ 430 የሚሆኑ የተለያዩ ኅብረት ሥራ ማህበራት 92,000 የሚጠጉ ሰራተኞችን ቀጥረው እያሰሩ ይገኛሉ፡፡ **በፊንላንድ** 30%፣ **በፊሊፒንስ** 24% እና **በአርጀንቲና** 58% በገጠር የኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ በኮምዩኒኬሽን አገልግሎት፣ በውሃ አገልግሎት፣ በሸቀጣ ሸቀጥ አቅርቦትና አገልግሎት፣ በቤቶች አገልግሎት፣ በቱሪዝም አገልግሎትና ዕደ ጥበባት ወዘተ በኅብረት ሥራ ማህበራት በመደራጀት የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

**በህንድ** ከ100,000 የማንሱ የወተት እና የወተት ተዋጾ የህብረት ስራ ማህበራት የሚገኙ ሲሆን 12 ሚለዮን ለሚሆኑ ሴቶች የስራ እድል ለመፍጠር ችሏል፡፡ **በቤኒን** ካሉት ስራ አጦች ውስጥ 90% የሚሆኑት በተለያዩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ማለትም በቁጠባ አገልግሎት፣ በገጠር ባንክ አገልግሎት፣ በኢንሹራንስ አገልግሎት፣ በጤና አገልግሎት፣ በኤሌክትሪክ አገልግሎት በሚሰጡ ኅብረት ሥራ ማህበራት በመደራጀት የሥራ ዕድል አግኝተዋል፡፡

በአጠቃላይ በዓለም ላይ ህብረት ስራ ማህበራት ስራ እድል ከመፍጠር አንጻር በቀጥታ ለ250 ሚለዮን ሰዎችን የስራ እድል በመፍጠር ተጠቃሚ ማድረግ እንደቻሉ መረጃው ያሳያል፡፡ በተጨማሪ 12.6 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዋች በ770,000 ኅብረት ሥራ ማህበራት ጽ/ቤት ውስጥ ተቀጥረው በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡

(ICA press releases 10 oct 2014)

### ከማህበራዊ አገልግሎት አንፃር፡-

**በጃፓን** በሸማቶች የኅብረት ሥራ ማህበራት ከታቀፉ አባላት ውስጥ ሴቶች 95% የሚሸፍኑ ሆኖ ባጎለበቱት አቅም መነሻነት ከፍተኛውን የአመራር ሚና በመጫወት ላይ እንደሚገኙ መረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡ በጤና ዘርፍም 125 የሕክምና የኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት 3 ሚሊየን የሚሆኑ አባላትና ቤተሰቦቻቸው የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በመሆን ላይ ይገኛሉ ፡፡ **በኮትዲቯር** ኅብረት ሥራ ማህበራት ትምህርት ቤቶች ግንባታ፣ ለመንገድ ስራ እና ለእናቶችና ህጻናት መታከሚያ የሚሆን ክልኒክ ግንባታ እ.ኤ.አ. እስከ 2002 ድረስ ወደ 26 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር መዋለንዋይ አፍስሰዋል፡፡

**በፊንላንድ** ውስጥ 84 የሚሆኑ በጤና መድን ሽፋን ላይ የተሰማሩ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚገኙ ሲሆን 535,000 አባላት እና ከ1000 በላይ ቅጥር ሰራተኞች አሏቸው፡፡ በአገሪቱ የጤና መድን ሽፋን ውስጥ 9 በመቶ ድርሻ አላቸው፡፡ **በአሜሪካን** ውስጥ በጤና አገልግሎት፣ በህጻናት እንክብካቤ፣ በቤቶች ግንባታ አገልግሎት፣ በትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ እና በትምህርት አገልግሎት በአጠቃላይ 11,311 የሚሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት በማህበራዊ አገልግሎት የተሰማሩ ከ1 ሚሊዮን በላይ አባላት እና 91,600 ቅጥር ሰራተኞችያላቸው ሲሆን ሀብታቸውም 1.6 ቢሊዮን እና አመታዊ ገቢያቸው 4.3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ደርሷል፡፡


**በኮሎምቢያ** ውስጥ ሳሉድኮፕ /SALUDCOOP/ተብሎ በሚታወቅ የጤና አጠባበቅ የኅብረት ሥራ ማህበር አማካኝነት 25% የሚሆነው የአገሪቱ ህዝብ የአገልግሎቱ ተጣቃሚ በመሆን ላይ የሚገኝ ሲሆን የስራ ዕድል ከመፍጠር አኳያም በአገሪቱ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ በሁለተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይጠቀሳል፡፡ **በካናዳ** ከ100 የማያንሱ የጤና አጠባበቅ የኅብርት ሥራ ማህበራት የሚገኙ ሲሆን በአገሪቱ በሚገኙ 8 የአስተዳደር ክልሎች ውስጥ በመሠራጨት ከ1ሚሊየን ለማያነሱ አባሎቻቸውና ቤተሰቦቻቸው መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ሽፋን በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ እንደ ዓለም አቀፉ የጤና የኅብረት ሥራ ቃል ኪዳን መረጃ መሠረት በዓለም ላይ ከ100 ሚሊየን የማያንስ ቤተሰብ በጤና አጠባበቅ የህብረት ሥራ ማህበራት ታቅፎ ሽፋን እያገኘ መሆኑ ያሳያል፡፡

ምንጭ፡ coop and sustainable devt, goal-ica-web site2015

## የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ነባራዊ ሁኔታ፡-

**የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት፡-** በአገራችን የተደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት በማምረት ተግባር ላይ የተሰማሩ ወይም ጥሬ ዕቃ ወደ አላቂ ዕቃ የሚቀይሩ ወይም በከፊል የተሰሩትን ወደ አላቂ ምርትነት በመቀየር ለአገልግሎት በሚውል ደረጃ የሚያመርቱና ለተጠቃሚዎች የሚያቀርቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ናቸው፡፡ በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሰኔ 30/2009 ዓ/ም መረጃ መሰረት የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጡ 82089 መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡


**የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የክልል ስርጭት**




ምንጭ፡- ፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሰኔ 2009 ዓመታዊ ሪፖርት

በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሰኔ 2009 ዓ/ም በወጣው መረጃ መሰረት በርካታ አይነት ኅብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅቶ የሚገኙ ሲሆን ብዛታቸው ከዓመት ወዳ አመት በከፍተኛ ደራጃ እያደገ ይገኛል፡፡


**የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት**




**ምንጭ፡- ፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሰኔ 2009 ዓመታዊ ሪፖርት**

በመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነት ሲታይ 39 በመቶ ድርሻ ይዞ የሚገኘው ግብርና ነክ ባልሆኑ፣ 31 በመቶ በግብርና የተሰማሩ፣ 25 በመቶ በገንዘብ ቁጠባና ብድር እና 5 በመቶ በሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ የተሰማሩ ናቸው፡፡


**አጠቃላይ አገራዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት በጾታ በሚከተለው ግራፍ ላይ ቀርቧል፡-**




ምንጭ፡- ፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሰኔ 2009 ዓመታዊ ሪፖርት


**የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ካፒታል መጠን፡-** ሌላው የስኬት መገለጫ ሆኖ የሚታየው የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ካፒታል መጠን ነው፡፡ ከላይ እንደሚታየው ከፍተኛውን የካፒታል መጠን ይዞ የሚገኘው የፋይናንስ ዘርፉ ሲሆን ይህም 59 በመቶ ድርሻ አለው፡፡ በመቀጠል የግብርና ዘርፍ 26 በመቶ ድርሻ ሲይዝ ግብርና ነክ ያልሆኑ 15 በመቶ ድርሻ አላቸው፡፡

**የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ካፒታል መጠን**




በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የ2009 ዓ.ም መረጃ መሠረት አጠቃላይ የመሠረታዊ እና ዩኒዬን ኅብረት ሥራ ማህበራት ካፒታል በብር እንደሚከተለው ይሆናል፡-

**የመሠረታዊ እና ዩኒዬን ኅብረት ሥራ ማህበራት ካፒታል**




ምንጭ፡- ፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሰኔ 2009 ዓመታዊ ሪፖርት


በኦሮሚያ ክልል በ1989 ዓ/ም የመጀመሪያው ዩኒየን ሞጆ ከተማ ላይ መመስረት የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች በአይነትና በብዛት በ7 ክልሎችና በሁለት ከተማ አስተዳደሮች በፈጣን ሁኔታ ለመስፋፋት ችለዋል፡፡

በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ በ2009 ዓ/ም በወጣው መረጃ መሰረት 381 የሚደርሱ የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች ይገኛሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ዩኒየን በማቋቋም ከፍተኛውን ቁጥር ይዘው የሚገኘው ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ አማራ፣ ትግራይ

DRAFT

ክልል እንደየደረጃው ሲሆኑ ልዩ ድጋፍ ከሚሹ ክልሎች ከፍተኛ የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች የሚገኙበት የቤንሻንጉል ክልል ሲሆን 21 ኅብረት ሥራ ዩኒየኖች ተደራጅተዋል፡፡

**የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች እና አባላት ብዛት**





ምንጭ፡- ፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሰኔ 2009 ዓመታዊ ሪፖርት

**የምርት ማሳደጊያ ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት፡-** አገራችን ለአለፉት 13 ተከታታይ አመታት ላስመዘገበችው የኢኮኖሚ ዕድገት የግብርናው ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ ለምርት እና ምርታማነት ዕድገት ወሳን የሆነው የአፈር ማዳበሪያ በዓይነት፣ በመጠን፣ በጊዜና በተፈለገበት ቦታ ለአርሶ አደሩ ከማቅረብ አንፃር የኅብረት ሥራ ማህበራት ግንባር ቀደም ድርሻ አላቸው፡፡ በዚህም መሠረት ከ1997 እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ 906,220 ቶን የአፈር ማዳበሪያ 11 የኅብረት ሥራ ዩኔየኖች ከውጭ በማስገባትና በማሰራጨት 70 በመቶ የሚሆነውን አቅርቦት በኅብረት ሥራ ማህበራት እንደተሸፈነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በግብርና ኅብረት ሥራ ማህበራት አመካኝነት ከ2003/04 እስከ 2008/09 ምርት ዘመን ቀርቦ የተሰራጨ የአፈር ማዳበሪያ ብዛት 50,470,000 ኩንታል የደረሰ ስሆን ከአገራዊ ስርጭቱ የ98 በመቶ ድርሻ አለው፡፡ በተጨማሪም የኅብረት ሥራ ማህበራት በእነዚህ ዘመናት 2,644,062 ኩ/ል ምርጥ ዘር እና 766,416 ሊትር ኬምካል በማቅረብ እነዳሰራጩ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

**የምርት ማሳደጊያ ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት**

DRAFT





ምንጭ:- ፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሰኔ 2009 ዓመታዊ ሪፖርት

በአሁኑ ሰዓት አምስት ኅብረት ሥራ ዩኒየኖች መርከብ ከአማራ፣ እንደርታ ከትግራይ፣ በቾ ወሊሶና ጊቤ ድዴሳ ከኦሮሚያ እና መሊቅ ከደቡብ ምጥን ማዳበሪያ (NPS) ፋብሪካ እያቋቋሙ ማምረት ጀምሯል፡፡

**የአገር ውስጥ እና የውጭ የሰብል ምርት ግብይት:-** ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኅብረት ሥራ ማህበራት ተሰብስቦ ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች በተለይም ቡና፣ ሰሊጥ፣ የተለያዩ የሰብል ምርቶች፣ እንሰሳት፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ወተትና ወተት ተዋፅኦ የመሳሰሉት መጠኑም ሆነ በጥራቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ከ2003 እስከ 2009 ዓ.ም ወደ ውጭ ከተላኩት የግብርና ምርቶች ውስጥ ቡና 100,501 ቶን በማቅረብ 533,163,718 ዶላር ያስገኙ ስሆን በተጨማሪ በ2008 እና 2009 ዓ.ም 65,950 ቶን ሰሊጥ በመላክ 11,496,134 ዶላር በድምሩ 166,451 ቶን ሰብሎችን በመላክ 544,659,852 የአሜሪካን ዶላር የውጭ ሚንዛሪ ለአገሪቷ አስገኝቷል፡፡

**የውጭ የሰብል ምርት ግብይት**





***ምንጭ:- ፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሰኔ 2009 ዓመታዊ ሪፖርት***

ከ2003 እስከ 2009 ዓ.ም ውስጥ **53,614,736** ኩ/ል የተለያዩ የግብርና ምርቶችን ለአገር ውስጥ ገበያ በማቅረብ አባላት ከምርቶቻቸው የተሸለ ተጠቃሚ በማድረግ በገበያ ማለጋጋት ውስጥ የራሳቸውን አስተጽኦ ለማበርከት ችለዋል፡፡ በዚህ መሠረት የአባላት ምርት የሆኑትን **129,756,108** ሊትር ወተት፣ **14,230** ኩ/ል ማር፣ **9,165,132** የቁም እንሰሳት በመሸጥ ለአባላት ከፍተኛ ገቢ አስገኝተዋል፡፡

**በግብርና ምርት ላይ እሴት በመጨመር፡-** በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሰኔ የ2009 ዓ.ም ድረስ ባለው መረጃ እንደሚሳየው በከፍተኛ፣ መካከለኛ እና አነስተኛ እሴት መጨመረ ተግበር ውስጥ የገቡ ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር **791** ደርሷል፡፡

**በግብርና ምርት ላይ እሴት ጭማሪ**





***ምንጭ፡- ፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሰኔ 2009 ዓመታዊ ሪፖርት***

**የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት፡-** የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት ለሸማች አባላት እና ህብረተሰቡ የእንዱስትሪና የፍጆታ እቃዎችን በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ፣ ካላስፈላጊ የዋጋ ንረት በመታደግ ሻማቹ ከአምራች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የከተማና የገጠር ትስስር በመፍጠር ከ2003 እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ ብቻ ከ **41.83** ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ ልውውጦችን አድረጓል፡፡

**የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት፡-** በአገራችን የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማደራጀት የተጀመረው ከረጅም አመታት በፊት ቢሆንም የማስፋፋት ሥራው ውስን የነበረና በተለይ በከተሞች አካባቢ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ እስከ 1991 ዓ.ም ድረስ **119,799** አባላትና ብር **78,772,710** ካፒታል ያላቸው **495** የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት ብቻ እንደነበሩ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከ1995 ዓ/ም ጀምሮ የኅብረት ሥራ ማህበራት በማደራጀት በሁሉም የሀገሪቱ ገጠርና ከተሞች እንዲስፋፉ የተደረገ ሲሆን በ2009 ዓ.ም መጨረሻ **4,180,330 (ወንዶች 2,476,330 እና ሴቶች 1,704,000)** ነው፡፡ የሴቶች 40.8% አባላት ድርሻ ያሏቸው **19,788** መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራትና **126** የገንዘብ ቁጠባን ብድር የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች የተቋቋሙ ሲሆን የሰበሰቡት የቁጠባ እና ካፒታል መጠን ብር **13,445,543,708.50** ቢሊዮን ደርሷል፡፡

**የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የካፒታል፣ ቁጠባና ብድር ሁኔታ**




***ምንጭ፡- ፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሰኔ 2009 ዓመታዊ ሪፖርት***

**በማዕድን ማምረትና ግብይት፡-** በማዕድን ማምረት እና ግብይት በኩልም የኅብረት ሥራ ማህበራት ሲሆን በ2005 ዓ.ም፣ በ2008 ዓ.ም እና በ2009 ዓ.ም ብቻ **691** የማዕድን አምራቾች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት 5,141 ኪ.ግ ወርቅ እና 79,259 ኪ.ግ ታንታለም ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በማቅረብ ኢኮኖሚውን በመደገፍ ረገድ የራሳቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

**አከባቢ ልማትና በማህበራዊ አገልግሎት፡-** የአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላትና ለአካባቢው ኅብረተሰብ የሚሰጡት አገልግሎት በኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ላይ ብቻ ሳይሆን የአካባቢና ማህበራዊ ልማትን ላይ ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ ናቸው፡፡ ለዚህም በምሳሌነት የሚጠቀሱት የቡና አምራች ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየን በሥሩ የሚገኙ አባል የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ያሉባቸውን ችግሮች በመለየት በዓለም አቀፍ ፍትሃዊ ንግድ

(International Fair Trade) ተሳትፎ ከምርቱ ተጠቃሚዎች ከሚያገኘው ተጨማሪ ክፍያ ***213*** ፕሮጀክቶችን በመንደፍ በመጀመሪያና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣ በጤና፣ በውሃ፣ በመንገድና ድልድይ ግንባታ ላይ በመሳተፍ አስተዋፅኦ በማድረግ **224,475** የኅብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

***የሥራ ዕድል ፈጠራ፡-*** *የፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንስ ሰኔ 2009 ዓ.ም መረጃ መሰረት በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት በቀጥር እና በመደራጀት የተፈጠረ የስራ እድል በድምሩ* ***1,425,000*** *ለመፍጠር ተችሏል፡፡ ከዚህም ከተፈጠረው የስራ እድል ቁጥር አንፃር ሲታይ በርካታ ቤተሰቦች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋር መንገድ ተጠቃሚዎች ሆነዋል፡፡*

**የሴቶችና ወጣቶች ተጠቃሚነት፡-** የኅብረት ሥራ መርህ እንደሚያስቀምጠው ኅብረት ሥራ ማህበራት ያለ አንዳች ጾታዊ ተጽእኖ ለሁሉም ማህበረሰብ አባልነት ክፍት እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ በአባልነት ከአመት ወደ አመት እያደገ በ2009 ዓ.ም መጨረሻ ***29.6*** በመቶ በላይ ማደግ ችሏል፡፡

**የኦዲት እና የቁጥጥር ስራ፡-**በአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራትን ከመደገፍ አንፃር መንግስት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ በየአመቱ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ጥራት ያለው የኦዲት እና የኢንስፔክሽን አገልግሎት በመስጠት በየአመቱ የሚሰጠውን አገልግሎት ተደራሽነት በማሳደግ በ2009 ዓ.ም የኦዲት አገልግሎት ሽፋን ***25*** በመቶ እና የኢንስፔክሽን ሽፋን ***35*** በመቶ እንዲደርስ አድርጎታል፡፡

**የድጋፍ አሰጣጥ ስርዓት፡-** መንግስት የኅብረት ሥራ ማህበራትን እንቅስቃሴ በማጠናከር የተቋቋሙለትን አላማ ማሳካት እንዲችሉ ጠንካራ አደረጃጀቶችንና መዋቅሮችን በየደረጃው በመዘርጋትና በማጠናከር፣ የአሰራር ስርዓቶችን፣ የፖሊሲ፣ የሕግና የቁጥጥር አሰራሮችን በመዘርጋት፣ የአቅም ግንባታ እና ሌሎች ሙዊ ድጋፎችን በመስጠት ድጋፍ በማድረግ ውጤታማ ኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲፈጠሩ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

# ክፍል አንድ፡- የኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጂ መሠረታዊ ዓላማዎች፣ መርሆዎችና አስፈላጊነት

## 1.1. ኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጂው ዓላማ

የኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጂ በመተግበር በየደረጃው ኅብረት ሥራ ላይ የሚታየውን የግንዛቤ፣ አደረጃጀት፣ አሰራር እና ግብአት ጋር ተያይዘው በኅብረት ሥራ ላይ የሚታዩ ትራንስፎርሜሽን ማነቆዎችን በመፍታት የአገራችን ኅብረት ሥራ ማህበራት በተሰማሩበት የስራ መስክ ሁሉ ተወደዳዳሪነታቸውን አሳድገው የአባላትና የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ የአባላት ባለቤትነትና ተቆጣጣሪነትን በማሳደግ የኅብረት ሥራ ማህበራት አንድ የኢኮኖሚ



DRAFT

እና የፖለቲካ ማህበረሰብ በመገንባት ሂደት በአገራችን ፈጣን የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገት ላይ የሚጠበቅባቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማስቻል ነው፡፡

## 1.2. ኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጂ መርሆዎች (guiding principles)

**ሀ) የአባላትን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ጠንካራ ኅብረት ሥራ ማህበራትን መፍጠር፡-**

የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት በማሻሻል፣ የአሰራር ስርዓት በማሻሻል፣ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅማቸውን በመገንባት፣ መሰረተ ልማት በማሟላት፣ በተማረ የሰው ሃይል ተግባሮቻቸውን እንዲመሩ በማድረግ፣ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የመደራደር አቅማቸውን ባማሳደግ የአባላትን ኑሮ ለማሻሻልና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ በየደረጃው ያሉትን ኅብረት ሥራ ማህበራት ማጠናከር ተቀዳሚ ተግበር ይሆናል፡፡ ለወደፊት የሚደራጁ ኅብረት ሥራ ማህበራትም ከላይ በተቀመጠው አሰራር ውስጥ ሆኖ አዋጭ በሆኑ የስራ ዘረፎች ላይ ይመሰረታል፡፡

**ለ) የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ባለቤትነት፣ ተቆጣጣሪነት፣ ተጠቃሚነትና አሳታፊነትን ማረጋገጥ፡-**

የኅብረት ሥራ ማህበራት ካላቸው ልዩ ባህሪ በመነሳት አባላት አጠቃላይ አደረጃጀቱን፣ አሰራሩን፣ አመራሩን በበላይነት በማስተዳደርና ዲሞክራሲያዊ በሆነ አኳሀን በመቆጣጠር ተገቢውን ውሳኔ በመስጠት፣ የአባላትን ሁለንተናዊ የነቃ ተሳትፎ በማረጋገጥ አባላት ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሁኑ ማድረግ ነው፡፡

**ሐ) የሀገሪቱን እምቅ ሀብትና አስተዳደራዊ መወቅርን መከተል፡-**

የአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት የአገሪቱን አስተዳደራዊ መወቅርና የአከባቢውን እምቅ ሀብት መሰረት በማድረግ አዋጭነታቸው በተረጋገጠ ዘርፎች እንዲሰማሩ በማድረግ ነው፡፡

**መ) የገጠር ከተማ የአምራችና ሸማች (ኢኮኖሚ) ትስስርን ማጠናከር፡-**

ጥራትና ብዛትን መሰረት ያደረገ የምርት አቅርቦት በማሳደግ፣ በገበያ ተኮር ምርቶችን በማምረት፣ ምርት ማሰባሰብ፣ ማከማቸት፣ እሴት በመጨመር፣ ደረጃ በመስጠት፣ ማስታዋወቅ፣ የገበያ መረጃ በመስጠት፣ የማጓጓዝ፣ የገበያ ማዕከላትና መሰረተ ልማት በማስፋፈት ቀልጣፋ የምርት ቅብብሎሽ አገልግሎት አሰጣትን በመዘርጋት ሕግን መሰረት ያደረገ የጋራ የትስስር ተጠቃሚነት አሰራር ላይ ተመሰረተ ነው፡፡

**ሠ) የቁጠባ እና የፋይናንስ አቅርቦትን በማሳደግ አባላትን የኢንቨስትመንት ማስፋፋት፡-**

የአባላት የቁጠባ ባህል እንዲያድግ በማድረግ፣ የኅብረት ሥራ የፋይናንስ ተቋማትን በስፋት በማደራጀትና አገልግሎት አሰጣጣቸውን በማስፋፋትና በማጠናከር፣ ለግብዓት፣ ለምርትና ለአገልጎት ግብይት የሚውል የፋይናንስ አቅርቦት አማራጮችን በማስፋት፣ የአደጋ ስጋት ለመቀነስ የሚያግዙ አሰራሮችን በማጠናከር፡፡

**ረ) የኅብረት ሥራ መርሆ እና ሕግን መተግበር፡-**

የኅብረት ሥራ ማህበራት የተቋቋሙበትን መርህ እና በሕግ የበላይነት ማዕቀፍ ውስጥ በመስራት ምዝበራና ብክነት በመከላከል የአባላትን፣ የመንግስት እና የኅብረተሰቡን ተአማኒነት በማግኘት ተልዕኮአቸውን መወጣት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

**ሰ) የኅብረት ሥራ ጽንሰ-ሐሳብ በማስረጽ የኅብረት ሥራ ልማት ማሳደግ፡-**

ኅብረተሰቡ ስለ ኅብረት ሥራ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ጥናትን መሰረት ባደረገ ሁኔታ የተለያዩ ትምህርትና ስልጠና በተደራጀ መልኩ በመስጠት፣ የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን፣ አውደሪይ፣ ስምፖዚየም፣ ኤግዚቢሽኖችን በማዘጋጀት፣ የሚዲያ አውታሮችን በመጠቀም ሰፋፊ ካምፔኖችን በማካሄድ የኅብረት ሥራ ልማት ማፋጠን ነው፡፡

**ሸ) በሰለጠነ የሰው ሃይል መመራት፡-**

የኅብረት ሥራ አስተምህሮ እና ቢዝነስ መሰረት ያደረገ ከትምህርት ተቋማት ጋር በመቀናጀት በየደረጃው የሰለጠነ የሰው ሃይል እንዲኖር በማድረግ፣ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መሰረት አቅማቸውን በመገንባትና በማትጋት በኅብረት ሥራ ሴክተር ተቀጥረው በቁርጠኝነትና በትጋት እንዲሰሩ ማድረግ ነው፡፡

**ቀ) የስርዓተ ፆታ አካታችነት ቅድሚያ መስጠት፡-**

በኅብረት ሥራ ልማት የሴቶችና የወጣቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በአበልነት፣ በአመራርነት፣ ተሳትፏቸውን በማሳደግ በኅብረት ሥራ ማህበራት አባልነት ሴቶች 50 በመቶ፣ በአመራር 30 በመቶ፣ ወጣቶች በአባልነት 30 በመቶ፣ በአመራር 20 በመቶ እና በሁሉም በሴክተሩ ውስጥ በሚቀረጹ ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ ለማድረግ ልዩ ትኩረትና ድጋፍ በማድረግ ነው፡፡

**በ) ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር፡-**

የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሮቻቸው ከመንግስትና ሌሎች አካለት ጋር ሲለሚያገናኛቸው ግንኙነቱ ውጤታማ እንዲሆን አሰራሮችን በመዘርጋት፣ በጋራ ማቀድ፣ መገምገምና የጋራ አመራር በመስጠት እንዲተገበር በማድረግ ነው፡፡

**ተ) ማህበራዊ ሃላፊነት መወጣት፡-**

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከባህሪያቸው በመነሳት ለሰው ልጅ ቅዲሚያ የሚሰጡ ተቋማት በመሆናቸው በአከባቢያቸው ለሚኖረው ኅብረተሰብ ጥናት መሰረት በማድረግ ማህበራዊ ተቋማትን ማሟላት፣ አቅመ ደካሞችን መደገፍ፣ አካል ጉዳተኞች ለአከባቢ ጥበቃ በማድረግ፣ ምቹ የመኖሪያ አከባቢ እንደፈጠር በማድረግ የሕዝብ አለኝታነታቸውን በማረጋገጥ ነው፡፡

**ቸ) የኅብረት ሥራ ማህበራት የተለዩ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማስፋት፡-**

በየኅብረት ሥራ ማህበራቱ አካባቢ ያሉ የአደረጃጀት፣ የአመራር፣ የአሰራርና የተግባራት አፈፃፀም ምርጥ ተሞክሮዎችን በመለየት፣ በመቀመር እንደየነባራዊ ሁኔታ በጥናት ላይ በመመስረት እንዲሰፋ በማድረግ ነው፡፡

በተጨማሪም ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የሚጣጣሙ የውጭ ሀገር የኅብረት ሥራ ልመዶችንና ተሞክሮዎችን በመውሰድ እና ስራ ላይ ማዋል፡፡

**ነ) የመንግስት የመደገፍ ሚና፡-**

እንደኛ ባሉት ሀገር የኅብረት ሥራ ማህበራት ባልተጠናከሩበት ሁኔታ በየደረጃው የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራትን አለማ ከግብ ለማድረስ እንዲቻል መንግስት የመደገፍ ሚና ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

## 1.3. ለስትራቴጂው መነሻ ምክንያቶች

የኅብረት ሥራ ልማት ፖሊሲው መዘጋጀት መነሻ የሆኑ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም ለዚህ ፖሊሲ መቀረፅ ዋና መነሻ ምክንያቶች መካከል፡

- የአገሪቱን የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴ የሚመራና የወደፊት የጉዞ አቅጣጫውን የሚያመላክት ሁሉ-አቀፍ የኅብረት ሥራ ፖሊሲ አለመኖር፣
- የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የኅብረት ሥራ ማህበራቸው ባለቤቶች፣ ተጠቃሚዎች፣ የበላይ ተቆጣጣሪ እንዲሆኑ እና ያላቸውን ተሳታፊነትን ለማሳደግ፣
- አገሪቷ ያላትን እምቅ ሀብት በአግባቡ መጠቀም እንዲቻል በሶሸዮ ኢኮኖሚ ጥናት መሰረት አዋጭነቱን በማረጋገጥ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማደራጀት አለመቻል፤
- አገሪቷ የሚተከተለውን የኢኮኖሚ ስርዓት መሰረት በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ውጤታማ ሊያደረግ የሚችል፣ የሚደጋገፍ፣ የሚቀናጅ እና የሚናበብ ጠንካራ የኅብረት ሥራ ማህበራት አወቃቀር እንዲኖር፣
- የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት የጠቅላላ ጉባኤ፣ የሥራ አመራርና የቁጥጥር፣ የቅጥር ባለሙያዎች ግልፅ የሆነ ተግባርና ሃላፊነት እንዲኖራቸው እና በሠለጠነ ሰው ሃይል እንዲመሩ ለማድረግ፣
- የኅብረት ሥራ ማህበራት መንግስትንም ጨምሮ ከሌሎች አካላት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ግልፅና በመርህ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን፣

## 1.4. ኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጂ አስፈላጊነት

በአገራችን የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባሎቻቸው ተገቢውን አገልግሎት በመስጠት የአባላትን መሰረታዊ ችግሮችን በመፍታት፣ ተጠቃሚነታቸውን በመረጋገጥ፣ ሁሉ አቀፍ ድጋፍ በመስጠት በአገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ውስጥ የጎላ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ፡፡ በአገራችን እየተካሄደ ያለውን የኅብረት ሥራ ማህበራት የልማት እንቅስቃሴ በሚፈለገው ደረጃ ለማስቀጠል የሚደረጉ ጥረቶችን የሚገዳደሩ በርካታ ማነቆዎች አሏቸው፡፡ እነዚህ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ማነቆዎችን በቀጣይነት ለመፍታት የኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጂ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

DRAFT

በመሆኑም የኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጂ ማዘጋጀት ያስፈለገበት መሰረታዊ ጉዳዮች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

- የኅብረት ሥራ ማኅበራት የአባላትን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ በሀገር ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዕድገት ውስጥ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ለማድረግ፣
- ጠንካራ የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትና አሰራር እንዲኖር ለማድረግ፣
- የወጣቶች፣ ሴቶችና የአካል ጉዳተኞች በኅብረት ሥራ ማኅበራት ተደራጅተው የተሻለ አግልግሎት አግኝተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ፣
- የገጠርና የከተማ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ትስስር ስርዓት በተደራጀ መልኩ እንዲጠናከር በማድረግ ኅብረተሰቡ ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት ፊትሃዊ ተጠቃሚነቱ እንዲረጋገጥ ለማስቻል፣
- የኅብረት ሥራ ማህበራት ጥራትና ብዛት ያለውን የአባላትን ምርት በተደራጀ ሁኔታ በማሰባሰብ፣ በማከማቸት፣ እሴት በመጨመር፣ በተለይም በተቀናጅ የግብርና የኢንዱስት ፓርኮች ጋር የጠበቀ ትስስር በማድረግ ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ በቀጣይነት በማቅረብ አባላትና አገሪቱን ተጠቃሚነት ለማሳደግ፣
- የኅብረት ሥራ ማህበራት ሕግና ሕጋዊነትን ተከትለው በመስራት የአባላትን ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ የመልካም አስተዳደር ስርዓትን በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ለማስፈን፣
- የኅብረት ሥራ ማህበራት የቁጠባ የኢንቨስትመንት አቅም ለማሳደግ፣
- ሕብረተሰቡ በኅብረት ሥራ ማህበራት በመደራጀት የሚያገኘውን ጥቅም እንዲገነዘብ የኅብረት ሥራ ትምህርት፣ ስልጠና፣ ጥናትና ምርምር ስርዓት በተደራጀ ሁኔታ እንዲተገበር ለማድረግ፣ የስልጠና ተቋማዊ አደረጃጀትን በመፍጠርና በማጠናከር በተለይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሮቻቸውን በሰለጠነ የሰው ሃይል እንዲመሩ በማስቻል የሴክተሩን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ለማሰደግ፣
- የኅብረት ሥራ ማህበራት የኅብረተሰቡን የፋይናንስ አካታችነት እና የቁጠባ ባህልን በማሳደግ ቁጠባን በስፋት በማሰባሰብ የብድር አማራጮችን በማስፋት የኅብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ ችግር በመፍታት የአባላትን የኢንቨስትመንት አቅም የሚያሳደግ አባል ተኮር የአገልግሎት አሰጣጥን ለማጎልበት፣
- የአባላትን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና የሀገሪቱን ኢኮኖሚና ማኅበራዊ እድገት ለማፋጠን እና የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማጠናከር እና የአደረጃጀት አቅጣጫዎችን ለይቶ ለማስቀመጥ፣
- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የአገልግሎት አሰጣጥ በመመዘን የብቃት እውቅና ደረጃ በመስጠት የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ለማሻሻልና የድጋፍ አሰጣጥን ስርዓት ለመገንባት፣

DRAFT

- የኅብረት ሥራ ማህበራት ከመንግሥት እንዲሁም ከሌሎች ዓለም አቀፍ እና አገር አቀፍ አካላት ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት ግልፅ የአሰራር ስርዓት ለማስቀመጥ፣
- በገጠር የግብርና ምርትና ምርታማነትን እድገትን ለመደገፍ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች አቅርቦትና ስርጭት ተደራሽ ለማድረግ፣
- በአገር ውስጥ ግብይት በገጠርና በከተማ አምራችና ሸማቹን በማገናኘት የገበያ ሰንሰለቱን በማሳጠር የፍጆታ ምርቶችን እሴት በመጨመር በጥራት፣ በጊዜና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ፍትሃዊ የገበያ ዋጋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ፣
- በውጭ ግብይት ላይ በስፋት በመሳተፍ አባላት የተሻለ የገበያ ዋጋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ገቢያቸውን በማሳደግ አገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማድረግ፣
- የግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎትን ለማሻሻል፣
- በከተማ አካባቢ የዜጎች አንዱ ትልቅ አጀንዳ የሆነውን የከተማ ነዋሪዎች የቤት ችግር ለመፍታት የመኖሪያ ቤቶች ኅብረት ሥራ ማህበራትን በማደራጀት ዜጎችን የቤት ባለቤት ለማድረግ፣
- ለአባላትና አባል ላልሆኑትም የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣

ሴክቴሩ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት በመወጣት የአባላትንና የሕብረተሰቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ለአገር ኢኮኖሚ ግንባታ የበኩሉን ሚና እንዳያበረክት እንቅፋት የሆኑ ዋና ዋና ማነቆዎችን በመለየት የሚፈቱበት ስትራቴጂ ተለይተዋል፡፡ የስትራቴጂው ዝግጂት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተላይም ከዩኒቨርስቲዎች እና ከሴክተሩ ጋር አብረው ከሚሠሩ አጋር አካላት ጋር በተካሄደ ተከታታይ ምክክር እንዱሁም የሌሎች አገሮችን መልካም ተሞክሮ መሰረት በማድረግ እና የአገራችን ፖለቲካዊ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተዘጋጀ ነው፡፡

የዲሞክራሲያዊ ባህልን በማዳበር ያላቸውን ድርሻ ይበልጥ ለማጎልበት፣የተረጋጋ ኢኮኖሚና ማህበራዊ መሰረት ያለውን ሕብረተሰብ ለመፍጠር እና ድህነትን በማስወገድ ረገድ እያበረከቱ ያሉትን አስተዋጽኦ ለማሳደግ፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት በአገር አቀፍ እና በአለም አቀፍ ብቁና ተወዳዳሪ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተቋማት በመሆን በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ድርሻቸውን ለማጉላት የሚያስችል ስትራቴጂ በማዘጋጀት ችግሩን መፍታት አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡

## 1.5. ኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጂው ተፈፃሚነት ወሰን

በመላ ሀገሪቱ በተቋቋሙ የኅብረት ሥራ ማህበራት እና የኅብረት ሥራ ማህበራትን ጉዳይ በሚመለከት የሚሳተፉ አካላት ላይ የሚፈጸም ይሆናል፣

## 1.6. ኅብረት ሥራ ሴክተር ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች ፣

**ራዕይ፣** በ2025 ዓ.ም የአባላትን ኑሮ በላቀ ደረጃ የለወጡ እና በአገሪቱ ኢኮኖሚ ግንባታ የላቀ ሚና ያበረከቱ ጠንካራና ተወዳዳሪ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ተፈጥረው ማየት ነው፡፡

**ተልዕኮ፣**

‹‹በገጠርና በከተማ የሚኖረው ህብረተሰብ የአካባቢውን ሃብት መሰረት አድርጎ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሩን ለመፍታት በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ በተለያየ አይነትና ደረጃ የህብረት ስራ ማህበራትን በማጠናከርና በማደራጀት፣ የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን በማስፋፋት፣ አቅማቸውን በመገንባት፣ የግብይት ድርሻቸውን በማሳደግ፤ የመቆጠብ ባህልና መጠን በማሳደግ፣ የመበደር አቅም በመፍጠር፤ ህጋዊነታቸውንና ደህንነታቸውን በማስጠበቅ፤ የአገልግሎት አሰጣጣቸውን በማዘመን የአባላትን ተጠቃሚነት ያረጋገጡ ውጤታማና ተወዳዳሪ የኅብረት ስራ ማህበራትን መፍጠር፡፡››

## 1.7. የኅብረት ሥራ ትርጉም፣ መርሆ፣ ዕሴቶች፣

### የኅብረት ሥራ ትርጉም፡

*“ኅብረት ሥራ ማህበር” ማለት ሰዎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ስነልቦናዊና ሌሎች የጋራ ፍላጎቶቻቸውን ለሟሟላት እና በተናጠል ሊፈቱ ያልቻሏቸውን ችግሮች በጋራ ለማቃለል ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ሰዎች በፈቃደኝነት የሚያቋቁሙት፣ በጋራ ባለቤትነት የሚያስተዳድሩት፣ በኅብረት ሥራ መርህ መሠረት የሚመሩትና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚቆጣጠሩት ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ማህበር ነው” በሚል የጋራ ተደርጓል፡፡*

### የኅብረት ሥራ ማህበራት መሠረታዊ መርሆዎች፡

1. የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባልነት በማኅበራቱ አገልግሎት ለመጠቀም ለሚፈልጉና የአባልነት ግዴታዎችን ለመቀበል ፈቃደኛ ለሆኑ ሰዎች ሁሉ በጾታ፣ በማኅበራዊ አቋም፣ በዘር፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳተኝነት ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ ለሁሉም ክፍት ይሆናል፡፡

2. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ፖሊሲ በማውጣትና ውሳኔዎችን በማስተላለፍ የነቃ ተሳትፎ በሚያደርጉ አባላት የሚመሩ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች፣ እያንዳንዱ አባል እኩል ድምጽ ያለው እንዲሁም አንድ አባል አንድ ድምጽ ብቻ ያለው ይሆናል፡፡

3. ከትርፍ ላይ ለመጠባበቂያ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ተቀንሶ ከተቀመጠ በኋላ አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ በገዙት ዕጣ መጠን እና ባደረጉት ተሣትፎ መሠረት ቀሪው ትርፍ ይከፋፈላል፡፡

4. ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከሌሎች አካላት ጋር መንግሥትንም ጨምሮ ስምምነት የሚያደርጉት ወይም ከኅብረት ሥራ ማኅበራቸው ውጭ ከሚገኝ ምንጭ ገንዘብ በመበደር ካፒታላቸውን ማሳደግ የሚችሉት

የአባላት ዲሞክራሲያዊ ቁጥጥርን በሚያረጋግጥ፣የኅብረት ሥራ ማህበራቸውን የራስ በራስ ማስተዳዳር መብት በሚጠብቅ እንዲሁም የራስ አገዝ ባህሪውን በማይነካ ሁኔታ መሆን ይኖርበታል፡፡

5. የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት፣ ተመራጮች፣ ሥራ አስኪያጅ እና ሠራተኞች ለኅብረት ሥራ ማኅበራቸው ዕድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋሉ፤ ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ምንነትና ጥቅም ለሕዝቡ በተለይም ለወጣቱ ያስተዋውቃሉ፡፡

6. በአካባቢ፣ በሀገር አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት መዋቅሮች ጋር በመተባበር የኅብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴን በማጠናከር አባሎቻቸውን በሚገባ ያገለግላሉ፡፡

7. የኅብረት ሥራ ማኅበር አባሎቻቸው ባፀደቋቸው ፖሊሲች አማካይነት በአካባቢያቸው ላለው ኅብረተሰብ ዘላቂ ልማት ለማምጣት የሚያስችል ተግባር ያከናውናሉ፡፡

## የኅብረት ሥራ ማህበራት እና የአባላት እሴቶች፡

### የኅብረት ሥራ ማህበራት እሴቶች፣

ሀ. ራስን በራስ መርዳት፣

ለ. የግል ሃላፊነትን መወጣት፣

ሐ. የዴሞክራሲ ባህልን ማስፋፋት፣

መ. እኩልነት፣

ሠ. ፍትሃዊነት፣

ረ. ወንድማማችነት፣

### የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሥነ-ምግባር እሴቶች፣

ሀ. ታማኝነት፣

ለ. ግልፀኝነት፣

ሐ. ተጠያቂነት፣

መ. አሳታፊነት፣

ሐ. ማህበራዊ ኃላፊነት፣

መ. ለሌሎች ማሰብ፣

# ክፍል ሁለት፡- የኅብረት ሥራ ሴክተር ነባራዊ ሁኔታዎች

## 2.1. የነባራዊ ሁኔታዎች ትንተና

የኅብረት ሥራ በአገራች ከተጀመረ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ዕድሜ ቢያስቆጥርም ከባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በፊት ሥርዓቱን እና በሥርዓቱ ውስጥ ያሉትን ሹማምንቶች ከማገልገል ባለፈ በአገሪቱ የተጫወተ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትም ሆነ አባላትን እና ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር አጅግ ዘገምተኛ ጉዞ ላይ ነበር፡፡ ከዛሬ ሀያ ሶስት ዓመት ወዲህ ግን የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከማንኛውም ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው በራሳቸው ፍላጎት መሠረት እንዲደራጁ የአደረጃጀት ለውጥ ከተደረገ ወዲህ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ብዛት በቁጥርም ይሁን በዓይነት እጅግ ከፍተኛ ዕድገት አሳይተዋል፡፡

ይህ እንደተጠበቃ ሆኖ አሁን ከደረስንበት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዕድገትና ዘመናዊ በሆነ የንግድ ውስብስብነት ሥራ አንጻር፣ ከግብርና ወደኢንዱስትራላይዛሽን ለሚደረገው ሽግግር እና ለአገር አኮኖሚ ግንባታ የበኩላቸውን ሚና የበለጠ እንዲጫወቱ ለማድረግ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የአደረጃጀት፣ የመዋቅርና የአሠራር ለውጥ በሚያስፈልግበት ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ አንጻር የኅብረት ሥራን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ እንዲያስችል ያሉ ጥንካሬዎች፣ መልካም ኢጋጣሚዎች፣ ድክመቶች እና ሥጋቶችን በመለየት ማስቀመጡ በራሱ መልካም እንደሆነ መውሰድ ጥሩ ይሆናል፡፡

## 2.2. የኅብረት ሥራ ሴክተር ውስጣዊና ውጫዊ ትንተና (ጥ.ድ.መ.ሰ)፡

ለኅብረት ሥራ

ማህበራት እድገት ወሳኝ የሆኑ የኅብረት ሥራ ሴክተር ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ተተንትነዋል፡፡ ከውስጣዊ ጉዳዮች ዕይታ አንፃር ከአመራር፣ ከሀብት፣ ከሰው ሀይልና ከአገልግሎት አቅርቦት እንዲሁም ከውጫዊ ጉዳዮች ዕይታ አንፃር ከፖለቲካ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከማህበራዊና ቴክኖሎጂ ሁኔታዎች የኅብረት ሥራ ሴክተሩን የጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም ኢጋጣሚ እና ስጋቶች (ጥ.ድ.መ.ስ) ትንተና እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

## ሰንጠረዥ 1፡ ውስጣዊ ሁኔታዎች ትንተና

| ተ.ቁ | ውስጣዊ ጉዳዮች | ጠንክራ ጎን | ደካማ ጎን |
|---|---|---|---|
| 1 | አመራር | • ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነትን የሚከተል መሆኑ<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለመምራት በየደረጃው ያለው የአመራር አካላት ተነሳሽነት እየጨመረ ምመጣቱ፣<br>• በየደረጃው ያለው አመራር ተቀናጅቶ በመስራት በኩል ጥሩ ጅምሮች ማኖራቸው፣<br>• በአብዛኛው ከአቅም ገንቢዎች ጋር ያለው የስራ ግኑኝነት ጅምር መኖሩ፣ | • አመራር አካላት በሚፈለገው ደረጃ የአመራርነት ሚናቸውን አለመወጣት፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ መሆን፣<br>• የአባላት የባለቤትነት ስሜትና ተሳትፎ በሚገባው ደረጃ አለማደግ፣<br>• አመራርና ቅጥር ሠራተኞች የክህሎት፣ የእውቀትና የአመለካከት ክፍተት መኖር፣<br>• የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ደካማ መሆን<br>• አዋጆች ደንቦች መመሪያዎችና ማንዋሎች ተከትሎ አለመስራት፣<br>• የጠባቂነት አስተሳሰብ መኖሩ<br>• የሴቶችና የወጣቶች ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ትኩረት ሰጥቶ አለመስራት፣<br>• መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚደረጉ ጥረቶች ደከማ መሆን፣<br>• የአባላትን ችግር የሚፈታ እቅድ አሳታፊ በሆነ መንገድ አዘጋጅቶ አለመተግበር፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ማስፋፋት አለመቻል፡፡ |
| 2 | የሰው ሀይል | • በተለይ በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ደረጃ በሰለጠነ የሰው ሀይል ስራቸውን ለመምራት ጅማሮ መኖሩ፣<br>• አጫጭር ስልጠናዎች ለሠራተኛው መሰጠት መጀመሩ፣ | • በሰለጠነ የሰው ሃይል ተግባሮቻቸውን አለመምራት፣<br>• በአብዛኛው የቅጥር ሰራተኛ የእውቀት፣ የክሎትና አመለካከት ችግር ያለበት መሆኑ፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራትን አሰራር ስርዓት ተከትሎ አለመስራት፣ |
| 3 | ሀብት | • ካፒታላቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱ፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የቁጠባ በህልና መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ማምጣቱ፣<br>• በተለይ በአንዳንድ የኅብረት ሥራ ማህበራት የተሻለ መሰረተ ልማቶችን በመዘረጋት የተሻለ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸው፣<br>• የተሻለ የተለያዩ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት አግልግሎት መስጠት መጀመራቸው፣ | • ጠንካራ የንብረት አስተዳደር አሰራር ዘርግቶ መስራት አለመቻል፣<br>• የሀብትና የንብረት አያያዝና አስተዳደር ጠንካራ ባለመሆኑ ለምዝበራ እና ለብክነት የተጋለጠ መሆኑ፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራት ንብረቶች ከዓላማ ውጭ ላልተፈለገ ተግባር የሚውል መሆኑ፣<br>• አብዛኛው የኅብረት ሥራ ማህበራት አስፈላጊውን መሰረተ- ልማት በመዘርጋት አገልግሎት መስጠት አለመቻል፣<br>• የውስጥ አቅማቸውን አሟጦ በመጠቀም ካፒታላቸውን በሚፈለገው ደረጃ ማሳደግ አለመቻል፣<br>• የአገልግሎት ጊዜ የጨረሱና አግልግሎት መስጠት የማይችሉ ንብረቶችን የንብረት አወጋገድ ስርአትን ተከትሎ ማስወገድ አለመቻል፣<br>• ተካባችና ለአባላት ያልተከፋፈሉ ሀብት ስራ ላይ ለማዋል ግልፅ አሰራር አለመኖር፣ |

DRAFT

**…የቀጠለ**

| ተ.ቁ | ውስጣዊ ጉዳዮች | ጠንክራ ጎን | ደካማ ጎን |
|---|---|---|---|
| 4 | የአገልግሎት አቅርቦት | • የተሻለ አግልግሎት ተደራሽ ለማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በስፋትና በአይነት መደራጀታቸው፣<br>• የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን በስፋት ማቅረብና ማሰራጨት መቻሉ፣<br>• የውጭ ግብይት ተሳትፎዋቸውን ተለይም በቡና ገብይት ላይ አበረታች ጥረት መኖሩ፣<br>• የቁጠባ ማሰባሰብና የብድር አግልግሎት አሰጣጣች እየተሻሻለ መምጣቱ፣<br>• የፊጆታ ምርቶችን ለአባላትና ለኅብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ በተሻለ ተጠቃሚ ማድረግ መጀመራቸው፣<br>• ከአባላት ለሚሰበስቡት ምርት የሚከፍሉት ክፍያ የተሻለ መሆን፣ | • አብዛኞቹ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡት አገልግሎት ውስን እና ደካማ መሆን፣<br>• በኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ከጥራት ይልቅ ቁጥር ማበራከት ላይ ማተኮር፤<br>• ጠንካራ የአገልግሎት አሰጣጥን እንዲኖር የሚደግፉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴረሽኖች፣ ባንክ፣ ኢንሹራንስ እና የኅብረት ሥራ ሊግ ማቋቋም አለመቻል፣<br>• በአገልግሎት አሰጣጣቸው ደካማ የሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች ጠንካራ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በመዋሃድ ወይም በመከፈል አገልግሎት መስጠት አለመቻል፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራት የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የሚደረጉ የአቅም ግንባታ ተግባራት ችግር ፈች እና ተከታታይነት የሌለው መሆን፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራትን በተደራጀ መልኩ የክህሎት፣ የዕውቀት ክፍትተ የሚሞላ እና የጥናትና ምርምር የሚያካሂድ የልህቀት ማዕከላት አለመኖር፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራት የመረጃ አያያዝ ስርዓት ደካማ መሆኑ፣<br>• የውስጥ አሰራራቸውን ለማጠናከር የሚያስፈልጉ የአሰራር ስርአቶችን በሚፈለገው ደረጃ ዘርግቶ አገልግሎት መስጠት አለመቻል፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላትን በብዛት ማፍራት አለመቻል፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራት የአገር ውስጥ እና የውጭ ግብይት ተሳትፎአቸው በሚፈለገው ደረጃ አለማደግ፣<br>• በእሴት መጨመር እና አግሮ-ፕሮሰስንግ ተግባራት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያላቸው ተሳትፎ ደካማ መሆን፣<br>• በእቅድ ለይ የተመሰረተ ግዝዎች በወቅቱ አለመፈጸም<br>• በመካናይዘሽን አቅርቦትና አገልግሎት እና የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያላቸው ተሳትፎ ደካማ መሆን፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራት እርስ በርሳቸው እና ከሌሎች ተቋማት ጋር የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ ጠንካራና ውጤታ የግብይት ትስስር በመፍጠር በመስራት በኩል ውስንነት ያለባቸው መሆኑ፣<br>• የሚሰበሰበው የቁጠባ መጠን ውስን በመሆኑ የአባላትን የብድር ፍላጎት ማርካት አለመቻል፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራት ከላይ ወደ ታች እና አምዳዊ ግንኙነት በሚፈለገው ደረጃ የተጠናከረ እና የተናበበ አለመሆን፣<br>• የሚሰጡትን የማህበራዊ አግልግሎት በእቅድ ላይ ተመስርቶ በአሳታፊነት አለመምራት፣ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | • የኅብረት ሥራ ማህበራት አገልግሎታቸውን በተገቢው ማስተዋወቅ አለመቻል፣ |

## ሰንጠረዥ 2፡ ውጫዊ ሁኔታዎች

| ተ.ቁ | ውጫዊ ጉዳዮች | ምቹ ሁኔታዎች | ስጋቶች |
|---|---|---|---|
| 1 | ፖለቲካዊ ሁኔታዎች | • የዜጎች የመደራጀት መብት በህገ መንግስቱ መፈቀዱ<br>• መንግስት የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ቁርጠኛ መሆኑ፣<br>• የህብረት ስራ ማህበራትን የሚደግፉ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መኖራቸው፣<br>• አህጉራዊና ክፍለ አህጉራዊ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ግንኙነቶች እየተጠናከረ መምጣቱ፣<br>• የሀገሪቱ የውጭ ፖሊሲ ግኑኝነት እያደገና እየተስፋፋ መምጣቱ፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚደግፉ እና የሚቆጣጠሩ የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት ተደራጅቶ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑ፣<br>• ሰፊ የሕዝብ ተሳትፎን ለማረጋገጥ የሚያስች ያልተማከለ የአሰራር አቅጣጫ መኖሩ | • በየደረጃው ያለው አመራር የኅብረት ስራ ማህበራት በኢኮኖሚው ውስጥ ያላቸውን ሚና በውል ተገንዝቦ ድጋፍ አለማድረግ ችግር ሊፈጠር ይችላል፣<br>• በየደረጃው የሚገኘው አስፈጻሚዎች ዘንድ በኅብረት ሥራ በአዋጆች፤ ደንቦችና መመሪያዎች ዙሪያ እኩል ግንዛቤ ባለመኖሩ ተገቢውን ትኩረትና ድጋፍ ላይሰጥ ይችላል፣<br>• የመልካም አስተዳደር በሚፈለገው መልኩ አለመስፈንና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ሙሉ በሙሉ ላይወገድ ይችላል፣<br>• የአለም ፖለቲካል ኢኮኖሚ አለመረጋጋት የገበያ እጥረትና የልማት ድጋፍ መቀነስ<br>• በየደረጃው ጣልቃ ገቢነት መኖር፣ |
| 2 | **ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች** | • የገበያ መር የኢኮኖሚ ስርዓት መኖሩ፣<br>• የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እያደገ መምጣቱና ሰፊ ገበያ መፈጠሩ፣<br>• የግብርና ምርት እና ምርታማነት በየጊዜው እድገት እያስመዘገበ መሆኑ፣<br>• የፋይናንስ ተቋማት መስፋፋት፣<br>• አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያቀርቡ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት እየተስፋፋ መምጣታቸው፣<br>• በአለም ገበያ ጥራት ያላቸው የግብርና ምርቶች ተፈላጊነት እያደገ መምጣቱ፣<br>• አግሮ-ፕሮሰሲንግ ተቋማት እየተበራከቱ መምጣት፣<br>• በአገሪቱ ለውጭ ንግድ የሚሰጠው ትኩረትና ድጋፍ እየጨመረ መምጣቱ፣<br>• በአገሪቱ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እየተበራከተ መምጣቱ፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራት በኢንቨስትመንት መስክ እንዲሰማሩ የሚረዳ የህግ ማዕቀፍ መኖሩ፣ | • የአለም ኢኮኖሚ አለመረጋጋት እና የገበያ ዋጋ መዋዠቅ ችግር መኖር፣<br>• የፋይናንስ ተቋማት ለኅብረት ሥራ ማህበራት ብድር ለመስጠት የሚያስቀምጡት ቅድመ ሁኔታ ላያሰራ ይችላል፣<br>• የኅብረት ሥራ ማህበራት ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡት ምርት የዓለም አቀፍ የገበያ ጥራት ደረጃ መስፋርትን ላያሟሉ ይችላሉ፣<br>• በዓለም አቀፍ ገበያ ትስስር ለመፍጠር የመረጃ፣ የእውቀትና የክህሎት ክፍተት ሊኖር ይችላል፣<br>• ለአለም ገበያ የሚቀርበው የኤክስፖርት ምርቶች በሚፈለገው መጠን ላይኖር ይችላል፣<br>• በዓለም ላይ እየተከሰተ ያለው የአየር ንብረት ለውጥ በልማቱ ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትል ይችላል፣ |

DRAFT

| ተ.ቁ | ውጫዊ ጉዳዮች | ምቹ ሁኔታዎች | ስጋቶች |
|---|---|---|---|
| 3 | ማህበራዊ ሁኔታዎች | • በኅብረት ሥራ ማህበራት ሊደራጅ የሚችል በርካታ የሕብረተሰብ ክፍል መኖሩ፣<br>• የትምህርት ተቋማት መስፋፋትና የተማረ የሰው ሃይል በስፋት መኖሩ፣<br>• አጋዥ የሆኑ ባህላዊ አደረጃጀቶች በስፋት መኖራቸው፣<br>• ሰፊ የሰው ጉልበት፣ ምቹ የተፈጥሮ ሀብትና አመቺ ስነ ምህዳር መኖሩ፣<br>• መከላከልን መሰረት ያደረገ የጤና ፖሊሲን መሰረት ደረገ መሰረተ ልማት መስፋፋትና ጤናማ የሰው ሀይል ለማፍራት አስተዋእፆ ማድረግ፣<br>• ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ተጠቃሚና ተሳታፊ ለማድረግ ትኩረት መሰጠቱ፣<br>• በሀገሪቱ ያሉ የገበሬ ማሰልጠኛ ጣቢያዎች መኖራቸው፣<br>• በየትምህርት ቤቶች የኅብረት ሥራ ክበባትን ለማስፋፋት እና ግንዛቤ ለማስጨበጥ ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸው፣<br>• የመንገድ፣ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ የማብራት እና ሌሎች መሰረተ ልማቶች መስፋፋታቸው፣<br>• ለጎልማሶች ትምህርት ትኩረት መሰጠቱ፣ | • ሕብረተሰቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፋይዳ ላይ ያለው ግንዛቤና አመለካከት በሚፈለገው ደረጃ ላይዳብር ይችላል፣<br>• የአየር ንብረት ለውጥ ችግር ሊከሰት ይችላል፣<br>• ጠንካራ የስራ ባህልና አመለካከት በሚፈለገው ደረጃ ላይዳብር ይችላል፣<br>• መሰረተ-ልማቶች በሚፈለገው ደረጃ ላይስፋፋ ይችላል፣<br>• ስራ አጥነት በሚፈለገው መጠን ያለመቀነስ፣<br>• የህብረተሰቡ ከገጠር ወደ ከተማ መፍለስ፣ |
| 4 | ቴክኖሎጂያዊ ሁኔታዎች | • የዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች እየተስፋፋ መሆኑ፣<br>• ህብረተሰቡ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ያለው ተነሳሽነት እየጨመረ መምጣቱ፣<br>• የሚዲያ ተቋማት መስፋፋት፣<br>• የግብርና ቴክኖሎጂዎች መስፋፈት፣ | • የቴክኖሎጂ ውጤቶች አቅርቦት በሚፈለገው መጠን እና ጥራት ደረጃ ላይገኝ ይችላል፣<br>• የቴክኖሎጂ ውጤቶች ዋጋ እየናረ በመሄድ ከኅብረት ሥራ ማህበራት አቅም በላይ ልሆን ይችላል፣<br>• ህብረተሰቡ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክህሎት በሚፈለገው ደረጃ ላይዳብር ይችላል፣<br>• ቴክኖሎጂዎች ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሳይሰጡ ከአገልግሎት መውጣት |

# ክፍል ሦስት፡-የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀትና አወቃቀር የምንከተለው ስትራቴጂ

አገራችን ከምትከተለው የሶሽዮ-ኢኮኖሚ ስርዓት መሰረት በማድረግ በዬትኛውም ደረጃ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከመቋቋማቸው አስቀድሞ የኅብረት ሥራ መርህንና የአደረጃጀት መመሪያውን መሰረት በማድረግ በአባላት በቂ ግንዛቤ በማደራጀት እና አባላትና ኅብረት ሥራ ማህበራት በአሰራር ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የግንኙነት ስርዓት እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡ አገራችን ከምትከተለው ሶሽዮ-ኢኮኖሚ ስርዓት እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚተገብሩት ተግባር ዓይነትና ከባህሪያቸው አንፃር የኅብረት ሥራ ማህበራት የቀጣይ የአደረጃጀት የትኩረት አቅጣጫ በግልፅ ማስቀመጥ ያስቀምጣል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን መሰረታዊ ችግር ሊፈታ የሚችል አደረጃጀት እርከን በመዘርጋት ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተደራሽ የሆነ አገልግሎት በመስጠት አባላትን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ያሉባቸውን የማስፈፀም አቅም፣ የፋይናንስ ችግር፣ የአመራርና አስተዳደር፣ የገበያ ትስስር እና ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮችን በመፍታት የተቋቋሙለትን መሠረታዊ ዓላማ ለማሳካት ሲባል መርሆዎቻቸውን መሰረት በማደረግ የኅንዮሽና አምዳዊ ግንኙነቶችን በመፍጠር ጠንካራ የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴ ለመፍጠር ወሳኝና አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡ በአገራችን ፈጣን እና ቀጣይነት ካለው ልማት ኅብረተሰቡን በየደረጃው ተጠቃሚ በማድረግ ድህነትን በማስወገድና የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ በአገራቱ የልማት ውስጥ ወሳኝ መሳሪያዎች ከሆኑት መካከል የኅብረት ሥራ ማህበራት ያላቸው ሚና የላቀ ነው፡፡

ከዚህም አንፃር የኅብረት ሥራ ማህበራት አብዛኛውን የኅብረተሰብ ክፍል ያቀፉ በመሆናቸው አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በማስፋፋት የስራ እድል መፍጠር፣ የቁጠባ ባህልን በማሰደግ አማራጭ የብድር ምንጭ እንዲሆኑ ማስቻል፣ የወጪ ምርቶችን (የኤክስፖርት) በጥራትና በብዛት በማቅረብ የውጭ ምንዛሪን በማሳደግ፣ የምርት ማሳደጊያ ግብአቶችን አቅርቦትና ስርጭትን ተደራሽ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ እንዲሁም የከተማ እና የገጠር ትስስርን በማጠናከር ሂደት ያላቸው ሚና የጎላ በመሆኑ ነው፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም ዓይነትና ደረጃ የሚገኙ አጣቃላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴ የሚወክል፣ ለኅብረት ሥራ ማህራት እድገት የሚሰራ፣የኅብረት ሥራ ማህበራትን እንቅስቃሴ በብሔራዊ ደረጃ የሚመራ፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚቋቋሚና የሚተዳደር ነፃ ድርጅት በማቋቋም ጠንካራ የኅብረት ሥራ ማህበራት ንቅናቄ ለመፍጠር ነው፡፡

## አምድ1፡- በአገራችን የሶሺዮ-ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት

### ሀ/ ነባራዊ ሁኔታ

### በአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ሰዎች የጋራ ችግሮቻቸውን ለመቅረፍና ኪሳራን ወይም ወጪን ለመቀነስ ፍጹም በሆነ ፈቃደኝነት የሚያቋቁሚቸው ራስ ገዝ ድርጅቶች ናቸው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁት የአደረጃጀት ሂደቱን ተከትሎ በተደራጁ ሙሉና ነፃ ፍላጎት መሰረት በሚረጋገጥ የአዋጭነት የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ነው፡፡

በዚህም መሰረት ማንኛውም ዜጋ በኅብረት ሥራ ማህበር የመደራጀት ሕገ-መንግስታዊ መብቱን በመጠቀም ያለውን ሀብት፣ እውቀትና ጉልበት በማቀናጀት በራሱ ሙሉ ፈቃደኝነት ፍትሃዊ ተጠቃሚነቱን በሚያረጋግጡ በተለያዩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች በመደራጀት ያሉበትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቹን መቅረፍ ይችላል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት ሂደቱ የሚከናወነው በተቀመጠ ግልፅ የአደረጃጀት መመሪያ መሰረት ነው፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከመደራጀታቸው በፊት ያሉ አማራጭ እድሎችና በአካባቢ ያለውን ሀብት በመለየት፣ የሚደራጁባቸውን መልከዓ-ምድር አቀማመጥና የሕዝቡን የአሰፋፈርና አኗኗር ሁኔታ፣ የሚደራጀው የኅብረት ሥራ ማህበራት ውጤታማ የሚሆንበትን አቅጣጫ በመለየት ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ያለውን ሀብት አደራጅቶና አቀናጅቶ ለመጠቀም እንዲቻል የሚደራጀውን አካል የውስጥ አቅም እና ከውጭ ያሉትን እድሎችን በመለየት የሚደራጁ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ሕጋዊ፣ አከባቢያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ቴክኒካዊ ሁኔታዎችን በማጥናት ለአባላት ያላቸውን ፋይዳ እና አዋጭ መሆናቸውን በማረጋገጥ ተገቢውን ውሳኔ ለመስጥት የሶሽዮ-ኢኮኖሚ ጥናት ማጥናት አስፈላጊና ዋናው ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች በሚደራጁበት ጊዜ በሙያ የታገዘ ጥልቅ ጥናት ባይሆንም በአብዛኛው ከመደራጀታቸው በፊት የአዋጭነት ጥናት ይጠናል፡፡ በአብዛኛው የሚደራጁት የኅብረት ሥራ ማህበራት የሶሽዮ ኢኮኖሚ አዋጭነት ተጠንቶ የሚደራጁባቸው መስኮች በግልፅ ተለይተው አይደለም፡፡

በመዋሃድም ሆነ በመከፈል የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ቀደም ብሎ የአዋጭነት ጥናት ከተደረገ በኋላ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ ጠንካራ የአዋጭነት ጥናት ተካሂዶ በጥናቱ ላይ በመመስረት አዋጭ አይደለም ተብሎ ሳያይደራጅ የቀረ የኅብረት ሥራ ማህበር የለም፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁባቸው የስራ መስኮች እየተወሰኑ ያሉት በተደራጁ ፍላጎት ላይ እንጂ አጠቃላይ በጥናት በመለየት የትኩረት አቅጣጫ ተለይቶ አይደለም፡፡ ሀገራችን ከምትከተለው የልማት አቅጣጫ አንፃር ትኩረት ማድረግ

የሚገባን የሥራ መስኮችን የመለየት ስራዎች አልተሰራም፡፡ በማምረት፣ በአገልግሎት እና በሁለቱም ዓይነቶች በመደራጀት እየሰሩ ያሉት ግልፅ አሰራር ባለመኖሩ ምክንያት ሁሉም የተቀላቀለ ስራ ሲያከናውኑ ይታያል፡፡ ግልፅ አቅጣጫ ባለመኖሩ ምክንያት ለአብነት በማምረት ተግባር ላይ የተሰማሩ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያከናውኗቸው ግልፅ ተግባራት ያሏቸው ሲሆን ከዓላማቸው በመውጣት ሌላ ተግባር ላይ መሰማራት ሲፈልጉ ሁለገብ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት ብለው ሲደራጁ አንዳንድ የሁለገብ ገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው ይገኛሉ፡፡

## የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁባቸው የሥራ ዓይነቶች፡-

በአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁባቸው በጥናት የተለየ ግልፅ የሥራ አይነቶች ባይኖርም በገጠርም ሆነ በከተማ በአደራጁ፣ በባለድርሻ አካላት፣ በአቅም ገንቢዎችና በተደራጁ አባላት ፍላጎት ላይ በመመስራት የተፈለገው አይነት የኅብረት ሥራ ማህበራት ሲደራጁ ኖረዋል፡፡ የዚህ አይነት አደረጃጀት በአሁን ጊዜ ተመሳሳይ የሆኑ እና እርስ በራሳቸው የሚወዳደሩና አቅም የሌላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት እየተስፋፉ ይገኛሉ፡፡

ሆኖም የሚደራጁባቸው የስራ አይነቶች አዋጭነት እና ጠቀሜታ በሚገባ ስለማይጠና የተቋቋመለትን አላማ ሳያሳኩ ቆይተዋል፡፡ የአደረጃጀት አይነት ባህሪውን በመለየት የተለያየ ድጋፍ ለመስጠት ሙያው የሚጠይቀውን እውቀት ለማቀናጀት ችግር ፈጥሯል፡፡ በተለይ በዚህ ሁኔታ በተደራጁት የኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት፣ አቅም ገንቢዎችና የሚያደራጀው አካል ተናበው አለመስራት ይታያል፡፡

## የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት እርከን፡-

በየደረጃው የሚኖሩት የአደረጃጀት እርከኖች የራሳቸው የሆነ ተግባርና ኃላፊነት አላቸው፡፡ ግለሰብ አባላት የማይፈቱ ችግሮችን በጋራ በመሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር በመደራጀት፣ በመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር የማይፈቱ ችግሮች በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን በማደራጀት፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን የማይፈቱ ችግሮችን በኅብርት ሥራ ፌዴሬሽን በማደራጀት ችግሮች እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡

በዚህም መሰረት በሀገራችን ከመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ጀምሮ እስከ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን የተደራጀ ሲሆን በተለይ በኦሮሚያ፣ በትግራይ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች እስከ ፌዴሬሽን ተደራጅተዋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት እርከን ከሀገር ሀገር የተለያየ ነው፡፡ ለአብነት በጀርመን፣ በጃፓን፣ በኔዘርላንድ፣ በአሜሪካ፣ በኬንያ ፣ በዩጋንዳ፣ በደቡብ ኮሪያ፣ ያለው አደረጃጀት ሲታይ ወጥነት የለውም፡፡

ማናቸውም አደረጃጀት እርከኖች የአባላቱን የመደራደር አቅም፣ የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም እንዲሁም የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የአደረጃጀት እርከኑ ሊያጥር ወይም ሊረዝም ይችላል፡፡ በአንዳንድ አገራት በተለያዩ

ምክንያቶች ያላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት እርከን ሲረዝም እና እርከኖቹ በሰፉ ቁጥር ተጠቃሚ የሚሆኑ እንዳሉ ሁሉ እርከኑ ባጠረ ቁጥር የበለጠ የሚጠቀሙ ሀገራት አሉ፡፡ ይህም ሆኖ ሁለቱም የራሳቸው አንፃራዊ ጠቀሜታና ጉዳት አላቸው፡፡ ከዚህ አንፃር በሀገራችን ያለው አደረጃጀት ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ሦስት የአደረጃጀት እርከን ያለው ሲሆን የኅብረት ሥራ ማህበራት የመደራደር አቅም ሲያድግ በሂደት እየተዋሃዱ አባላትን የበለጠ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ ያሉት አደረጃጀቶች ራሳቸውን ችለው እርስ በርስ በመደጋገፍና በመረዳዳት አብረው ለማደግ የሚያደርጉት ጥረት የሚፈለገውን ያህል ባይሆንም የሚበረታታ ነው፡፡ ነገር ግን በየደረጃው ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀቶች እርስ በርስ የማይወዳደሩ፣ ጠንካራና ውጤታማ እንዲሆኑ ለእያንዳንዱ የጠራ ተግባርና ሃላፊነት በመስጠት የአላማ እና የሚና መደበላለቅ እንዳይኖር በማድረግና እሴት የማይጨምር እርከን እንዳይኖር በሕግና በአሰራር በመደገፍ የማጠናከር ስራዎችን በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡

## ለ. በኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት የሚታዩ ማነቆዎች፡-

### ማነቆ 1፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጭነት ባለው መልኩ አለመደራጀት፣

የኅብረት ሥራ ማህበራት ሲደራጁ የሶሽዮ ኢኮኖሚ አዋጭነት ጥናት አይጠናላቸውም፡፡ እንዲሁም አዋጭ የሆኑ የስራ መስኮች በግልፅ ተለይቶና ታምኖበት አይደራጅም፡፡ በየደረጃው ያሉ ባለሙያዎች ስለ ሶሽዮ-ኢኮኖሚ አዋጭነት ጥናት በቂ እውቀት እና ግንዛቤ ስለሌላቸው የኅብረት ሥራን መርህ ተከትሎ አጥንተው አያደራጁም፡፡

በመዋሃድም ሆነ በመከፈል በአዲስ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተገቢው የአዋጭነት ጥናት ተደርጎ እንደገና እንዲደራጁ አይደረግም፡፡ የአካባቢን ሀብትና የኅብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ አዋጭነት ጥናት እንዴት እንደሚጠና የሚያሳይ ግልፅ አሰራር አልተዘረጋም፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚፈቱት ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግሮች በግልፅ ሳይታወቁ እና ያሉ ሀብቶች በግልፅ ሳይለዩ በአንድ አከባቢ ያለምንም ጥናት በዘፈቀደ ተመሳሳይ ተግባር ላይ ኅብረት ማህበራት በውድድር ስሜት የጊዜያዊ ችግር መፍቻ ብቻ ሆነው እንዲደራጁ እየተደረገ ነው፡፡

### ማነቆ 2፡ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ያለ በቂ ግንዛቤና ፈቃደኝነት ማደራጀት እና የተጠናከረ ግንኙነት አለመኖር፣

የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያ ተከትሎ አለማደራጀት በስፋት ይታያል፡፡ የሕብረተሰብ አመለካከት በመቀየር የኅብረት ሥራ ፅንሰ-ሐሳብ ለማስረፅ እንዲቻል ባለሙያው በቂ የአቅም ግንባታ ስልጠና አያገኝም፡፡

አብዛኛው የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ስለኅብረት ሥራ ጽንሰ ሀሳብ፣ አስፈላጊነት፣ ጠቀሜታ ተረድተው በቂ ግንዛቤ በመያዝ በሙሉ ፈቃደኝነት እየተደራጁ አይደለም፡፡ በዚህ ምክንያት አባላት ያላቸው አመኔታ ዝቅተኛ በመሆኑ የታወጁ እጣዎች ስለማይገዙ ሳይሸጡ ለአመታት ይቆያሉ፡፡ ለሕብረተሰቡ የተለያዩ ግንዛቤ መፍጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም የማስተማሪያና ቅስቀሳ መድረኮች በሚገባ አልተፈጠሩም፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትም በዓላማዎችና አጠቃላይ ተግባራት ላይ በቂ ስትራቴጂ በመንደፍ የአባላትን ግንዛቤ ለማሳደግ አይሰሩም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት እና አባላት በጊዜያዊ ፍላጎት ማሟላት ላይ ማተኮር ይታያል፡፡ አባላት በኅብረት ሥራ ማህበር ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው፡፡ አባላት ምርታቸውን በሚፈለገው መጠን ለኅብረት ሥራ ማህበራቸው አያቀርቡም፡፡ አባላት የኅብረት ሥራ ማህበሩ በሚፈልጋቸው ጊዜ አይገኙም፡፡ አባላት በኅብረት ሥራ ማህበሩ የአመራር ምርጫ ሆነ በሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጉዳዮች ላይ በንቃት አይሳተፉም፡፡

በመሆኑም የሚታዩ ችግሮች እንዲፈቱ ከአባላት ጋር በጋራ በመሆን ከመፍታት ይልቅ የበይ ተመልካች በመሆን በሚታዩ ችግሮችና ደካማ ጎኖች ላይ አስተያየት ከመስጠት ባለፈ የመፍትሄ አካል እየሆኑ አይደለም፡፡

### ማነቆ 3፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትና አመዘጋገብ አሰራር ወጥነት የሌለው መሆን

የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትና የምዝገባ አሰራር ወጥነት የሌለው በመሆኑ ከክልል ክልል የተለያየ ነው፡፡ የጊዜያዊ የምስክር ወረቀት አጠቃቀም በሕጉ መሰረት ስራ ላይ አይውልም፡፡ በአብዛኛው ኅብረት ሥራ ማህበራት የእጣ ሠርተፊኬት ለአባላት በወቅቱ አይሰጥም፡፡ ስለ እጣ ሰርተፊኬት ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ ነው፡፡ የአባላት መነሻ ቁጥር በጥናት ያልተደገፈ እና የተደራጁን ችግር የሚፈታ አይደለም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የስራ ክልል አወሳሰን ላይ ችግር ይታያል፡፡

### ማነቆ 4፡- በሀገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁባቸው ግልጽና አዋጭ የሆኑ የስራ መስኮች በበቂ ሁኔታ መለየት አለመቻል

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁባቸው ግልፅ የሆኑ የስራ ዘርፎች አልተለዩም፡፡ በዚህም ምክንያት የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚተገብሩት ተግባር ዓይነትና ባህሪያቸውን መሰረት አድርጎ አለማደራጀት፡፡ የአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት የወደፊት የአደረጃጀትም ይሁን የአቅጣጫ ጠቋሚ ትኩረት ተሰጥቶት በግልፅ አልተቀመጠም፡፡

### ማነቆ 5፡- ግልጽና ወጥ የሆነ የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ዓይነትና ስያሜ አለመኖር

የኅብረት ሥራ ማህበራት በምን ዘርፍ ላይ ቢደራጁ ሊጠቅሙ እንደሚችሉ በግልፅ አልተቀመጠም፡፡ መንግስት ከሚከተለው የልማት አቅጣጫ የምንከተለው የአደረጃጀት የሥራ አይነት እና የሚያገኙት የድጋፍ ሁኔታ በግልፅ አልተቀመጠም፡፡

**ማነቆ 6፡- የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴ የሚመራ ጠንካራ አደረጃጀት አለመኖር**

በየደረጃ ያሉ የአደረጃጀት እርከኖች ተግባርና ሃለፊነት በግልፅ አለመቀመጥና አንዱ የሌላውን ተግባር ተክቶ መስራት፣ ችግር የማይፈቱ፣ እሴት የማይጨምሩና አላስፈላጊ ወጭ የሚፈጥሩ ሆነዋል፡፡ የኅብረት ሥራ ፌዴሬሽን አደራጃጀት ላይ የጋራ ግልፅነት አለመፈጠር፡፡ በየደረጃው የሚመሰረቱ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ ክልላቸው ወይም ወሰናቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አዋጭነትና ጠቀሜታን መሰረት ያደረገ አለመሆን ችግር ይታያል፡፡ የኅብረት ሥራ ዩንዬኖች በተጠናከረ ሁኔታ ተገቢውን አግልግሎት ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት አለመስጠት፡፡

**ማነቆ 7፡- ለኅብረት ሥራ ማህበራት ግልፅ መብትና ግዴታ፣ተግባርና ሃላፊነት አለመኖር**

በየደረጃው የተፈጠሩ የኅብረት ሥራ እርከኖች የእርስ በርስ ግንኙነትም ሆነ ከሌሎች ጋር ሲለሚኖራቸው የስራ ግንኙነት በግልፅ አለመታወቅና አልፎ አልፎ እርስ በርስ መወዳደር ይታያል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አሁን ከደረሱበት የእድገት ደረጃ አንፃር አደረጃጀት ጣራዉ ያላለቀ ቤት ሆኖ ቆይቷል፡፡ ከዚህም የተነሳ በዓለም አቀፍም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚወክል አካል አልተደራጀም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትም ሆነ ሀገራችን ማግኘት ያለባቸውን ጥቅም አላገኙም፡፡

**ሐ. ማነቆዎችን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች**

**በአገራችን የሶሺዮ-ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት፡**

***በ2025 ዓ.ም የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባለት እድገት በገጠር አርሶ/አርብቶ አደር 85 በመቶ እና በከተማ 75 በመቶ ይደረሳል፡፡***

**መፍትሄ 1፡- የአዋጭነት ጥናት ውጤትን መሰረት በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማደራጀት፣**

በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ ማንኛውም ዓይነት የኅብረት ሥራ ማህበር ከመደራጀቱ በፊት አስቀድሞ በሀገር አቀፍ ወይም በክልል ደረጃ ያለውን የአከባቢውን እምቅ እንዲሁም የኅብረት ሥራ ማህበራት በራሳቸው የሚፈጥሩትን ፖቴንሽል መሠረት በማድረግ ምን ዓይነት የኅብረት ሥራ ማህበራት ማደራጀት እንደሚቻል መወሰን ይኖርበታል፡፡ ለዚህም የሚያግዝ የሶሽዮ ኢኮኖሚ አዋጭነት ጥናት ይካሄዳል፡፡ ማንኛውም ዜጋ ያለው የመደራጀት መብት

DRAFT

እንደተጠበቀ ሆኖ የአከባቢውን ሀብት፣ እውቀትና የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አዋጭነትን መሰረት በማድረግ በበቂ ግንዛቤና ፈቃደኝነት ላይ በመመስረት እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡

በዚህም መሰረት የሚደረገው አዋጭነት ጥናት ሁሉንም አከላት ባሳተፈ ሁኔታ የአካባቢን ሀብትና የኅብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ እና ዜጎች የሚደራጁባቸው ግልፅና ውጤታማ የሆኑ የስራ መስኮችን በመለየት ለማደረጀት ስራ ዝግጁ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ አዋጭነት ጥናትን መሰረት ሳያደረግ፣ ያሉትን የአከባቢውን ሀብትና የሕብረተሰቡን ችግር ሳያገናዝብ በዘፈቀደ በውድድር ስሜት የሚደራጅ የኅብረት ሥራ ማህበር ከሚፈታው ችግርና ከሚያስገኘው ፋይዳ ይልቅ ጉዳቱ ስለሚያመዝን በዚህ መንገድ አይደራጅም፡፡

ማንኛውም ነባር የኅብረት ሥራ ማህበር በመዋሃድም ወይም በመከፈል በአዲስ መልክ መደራጀት ይችላል፡፡ ሆኖም ፈርሶ እንደገና ከመደራጀቱ በፊት አስቀድሞ በመዋሃድም ሆነ በመከፈል በአዲስ መልክ ሲለሚደራጀው የኅብረት ሥራ ማህበር የአሰራር ሂደቱን ተከትሎ ተገቢውን የአዋጭነት ጥናት ማካሄድ ይኖርበታል፡፡ በጥናት ውጤቱ መሰረት መልሰው ለሚደራጁት አባላት እና ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ከተወሰነ በኋላ ነባሩ የኅብረት ሥራ ማህበር ህጉን ተከትሎ እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡ ሕጉን ተከትሎ የማፍረስ ሂደት ከተካሄደ በኋላ በተጠናው የአዋጭነት ጥናት መሰረት አዲስ የኅብረት ሥራ ማህበር ይደራጃል፡፡

በማዋሃድ ወይም በመከፍል የሚደረግ አደረጃጀት ውሳኔ ተግባራዊ የሚሆነው በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ሲወሰን ነው፡፡ በተጨማሪ የሚደራጀው ኅብረት ሥራ ማህበር የአካባቢውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ እና ሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ እና ጉዳት የማያስከትል መሆኑ በመዝጋቢው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

በየደረጃው ያለውን አደራጅ ባለሙያ ስለሶሽዮ-ኢኮኖሚክ እና በአዋጭነት ጥናት እና አተገባበር ላይ በቂ ክህሎትና እውቀት ኖሮት በኅብረት ሥራ መርህ መሰረት የትኩረት አከባቢዎችን በመለየት ተገቢውን ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት እንዲያደራጅ ተከታታይነት ያለው ግንዛቤ ማበልፀግ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ ለዚህም የሚያግዙ አስፈላጊ የሆኑ አሰራሮችን በመዘርጋት፣ የማስፈፀሚያ ማኑዋል በማዘጋጀት ተመሳሳይና ወጥነት ያለው አሰራር እንዲኖር ተገቢው ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ለስራው ውጤታማነት የሚያግዝ የተለያዩ ሙያዊ የቴክኒክ ድጋፎች በተጠናከረ መልኩ ይሰጣል፡፡ ለዚህም አፈፃፀም በየደረጃው ያለው የመንግስት አካል ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው በመደገፍ እንዲጠናከሩ ያደርጋል፡፡

በግልፅ ፍላጎት ላይ ብቻ በመመስረት አዲስ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማደራጀት ብቻውን ውጤታማ አያደርግም፡፡ ስለዚህ ለወደፊት ዋነኛው የትኩረት አቅጣጫችን የሚሆነው በበቂ የሶሽዮ-ኢኮኖሚ እና አዋጭነት ጥናት ላይ በመመስረት ያሉ እምቅ ሀብቶችን በመለየት፣ የሚደራጁባቸውን የስራ መስኮች በመወሰን ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር የጋራ አሰራር በመዘርጋት ግልፅነት በመፍጠርና ግንዛቤን በማሳደግ ተግባረዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡

በአርሶ/አርብቶ አደሩ አመራረት ባህልና በአካባቢው አግሮ ኢኮሎጂ /ሥነ ምህዳር/ ላይ የተመሰረተ እስፔሻላይዜሽን አመራረትን መሠረት ያደረገ የተለያዩ ዓይነት የግብርና የኅብረት ሥራ ማህበራት የማደራጀት ነባሮቹን የማጠናከር ስራ በቀጣይ ተጠናክሮ የሚከናወን ይሆናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዘላቂ የግብርና ልማትን ለማረጋገጥና በየጊዜው የሚከሰተውን የድርቅ አደጋ ለመከላከል የአነስተኛ መስኖ ልማት ኅብረት ሥራ ማህበራትን በማደራጀት በአገሪቱ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በልዩ ትኩረት ይሰራል፡፡ በተለይም በአርብቶ አደሩ አከባቢ ከእንስሳት እርባታውና ተዋጽኦ ጎን ለጎን ከፍተኛ ዋጋ በሚያወጡ የኤክስፖርት ምርቶች፣ በምግብ ሰብል ምርት፣ በማዕድንና በዱር ሙጫ ምርት፣ በቃጫ ምርቶች ላይ እና በሌሎች ያካባቢውን ሀብት መሠረት ትኩረት የሚያደርጉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓነቶች በማደራጀት የህብረተሰቡን ገቢ ለማሳደግ ይሰራል፡፡

በሀገሪቱ ከተሞች ዋነኛ ችግር የሆነውን የመኖሪያ ቤት ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በአባላት ነፃ ፍላጎት መሰረት የመኖሪያ ቤቶች፣ የጋራ ቤቶች (የኮንዶሚኒዬም) እና በተለይም የገጠር ከተሞች መሠረት በማድረግ ወጭ ቆጣቢ የመኖርያ ቤቶችን በማገንባት ኅብረት ሥራ ማህበራትን በስፋት የማደራጀት ስራ ይከናወናል፡፡ ለዚህም ስኬት የኅብረት ሥራ ማህበራት ዋነኛ አማራጮች ቢሆኑም የሚያጋጥሙትን የአመለካከት፣ የክህሎት፣ የአሰራርና ግብዓት ችግሮችን በተደራጀ መልኩ ለመፍታት እንዲቻል በዘርፉ ላይ ከተሰማሩ አካላት ጋር ተደጋግፈውና ተቀናጅው ይሰራሉ፡፡ ለዚህም ግልፅ አሰራርና የአፈፃፀም አቅጣጫዎች ይዘረጋሉ፡፡

የገጠሩንም ሆነ የከተማውን ህብረተሰብ በማዕድን ግብይት የኅብረት ሥራ ማህበራት በማደራጀት ለዜጎች ሰፊ የሥራ ዕድል ከመፍጠር ባለፈ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ እንዲኖራቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመቀናጀት ተገቢው ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በአምራቹና በሸማቹ መካከል ቀጣይነት ያለው ጠንካራ የቢዝነስ ትስስር እንዲኖር ለማድረግ አዳዲስ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲደራጁና ነባሮቹ እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን በገጠሩ አካባቢ የሚኖረው ኅብረተሰብ የመሠረተ ልማት ተጠቃሚ ለማድረግ በተለይም በኤሌክትሪክና በቴሌኮሚኒኬሽን ኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲደራጁ የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው ተገቢው ድጋፍ እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

### መፍትሄ 2፡- ኅብረት ሥራ ማህበራትን በበቂ ግንዛቤና ፈቃደኝነት ማደራጀት እና የተጠናከረ ግንኙነት እንዲኖራቸው ማድረግ፣

የኅብረት ሥራ ማህበራትን ከማደራጀት አስቀድሞ ሕብረተሰቡ ስለኅብረት ሥራ ያለውን አመለካከት፣ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን እና ምቹ ሁኔታዎችን በመጠቀም በተከታታይ ግንዛቤ የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡ ለዚህም የአከባቢው ነባራዊ ሁኔታ መስረት በማድረግ በሀገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም እና ትላልቅ የንቅናቄ መድረኮች (public campaign) በማዘጋጀት ግንዛቤው በተሻለ

ደረጃ ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በዚህም መሰረት ህብረተሰቡን ለማስተማሪና ለመቀስቀስ በሚደረገው ሂደት የሚዲያ ተቋማት ቁልፍ ሚናቸውን እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማበራትን ለማደራጀት ያሉ የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያዎችን በመከተል እንዲደራጁ እና የተደራጁ አካለት ይህን አሰራር በመከተል ከኅብረት ሥራ ማህበራቸው ጋር የጠበቀ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህ ውጤታማ እንዲሆን የተደራጁ አባላት ስለኅብረት ሥራ ማህበራቸው አሰራር፣ አፈፃፀምና አካሄድ በግልፅ በየጊዜው በማወያየት አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ በበላይነት የመምራት ሚናቸውን ማስቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህም አንፃር እያንዳንዱ አባል የሚጠበቅበትን ግዴታ በአግባቡ አውቆ መወጣት ይኖርበታል፡፡

አባላት በሕጋቸው ውስጥ ላስቀመጡት አሰራር ተገዥ በመሆን በኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ተሳትፎ በማሳደግ ኃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ በየትኛው ደረጃ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት በድጋፍ አሰጣጥ ሰበብ የሚደረግ ጣልቃገብነት ሳይኖር በራሳቸው በአባላት ሙሉ ፍላጎትና ፈቃደኝነት መሰረት እንዲደራጁ ይደረጋል፡፡

በየደረጃው ያለው አደራጅ ባለሙያ ለኅብረተሰቡ ስለኅብረት ሥራ ማህበር ጽንሰ-ሐሳብና አስፈላጊነት ተከታታይነት ያለው ግንዛቤን የማስረፅ ስራዎችን መስራት እና ለኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የግንዛቤ ክፍተቶችን በመለየት የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት ይኖርበታል፡፡ የአደራጅ ባለሙያዎችን የክህሎትና የእውቀት ክፍተቶችን በመለየት በየደረጃው ለሚገኙ ባለሙያዎች የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ስልጠናዎችን በመስጠት የመፈፀምና የማስፈፀም አቅማቸው እንዲገነባ ይደረጋል፡፡

ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የትኛውም ዓይነት የኅብረት ሥራ ማህበር ከአባላት ፍላጎትና ፍቃደኝነት ውጪ እንዲደራጁ የሚደረገውን አሰራር አይኖርም፡፡ በዚህም መሰረት በየትኛውም ደረጃ በኅብረት ሥራ ማህበር የሚደራጁ አካላት ያለማንም አስገዳጅነትና ጣልቃ ገብነት በራሳቸው በተዳረጁ ሙሉ ፍላጎት መሰረት በማንኛውም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የልማት ዘርፎች የኅብረት ሥራ ማህበራትን እሴትና መርሆ በማይጥስና የተደራጁን ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ በተለዩ የሥራ መስኮች እንዲደራጁ ይደረጋል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት ማናቸውም ጉዳዮች ላይ አባላት በነቃ ተሳትፎ በባለቤትነት የመወሰን፣ የመቆጣጠርና የመጠቀም ስልጣንና ኃላፊነት ያላቸው አካላት ናቸው፡፡ አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበራቸው ጋር በመተዳደሪያ ደንብና በሚገቡት ውል መሰረት በወቅቱ ምርቶቻቸውን ለኅብረት ሥራ ማህበራቸው በማቅረብ ያለው የገበያ ችግር እንዲፈታላቸው ይደረጋል፡፡ በዚህም ሂደት የሚታዩ የግንኙነት፣ የአሰራርና የግንዛቤ ችግሮች በጥብቅ ክትትልና ድጋፍ እንዲፈቱ አስፈላጊ የአሰራር ስርዓት ዘርጋት እና የአቅም ግንባታ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ለዚህም ስራ የኅብረት ሥራ

ማህበራት ሌላውን አካል መጠበቅ ሳያስፈልግ ማንኛውንም የአቅም ግንባታ ትግብራትን በራሳቸው አቅደው ማከናወን አለባቸው፡፡

አባላት ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጉዳዮች ላይ በሕጋቸው መሰረት በመገናኘት በነፃነት ይወስናሉ፣ አመራሮቻቸውን ድሞክራሲዊ በሆነ መንገድ ይመርጣሉ፣ የሚጠበቅባቸውን ግዴታዎች ይወጣሉ፣ የወደፊት አቅጣጫዎችን ያስቀምጣሉ፣ የሚታዩ ችግሮች እንዲፈቱ በነቃ ተሳትፏቸው እንዲረጋገጥ ያደርጋሉ፡፡ አባላት ወደ ኅብረት ሥራ ማህበራቸው የሚመጡት በራሳቸው ሲቸገሩ ወይም አገልግሎት ለማግኘት ብቻ ሳይሆን አባላት እንዲገኙላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ሲፈልጓቸው ጭምር መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትም በራሳቸው አባላት ስለ ኅብረት ስራ ማህበሩ ራዕይ፣ ዓላማና ተግባራት ላይ የአባላትን ግንዛቤ በማሳደግ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የወደ ፊት የጉዞ አቅጣጫ የሚያሳይ ግልፅና አሳታፊ ስትራቴጂ መንደፍ ይኖርባቸዋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትን አሰራር የሚፃረር ወይም የሚከለክል ማንኛውም ዓይነት ሕገወጥ አሰራር አይኖርም፡፡

### መፍትሄ 3፡- ወጥነት ያለው የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀትና ምዝገባ አሰራር እንዲኖር ማድረግ፣

አባልነት በሁሉም ኅብረት ስራ ማህበራት ለሁሉም ክፍት እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ መሰረታዊ የኅብረት ስራ ማህበራት ዓይነቶች ካላቸው የስራ ባህሪና ውስን ሀብት ተገቢውን አገልግሎት ለሁሉም አባል መስጠት እንዲችሉ የአባላት ዝቅተኛው የመነሻ ቁጥር በሕግ በሚቀመጠው አግባብ ሆኖ አዋጭነቱ በጥናት በሚረጋገጠው መሰረት የሚደራጅ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን እንደየኅብረት ሥራ ማህበራቱ አይነት፣ የሚደራጁበት ሀብት ውስንነት፣ ከተደራጆች ቁጥር እና ካላቸው ልዩ ባህሪ በመነሳት የአባላት ዝቅተኛው የመነሻ ቁጥር በጥናት ሊወሰን ይችላል፡፡

ማንኛውም የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር የሚመዘገበው ክልሉ በሚወስነው በክልል ወይም በዞን ወይም በወረዳ መዝጋቢ አካላት ጋር ቀርቦ የሚመዘገብ ይሆናል፡፡ ማንኛውም አዲስ የሚቋቋም የኅብረት ስራ ማህበራት ዩኒዮን ወይም ፌዴሬሽን በተቋቋሙበት ክልል መዝጋቢ አካላት ጋር ቀርቦ ይመዘገባል፡፡ በሁለት ዞኖች መካከል የሚቋቋሙ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት በክልል ደረጃ ይመዘገባሉ፡፡ እንዲሁም በልዩ ባህሪያቸው ምክንያት በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጁ የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ በፌዴራል ደረጃ ባለው መዝጋቢ አካል ቀርበው የሚመዘገቡ ይሆናል፡፡

በዚህ መሰረት ለሚደረጅ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሕጋዊነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡ ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጠው የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በፌዴራል ወይም በክልል ደረጃ በሚስጥር የሚታተም ሆኖ በሚቀመጠው የሕግ አሰራር መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር በተመዘገበበት ዓላማና በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በተፈቀደለት የሥራ መስክ ብቻ ይሠራል፡፡ ማንኛውም ተመሳሳይ፣ አሳሳች፣ ለሞራል ተቃራኒ የሆነ እና በህግ ተቀባይነት የሌለው ስምና አርማ ያለው፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ጥናት የሌለው፣ የራሱ የሆነ የንግድ ስራ ዕቅድ የሌለው፣ የወጡ መመሪያዎችን የሚጻረር እና ሌሎች የምዝገባ መስፈርቶችን የማያሟላ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር አይመዘገብም፡፡

ሆኖም የኅብረት ሥራ ማህበር ያገኘውን የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሕግ በሚቀመጠው መሰረት ማሳደስ ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ያላሳደሰ ኅብረት ሥራ ማህበር የምዝገባውን ሕግ ተከትሎ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ለመዝጋቢው አካል በማስረከብ ህልውናውን እንዲያጣ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬንና ፌዴሬሽን አባል ሆነው የሚደራጁት አባላት ከመደራጀታቸው አስቀድመው ከመዝጋቢው አካል የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት ያገኙ መሆን አለባቸው፡፡ ማንኛውም መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ተቋቁመው አገልግሎት በመስጠት ላያ ያለ ወይም አዲስ ተቋቁሞ ሕጋዊ እውቅና እንዳገኘ በቀጣይ ወደ ሚገኘው ተመሳሳይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ወይም ፌዴሬሽን አባል መሆን አለበት፡፡

## የአገራችን ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁባቸው የሥራ መስኮች፡

### መፍትሄ 4፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በግልፅ በተለዩና አዋጭ በሆኑ የስራ መስኮች ማደራጀት

የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደሚተገብሩት ተግበርና ባህሪቸው አንፃር የሚደራጁባቸው መስኮች ሊለያይ እንደሚችል ቢታመንም ሀገሪቷ በሚኖራት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የሥራ ዘርፎች መሰረት በማድረግ በተለያዩ የኅብረት ሥራ ዓይነቶች በማምረት ወይም በአገልግሎት ወይም በማምረት እና በአገልግሎት ተግባራትን አጣምሮ የሚያከናከውኑ ሆነው ሊደራጁ ይችላሉ፡፡

**በማምረት ዘርፍ፡-** በማምረት ሥራ ላይ የተሠማራ ወይም ጥሬ ዕቃ ወደ አላቂ ዕቃ በመቀየር ወይም በከፊል የተሠሩትን ወደ አላቂ ምርትነት በመቀየር ለአገልግሎት በሚውል ደረጃ የሚያመርትና ለተጠቃሚዎች በማቅረብ ሥራ ላይ የተሰማራ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ አንፃር በማምረት ተግባር ላይ ከሚሳተፉ ዘርፎች መካከል በከፊሉ **በግብርና ዘርፍ** ማለትም (በእንሰሳት እና እንሰሳት ተዋፅኦ፣ በእርሻና የእርሻ ውጤቶች ኅብረት ሥራ ማህበር)፣ የግንባታ እና ኮንስትራክሽን ጥሬ ዕቃዎች እና ውጤቶች፣ የኢንዱስትሪ እና የዕደ ጥበብ ውጤቶች ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

በመሆኑም በሀገራችን በማምረት ተግባር ላይ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያከናውኗቸው ተግባራት፣ መብትና ግዴታቸውን በግልፅ በመለየት እና በሌሎች የስራ መስኮች ላይ ከተደራጁ ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ስለሚኖራቸው የስራ የግንኙነት አግባብ ግልፅ የሆነ አሰራር ኢንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ በዚህም መሰረት ሌሎች ሕጎችና



DRAFT

አሰራሮችን ባገናዘበ ሁኔታ ክፍተቶችን በማየት የአባላትን ችግር በሂደት ለመፍታት የሚያስችሉ የተለያዩ አገልግሎቶች በማስፋፋት የሚሰሩበት ጥናትን መሰረት ያደረገ አሰራር እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡

**በአገልግሎት ዘርፍ፡-** አባላት በግል ማግኘት የማይችሉትን የተለያዩ አገልግሎቶች በኅብረት ስራ ማህበራቸው አማካይነት በቀላሉ እንዲያገኙ በማድረግ ተግበር ላይ መሰማራት ይችላሉ፡፡ ከዚህም አንፃር በአገልግሎት ሰጪነት ሊሚሰማሩባቸው ከሚችሉ ዘርፎች መካከል በፊጀታ ምርቶች አቅርቦት (ሸማቾች) አገልግሎት፣ በጽዳትና ውበት ጥበቃ አገልግሎት (የቆሻሻ ማንሳት፣ የመኪና ዕጥበት፣ የአልባሳት ዕጥበት፣ የቤቶችና ግቢ ጽዳት፣የማስታወቂያ፣ ወዘተ) አገልግሎት፣ በገንዘብ ቁጠባና ብድር አገልግሎት፣ በመኖሪያ ቤቶች ስራ አገልግሎት፣ በባልትና ውጤቶች እና የምግብ ዝግጅት አገልግሎት ላይ የተሰማሩ ሊሆን ይችላል፡፡

**በማምረት እና በአገልግሎት ዘርፎች፡-** ሁለቱንም የማምረት እና የአገልግሎት ሁለገብ ተግባራት አጣምረው በአንድነት ለማከናወን በኅብረት ሥራ ማህበር በመደራጀት ሊሰማሩ ይችላሉ፡፡ በዚህም መሰረት የገበሬዎች ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማህበር (ምርት ተረክቦ መሸጥ፣ የምርት ማምረቻ ግብአት ለአባላት ማቅረብ፣ የፍጆታ ዕቃዎችን ለአባላት ማቅረብ) እና በመሳሰሉት ዘርፎች ላይ በመደራጀት አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፡፡

በቀጣይም በሀገሪቱ ያሉ እምቅ ሀብቶችን መሰረት ያደረገ ጥናት በማካሄድ ዜጎች በስፋት ተደራጅተው የሚሰሩበት ምቹ የስራ እድሎችን በመፍጠር ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በጋራ በመቀናጀት በልዩ ትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡ እንዲሁም ለወደፊት በልዩ ትኩረት ውጤታማ የሆኑ አደረጃጀቶችን በጥናት በመለየት ስፔሻላይዜሽንና ዳይቨርስፊኬሽንን እና የክልሎችን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት ባደረገ መልኩ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲኖሩ ይደረጋል፡፡

የማምረትና የአገልግሎት ተግባራትን አጣምረው ሁለገብ ተግባራትን የሚሰጡ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁበት ግልፅና የጠራ አሰራር እንዲኖር እና የተደበላለቁ አሰራሮችና አደረጃጀቶች እንዲስተካከሉ ይደረጋል፡፡በተለይ ሀገራችን ከምትከተለው ሶሽዮ-ኢኮኖሚ ስርዓት አንፃር በቀጣይ ኢንዱስትሪውን በግብዓት በመደገፍ ለማስቀጠል እንዲቻል በግብርና ዘርፍ፣ በኢንዱስትሪና እሴት በጨመር ዘርፍ እና በፋይናንስ ዘርፍ ተግባር ላይ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማበራት የሚደራጁ ሲሆን ነባሮቹም በአሰራርና በአደረጃጀት እንዲስተካከሉ ይደረጋል፡፡

### *የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁባቸው የሥራ ዓይነቶች፣*

### *መፍትሄ 5፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት ዓይነትና ስያሜ ግልፅና ወጥ ማድረግ፣*

በአገራችን እንደሚያከናውኑት ተግበርና ባህሪ አንፃር የተለያዩ ዓይነት የኅብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው ይገኛሉ፡፡ ይህን ማነቆ ለመፍታት ለወደፊት በዋናነት ትኩረት ተደርጎ የሚደራጁባቸው የስራ ዓይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

**የግብርና ምርቶች ማምረት እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት፡** አርሶ አደሩ ያመረተውን ዋና ዋና የግብርና ምርቶች በሰብል ምርቶች ግብይት (ቡና፣ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ቦሎቄ፣ አተር፣ ምስር፣ ሽምብራ)፣ እንስሳት ምርት ግብይት (በወተትና የወተት ተዋጽኦ፣ ቆዳና ሌጦ)፣ በዓሳ ምርት ግብይት፣ በደንና የደን ውጤቶች ምርት ግብይት፣ በቃጫ ምርቶች ወዘተ ምርቶችን በማሰባሰብ፣ በመከዘን፣ በማጓዝ፣ ደረጃ በመስጠትና ጥራት በማስጠበቅ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ በሂደትም በተሰበሰበው ምርት ላይ እሴት ጨምሮ የተሻለ የገበያ መዳረሻዎችን በማፈላለግ ሸጦ ከሚገኘው የገበያ ዋጋ ተጠቃሚ ያደርጋሉ፡፡

**በፍጆታ ምርቶች ግብይት** (የፍጆታ፣ የኢንዱስትሪ ምርቶችና የግብርና ግብዓት አቅርቦት፣) አባላት የሚፈልጉትን ጥራት ያለው የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችና አገልግሎቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በወቅቱ በማቅረብ ተጠቃሚ ያደርጋሉ፡፡

**በማምረት ሥራ** (የሁለገብ ሥራ የሚሰሩ)፡ የግብርና ምርቶችን ወይም የፋብሪካ ውጤቶችን በጋራ በማምረትና የገበያ መዳረሻዎችን በማፈላለግ ሸጠው ሁሉንም አባላት የዋጋው ተጠቃሚ ያደርጋሉ፡፡ በሁለገብ ተግበር የሚያከናውኑ የገበሬዎች ሁለገብ፣ የማዕድን አምራቾች፣ በኢንዱስትሪ እና በዕደ ጥበብ ውጤቶች አምራቾች፣ በባህርዛፍ ዘይት አምራች፣ የፋብርካ ውጤቶችና እርሻ ምርቶች አቅራቢዎች፣ ማዳበሪያ በጆይንት ቬንቸር አምራቾች፣ በግንባታ እና ኮንስትራክሽን ጥሬ ዕቃዎች ምርት ውጤቶች አምራቾች ላይ በመሰማራት አባላትን ተጠቃሚ ያደርጋሉ፡፡

**በፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ፡-** የገንዘብ ቁጠባና ብድር አገልግሎት፣ የባንክ አገልግሎት፣ በኢንሹራንስ አገልግሎት የኅብረት ሥራ ማህበራትን በማደራጀት ለአባላት እና ለህብረተሰቡ የተለያዩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በመስጠት ተጠቃሚ ያደርጋሉ፡፡

**የቤቶች አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ፡-** በመኖሪያ ቤቶች፣ የጋራ መኖሪያ (ኮንዶሚኒየም) ቤቶች፣ በሪል ስቴት ግንባታ፣ በተለይም የገጠር ከተሞች መሠረት በማድረግ ወጭ ቆጣቢ ቤቶች በማገንባት እና የሚፈልገውን ጥራት ያለው አግልግሎት በዝቅተኛ ዋጋና በወቅቱ ለመስጠት አባላትን በኅብረት ሥራ ማህበራት በማደራጀት ተጠቃሚ ያድረጋሉ፡፡

**የሃይልና የመሰረታዊ አገልግሎቶች (Energy & Utilities)፡-** ለአባላት ጥራት ያለው የገጠር ኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት፣ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ በትራንስፖርት ኅብረት ሥራ ማህበር በማደራጀት አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

**በምግብ ዝግጅትና አቅርቦት አገልግሎት፡-** ላይ በምግብ ዝግጅት፣ የባልትና እና የባልትና ውጤቶች፣ በአከባቢ ጥበቃና በጤና አግልግሎት (በጤና ጥበቃ፣ የጽዳትና ውበት ጥበቃ) ላይ እና በሌሎች በማህበራዊ አገልግሎቶች የተለያዩ አገልግሎቶችን ለአባላት በመስጠት ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ አባላት ከሚደራጁባቸው የአገልግለት ኅብረት

DRAFT

ሥራ ማህበራት (በህፃናት ጥበቃና እንክብካቤ፣ በአረጋዊያን እንክብካቤ፣ በቀብር ማስፈጸም ስርዓት እና በሌሎች ተግባራት ላይ ተደራጅተው አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

**የሠራተኞች የኅብረት ሥራ ማህበር፡-** በአንድ ድርጅት ወይም ተቋም ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች በጋራ የሚያቋቁሙት የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፡፡ ይህ አደረጃጀት በባህሪው የተለየና አዲስ ቢሆንም ውጤታማና ስኬታማ ከመሆኑ የተነሳ ታዋቂነትን በማግኘቱ በሀገራችን የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው በልዩ ትኩረት በማደራጀት አባል ሠራተኞችን ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል፡፡

**በማምረቻ ፋብሪካ/ ኢንዱስትሪ ተግባር ላይ የተሰማሩ፡-** በእርሻ መሣሪያዎች ማምረትና ማሰራጨት፣ በምርት ማሸጊያዎች ማምረትና ማሰራጨት፣ የስኳር ማምረቻ ኢዱስትሪዎች፣ የጥጥ መዳመጫ ፋብሪካዎች፣ የጥጥ መፈልቀቂያ ፋብሪካዎች፣ የሲምንቶ ማምረቻ ፋብሪካዎች፣ በቴክኖሎጅ አቅርቦት፣ በጥሬ ምርት በመረከብ በማቀነባበርና በማሰራጨት እና በሌሎች ተግባራት ላይ ዜጎች በኅብረት ሥራ ማህበራት ሊደራጁ ይችላሉ፡፡

**ሙያን መሰረት አድርገው የሚደራጁ፡-** ሂሳብ ባለሙያዎች፣ የመሃንዲስ ባለሙያዎች፣ የጤና ባለሙዎች፣ የሕግ ባለሙያዎች፣ መምህራን እና ሌሎች ሙያቸው በሚፈቅድ መሰረት በኅብረት ሥራ ተደራጅተው አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡፡ በዚህ መሰረት የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደሌሎቹ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚታዩ ይሆናል፡፡ ሙያን መሠረት አድርጎ የሚደራጅ ማንኛውም አባል ከሚመለከተው አካል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም ሙያ ላይ የተደራጁ ኅብረት ሥራ ማህበራት እሴት ጨምረው ለሚያመርቱት ምርት ወይም ለሚሰጡት አገልግሎት የጥራት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለባቸው፡፡

በሀገሪቱ የሚደራጅ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ የሚወሰን የራሱ መጠሪያ ስምና አርማ ይኖረዋል፡፡ በዚህ መሰረት የሚሰየመው ስምና አርማ እያንዳንዱ ኅብረት ሥራ ማህበር በሚያመርተው ምርት ወይም በሚሰጠው አገልግሎት ወይም በሚያመርተው ምርት እና በሚሰጠው አገልግሎትና ዓይነት መሰረት የሚሰየም ይሆናል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚያደራጅና የሚመዘግብ አካል በራሱ ክልል ውስጥ ተደራጅተው ለሚመዘገቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተመሳሳይ ስምና አርማ አይሰጥም፡፡ የተሰጠውን ስምና አርማ ያለበቂ ምክንያት መቀየር አይቻልም፡፡ ምክንያቱም በዚህ ስም በመጠቀም በርካታ ተግባራት ሲከናወኑበት የቆዩ ከመሆኑ የተነሳና የሦስተኛ ወገን ጥቅምን ሳይጎዳ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ሲፀድቅ የሚለወጥ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት የተለወጠውን አዲስ ስም ወይም አርማ መዝጋቢው አካል እንደገና ይመዘግባል፡፡ የተለወጠውን ስም እና አርማ የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም መዝጋቢው አከልም ሆነ ስሙን የቀየረው ኅብረት ሥራ ማህበር ለሕብረተሰቡ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

ከማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ስም መጨረሻ "ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማህበር" የሚል ሀረግ ስምና አርማው በጉልህ ተጽፎ በሚታይ ስፍራ መለጠፍ አለበት፡፡ እንዲሁም ስያሜውም በኅበረት ሥራ ማህበሩ ማንኛውም ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች፣ በሰነዶች፣ በመዛግብት፣ በማህተም፣ በማስታወቂያዎች እና ደብዳቤዎች ላይ ሙሉ ስሙ መጻፍና መለጠፍ አለበት፡፡

***ውጤታማ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት እርከን መፍጠር፣***

***መፍትሄ 6፡- የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴ ሊመራ የሚችል ጠንካራ አደረጃጀት መፍጠር***

የኅብረት ሥራ ማህበራት አወቃቀር እንደየኅብረት ሥራ ማህበራቱ ዓይነትና ተግባር ሊለያይ እንደሚችል ቢታመንም ሀገራችን ከምትከተለው የኢኮኖሚ ስርዓት አንፃር የኅብረት ሥራ ማህበራት አወቃቀር ሦስት የአደረጃጀት እርከኖች ወይም ደረጃዎች ይኖሩታል፡፡ እነሱም መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩንዬን እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ናቸው፡፡

የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አዋጭነት ታይቶ የኅብረት ሥራ ማህበራት እርከን አስፈላጊነት የሚወሰን ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ውሳኔው የኅብረት ሥራ ማህበራት ውሳኔ ሲሆን መንግስት ግን አዋጭነቱን በተመለከተ ከጣልቃ ገብነት ነፃ በሆነ መልኩ የማማከርና የሙያዊ ድጋፍ ሚናውን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡

ማንኛውም አባል በራሱ ፈቃድ በተደጋጋሚ ግዴታዎችን ባለማክበሩ ወይም በማህበሩ ላይ ጥፋት በመፈጸሙ ምክንያት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዲወጣ በጠቅላላ ጉባዔ ሊወሰንበት ይችላል፡፡ ማንኛውም የሚደራጅ የኅብረት ሥራ ማህበር ሥራውን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልገውን ካፒታል ማግኘት እንዲችል እኩል ዋጋ እና ብዛት ያላቸውን ዕጣዎች በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የሚከፈል በጠቅላላ ጉባኤ አስወስኖ እንዲሸጡ ያደርጋል፡፡

***መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር፡-*** በግለሰብ አባላት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ላይ ተመስርተው በተወሰነ አካባቢ በሚኖሩ ወይም በሚሠሩ ወይም በተወሰነ ሙያ ላይ በተሰማሩ ግለሰቦች የሚደራጅ ኅብረት ሥራ ማህበር ነው፡፡ ከልዩ ባህሪያቸውና ከስራው ስፋት በመነሳት የሚኖራቸው የሥራ ክልል መዳረሻው በአንድ ክልል ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን የሚሸፍን ሊሆን ይችላል፡፡

የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በአንድ ዞን ወይም ወረዳ ወይም ቀበሌ የሥራ ክልል ውስጥ በአደረጃጀት ሕጉ መሰረት አዋጭነታቸው ታይቶ ቀደም ሲል በሥራ ክልሉ የተደራጁትን የኅብረት ሥራ ማህበራትን ህልውና በማይነካ ሁኔታ የሥራ ክልል ውስጥ ከአንድ በላይ የተለያየ ዓላማ እና ተግባር ያላቸው መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊደራጁ ይችላሉ፡፡

እያንዳንዱ አባል በውሳኔ አሰጣጥም ሆነ በኢኮኖሚያዊና በማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አንድ ሰው አንድ ድምፅ በሚል መርህ መሰረት በቀጥታ እና በነቃ ሁኔታ የሚሳተፍበት ይሆናል፡፡ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አንድ ዓይነት ወይም ሁለገብ ተግባር ሊያከናውን ይችላል፡፡ በዚህ መሰረት መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በአባላት የሚመሩና የሚተዳደሩ ሲሆን እርስ በርስ እንዲደጋገፉ የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ፡፡

**መፍትሄ 7፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት መብትና ግዴታ፣ ተግባርና ኃላፊነት እንዲኖራቸው ማስቻል፣**

የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ግልፅ ተግባርና ሃላፊነት ያላቸው ሆኖ የሚኖራቸው ተግባርና ሃላፊነት መካከል በዋናነት ለአካባቢው ህብረተሰብ ስለኅብረት ሥራ ማህበር ፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ማስጨበጥ እና በአካባቢ ልማት እና ጥበቃ ሥራ ላይ ይሳተፋሉ፡፡

በተለይ ለአባላት በቅድመ ምርት እና በድህረ ምርት ላይ ስለምርት ጥራት ግንዛቤያቸውን በማሳደግ ጥራት ያለውን የአባላትን ምርት በመረከብ ዕሴት በመጨመር አባል ለሆኑባቸው ዩኒዬን ወይም ፌዴሬሽን ማስረከብ ወይም የተሻለ የገበያ መዳረሻ በማፈላለግ መሸጥ ይችላሉ፡፡ የቁጠባና ብድር ባህልን በማስፋፋት የአባላትን ኑሮ እንዲያሻሽሉ በማድረግ፤ ለአባላት የብድርና የህይወት መድን ዋስትና አገልግሎት በመስጠት፤ የአባላት የፋይናንስ አቅም የሚያጎለብቱ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ አባላት የአካባቢያቸውን ሀብት በመጠቀም ወደ ኢንቨስትመንት እንዲገቡ ያደርጋሉ፡፡

ከአባላት የሰበሰቡትን ምርት፣ ግብዓት እና የፍጆታ ዕቃዎች ማከማቻ የተለያየ አይነትና ደረጃ ያለው ዘመናዊ መጋዘን በራሳቸው እና ከሌሎች ድጋፍ ሰጪዎች ጋር ወጪን በመጋራት የመገንባት፤ ለአባላት በኪራይ የቴክኒክ መሳሪያዎች ወይም ማሽነሪዎች አገልግሎት የመስጠት፣ የአባላትን ክህሎት ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥልጠናዎችን ከመንግስት እና ከሌሎች አቅም ገንቢዎች ጋር ተቀናጅቶ የመስጠት፣ ለአባላትና ለዜጎች የሥራ ዕድል የመፍጠር ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡

**የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን፡-** ተመሳሳይ ዓላማና ተግባር ላይ የተሰማሩ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱ እየታየ ከአቅማቸው በላይ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን እንዲያስችላቸው የሚያቋቁሟቸው አደረጃጀት ሲሆን በቂ ኢኮኖሚዊ ብቃት እንዲኖራቸውና ተወዳደሪ ሆነው በዘላቂነት እንዲቀጥሉ ይረዳቸዋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እንደየክልሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መሠረት የሚደራጁና አመራራቸውም በውክልና ላይ የተመሰረተ ሆኖ በወረዳ፣ በዞን፣ በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ ሊደራጁ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ከምስረታ በኋላ ሌሎች ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸው መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በአባልነት ሊታቀፉ ይችላሉ፡፡ አደረጃጀቱ አስተዳደራዊ ወሰን ሊከተል ወይም ላይከተል ይችላል፡፡

የኅብረት ስራ ማህበራት ዩኒዬን የራሱ ተግባርና ኃላፊነት ያለው ሆኖ በዋናነት የሚያተኩረው የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ አቅም የሚያጎለብቱ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ ሥራ ላይ እንዲውሉ እገዛ ያደርጋል፡፡ የሥራ ፈጣራ ክህሎትን በማዳበር ዜጎች የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

አባል ኅብረት ስራ ማህበራት በሰለጠነ የሰው ሀይል እንዲጠቀሙ ዕገዛ በማድረግ እና የኦዲት ወጪ በመጋራት የሂሳብ አያያዝ ዘመናዊ እና ወቅታዊ እንዲሆን ያግዛሉ፡፡ ለአባለት ምርት፣ ግብዓት እና የፍጆታ ዕቃዎች ማከማቻ የሚሆን የተለያየ አይነትና ደረጃ ያለው ዘመናዊ መጋዘን በራሳቸው እና ወጪን በመጋራት በመገንባት ለአገልግሎት እንዲውል ያደርጋሉ፡፡ ዘመናዊ የምርት መሸጫ ሱቆች እና የምርት መሸጫ ማዕከላት በዋና ዋና ከተሞች በመገንባት አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋሉ፡፡ የአባላትን ምርት በመረከብ፣ ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ እሴት ጨምሮ በማቅረብ አባላት ከምርታቸው ፍትሃዊ የገበያ ዋጋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፡፡

አባላት ለሚገዟቸው ወይም ለሚከራዩት የቴክኒክ መሳሪያዎች ወይም ማሽነሪዎች አስፈላጊ መስፈርቶችን (እስፔስፍኬሽን) በማዘጋጀት ያግዛሉ፡፡ ለአባላት የቴክኒክ መሳሪያዎችን እና ማሽነሪዎችን የመጠገን እንዲሁም በኪራይ ወይም አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ለአባላት የብድር፣ የአነስተኛ መድን ዋስትና አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና ፌዴሬሽን በአባላት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ሳይገቡ ለታችኛው እርከን ድጋፍ መስጠት አለባቸው፡፡ በዚህም መሰረት በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች እና ፌዴሬሽኖች የተወሰኑ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የሚተላለፉ ውሳኔዎች በአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤ አባላትም ለነዚህ የጋራ አሰራሮች ይገዛሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና ፌዴሬሽን ከአባላት ጋር በሚያደረጉት ስምምነቶች መሰረት ደንብና መመሪያውን ተከትለው በየደረጃው የሚገኙ አባላትን ማገልገል ይኖርባቸዋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች በዋናነት የአባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች በመፍታት አባላት በተሰማሩበት መስክ ሥልጠና እና የማማከር አገልግሎት በመስጠት አባላት የኅብረት ሥራ ማህበር የመቆጣጠርና የመወሰን አቅማቸውን በማሳደግ እንዲጠናከሩ ያደርጋሉ፡፡ አባላት የሚፈልጉትን የተለያዩ የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን፣ የፍጆታ እቃዎችን በጅምላ በማቅረብ፣ ለዚህ የሚሆን አማራጭ ብድር በማቅረብና የመጋዘን አገልግሎት በመስጠት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፡፡ በአባላት ምርት ላይ እሴት መጨመር እና ሌሎች ተግባራት ያከናውናሉ፡፡ የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ዕቅድ መሰረት በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን የራሳቸውን እቅድ ያቅዳሉ፡፡

**የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን** ተመሳሳይ ዓላማና ተግባር ባላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒኖች ኢኮኖሚያዊ አዋጭነታቸው እና ማህበራዊ ጠቀሜታቸው ታይቶ በፌዴራል ወይም በክልል ደረጃ የሚደራጁ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ከመስራቾቹ ውጭ ሌሎች ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን

እንዲሁም በማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አባል ያልሆነ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ፌዴሬሽኑ ከተመሠረተ በኋላ አባል ሊሆን ይችላል፡፡

እነዚህ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖች ዘላቂና አስተማማኝ የአገር ውስጥና የውጪ ገበያ በመመስረትና ኢንዱስትሪንና ስፔሻላይዜሽንን በማስፋፋት ላይ ያተኩራሉ፡፡ የፌዴሬሽኖቹ አደረጃጀት በሚደረገው የአዋጭነት ጥናት መሰረት ሆኖ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ማለትም በግብርና ዘርፍ የሰብል አብቃይና አምራቾችና ግብይት፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ በቡና አብቃይና ግብይት፣ የማር አምራቾችና ግብይት፣ በፋይናንስ ዘርፍ በገንዘብ ቁጠባና ብድር እንዲሁም ግብርና ነክ ያልሆኑ የሸማቾች፣ መኖሪያ ቤት፣ እደ ጥበብ እና ሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖች ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡

በየደረጃው የሚመሰረቱ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ ክልላቸው ወይም ወሰናቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አዋጭነትና ጠቀሜታን መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር የሥራ ክልል ወይም ወሰናቸው ስነምዳርን በማከለ መልኩ፣ የመልካ ምድር አቀማመጥ፣ የሕዝቦች አሰፋፈር፣ የሕዝብ ጥግጋትን፣ በአየር ንብረት፣ ከሚሰማሩባቸው ተግባራት (የሥራ መስኮች) እና ሌሎች ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ ሊወሰን ይችላል፡፡ የእያንዳንዱ የኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ ክልል በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ የሚወሰን ሆኖ በአዲስ የሚዋሃዱ የኅብረት ሥራ ማህበራትም ቀደም ሲል የነበራቸውን የሥራ ክልል በአዲስ በሚደራጀው የኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ ክልል ውስጥ የሚጠቃለል ይሆናል፡፡

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የኅብረት ሥራ ማህበራት እርስ በርሳቸው እንዳይወዳዳደሩና ከተቋቋሙበት ዓላማቸው እንዳይወጡ እንዲያስችላቸው የመደራደር አቅማቸውን በማሳደግ በአንድ የስራ ክልል ተመሳሳይ ተግባር ላይ የተሰማሩ ተመሳሳይ ኅብረት ሥራ ማህበራት አይደራጁም፡፡

በየደረጃው ከመሰረታዊ እስከ ፌደሬሽን ባለው የአደረጃጀት እርከን የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት አንዱ የሚሰራውን ሌለኛው ደግሞ በመስራት እርስ በራሳቸው ተወዳዳሪና ተፎካካሪ በመሆን ተጠላልፈው እንዳይወድቁና ውጤታማ እንዲሆኑ በግልፅ የተቀመጡ ተግባርና ሃላፊነቶችን እንዲኖራቸው በማድረግ እንዲደራጁ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግን የሚደራጁት የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት እርከኖች በተሰማሩበት ተመሳሳይ የስራ መስክ ላይ ውጤታማ በሚያደረግቸው ላይ ትኩረት (specialization) በማድረግ ሊደራጁ ይችላሉ፡፡

በአገራችን እስከ ዛሬ ድረስ ጠንካራ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለመፍጠር አሁን ያለው የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴ (Movement) በኢኮኖሚና ማህበራዊ ጥንካሬያቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማሳደሩም በላይ በአሁን ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኅብረት ሥራ እድገት የደረሰበትን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ትስስር ፈጥሮ የአባላትን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ

ዓላመቸውን ለማሳካት ብሎም የሀገር ገፅታ ከመገንባት አንፃር በአደረጃጀት ያሉትን ችግሮችን በመፍታና የኅብረት ሥራ ፌዴሬሽኖችን በማደራጀት ጠንካራ የሀገር ውስጥና የውጭ ግንኙነት እንዲኖር ይደረጋል፡፡ በዚህም ሂደት የመንግስት ድጋፍ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ለአባላት እድገት የሚያግዙ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል የራሱ ተግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል፡፡ ከእነዚህ ተግባርና ኃላፊነቶች መካከል የአባላትን የፋይናንስ አቅም የሚያጎለብቱ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ ሥራ ላይ እንዲውሉ እገዛ ያደርጋሉ፡፡ የሥራ ፈጣራን በማበረታታት እና የሥራ ዕድል በመፍጠር እና በሰለጠነ የሰው ሀይል እንዲመሩ ድጋፍ ያድርጋል፡፡ የኦዲት ወጪ በመጋራት የአባል ኅብረት ስራ ማህበራት የስራ አፈፃፀም በወቅቱ እንዲመረመር የሂሳብ አያያዝ ዘመናዊ እና ወቅታዊ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ የአባላትን ምርት ተረክቦ እሴት በመጨመር ለውጭ ገበያ በማቅረብ አባላት ለምርታቸውን ፍትሃዊ የገበያ ዋጋ እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡

የአባላት ምርት የተሻለ ገበያ እንዲገን ለማድረግ በዋና ዋና ከተሞችና በመንገድ ዳር የገበያ ማዕከላትና የመሸጫ ሱቆችን በመገንባት አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋሉ፡፡ አስፈላጊ ባለሙያዎችን በመቅጠር በመሸነሪ እና ሌሎች መሳሪዎችን ለመግዛት የሚያስችል ስፔስፍኬሽን ዝግጅት ላይ ለአባለት ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ የተለያዩ ማሽነሪዎችን በመግዛት በኪራይ ወይም በነፃ ለአባላት አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ለአባላት የአነስተኛ መድን ዋስትና አገልግሎትና ከአባላት አቅም በላይ የሆኑ ሌሎች አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፡፡

ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በሀገሪቱ የወጡ የኅብረት ሥራ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያዎች እና ሌሎች መንግስት የሚያወጣቸው ህጎችን አክብሮ የመሥራት፣ በጠቅላላ ጉባኤ በጸደቁ እቅዶች መሰረት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ለሂሳብ ሥራ የሚያስፈልጉ መዛግብት፣ ሰነዶችና የተለያዩ ቅጻቅጾችን በማሟላት በአግባቡ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ ሂሳባቸውን በየዕለቱ መመዝገብ፣ በየወሩ በመዝጋት ወቅታዊ ማድረግ እና በህጉ መሠረት ማስመርመር፣ ከተጣራ ትርፍ ውስጥ ለኅብረት ሥራ ፈንድ የሚከፈለውን ሂሰብ በወቅቱ ፈንዱን ለሚያስተዳድረው አካል መላክ፣ ድርሻን በወቅቱ ማከፋፈል እና የስራ አፈፃፀምን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

በተጨማሪ ጥራት ያለውን ምርት እና አገልግሎት ለአባላት በወቅቱ የማቅረብ እና ማንኛውም ኅብረት ስራ ማህበር በተቋቋሙበት የሥራ ክልል በማምረት ሆነ አገልግሎት በመስጠት ሂደት አካባቢያቸውን የመጠበቅ፣ የማልማት እና የመንከባከብ ግዴታ አለበት፡፡

የአባላትን ምርት በወቅቱ የገበያ ዋጋ በማሰባሰብ በዚያው የምርት ዘመን ውስጥ በጥሬው ወይም እሴት በመጨመር የመሸጥ እና ለአባላት የሚሰጡ አገልግሎቶችን አባል ላልሆኑት ከሚሰጡ አገልግሎቶች የዋጋ ልዩነት እና የቅድሚያ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ አለባቸው፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖችን በመወከል የአባላትን ጥቅም የሚያስከብሩ አገራዊና አለማቀፋዊ የቢዚነስ ግንኙነቶችን ያደርጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ዋና ዓለማ አባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መሰረታዊ ችግሮችን ለይቶ በመፍታት በሚያድረጉት የጋራ ስምምነት መሠረት አግልግሎት እንዲያገኙ ማገዝ ነው፡፡

የአበል የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳባቸው ኦዲት የሚያደረግበት አሰራር እንዲኖር እና በወቅቱ ኦድት እንዲደረግ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ የኅብረት ሥራ አስተሳሰብና ጽንሰ-ሃሰብ ለማስረጽ እና ገጽታ የመገንባት ሥራ በመሥራት የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ከማጠናከር በተጨማሪ አገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት በመፍጠርና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመዘርጋት፣ ከአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ከአቅም በላይ የሆኑ የጅምላ ግብይት ሥራዎች ላይ ይሳተፋል፡፡

ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት እድገት የሚያግዙ የተለያዩ የእሴት መጨመሪያ ኢንዱስትሪዎች በማቋቋም ወይም አባላት እንዲያቋቁሙ አቅም በመፍጠር፣ ተግባር ተኮር ጥናት እና ምርምር በማካሄድ፣ የማማከር አገልግሎት በመስጠት፣ የሰው ሀብት ልማት በማካሄድ፣ የፋይናንስ እና የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴው በዘላቂነት እንዲቀጥል ያግዛል፡፡

ለኅብረት ሥራ ማህበራት ልማት የሚያግዝ የኅብረት ሥራ ፈንድ በማቋቋም እና በማስተዳደር፣ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅና የመሠረተ-ልማት ግንባታዎችን በማስተባበር እና በመደገፍ እንዲሁም ሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራትን እድገት የሚያስቀጥሉ ተግባራት ያከናውናሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበር አባል በተሳትፎው መጠን የሚሰጠውን አገልግሎትና ጥቅም የማግኘት፣ ጉባዔዎች ላይ የመካፈልና ድምጽ የመስጠት፣ የመምረጥና የመመረጥ፣ መብቶቹ እና ጥቅሞቹ ተከብረውለት በጥያቄው መሠረት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የመሰናበት መብቶች ይኖሩታል፡፡

## አምድ 2፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሥራ ግንኙነት ማጠናከር፣

### ሀ. የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሥራ ግንኙነት ነባራዊ ሁኔታ

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያካናውኗቸውን ተግባራት ውጤታማነት ለማገዝ ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የተለያዩ ግንኙነቶችን በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የዓለም አቀፍ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የጎንዮሽ እና አምዳዊ ግንኙነቶችን በመፍጠር አባላትን በተሻለ ደረጃ ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም መሰረት ተመሳሳይ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት የመደራደር አቅማቸውን

በማጠናከር በራሳቸው መፍታት የማይችሉትን ችግር በጋራ ተባብረው ለመፍታት አምዳዊ ግንኙነት በመፍጠር የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን በመመስረት ችግሮቻቸውን በመፍታት አባላትን በተሻለ ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

በተመሳሳይ የአደረጃጀት እርከን ላይ ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋናንስና የገበያ መዳረሻ ችግሮችን፣ ተግባሮቻቸውን በማስፋፋት ተቀናጅተውና ተደጋግፎ አብሮ ለማደግ የጎንዮሽ ግንኙነት ፈጥረው በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ መሰረታዊ የአምራች ኅብረት ሥራ ማህበራት ከገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ወይም ከሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በጋራ ስምምነት የሚያደርጉት የግንኙነት አግባብ አሏቸው፡፡

## ለ. የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሥራ ግንኙነት ከማጠናከር ያሉ ማነቆዎች፣

### ማነቆ 1፡- የጋራ ተጠቃሚነትን ያረጋገጠና ግልጽ የሆነ ግንኙነት አለመኖር

በየደረጃው ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያደርጉት የስራ ግንኙነት የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያላደረገና ችግሮቻቸውን የማይፈታ ከመሆኑ ባሻገር ትርፍን መሰረት ያደረገና የጋራ ጥቅምን የማያስጠብቅና ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት መኖሩ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አልፎ አልፎ ከአባላት ውጭ የሚያደረጉት ግንኙነቶች በአባላት አመኔታ የሌለውና ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ የሚፈለገውን ያህል ውጤት አላስገኘም፡፡ ከኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን እና ዩኒዬን ወደ ግለሰብ አባላት በቀጥታ ስለሚሄዱ ጥቅሞች የተዘረጋ ግልፅ አሰራር ባለመኖሩ ያልተጣጣመና ከአላማቸው የተለየ እድገት መታየቱ፡፡

በየደረጃው ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት በግልጽና በጋራ በስምምነት አለማስቀመጥ፣ ጠንካራ እና ግልፅ የግንኙነት፣ የድጋፍና የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት አለመኖር፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከየት ወዴት እንደሚያድጉ የሚያመላክት ግልፅ አቅጣጫ ባለመኖሩ የሚደረጉ ድጋፎች ጊዜያዊ በመሆናቸው የአባላትን መሰረታዊ ችግሮችን ለይቶ በመፍታት ላይ ያተኮሩ አይደሉም፡፡

### ማነቆ 2፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የተቀናጀ ግንኙነት አሰራር አለመኖር

በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚደረግ አምዳዊም ሆነ የጎንዮሽ የእርስ በርስ ግንኙነት ጠቀሜታ ግልፅ አሰራር የሌለውና የተቀናጀ አለመሆን፡፡ የሚደረገውም የእርስ በርስ ግንኙነት በመደጋገፍና በመተጋገዝ መርህ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን የበላይ እና የበታች ዓይነት ግንኙነት ያለው ነው፡፡

DRAFT

ይህ በመሆኑ በመሰራታዊና በዩኒየኖች መካከል ተቀናጅቶ ከመስራት ይልቅ በመካከላቸው አላስፈላጊ ውድድር ይስተዋላል፡፡ በጋራ ተቀናጅተውና የጋራ የሆነ እቅድ ኖሯቸው ያለውን ክፍተት ለመሙላት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ አነስተኛ ነው፡፡ አንዳንድ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች አባላትን ለመደገፍ ችግሮችን በጋራ ለይቶ በማቀድ በቅንጅት መፍታት አለመቻል፡፡ የአባላት ሙብትና ግዴት፣ ስለ አባላት የእጣ ድርሻ በግልፅ አለመቀመጥ ችግር ይታያል፡፡

### ሐ. ማነቆዎችን ለመፍታት የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ የመፍትሄ አቅጣጫዎች፡

#### መፍትሄ 1፡- ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ የግንኙነት አሰራር ስርዓት መገንባት፣

በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚደረገው ግንኙነት የበላይ እና የበታች አሰራር የሌለበት፣ ትርፍን በማካበት ላይ ብቻ ያልተመሰረተ፣ እርስ በርስ በመደጋገፍና በመተጋገዝ መርህ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት የግንኙነቱ ዋና ዓላማና መሰረት የሚሆነው የአባላትን የበላይ ወሳኝነትና ተጠቃሚነት ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚደረጉ ማናቸውም ግንኙነቶች ተመጋጋቢና የጋራ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ እንዲሁም ቀጣይነት ያለው የቢዚነስ ትስስርን ዕውን ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ መሆን አለበት፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚደረገው ግንኙነት የአባላት ቀጥተኛ ተሳትፎና የውሳኔ ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ሳይሸራረፍ ዲሞክራሲያዊ በሆነ አኳኋን የሚከበርበት የጋራ የአሰራር ስርዓት ይፈጠራል፡፡ በዚህም መሰረት የሚደረጉ ግንኙነቶች በአባላት ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረቱና ሕጋዊነት ያላቸው ይሆናሉ፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ግንኙነት በጋራ በተዘጋጀ አሰራር መሰረት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡ የትኛውንም ግንኙነት የሚያደረጉ የኅብረት ሥራ ማህበራት በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ መሰረት የተደራጁና የተመዘገቡ ብቻ ይሆናሉ፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ይሁንታ ካገኘ ብቻ ሕጋዊ ሆኖ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡

የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት ምርት በማሰባሰብ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ስያቀርቡ ዩኒዬኑ ደግሞ በተረከበው ምርት ላይ እሴት በመጨመር ለአገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ገበያ በማቅረብ ፍትሃዊ የገበያ ዋጋ ተጠቃሚ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም በየደረጃው መከናወን ሲለሚገባቸው ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ አሰራር በመዘርጋት በጋራ መግባባት ተቀናጅተው እንዲያከናውኑ ይደረጋል፡፡

የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግር በመፍታት ኅብረተሰቡን በመቀስቀስ ስለኅብረት ሥራ ማህበር ግንባዜ በማስጨበጥ የአባላት ምርትና ምርታማነት እንዲጨመርና ገቢያቸው አድጎ የማደራደር አቅማቸውን ለማሳደግ ይሰራሉ፡፡ የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት ምርቶች መሻጫ አማራጭ የገበያ ቦታዎችን በማፈላለግ ገበያ የሚፈልገውን ምርት ለማምረት እንዲቻል ለአባላት የገበያ መረጃዎችን በቅርበት

እንዲያገኝ ያደርጋሉ፡፡ ከአባላት ለሚሰበስቡት ምርት ማከማቻ የሚሆን የመጋዘን አገልግሎት መስጠት እና የአባላትን ችግር የሚፈቱ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ ይተገብራሉ፡፡

አባለት ጥራት ያለው ምርት በተገቢው መጠን የማምረት አቅምና ክህሎትን ለማሳደግ በየጊዜው የኤክስቴንሽን አግልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ተገቢውን የጥራት ደረጃ ምደባ በማውጣትና ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር የተሻለ የገበያ ዋጋ እንዲያገኙ ለማድረግ የሚረዳ በቅድመ ምርትና ድህረ ምርት ላይ የአቅም ግንባት ሥልጠና ይሰጣል፡፡

አባላት ሽጦ ማምረት የሚለውን የገበያ መርህ በመከተል ቀድመው የሸጡትን ምርት በገቡት ውል መሰረት ምርታቸውን በቅርፅ፣ በመጠን፣ በዓይነት፣ በይዘት በመለየት እሴት ጨምረው ለኅብረት ሥራ ማህበራት በጥራትና በወቅቱ በሚፈለገው መጠን ማቅረብ እንዲችሉ ተከታታይነት ያለው የምክርና የስልጠና አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን የኅብረት ሥራ መርህን ተከትለው በአከባቢ ልማትና ጥበቃ ስራዎች ላይ ይሳተፋሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ከአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነቶች ጠንካራና ግልፅ በሆነ አሰራር በመዘርጋት የሚከናወን ይሆናል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚደረገው ግንኙነት የአባል ኅብረት ሥራ ማህበራትን ህልውና እና ተጠቃሚነት በማይጎዳ ሁኔታ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት የሚደረጉት ግንኙነቶችም ዋና ትኩረታቸው የሚሆነው የጥራት ደረጃውን ተከትሎ የአባላትን ምርት በመረከብ እሴት በመጨመርና የተሻለ ገበያ መዳረሻዎችን በማፈላለግ አባላት የገበያ ዋጋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለአባላት የሀገር ውስጥና የውጭ ወቅታዊ የገበያ መዳረሻዎችን በመስጠት ከተለያዩ አካላት ጋር ቀጣይነት ያለው የገበያ ትስስር እንዲያደርጉ ያዛል፡፡

የአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት የቅድመ ኦዲት ስራዎች ላይ በማገዝ ለኦዲት ዝገጁ ማድረግና ኦዲት በማስደርግ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት፣ ሊከሰቱ የሚችሉ የአደጋ ወይም ስጋት በመቀነስ፣ የአባላትን የመፈፀም አቅም ለማሳደግ የአቅም ግንባታ ስልጠና እና የልምድ ልውውጦችን በማድረግ ጠንካራ የአሰራር ግንኙነት እንዲኖር ይደረጋል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት ህግና አሰራርን መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬንና በመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል ያለውን የግንኙነት ችግር የሚፈታ የአሰራር ስርዓ በመዘርጋት ጉዳዮች በቀጣይ በውይይት እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበር አባል መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎችና ውሣኔዎች የማክበርና ተግባራትን የማከናወን፣ ዝቅተኛውን የአባልነት የዕጣና የመመዝገቢያ ክፍያዎችን የመክፈል፣ የጋራ ንብረት የመንከባከብ፣ በገባው ውል መሠረት ወደ ገበያ ከሚያቀርበው ምርት እና ከገበያ ከሚገዛው አገልግሎት ወይም ምርት በውሉ መሰረት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ጋር የግብይት ግንኙነት የማድረግ፣ የወጡ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል፡፡

**የተቀናጀ የአምዳዊ የግንኙነት ስርዓት መገንባት፡-**

**መፍትሄ 2፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የተቀናጀ የግንኙነት አሰራር መገንባት፣**

በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚደረግ አምዳዊ ግንኙነት በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ልምዶችን ለመለዋወጥ የሚያስችሉ አሰራሮችን የተከተለና በጋራ መስማማት የሚመራ የአለቃና የምንዝር ወይም የአዛዥና ታዛዥ የሌለበት፣ የአባላት ቀጥተኛ ተሳትፎና የውሳኔ ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ሳይሸራረፍ ዲሞክራሲያዊ በሆነ አኳኋን የሚከበርበት የግንኙነት ስርዓት ይሆናል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለይኛው ኅብረት በመፍጠር እሴት በመጨመር፣ የግብይት ሰንሰለትን በማሳጠር ውጤታማ የግብይት ስርዓት ለመፍጠር፣ ሀብትን በአግባቡ በመጠቀም የመደራደር አቅምን ለማሳደግ፣ ወጥነት ያለውን ምርት በጥራት ለማግኘት አምዳዊ ግንኙነት ሊመሰርቱ ይችላሉ፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል በሚደረገው አምዳዊ ግንኙነት መኖሩ ለማምረት የሚያገለግሉ ሀብቶችን በአግባቡ ለመጠቀም እና ወጪዎችን ለመቀነስ፣ የተሻለ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸውን አመራርና ሠራተኞች ለማግኘት፣ የመደራደር አቅምን በማጎልበት በጅምላ የመግዛት እና የነጠላ ዋጋን የማስቀነስ፣ ተከታታይነት ያለው የማምረት ሂደት እንዲኖር በአይነት፣ በጥራትና በብዛት በሚቀርበው ፍላጎት መሠረት ለማቀናጀት ያገለግላል፡፡ ጤናማ ያልሆነ የእርስ በርስ ውድድርን በማስወገድ አቅርቦት ለማመጣጠን፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ምርት ጥራት በማስጠበቅ፣ ደረጃ በመስጠት (ግሬዲንግና ስታንደርዳይዚንግ)፣ በመሻግ፣ ልዩ ምልክት በመስጠት (ብራንድ) በመጠቀም የአባላትን ምርት ገበያ ላይ ተፈላጊነት እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚደረገው አምዳዊ ግንኙነት በጋራ የካፒታል ችግራቸውን ለመፍታት፣ የኢንቨስትሜንት አቅማቸው ለማሳደግ፣ በአገር ኢኮኖሚ ግንባታ ውስጥ ያላቸው አስተዋጽኦ ለማጎልበት ያግዛል፡፡ በተጨማሪም በአገር ውስጥና በውጭ ሀገር ያለውን ግብይት ድርሻ በማሳደግ፣ የአባላት ነጻ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ያረጋግጣል፡፡ ምርትና ምርታመነት እንዲጨምርና የሚሰጡት አገልግሎቶችን ተደራሽ ያደርጋሉ፤ የመሰረተ ልማት እንዲስፋፋ ያግዛሉ፡፡

**የተቀናጀ የጎንዮሽ የግንኙነት ስርዓት መገንባት፡-**

ሸማችና አምራች ኅብረት ሥራ ማህበራት በሚያደርጉት የጎንዮሽ ግንኙነት የአምራቹ የጥራት፣ የዋጋ መውረድ፣ በሸማቹ የዋጋ መናር ሳከሰት ዕርስ በርስ በመተጋገዝ አባላትን ተጠቃሚ የሚያደርግ ግንኙነት እንዲኖር ይደረጋል፤ ለዚህም የሚመሩበት የጋራ አሰራር ይኖራቸዋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአስተዳደራዊ ቁጥጥር አመችነት፣ የሥራ አድማስንና አገልግሎቶችን ለማስፋት፣ ተግባራትን በጋራ ለማከናወንና የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ፣ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል ሲባል ዘላቂነት ያለው የጎንዮሽ

ግንኙነት ሊመሰርቱ ይችላሉ፡፡ አምራቹንና ሸማቹን ከብዘበዛ በማዳን፣ ያልተበረዘ ምርት እና ትክክለኛ ዕቃ ወደ ተጠቃሚ ያደርጋሉ፡፡

በአምራችና ሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚደረግ ግንኙነት የገበያ ዋጋ ተጠቃሚ ለማድረግ፣ የተሻለ ቴክኖሎጅ፣ እውቀት፣ ክህሎት፣ ሀብትና ልምድ በመለዋወጥ አምራቹ በተሻለ ለማምረት እንዲበረታታ እንዲሁም ሸማቹ የገበያ ዋጋ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

በግንኙነቱ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ለማምርትና ለግብይት የሚሆን ብድር ለሁለገብ ኅብረት ሥራ ማህበራት በማቅረብ አርሶ/አርብቶ አደሮችን የፋይናንስ ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

## አምድ 3፡- ጠንከራ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ሊግ መፍጠር፣

### ሀ. የኅብረት ሥራ ማህበራትን ሊግ ለመፍጠር ያለው ነባራዊ ሁኔታ

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት እርከን ደረጃ ሳይሆን የኅብረት ሥራ ማህበራትን በሙሉ የሚወክል የቢዝነስ ስራ የማይሰራ በአቅም ግንበታ እና በስርዓት ዝርጋታ ላይ የሚሰራ ድርጅት ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊጉ ምክር ቤት በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴ አካል ሆኖ በብሔራዊ ደረጃ የኅብረት ሥራ ማህበራትን እንቅስቃሴ የሚያስተባብር የኅብረት ሥራ አፈቀላጤ ሆኖ ያገለግላል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ በአሁን ጊዜ በሀገራችን ሊደራጅ አልቻለም፡፡ ሊግን ለማደራጀት የኅብረት ሥራ ፌዴሬሽን መኖር የግድ አይሆንም፡፡ የሀገራችንን ኅብረት ሥራ ማህበራት ከዓለም ካሉት ሀገራት ጋር በኢኮኖሚና በማህበራዊ ለማስተሳሰር እጅግ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን የኅብረት ሥራ ሊግ ባለመደራጀቱ ምክንያት የሀገራችን ኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ የእውቀት፣ ተክኖሎጂ ሽግግር፣ የፋይናንስ ድጋፍ፣ የሰው ሀይል ልማት፣ ልምድ ልውውጦችን ለማግኘት አልቻለችም፡፡ ከዚህም ውጭ የሀገራችን ኅብረት ሥራ ማህበራት የዓለም አቀፍ ኅብረት ሥራ ማህበራት ኅብረት አባል ብትሆን ሀገራችን የአፍሪካ ህብረት መዲና በመሆኗ ብቻ የአለም አቀፍ የኅብረት ሥራ የአፈሪካን ቅርንጫፍ መቀመጫ መሆኗ አይቀርም፡፡ በዚህም በርካታ ጥቅሞቸን ልታገኝ ትችላለች፡፡

ሀገራችን የኅብረቱ አባል ባትሆንም የአለም አቀፍ ህብረቱን መርሆ በመውሰድ የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ የሕግ አካል አድረጋ በመጠቀም ላይ ትገኛለች፡፡ በተለይ የሀገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴ ሲታይ ከዓለም በከፍተኛ ደረጃ ላይ እንገኛለን፡፡ ለምሳሌ ኬኒያ ጥቅት የኅብረት ሥራ ማህበራትን ይዛ በአገር አቀፍ ደረጃ የኅብረቱ አባል በ (KSCCOU) አማካንነት በመሆኗ የአለም አቀፍ የኅብረት ሥራ ህብረት የአፍሪካ መቀመጫ በመሆን በርካታ ጥቅሞችን ሊታገኝ ችላለች፡፡

እንዲሁም ኡጋንዳ በሀገር አቀፍ ደረጃ የኅብረት ሥራ ኅብረት ወይም Uganda Cooperative Alliance (UCA) በማቋቋም ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ እንዲሁም በሌሎች የዓለም ሀገራት በተመሳሳይ መልኩ የኅበረቱ አባል በመሆን የየሀገራቸውን የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴውን ተጠናክሮ እንዲቀጥል እያደረገ ይገኛል፡፡ የነዚህን ሀገራት ልምድና ተሞክሮ በመውሰድ የኅብረቱ አባል ለመሆን ሀገር አቀፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ ማቋቋም ቅድሚያ የሚሰጠው አጭር ጊዜ የትኩረት አቅጣጫችን ይሆናል፡፡

## ለ. የኅብረት ሥራ ማህበራትን ሊግ ለመፍጠር ያሉ ማነቆዎች፡-

### ማነቆ 1፡- የሀገሪቱን ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚወክል የኅብረት ሥራ አካል አለመኖር

ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሊግ አደረጃጀት፣ አስተዳር እና የፋይናንስ ምንጩ ስለማይታወቅ አይሳካም ብሎ መስጋት፡፡ ተጠሪነቱ እና ያለው ግንኙነት ግልፅ አለመሆን፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ላይ ግልፅ ግንዛቤ ባለመኖሩ በአሁን ጊዜ በሀገራችን ሊደራጅ አልቻለም፡፡ ከዓለም ሀገራት ጋር በኢኮኖሚና በማህበራዊ ትስስር እጅግ ጠቀሜታው ያለው መሆኑን አለማወቅ ችግር ይታያል፡፡

የኅብረት ሥራ ሊግ ባለመኖሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት የእውቀት፣ ተክኖሎጂ ሽግግር፣ የፋይናንስ ድጋፍ፣ የሰው ሀይል ልማት፣ ልምድ ልውውጦችን በሚፈለገው ደረጃ ማግኘት አልቻሉም፡፡ ሀገራችን የአፍሪካ ህብረት መዲና በመሆኗ ብቻ የአለም አቀፍ የኅብረት ሥራ የአፈሪካን ቅርንጫፍ መቀመጫ የመሆን እድል ሊጉ ባለመቋቋሙ ተጠቃሚ ልትሆን አልቻለችም፡፡

## ሐ. ማነቆዎችን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፡-

### መፍትሄ 1፡- የሀገሪቱን ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚወክል የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ ማቋቋም

### የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ አደረጃጀት፡-

የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ በሁሉም አይነት የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጅ ይሆናል፡፡ ሊጉ የሀገሪቱን የኅብረት ሥራ ማበራትን የሚወከል ሆኖ የራሱ ጠቅላላ ጉባኤ፣ የስራ አመራር፣ ቁጥጥር ኮሚቴ እና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች ያሉት ድርጅታዊ መዋቅር እንዲኖረው ይደረጋል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጀው ሊግ ሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራትን አደረጃጀትና አመዘጋገብ አሰራርን ተከትሎ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በሚመዘግበው አካል ይሆናል፡፡

ሊጉ የኅብረት ሥራ ማህበራት መዋቅር አካል ሳይሆን የኅብረት ሥራ ማህበራትን በመወከል ጥቅማቸውን የሚያስከብር አካል ይሆናል፡፡ የሊጉን የእለት ተእለት ተግባራት የሚያከናውኑ ፕሮፌሽናል ባለሙያዎች ይኖሩታል፡፡ የፋይናንስ

ምንጮቹም ከኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚሰበሰብ መዋጮ፣ ከሚሰጣቸው ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ከሚያገኝ ገቢ እና የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮችን በመንደፍ ከሚገኘው ሆናል፡፡ ሊግ ተጠሪነቱ ለሀገሪቱ አጠቃላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሆኖ የሚሰራበት የራሱ የውስጥ አሰራር ስርዓቶች ይኖሩታል፡፡

## የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ በሀገር ውስጥ የሚኖረው ሚና

የኅብረት ሥራ ማበራት መረጃ ለመንግስትም ሆነ ለሌሎች አካላት ማድረስና ኅብረት ሥራ ትምህርት ስልጠና ይሰጣል፡፡ ሊጉ ከሚመለከታቸው አካለት ጋር በመሆን የኅብረት ሥራ ማህበራት ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ካሪኩለም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡ ለዚህም የሚሆን የኅብረት ሥራ ማህበራት የልዕቀት ማዕከላትን በማቋቋም በበላይነት ይመራል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት ዙሪያ የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮችን ለመደገፍ የሚያስችል የትምህርት፣ የኦዲት፣ የጥናትና ምርምር ስራዎችን የሚደግፍ ፋንድ ይኖረዋል፡፡ የኢንዱስትሪና ግብርንና ሴክተር ማዕከል ያደረገ ሁሉ አቀፍ የኅብረት ሥራ የጥናትና ምርምር ማዕከል ይኖረዋል፡፡

ሊጉ የኅብረት ሥራ ማህበራትን መብት የማስከበር፣ በኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ እና ድርሻ በማስጠናት ለመንግስትና ሌሎች አካለት ማቅረብ፣ የሀገሪቱን የኅብረት ሥራ ማህበራት ወክሎ አገር አቀፍና አለም አቀፍ የሥራ ግንኙነቶችን ያደርጋል፡፡ ለኅብረት ሥራ ማህበራት እድገት የሚረዳ የማማከርና የቴክኒክ አገልግሎት በመስጠት፣ የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያገኙ በማገዝ፣፣ የኅብረት ስራፅንሰ-ሃሳብ ግንዛቤ ማስረፅ፣ በአካባቢ ልማት ጥበቃ እና እንክብካቤ ላይ በመሳተፍ፣ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ( ሶፍተዌሮች)፣ ዘመናዊ የሂሳብ ዝርጋታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማገዝ ዋነኛ ተግባሩ ይሆናል፡፡

ዜጎችን በደን ልማትና ጥበቃ፣ በአፈር ለምነት ጥበቃና እንክብካቤ፣ በካርቦን ንግድ ላይ በኅብረት ሥራ ማህበራት በማደራጀት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደግፋል፡፡ በተፈጥሮ (በእሳት አደጋ፣ በመሬት መንቀጥቀጥና መንሸራተት፣ በጎርፍ) እና በሰው ሰራሽ (በማዕድን ቁፋሮ፣ በደን ጭፍጨፋና ውድመት፣ በኢንዱስትሪዎች ጭስ ብክለት) ምክንያት የተፈጠረ የአየር ብክለት፣ የተጎዱ ወይም የተራቆቱ አከባቢዎች ላይ ጥናቶችን በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መልሰው የሚያገግምበት እና ለዜጎች አገልግሎት ላይ የሚሰጥበት አሰራር በመንደፍ ኅብረት ሥራ ማበራት እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ ቅስቀሳዎችንና እንቅስቃሴዎችን በተጠናከረ መልኩ እንዲካሄዱ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ የተለያዩ ትላልቅ የሕዝብ የንቅናቄ መድረኮችን (campaign) በማቀናጀት እንዲተገበር ያደርጋል፡፡ ትላልቅ ሀገር አቀፍና አለም አቀፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት ወርክሾፖችን፣ ኮንፍራንሶች፣ ኤግዚቢሽኖች እና ሌሎች ትምህርታዊ ፕሮግራሞች እንዲካሄዱ ያደርጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ጽንሰ-ሀሳብ ለማስረፅ የሚረዱ የተለያዩ የኅብረት ሥራ ልሳን የሚታተምበት ሀገር አቀፍና አለም አቀፍ መጋዘን፣ ጆርናሎች የማሳተሚያ ቤት በማቋቋም እንዲሁም የራሱ የሚዲያ ተቋማት (ሬዲዮ፣

ቴሌቭዥን) ይኖረዋል፡፡ የሀገሪቱ የኅብረት ሥራ ታሪክ ለቀጣዩ ትውልድ ማስቀመጥ እንዲቻል የሁሉንም የኅብረት ሥራ ማህበራት የተደራጀ ታሪካዊ ቅርሶችን የሚያስቀምጥባትና የሚያስጎበኝበት የመረጃ፣ ቤተ-መጻሕፍትና ቤተ-መዘክር (ሙዝየም) ይኖረዋል፡፡

### የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በማጠናከር የሚኖረው ሚና፡-

የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ጠንካራ፣ ጤናማና ታታሪ ሆነው ተግባሮቻቸውን በማከናወን የሀገሪቱን ልማት የሚያስቀጥሉ ዜጎች እንዲሆኑ የግልና በአከባቢ ንፅህና አጠባበቅ፣ በስነ-ምግብ ስርዓት፣ በተላለፊ በሽታዎች ላይ አባላት ተከታታይነት ያለው ግንዛቤ የሚያገኙበትን አሰራር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይቀይሳል፡፡

ለኅብረት ሥራ ማህበራት እድገት የሚያግዝ ሁሉንም የኅብረት ሥራ ማህበራት ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበና ችግሮችን በመፍታት የወደፊት አቅጣጫ የሚያመላክት የፖሊሲና የስትራቴጂ ሃሳቦችን ያቀርባል፡፡ እንዲሁም የወጡ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን መሰረት በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሕጎችን፣ መተዳደሪያ ደንቦችን፣ የውሰጠ ደንቦችን፣ ለስራ የሚያግዙ ማኑዋሎችን እና የተለያዩ መጽሔቶችን ያዘጋጃል፡፡ የተዘጋጁ ሠነዶችን እንደየኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነት ተዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አግባብ ካለው የመንግስት አካል ጋር በመሆን በኅበረት ሥራ ማህራት ተግባራዊ የሚደረግበትን አሰራርና ስርዓት ይዘረጋል፡፡

### ለኅብረት ሥራ ማህበራት ሊጉ ከውጭ አካላት ጋር የሚኖረው ግንኙነት፡-

በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጀው የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሊግ በአህጉራዊ እና በአለም አቀፍ ደረጃ በተቋቋሙ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ድርጅቶች አባል ሊሆን ይችላል፡፡

በዓለም አቀፍ መደረኮች ለአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት አፈቀላጤ በመሆንና እንቅስቃሴያቸውን በማሳወቅ፣ መብትና ተጠቃሚነታቸውን በማስከበር፣ በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎና ሚናን በማጉላት የማስታዋወቅ (የፕሮሞሽን) ስራዎችን በስፋት የሚሰራ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት ሊጉ ሙሉ በሙሉ ከማናቸውም ዓይነት ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆኖ በመስራት በኅብረት ሥራ ማህበራትም አግባብነት የሌለው ጣልቃ ገብነት እንዳይኖር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትኩረት ይሰራል፡፡

ከዓለም አቀፍ የስራ ድርጅት (ILO) ጋር በመሆን በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ተቀጥረው ያሉ ሠራታኞች መብት እንዲከበርና ምቹ የስራ አካባቢ እንዲፈጠር በማድረግ ዜጎች የሚደራጁባቸውን አዳዲስ የስራ መስኮችን በጥናት በመለየት አማራጭ የስራ እድሎችን በመፍጠር፣ የዜጎችን ከከተማ ወደ ገጠር፣ እንዲሁም ወደ ሌላ ሀገር የሚደረገውን ስደት በማስቀረት ተረጋግተው እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡

## ክፍል አራት፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የማጠናከር፣ መፈፀምና የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራቴጂ

የአገራችንን ማህበረዊና ኢኮኖሚዊ ሁኔታን እና የልማታችን የትኩረት አቅጣጫን መሰረት በማድረግ ግልፅ በሆነ ጥናት የተለየና በቀጣይ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁባቸውን የኅብረት ሥራ ማህበራት አይነቶች ወጥነት ባለው ሁኔታ በመለየት የትኩረትና የድጋፍ አግባብ ለማስቀመጥ ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጠንካራ አመራር የሚመነጨው ጠንካራ ጠቅላል ጉባኤ ሲኖረው ነው፡፡ ጠናካራ አመራር በመገንባት ግልፅነት፣ ተጠያቂነት፣ አሳታፊነት፣ የሕግ የበላይነት ስርዓትን በመገንባት የአባላትን ባለቤትነት፣ ተጠቃሚነትና ተቆጣጣሪነት እንዲጠናከር በማድረግ ግልፅና ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡

አባላት በኅብረት ሥራ ማህበራቸው ጉዳይ በበላይነት መወሰን እንዲችሉ የአባላትን የባለቤትነት፣ ተቆጣጣሪነት አቅማቸውን በማሳደግ እና ያላቸውን የተሳትፎና የግንዛቤ ደረጃ በማሳደግ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህራት ዘንድ ያለውን የአሰራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት በመጠናከር ጥራት ያለው አገልግሎት በሚፈለገው ጊዜና መጠን በማቅረብ የአባለትን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡ በኅብረት ሥራ ማህራት ዘንድ ያለውን የአሰራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት በመጠናከር ጥራት ያለው አገልግሎት በሚፈለገው ጊዜና መጠን በማቅረብ የአባለትን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባሎቻቸው ውጤታማ የሆነ የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ እና ምርታቸውን ወደ ኢንዱስትሪ ምርትነት በመለወጥ ወይም ከኢንዱስትሪ ተቋማት ጋር በማስተሳሰር የተሻለ የገበያ አማራጭ አገልግሎት በማግኘት ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት ዘንድ ያሉ የኅብረት ሥራ ትምህርትና ስልጠና እና የጥናትና ምርምር ላይ ያሉትን ማነቆዎችን በመለየት ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት በመፍጠር ከኅብረት ሥራ ሴክተር ጋር ተቀናጅቶ በመስራት ውጤታማ የኅብረት ሥራ አቅም ግንባታ ለማድረግ ነው፡፡

ለኅብረት ሥራ ማህበራት ልማት የሚያስፈልግ በጥናት ላይ የተመሰረተ በራሳቸው ወይም በመንግስት ድጋፍ መሰረተ ልማት በቀጣይ ማስፋፋት የሚቻልበትን አሰራር ለማስቀመጥ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአማራሩ፣ የቅጥር ሠራተኞችንና የአባላትን አቅም በመከታተል መገንባት እቅድ ተይዞ መሰራት ይኖርበታል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የመፈፀምና ማስፈፀም አቅማቸውን በስልጠና በመገንባት ያስቀመጡ ግቦቻቸውን በማሳካት ለአባላት ጥራ ያለውና ወቅታዊ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ መንግስት በቀጣይነት ጥናትን መሰረት ያደረጉ ተከታታይነት ያላቸው የአቅም ግንባታ ሚናውን እንዲወጣ ለማድረግ፡፡ አቅም ገንቢዎች ሚናቸውን በተገቢው

መንገድ በመለየት ለኅብረት ሥራ ማህበራት በተደራጀና በተቀናጀ ሁኔታ የአቅም ግንበታ ድጋፍ መስጠት እንዲችሉ ለማገዝ ነው፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስራ የሚያከናውኑ ማናቸውም ባለድርሻ አካላት ከኅብረት ሥራ ሴክተር ጋር ተቀናጅተው በጥናት በተለዩ ክፍተቶች ላይ አቅም ግንባታ ሚናቸውን እንዲወጡ ለማድረግ፡፡

## አምድ 4፡- የአገራችን የልማት አቅጣጫና የኅብረት ሥራ ማህበራት ትኩረት

### ሀ. የአገራችን የልማት አቅጣጫና የኅብረት ሥራ ማህበራት ትኩረት ነባራዊ ሁኔታ

የኅብረት ሥራ ማህበራት በገጠር የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ፣ በሚፈለገው መጠን በወቅቱ ለአርሶ/አርብቶ አደሩ በማቅረብና በማሰራጨት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በሀገር የምርት እድገት ውስጥ ጉልህ ሚናቸውን በመወጣት ላይ ናቸው፡፡ ለወደፊት ያሉበትን ማነቆዎችንና ችግሮችን በመፍታት ያሉትን መልካም ጅምሮችን አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡

በአገራችን የድህነት ቅነሳ እና ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ያለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ሁለንተናዊ ተሳትፎ እውን ሊሆን እንደማይችል በመረዳት የበለጠ ተጠናክረው እንዳይሰሩ የሚያደርጉ የአሰራር፣ የአደረጃጀትና የአመራር ችግሮችን በመፍታት፣ አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን በመስጠት ተጠናክረው እንዲሰሩ ማድረግ ለልማታችን ቀጣይነት ወሳኝና ቁልፍ ጉዳይ ሆኖ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ከተማና ገጠርንም ለማስተሳሰር የተቀመጠ ግልፅ አሰራር ባይኖርም የኅብት ሥራ ማህበራት የግብይት ትስስር በመፍጠር በርካታ ተግበራትን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ያመረቱትን ምርት በመረከብና የመጋዘን አገልግሎት በመስጠት የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የገበያ መዳረሻዎች በመጠቀም አላስፈላጊ የገበያ ሰንሰለቶችን በማሳጠር አባላትን ከገበያ ዋጋ ተጠቃሚ የማድረግ ሥራ በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም መሰረት በኅብረት ሥራ ዩኒዬኖች አማካኝነት ከ2003 እስከ 2009 ዓ.ም ብቻ 100,501 ቶን ቡና እና 65,950 ቶን ሰሊጥ ወደ ተለያዩ ሀገራት በመላክ 544,659,852 የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምኒዛር ማስገኘት ተችሏል፡፡

በሀገር ውስጥም አምራች ኅብረት ሥራ ማህበራትን ከሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራትና ከሌሎች አካላት ጋር ለማስተሳሰር በርካታ ጥረት ተደርጓል፡፡ በተደረገው የግብይት ትስስር በአገሪቱ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ያልተፈለገ የዋጋ ንረት እንዳይከሰት የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት ረድተዋል፡፡ በተጨማሪም ኢሊኖ ባስከተለው ድርቅ ሳቢያ ዜጎች እንዳይጎዳ የምግብ ሰብል፣ የፊጀታ እቃዎች፣ የእንስሳት መኖ እና ሌሎችንም በማቅረብ የአገር አለኝታነታቸውን አረጋግጠዋል፡፡

ከዚህም ጎን ለጎን የኅብረት ሥራ ማህበራት የአርሶ/አርብቶ አደሩን ምርት ተቀብለው በውጭ ሀገራት በመላክ የሀገራችን አርሶ አደር ከውጭው ሀገር ጋር በማገናኘት የአገር ገጽታ ከመገንባት ባለፈ ለሀገሪቱ የወጪ ምርቶችን (የኤክስፖርት) በጥራትና በብዛት በማቅረብ የውጭ ምንዛሪን በማስገኘት አበረታች ውጤት ታይቷል፡፡

የኅብረተሰቡንና የአባላትን የቁጠባ ባህል ለማዳበር በርካታ አቅም ግንባታ ስራዎችና ንቅናቄዎች ተካሂደዋል፡፡ በሀገሪቱ ውስጥ እያደገ ለመጣው የቁጠባ ባህልና መጠን የኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ ትልቅ ነው፡፡ ለኅብረት ሥራ ማህበራትና አባላት አማራጭ የብድር ምንጭ በመሆን አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን እንዲስፋፉ በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል፡፡ የተለያዩ የስራ መስኮችን በማስፋፈትና የፈጠራ ክህሎታቸውን በማዳበር ከራሳቸው አልፈው ለዜጎች የስራ እድሎችን ፈጥረዋል፡፡ ይህም ለምናደርገው የወደፊት የልማት ጉዞ ጥሩ መደላድል በመፍጠር ላይ ይገኛሉ፡፡

## ለ. ከአገራችን የልማት አቅጣጫ አንፃር በኅብረት ሥራ ማህበራት ትኩረት ላይ የሚታዩ ማነቆዎች

### ማነቆ 1፡- የገጠርና የከተማ ኅብረት ሥራ ማህበራት የትስስር ስርዓት አለመጠናከር

የአገራችን ትርንስፎርሜሽን ለማረጋገጥ በገጠርና በከተማ መካከል የተጠናከረ ትስስር መኖር እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትም ለዚህ ስኬታማነት ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ሆኖም ይህን የትስስር አለማ ኅብረት ሥራ ማህበራት በተገቢው በመረዳት በሚፈለገው ደረጃ ትስስር ለማፍጠር አለመቻል ችግር ይታያል፡፡ ኅብረተሰቡም ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የሚደረገውን ትስስር ጠቀሜታ ጠንቅቆ ባለማወቅ በከተማ እና በገጠር የሚደረጉ ትስስሮች በመሳተፍ በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ እየሆነ አይደለም፡፡

የገጠርም ሆነ በከተማ ትስስር የሚያተኩረው የኢንዱስትሪ እቃዎችን ለገጠሩ ነዋሪ ኅብረተሰብ ማቅረብ እና የግብርና ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለከተማው ኅብረተሰብ በማቅረብ ለሁለቱም ወገኖች የጋራ እድገት ድልድይ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ሆኖም ግን በገጠርም እና በከተማ የትስስሩን ወሳኝነት በመረዳት በኩል ሰፊ የግንዛቤ ክፍተት ይታያል፡፡ አብዛኛው በከተማም ሆነ በገጠር የሚገኙ በኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮች ጤናማ ትስስር ለማድረግ አለመፈልግ ችግሮች ይታያሉ፡፡ በተጨማሪም ትስስሮችን ለማካሄድ የሚደረዱ ግልፅ አሰራሮች አለመዘርጋት ችግር በስፋት ይስታወላል፡፡ በምርት ወይም በአገልግሎት ላይ ስለሚደረጉ የትስስሮች በግልፅ አለማወቅ እና የእያንዳንዱ ሚና በሚገባ አለማስቀመጥ ዋናው እየጋጠመ ያለ ማነቆ ነው፡፡ የትስስሩን አላማ እና ፋይዳ ባለመረዳት ሰፊ የአፈፃፀም ግድፈቶች ይታያሉ፡፡

### ማነቆ 2፡- ኅብረት ሥራ ማህበራት የድህነት ማስወገድ እና የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ ወሳኝ ተቋማት ስለመሆናቸው በቂ ግንዛቤና አመለካከት አለመዳበር



DRAFT

በድህነት ቅነሳ እና በምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ያላቸውን ሚና በጉልህ አለመረዳት፤ አማራጭ የፋይናንስ ምንጭ መሆናቸውን በውሉ አለመገንዘብና እንደ እሳት ማጥፍያ ብቻ ማየት፤ ለዜጎች እየፈጠሩ ያለውን የስራ እድል በውል አለመገንዘብ ችግር፤ የኅብረተሰቡን ቁጠባ ባህል በማሳደግ ሂደት ያላቸውን ሚና አለመረዳት ችግር፣ በወጪ ምርቶችን (ኤክስፖርት) ውስጥ በመሳተፍ ለሀገር የሚያስገኙትን የውጭ ምንዛሪ ውስጥ ያላቸውን ሚና አለመረዳት፤ በሀገሪቱ ምርትና ምርታማነት እድገት ያላቸውን ቁልፍ ድርሻ በማየት ያሉባቸውን እንቅፋቶችን አለመፍታትና የገጠር እና ከተማ በማስተሳሰር ሂደት ያላቸውን ሚና በመገንዘብ አለማጠናከር የሚታዩ ዋና ዋና ማነቆዎች ናቸው፡፡

**ማነቆ 3፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን በመከፈል ወይም በመዋሃድ መልሶ አለማጠናከር**

በመከፈል መልሶ ለማደራጀት የሚፈቅድ ሕግ ቢኖርም ለማስፈፀም የሚረዳ የተሟላ ግልፅ ማስፈፀሚያ መመሪያእና አሰራር የለም፡፡ እንዴት እንደሚፈርሱ፡፡ አዲሱ እንዴት እንደሚደራጅ፡፡ የሦስተኛ ወገን ጥቅም እንዴት እንደሚጠበቅ እና ፈርሰው እንዲዋሃዱ በኃላፊነትና በተጠያቂነት ላይ ተመስርቶ የሚወስን አከል ማን መሆን እንዳለበት በግልፅ አልተለየም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በምን ምክንያት እንደሚፈርሱና እንደሚዋሃዱ የተቀመጠ ግልፅ አሰራር የለም፡፡

**ሐ. ማነቆዎችን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች**

***ካሉት የኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ 80 በመቶ የሚሆኑት ተጠናክረው በላቀ ደረጃ የሚፈለገውን አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡***

**መፍትሄ 1፡- የገጠርና የከተማ ኅብረት ሥራ ማህበራት የትስስር ስርዓት ማጠናከር**

በከተማም ሆነ በገጠር ለሚኖሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮች ያለባቸውን የአመለካከትና የክህሎት ችግሮችን በመፍታት ጠንካራ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ ይህን ትስስር ከምዝበራና ብክነት በፀዳ ሁኔታ ለማካሄድ የሚደረዱ ግልፅ የሆነ አሰራር በመዘርጋት በአላማ እና ፋይዳ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ በከተማ እና በገጠር በሚደረጉ የምርት ወይም የአገልግሎት ትስስሮች ላይ የእያንዳንዱ የኅብረት ሥራ ማህበር ሚናውን፣ ሃላፊነትና ተጠያቂነቱን አውቆ እንዲፈፅም ይደረጋል፡፡

እያንዳንዱ አባል የኅብረት ሥራ ማህበር የተደራጀበትን ዓላማ ጠንቅቆ እንዲያውቅና በኅብረት ሥራ መርህ፣ እሴት፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ መተዳደሪ ደንብ፣ በኅብረት ሥራ አደረጃጀትና አስተዳደር ላይ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና በየደረጃው ባሉ የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ይሰጣል፡፡ በገጠርም ሆነ በከተማ ቀጣይነት ያለውና በስርዓት የሚመራ የኅብረተሰቡንና የአባላትን የቁጠባ ባህል ለማዳበርና የፋይናንስ አቅሙን አጎልብቶ ጠንካራ ትስስር መፍጠር እንዲችል በርካታ የአቅም ግንባታና የግንዛቤ መፍጠሪያ ስራዎች እና ትላልቅ ንቅናቄዎች በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት በየደረጃው በተከታታይ እንዲካሄዱ ይደረጋል፡፡

በከተማ ያሉትን የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኀብረት ሥራ ማህበራትን ገጠር ካሉት ጋር በፋይናንስ እንዲተሳሰሩ በማድረግ እንዲሁም በከተማ ያሉ የሸማቾች ኀብረት ሥራ ማህበራትን ገጠር ካሉት የግብርና ኀብረት ሥራ ማህበራት ጋር በማስተሳሰር የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኀብረት ሥራ ማህበራት ለገጠሩ የፋይናንስ ምንጭ ሆነው እንዲያገለግሉ የሚያግዝ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

የኀብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ ስራ መስኮችን በማስፋፋትና የስራ ፈጠራ ክህሎታቸውን በማዳበር ከራሳቸው አልፈው ለዜጎች የተለያዩ የስራ እድሎችን በስፋት መፍጠር እንዲችሉ በማገዝ ለምናካሄደው የወደፊት የልማት ጉዞ ጥሩ መደላድልና አቅም እንደሚፈጥር በመገንዘብ በየደረጃው ያለ ማንኛውም አካል በልዩ ትኩረት የኀብረት ሥራ ማህበራት እንዲጠናከሩ በተግባር እንዲደግፍ ተገቢው ድጋፍ እንዲደረግ ይደረጋል፡፡ ኀብረት ሥራ ማህበራት በመተጋገዝ መርህ ላይ የተመሰረተ አምዳዊ እና የጎንዮሽ ግንኙነት በአደረጃጀት እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ ይህም አምራች አርሶ/አርብቶ አደርና የከተማው ሸምቶ አደር ኀብረተሰብ ትስስር መጠናከር ለሚደረገው ዋነኛው ምሰሶ ነው፡፡

### መፍትሄ 2፡- ኀብረት ሥራ ማህበራት የድህነት ማስወገድ እና የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ ወሳኝ ተቋማት ስለመሆናቸው በቂ ግንዛቤ ማስረጽ፣

የኀብረት ሥራ ማህበራት የድህነት ቅነሳ እና ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በከተማ እና በገጠር ወሳኝ ድርጅቶች ሆነው በማገልገል ውጤታማ ስራ በማስመዝገብ ላይ ይገኛሉ፡፡ የኀብረት ሥራ ማህበራት በአገራችን የልማት አሻራ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው የእድገታችን አጋዥ ምሰሶዎች በመሆናቸው ድህነትንና ኋላቀርነትን ማስወገድ በሚያስችል ሁኔታ መጠናከር ይኖርባቸዋል፡፡ ስለሆነም አገራችንን በምግብ ሰብል ራሷን በማስቻል የከተማ እና የገጠር የአርስ በርስ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ትስስር ላይ ከፍተኛ ተዋናይ ሆነው እንዲሰሩ ማስቻል ይኖርበታል፡፡

በገጠር የተለያዩ ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችንና (አፈር ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ የፀረ-አረም መድሃኒቴችን...) የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ፣ በሚፈለገው መጠን፣ በወቅቱና ቦታ ለአርሶ አደሩ አቅርቦ በማሰራጨት ምርትና ምርታማነትን በመጨመር አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ በሀገር የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ጉልህ ሚናቸውን መወጣት እንዲችሉ አስፈላጊ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ለዚህም የአሰራር፣ የአደረጃጀትና የአመራር ችግሮችን በመፍታትና አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን በመስጠት ተጠናክረው እንዲሰሩ በማድረግ በድህነት ቅነሳ እና በምግብ ዋስትና ድርሻቸውን እንዲወጡ በትኩረት ይሰራል፡፡

የኀብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት ጥራት ያለውን ምርት በመረከብና የመጋዘን አገልግሎት በመስጠት ተደራሽ አማራጭ የገበያ መዳረሻዎችን በማፈላለግ እንዲሸጥና በሂደትም ሊደርስባቸው የሚችለውን አላስፈላጊ የገበያ ሰንሰለት በማሳጠር አርሶ አደሩ ላመረተው ምርት በቀጥታም ሆነ በተዘዋወር መንገድ የምርቱ ፍትሃዊ የገበያ ዋጋ ተጠቃሚ በማድረግ የድህነት ቅነሳ እና የምግብ ዋስትና የማረጋገጥ የድርሻቸውን እንዲወጡ ይደረጋል፡፡



DRAFT

በተጨማሪ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአርሶ አደሩን የወጪ ምርቶችን (የኤክስፖርት) በብዛትና በጥራት ተረክበው በውጭ ሀገራት በመላክ የሀገራችንን አርሶ አደር ከውጭው አለም ጋር በማገናኘት የአገር ገጽታ ከመገንባት ባለፈ አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪን በማስገኘት በድህነት ቅነሳ ላይ የበኩላቸውን እንዲወጡ በትኩረት ይሰራል፡፡

***መፍትሄ 3፡- የኅብረት ሥራ ማህራትን በመከፈል ወይም በመዋሃድ መልሶ በማደራጀት ማጠናከር፣***

በጥናት ላይ በመመስረት አዳዲስ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ከማደራጀት ጎን ለጎን ቀደም ሲል ተደራጅተው ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት በራሳቸው ፍላጎት በመከፈል ወይም በመዋሃድ በጥናት ላይ ተመስርቶ እንደገና በመደራጀት እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግን በመከፈል ወይም በመዋሃድ የማጠናከር ተግባር የሚከናወነው በጠቅላላ ጉባኤ አብላጫ ድምፅ ሲወሰን ብቻ ነው፡፡ በመዋሃድም ሆነ በከፈል ለመደራጀት የወሰኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት በቅዲሚያ ሂሳባቸውን በማስመርመርና ነባሮቹ የኅብረት ሥራ ማህበራት በሕጉ መሰረት ፈርሰው ህልውናቸውን ሲያጡ ከመዝግብ መሰረዛቸው ቀደም ብሎ ይረጋገጣል፡፡

በመከፈልም ይሁን በመዋሃድ እንደገና በአዲስ መልክ የሚደራጅ ኅብረት ሥራ ማህበር በሚደረገው የቅድመ ማደራጀት ሂደት ተከትሎ በመደራጀት በሕጉ መሰረት ተመዝግበው ሕጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ የመክፈል ወይም የማዋሃድ ተግባር የተሳካና ውጤታማ ለማድረግ እንዲሁም በዚህ ሳቢያ ሊከሰቱ የሚችሉ አላስፈላጊ የሆኑ ሕገ-ወጥ አሰራሮችን ለማስወገድና የአባላትንና የሦስተኛ ወገን ጥቅምና መብት በማስጠበቅ ስራው ኃላፊነትና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ እንዲከናወን የተጠናከረ ሙያዊ እገዛ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን በመክፈልም ሆነ በማዋሃድ የማጠናከር ስራ በአባላት ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ቢሆንም አሁን በአገራችን እጅግ ከፍተኛውን ቁጥር የያዘውን የኅብረት ሥራ ቁጥር ተጠናክረው እንዲወጡ ለማድረግ በማዋሃድና በመክፈል የማጠናከር ስራ አገራዊ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ በትኩረት የሚተገበር ይሆናል፡፡

## አምድ 5፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ጠንካራ አመራርና አስተዳደር ስርዓት መገንባት የአባላትን ባለቤትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣

***ሀ. ነባራዊ ሁኔታ***

**የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራርና አስተዳደር ስርዓት ግንባታ፡-**

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚቋቋሙት በአባላት ሙሉ ፍቃደኝነት፣ ፍላጎትና ተሳትፎ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚመሩ አመራሮች ከጠቅላላ ጉባኤ ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሁኔታ ይመርጣሉ፡፡ ከዚህ አንፃር የአገራችን

ኅብረት ሥራ ማህበራት እድገት ከደረሰበት ደረጃ ለማድረስ በጠቅላላው ጉባኤ ውሳኔ መሰረት በየጊዜው የራሳቸውን አመራሮች ዲሞክራሲዊ በሆነ መንገድ ሲመርጡ ቆይተዋል፡፡

ለአመራሮቹም ተግባርና ኃላፊነት ከተጠያቂነት ጋር በመስጠት እንዲመራ አድርገዋል፡፡ አመራሮቹም ተግባራትን ያቅዳሉ ሲፈቀድላቸውም ተግባራዊ በማድረግ እና የኅብረት ሥራ ማህበሩን በመምራት በስራ ዘመናቸው ያከናወኗቸውን ተግባራት ኦዲት እያስደረጉ ይገኛሉ፡፡ ያከናወኑትን የስራ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባአው በወቅቱ በማቅረብ አስገምግመው በማፀደቅ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ የተሰጣቸውን ኃላፊነት የማወጡ አመራሮችን በመገምገም ከሃላፊነት እድነሱና ላጠፉት ጥፋት ተጠያቂ በማድረግ ሲመሩ ቆይተዋል፡፡ የስራ አመራሩም የኅበረት ሥራ ማህበሩን የዕለት ተዕለት ተግባራትን የሚመሩ ቅጥር ሰራተኞችን መድበው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ለዚህም የሚመሩበት መመሪያዎችና አሰራሮች በማዘጋጀት ሲተገበሩ ቆይተዋል፡፡

ሆኖም ግን አባላት አመራሮቻቸውን በመምረጥ ሂደት በትክክል ተገንዝቦ በንቃት ሲሳተፉበት አይታይም፡፡ የሚመረጡ የሥራ አመራሮችም ትክክለኛውን የኅብረት ሥራ ማህበራት መርህ ተከትለው ተግባራቸውን በሚገባ አያከናውኑም፡፡ ጠቅላላ ጉባኤ ቢሆን የተሰጠውን ስልጠን በአግባቡ ተገንዝቦ ግልፅ አቅጣጫና መመሪያ እየሰጠ ሥራ አመራሩን አይመራም፡፡ ሥራ አመራሩም ቢሆን ስለ ተግባራት አፃፀም ተገቢውን ሪፖርት በወቅቱ ለጠቅላላው ጉባኤ አያቀርብም፡፡ አንዳንዴም ከተሰጠው ኃላፊነት በመውጣት ውሳኔዎችን ሲወስን ይታያል፡፡

የጠቅላላ ጉባኤው፣ የስራ አመራሩና አቅጥር ሠራተኛው የሚመሩባቸው አሰራሮች ባለመዘርጋትና ግንዛቤ ባለመፈጠሩ ምክንያት በኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባራት አፈፃፀም ላይ በርካታ የግልፅነትና የተጠያቂነት የአሰራር ችግሮች ይስታወላሉ፡፡

**የአባላት ባለቤትነትና ውሳኔ ሰጭና ፍትሃዊ ተጠቃሚ ማድረግ**

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁት በአባላት ነፃና ሙሉ ፍቃደኝነት መሰረት ነው፡፡ ከሚቋቋሙባቸው ምክንያቶች መካከል ዋናው የአባላትን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ አባላት በኅብረት ሥራ ማህበራቸው ጉዳይ ያላቸው ተሳትፎ እንደ ኅብረት ሥራ ማህበራቱ ዓይነትና ደረጃ ይለያያል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትና የኅብረት ሥራ ማህበሩ ቁርኝትና ግንኙነት ከሌሎች ዓይነት የኅብረት ሥራ ማህበራት ይለያል፡፡ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበር አባል ለሆኑና አባል ላልሆኑ አገልግሎት ሲለሚሰጡ የአባላት የባለቤትነት እና ተሳትፎ ደረጃ እንዲቀንስ አስታዋፆ አበርክቷል፡፡ የግብርና ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጧቸው አገልግሎቶች (የምርት ማሳደጊያ ግብዓት) ለአባልና አባል ላልሆነ አርሶ/ አርብቶ አደር በመሆኑ የአባላት ተሳትፎ እንዲቀንስ አስታዋፆ አበርክቷል፡፡



DRAFT

በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን በመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል ያለው የአባላት ተሳትፎ እና ውሳኔ የመስጠት አቅም ደረጃቸው ይለያያል፡፡ አብዛኞች ምርት ከአባለት ሰብስበው ኤክስፖርት የሚያደርጉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች የሚያደርጓቸው የግብይት ውል ስምምነቶች በሚፈለገው ደረጃና ጊዜ ስለማይወሰኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ማግኘት የሚገባቸውን ገቢ እያገኙ አይደለም፡፡ አባላት ሲደራጁ ስለኅብረት ሥራ ማህበራቸው በቂ ግንዛቤ ይዘው ስለማደራጁና ከተደራጁ በኋላ የሚፈለገውን አገልግሎትና ጥቅም ስለማያገኙ ስለኅብረት ሥራ ማህበራቸው ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ባግባቡ አይሳተፉም፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሮቻቸውን የሚመሩ በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ የተለያዩ የስራ አመራር ኮሚቴዎች አሏቸው፡፡ እነዚህ የኮሚቴ አባላት የሚሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት ተከትለው የኅብረት ሥራ ማህበራትን ተግባራት ይመራሉ፡፡ አብዛኞቹ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሮቻቸውን በሙያ የሚደግፉ የተለያዩ አይነት ሙያ ያሏቸው ባለሙያዎችን ቀጥረው በማሰራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም የኅብረት ሥራ ማህበራትን እንዲመሩ የሚመረጡ የኮሚቴ አባላት የክህሎት ማነስና አልፎ አልፎ በተግባርና ባህሪያቸው ግንባር ቀደም ያለመሆን ችግር ይታያል፡፡ በተጨማሪም ተግባሮቻቸውን በሙያ የሚደግፉ አስፈላጊ ባለሙያዎች በብዛትና በጥራት ቀጥሮ በማሰራት ላይ ሰፊ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡

## ሰንጠረዥ 3፡ የዕምበባ ሓያ የገጠር ገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃላ/የተ የኅብረት ሥራ ማህበር በሞደልነት የተወሰደ (bench mark)

**የአባላትና ካፒታል እድገት፡-** የኅብረት ስራ ማህበሩ በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በደቡባዊ ዞን እንዳመሆኒ ወረዳ መስዋእት ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው ስሆን እስከ 2008 ዓ.ም ባለው መረጃ መሰረት አባላት ድምር 1,468 (53.74 ሴቶች)፣ ካፒታል 1,522,388 ብር በላይ ደርሷል፡፡ በሥራ ክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ጠቅላላ 925 አባ/እማዎች ውስጥ 1468 ማለትም ቀበሌው ውስጥ የሚገኙ አባዋረና እማወራዎችን በሙሉ እና ወጣቶችን በስፋት አባል አድርጓል፡፡

የሚሰጡት የቁጠባ አይነት እና እድገት፡- ለአባላትና ለአከባቢው ሕብረተሰብ መደበኛ ቁጠባ፣ መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ፣ የጊዜ ገደብ ቁጠባ፣ የልጆች ቁጠባ እና የተቋማት ቁጠባ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በ2009 ዓ.ም ከቁጠባና ዕጣ ከ2,128,295 ብር በላይ ማሰባሰብ ተችለዋል፡፡

የብድር አገልግሎት እና የአባላት ተሳትፎ እና አመላለስ መስፋፋት፡- የአባላትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ለግብርና ዘርፍ በልዩ ትኩረት፣ ለቤት ግንባታ፣ ለንግድ ስራ፣ ለህክምና፣ ለትምህርት እና ለቤት ቁሳቁስ መግዣ በማውጣት በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት የብድር አገልግሎት ይሰጣል፡፡ በ2007ዓ.ም ድረስ በድምሩ 1,738 አባላት (በድግግሞሽ) ብር 7.58 ሚሊየን በላይ ለአባላት (3.4 ሚሊየን ለሴቶች) ብድር የሰጠ ስሆን አባላት በውጤታማ ተግባር ላይ በማዋል ብድሩን 100 በመቶ መመለስ መቻሉ፡፡

**ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ማስቀረት፡-** በ2007 ዓ.ም የኅብረት ሥራ ማህበሩ በራሱ ባደረገው ጥናት ማህበሩ ባለፉት አምስት ዓመታት ለአላስፈላጊ ወጭዎችን ይወጣ የነበረውን 4,455,000.00 ብር ማዳን ችለዋል፡፡

**የአባላት ተጠቃሚነትና ባለቤትነት ስሜት ማደግ፡-** በየዓመቱ ኦዲት ተደርጎ ምንም ጉድለት አለማሳየቱ፣ ትርፋማ መሆኑና የተገኘውም ትርፍ በየዓመቱ ለአባላት የትርፍ ክፍፍል ይሰጣል፡፡ በዚህ መሠረት የኅብረት ሥራ ማህበሩ የአባላት የባለቤትነት ስሜት

DRAFT

| |
|---|
| በከፍተኛ ደረጃ ማደጉ እና አመራሩም ጥንካሬ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥተዋል፡፡ |

**ለ. የኅብረት ሥራ ማህበራት ጠንካራ አመራርና አስተዳደር ስርዓት ለመገንባት ያሉ ማነቆዎች፡-**

**ማነቆ 1፡- ጠንካራ የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራርና አስተዳደር አለመኖር፣**

አባላት ተሟልተው በጠቅላላ ጉበኤ ስብሰባ ላይ በንቃት አለመሳተፍ፤ ተግባርና ሃላፊነታቸውን አለማወቅ፤ የመምራትና የማስተዳደር አቅማቸው ዝቅተኛ የመሆን ቸግር ይታያል፡፡ ጠቅላላ ጉባኤ ስራን በመገምገም ለመናጅመንት ግብረ መልስና ስምሪት በአግባቡ አለመስጠት፤ የተጠናከረ የውስጥና የውጭ የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት አለመኖር፤ ጠንካራ አመራርና አስተዳደር ስርዓት በአግባቡ አልተዘረጋም፡፡

በተጨማሪም የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚደግፉ አካለት ያለባቸውን የአመለካከት፣ የክህሎት፣ የግብዓት፣ የአሰራርና አደረጃጀት ችግሮችን በጥናት ለይቶ ተቀናጅቶ አለመደገፍ ክፍተቶች አሉ፡፡ ውጤታማ የሚያደርጉ መዋቅር በመዘርጋት፣ ሚዘናዊ አሰራር እንዲኖርና ለሚሰሩ ስራዎችም የተጠያቂነት አሰራር እንዲኖር ባለመደረጉ ሂሳብ በየዕለቱ በመመዝገብ፣ በየወሩ በመዝጋት ወቅታዊ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ሰፊ ክፍተት ይታያል፡፡ በገለልተኛ ኦዲተሮች ሂሳባቸውን በወቅቱ ማስመርምር አለመቻል ማነቆዎች ይታያሉ፡፡ የአመራሮቻቸውን አቅም በመገንባት ተግባሮቻቸውን እያከናወኑ አይደለም፡፡

**ማነቆ 2፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ጠንካራ የመልካም አስተዳደር አለመስፈን**

በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ግልፅነት ያለው ጠንካራ አሰራር በሚፈለገው ደረጃ አልተዘረጋም፡፡ የተጠያቂነት አሰራር ተጠናክሮ አለመተግበር፣ በአባላት፣ በህብረተሰብና በመንግስት መካከል ግልፅና ተዓማኒነት ያለው የእርስ በርስ ግንኙነት አለመጠናከር፣ የሥራ አመራር እና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት የኅብረት ሥራ ማህበራቸውን ተግባር በአግባቡ ለመምራት የክህሎትና አልፎ አልፎ የስነምግባር ችግሮች መታየት፣ አባላት የኅብረት ሥራ ማህበራቸውን የስራ እንቅስቃሴ በአግባቡ እንዲረዱ የተለያዩ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም እና ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ግልፅነት በመፍጠር ላይ ክፍተቶች መኖር እና አመራሩና ቅጥር ሰራተኞች አልፎ አልፎ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ድርጊት ሰለባ ሲሆኑ ይታያሉ፡፡



DRAFT

**ማነቆ 3፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት፣ አመራር አካላትና ቅጥር ሠራተኞች የሚጠበቅባቸውን ግዴታ አለመወጣት**

የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚፈልገው አሰራር መሰረት አለመመራት፣ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ሀብትና ንብረት ተገቢውን ጥበቃና ጥንቃቄ አለማድረግ፣ የአባላትን የስነ-ምግባር መርህ እና የሚጠበቅበትን ግዴታ በአግባቡ አለመወጣት፣ አላስፈላጊ ጥቅሞችን ለማግኘት ጥረት ማድረግ፣ ጥራቱን ያጓደለ ወይም መጠኑን የቀነሰ ምርት ማቅረብ፣ እና በአጠቃላይ የአባላት የበለቤትነት ስሜትና ተሳትፎ አነስተኛ መሆን ዋነኞቹ ማነቆዎች ናቸው፡፡

**ማነቆ 4፡ የአባላት ባለቤትነት፣ ውሳኔ ሰጭነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት በሚፈለገው ደረጃ አለመረጋገጥ፣**

የኅብረት ሥራ ማህበር በአባላት ፍላጎት፣ ቁርጠኝነት እና ትጋት ላይ አለመመስረት፡፡ የአባላት ተሳትፎና አለማደግ፡፡ አባላት በኅብረት ሥራ ማህበራቸው ጉዳይ በሚፈለገው ደረጃ ውሳኔ ሠጭ አለመሆን፡፡ የአባላት ተጠቃሚነት በሚፈለገው መጠን አለመረጋገጥ፡፡ ለዚህም አስፈላጊ ስልጠና እና ግንዛቤ አልተፈጠረም፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚወስኗቸው ውሳኔዎች በግልፅና በነፃ መወሰን አለመቻላቸው፣ ለአባላት የሚሆኑ አዳዲስ የቢዝነስ ሃሳቦችን ማፍለቅ አለመቻል፣ ካፒታል በማፍራትና በመጠቀም ለገበያ ተደራሽ መሆን አለመቻል፣ በዓለም አቀፍ ንግድ እና ሀገር አቀፍ በሚደረጉ የግብይት ውሳኔዎች ላይ ፈጣን ውሳኔ አለመስጠት፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሁሉም በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ ለአባላት የተለየ አገልግሎት አለመስጠት፣ አባላት በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጉዳይ ላይ ያላቸው የመወሰን አቅም ዝቅተኛ መሆን ችግሮች ይታያሉ፡፡

**ማነቆ 5፡- የኅብረት ስራ ማህበራት በተግባርና ባህሪያቸው ግንባር ቀደም በሆኑ አመራሮች አለመመራት**

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚመሩ የአመራር አካላት የዕውቀትና ክህሎት ችግር ያለባቸው መሆን ፣ አልፎ አልፎ በተግባርና ባህሪያቸው ግንባር ቀደም አለመሆን፣ የኅብረት ሥራ የግንባር ቀደም መለያ መስፈርቶች በአግባቡ አዘጋጅቶ ተግባራዊ አለማድረግ፣ የሚመረጡ አመራር አካላት የሚሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መምራት አለመቻል ችግሮች ይታያሉ፡፡

**ማነቆ 6፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሮቻቸውን በሰለጠነ የሰው ኃይል አለመምራት**

በሙያው የሰለጡኑ ባለሙያዎችን የመቅጠር ፍላጎት ማነስ፣ ለመቅጠር የፋይናንስ አቅም ችግር፣ የሚቀጠሩ ባለሙያዎችም አልፎ አልፎ የስነ ምግባር ችግር፣ የዕውቀትና የክህሎች ችግር ያለባቸው መሆን ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

### ሐ. ማነቆዎችን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች

### መፍትሄ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራርና አስተዳደርን ማጠናከር፣

የኅብረት ሥራ ማህበር አባላት ሁሉ በሚሳተፉበት ባለቤትነት፣ ተጠቃሚነትና በበላይ ተቆጣጣሪነት የሚመራና የሚተዳደር ድርጅት ነው፡፡ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሁኔታ በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ በሚመረጡ አመራሮች እንዲመሩ ይደረጋል፡፡

ለኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ አመራርና አስተዳደር ጠንካራ መሆን ዋናው የጀርባ አጥንት የሚሆነው የጠቅላላው ጉባኤ ጥንካሬ ነው፡፡ ጠቅላላ ጉባኤ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ቦርድ ወይም ኮሚቴ እና ማናጅምነት አፈፃፀምና ስልጣን የሚገመግምና የሚያረጋግጥ አካል ነው፡፡ ጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጠው ግብረ መልስና ስምሪት ለሥራ አሲኪያጅ ትልቅ መልካም አጋጣሚ ነው፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ውጤታማ እንዲሆኑና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ተልዕኮዎቻቸውን መወጣት እንዲችሉ ራሳቸውን በራሳቸው የመምራትና የማስተዳደር አቅማቸው በየጊዜው እየተፈተሸ እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡

ግልፅና አግባብነት ያለው የውስጥ ቁጥጥርና ክትትል ስርዓት በመዘርጋት እና ሂሳባቸው በወቅቱ በማስመርመር አሰራራቸው ላይ የሚታዩ ችግሮችን ፈትሾ እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን ልማት የሚደግፉ ማናቸውም አካላት መንግስትንም ጨምሮ በየደረጃው የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮች ያለባቸውን የአመለካከት፣ የክህሎት አቅም፣ የግብዓት አቅርቦትና የአሰራር ችግሮችን በየጊዜው በጥናት በመለየት በተግባር በመደገፍ የማጠናከር ስራ መሰራት ይኖርበታል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ አመራር፣ ስራ አስኪያጂና ቅጥር ሠራተኞች ለሚያከናውኗቸው ማንኛውም ተግባራት ሃላፊነትና ተጠያቂነት አለባቸው፡፡ ይህም የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባራቸውን በአግባቡ በመምራት ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራር አካለት በሚቀመጠው አሰራር መሰረት በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ በየጊዜው እየተመረጡ ተግባሮቻቸውን በአግባቡ እንዲመሩ ይደረጋል፡፡ የሚመረጡ የኮሚቴ አባላት በኅብረት ሥራ ማህበራት የልህቀት ማዕከላት ውስጥ ገብተው እንዲሰለጥኑ በማደረግ አቅማቸውን የመገንባት ስራ በትኩረት ይሰራል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጧቸው አግልግሎቶች የአባላትን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የአጭር፣ መካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶችን በማዘጋጀትና በማፀደቅ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራ አሲኪያጆች በሚሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት የኅብረት ሥራ ማህበራትን የዕለት ተዕለት ተግባራት የመወሰንና ሌሎች ተያያዥ የሆኑ ዕለታዊ ተግባራትን ይመራል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራ አመራር ቦርዱ ወይም ኮሚቴ በመተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተግባሮቻቸውን እንዲያከናውኑ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራር አካላት ተግባሮቻቸውን በትጋት እንዲወጡ ለተመረጡበት ኅብረት ሥራ ማህበር ሥራ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩና የግል ሥራቸው እንዳይበደል በሚሰጡት አገልግሎት በጥናት ላይ የተመሰረተ ክፍያ እንዲኖር የአሰራር ስርዓት ተዘርጎቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ መልካም አስተዳደር ከማስፈን ባሻገር የተለያዩ መደበኛ እና ልዩ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል፡፡ ልዩ ውሳኔ ከሚሰጥባቸው ጉዳዮች መካከል የኅብረት ስራ ማህበር አዲስ ሲመሰረት፣ ሲከስር፣ ሲዋሃድ፣ ሲከፈል፣ ሲፈርስ፣ ዕቅድ እና የኦዲት ሪፖርት ለማጽደቅ፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ እና ዕውቅና ውጤት ለማወቅ፣ የውሳኔ ሃሳብ ለመስጠትና ለማጽደቅ፣ የቋሚ ንብረት ግዢ፣ ኢንቨስትመንት እና አዲስ ስራዎችን ለማስፋፋት እና ለማካሄድ፣ በዕቅድ የተያዙ ፕሮጀክቶችን እና ብድሮችን ሥራ ላይ እንዲውሉ ማጽደቅ ናቸው፡፡

### መፍትሄ 2፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ጠንካራ የመልካም አስተዳደር ስርዓት ማስፈን

ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሚያከናውናቸው ተግባራት አሳታፊ፣ ግልፅ፣ ሕግን የተከተለ፣ በአባላት እና በሕብረተሰቡ ተዓማኒ የሆነና በተጠያቂነት የሚሰራ ይሆናል፡፡ ለዚህም የኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ቦርድ ወይም ኮሚቴ እና ማናጅምንት የሚያከናውናቸውን ተግባራት ለአባላት፣ ለቅጥር ሠራተኛ ግልፅ የሆነ አሰራር ዘርግቶ መስራት ይኖርበታል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያከናውኗቸው ማናቸውንም ተግባራት ትክከለኛውን የሂሳብ አሰራር ተከትለው (IFRS) የሂሳብ መግለጫ (Financial statement) በማዘጋጀት ለአባላትና ለመንግስት ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚህም መሰረት የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት፣ መንግስት ወቅታዊ መረጃ እንዲያውቁ እና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት አሰራር ውስጥ የመልካም አስተዳደር ስርዓት እንዲሰፍን ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡

### መፍትሄ 3፡- አባላት፣ አመራር አካለትና ቅጥር ሠራተኞች ግዴታቸውን እንዲወጡ ማድረግ፣

### የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት፡

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ አባላት የኅብረት ሥራ ማህበራቸው ምሰሶ ቢሆኑም አብዛኞቹ በትኩረት ግዴታቸውን እየተወጡ አይደሉም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ግዴታቸውን እንዲወጡ ስለ ኅብረት ሥራ ማህበር ጠቀሜታና ፋይዳ ተከታታይ የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት ይሰጣቸዋል፡፡ አባላት የኅብረት ሥራ ማህበራቸውን በባለቤትነት መምራትና የመቆጣጠር ግዴታቸውን እንዲወጡ የማጠናከር ስራ ይሰራል፡፡ የሚጠበቅባቸውን የዕጣ ክፍያ

የማያጠናቅቁ፣ በሚሰጡ አገልግሎቶች ወይም ግብይቶች ላይ እና በመደበኛ ስብሰባዎች ላይ የማይሳተፍ እና ግዴታውን የማይወጣ ማንኛውም አባል ተጠያቂ የሚሆንበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራር አካላት፡-

ማንኛውም መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በጠቅላላ ጉባኤ ቀጥተኛ ድምፅ የሚመረጥና ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ የሆነ የሥራ አመራር ይኖረዋል፡፡ በዚህም መሰረት የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ አባላት በማናቸውም ምክንያት ሥራቸውን ሲለቁ በሥራ ዘመናቸው ያከናወኑትን ተግባራት እንዲያስመረምሩና እንዲያስረክቡ የሚያግድድ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራር አካለት ግዴታቸውን በብቃት እንዲወጡ ለማስቻል ከመጀመሪያው አመራሮቹ ሲመረጡ በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ለአመራርነት ብቁ የሚያደርግ አመራር መመልመያ መስፈርት መሰረት እንዲመረጡ ይደረጋል፡፡ የሚመረጡ ግለሰቦች አስቀድሞ እና ወደ አመራር ከመጡም በኋላ ኃላፊነትና ግዴታቸውን ተረድተው ባግባቡ ስራቸውን እንዲያከናውኑ ስለኅብረት ሥራ ጽንሰ-ሀሳብና አመራር እውቀትና ክህሎት በኅብረት ሥራ የልህቀት ማዕከላት ተከታታይ ስልጠና እንዲገኙ ይደረጋል፡፡

### ስለኅብረት ሥራ ማህበራት ተቀጣሪ ባለሙያዎች፡-

ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የዕለት ተዕለት ሥራ የሚመራ ሥራ አስኪያጅ እና የክፍል ሃላፊዎች እንዲሁም የዕለት ተዕለት ሥራ ለማከናውን የሚቀጠሩ ባለሙያዎች እንዲኖሩት ይደረጋል፡፡

የኅብረት ስራ ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ እና ሌሎች የክፍል ሃላፊዎች ምልመላና ቅጥር በቅጥር ኮሚቴ የሚከናወን ሲሆን የቅጥር ሥራውን የሚያከናውን በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ የቅጥር ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡ በዚህም መሰረት ሌሎች ቅጥር ሠራተኞችን አቀጣጠር በሚመለከት ከቅጥር ኮሚቴ፣ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ አስኪጅ እና ከየክፍል ሃላፊዎች በሚወከሉበት የሚፈጸም ሆኖ የሥራ አሲኪያጅና የክፍል ሃላፊዎች ቅጥር በጠቅላላ ጉባኤ እንዲፀድቅ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ስለ ሠራተኞች አቀጣጠርና አስተዳደር አግባብ ግልፅ የአፈፃፀም መመሪያ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ቅጥር ሠራተኞች የኅብረት ሥራ ጽንሰ-ሐሳብ፣ መርሆ፣ እሴቶች እና ሕጎችን ባግባቡ ተረድተው ተግባሮቻቸውን እንዲፈፅሙ ተከታታይ ስልጠና እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

### መፍትሄ 4፡- የአባላት ባለቤትነት፣ ውሳኔ ሰጭነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ፣

### የአባላት ባለቤትነትና ውሳኔ ሰጭነት አቅም በማሳደግ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፡-

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚቋቋሙበት ዋና ዓላማ የአባላትን በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ተሳትፎ ማሳደግና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህም እውን የሚሆነው የአባላት ግንዛቤ ሲያድግና የባለቤትነት ስሜት ሲፈጠር፣ የውሳኔ ሰጭነት አቅም ሲገነባና የተቆጣጣሪነት አሰራር ሲዘረጋ ነው፡፡ ጠንካራ የሆነ የኅብረት ሥራ ማህበራት አሰራር ስርዓትና የባለቤትንት ስሜት ሳይገነባ ውጤታማና ቀጣይነት ያለውን የፍትሃዊ ተጠቃሚነት አሰራር ማምጣት አይቻልም፡፡

በመሆኑም የአባላትን ተሳትፎ ለማሳደግ፣ በውሳኔ ሰጭነት እንዲሳተፉ ለማድረግ፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚያቀርቡ አግልግሎቶች ላይ በንቃት ተሳትፈው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ለአባላት ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

በተለይም የኅብረት ሥራ ማህበራት በአሁን ጊዜ ከደረሱበት እድገት ደረጃ እና ከጊዜው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት የመሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት፣ የኅብረት ሥራ ዩኒዬኖች በተጠናከረ ሁኔታ በአበላት ፍላጎት መሰረት ፍትሃዊ የገበያ፣ የቁጠባ፣ የብድር፣ የመረጃ እና ሌሎች በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች ላይ ለአባላት በቂ አግልግሎት በማቅረብ ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ልማት በጠንካራ የአባላት ፍላጎት፣ ቁርጠኝነት እና ትጋት ላይ በመመሰረት ዕለት ተዕለት የሚያከናውኗቸው ተግባራት ግልፅነት ባለው አሰራርና ከውጭ ተፅዕኖ ነፃ በሆነ አኳኃን እንዲከናወን ጠንካራ የሆነ የክትትልና ድጋፍ አሰራር ተዘርግቶ በትኩረት ይተገበራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላትን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የውስጥ የካፒታል አቅም በማፍራት፣ ሙያዊ የቴክኒክ እውቀት በመጠቀም፣ አዳዲስ የስራ መስኮችን በማስፋፋት፣ ለገበያ ተደራሽ በመሆንና የራሳቸውን የፈጠራና የውሳኔ አሰጣጥ አቅማቸውን በማሳደግ የባለቤትነት ስሜት አዳብረው በነፃነት በመንቀሳቀስ ተግባሮቻቸውን እንዲያከናውኑ በትኩረት ይሰራል፡፡

ኅብረት ሥራ ማህበራት መዋቅራቸውን በማጠናከር፣ አሰራራቸውንና አገልግሎት አሰጣጣቸውን በማሻሻል፣ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅማቸውን በመገንባት፣ አባላት የተሻለ አገልግሎት በቅድሚያ የሚያገኙበትን ስርዓት በመዘርጋት ተልዕኮአቸውን መወጣት እንዲችሉ የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል ይደረግላቸዋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በግብይት ላይ የሚሰጡት ውሳኔ ዘመናዊና ቀልጣፋ በማድረግ የአባላትን ተሳትፎ በመጨመር ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የግብይት ስራ ላይ የአባላትን የባለቤትንት መብት ሳይነካ ባጠረ ሁኔታ የሚወሰንበት አሰራር ተዘርግቶ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

**መፍትሄ 5 ፡- የኅብረት ስራ ማህበራት በተግባርና በአመለካከታቸው ግንባር ቀደም በሆኑ አመራሮች እንዲመሩ ማድረግ፤**

***የኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራዎችን በግንባር ቀደም አባላት እና በሰለጠነ የሰው ሃይል መምራት፡-***

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት መካከል የተሻለ ብቃት ባላቸው የሰለጠኑ ግንባር ቀደም አባላት እንዲመሩ ለማስቻል ዓለም አቀፋዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት መርሆዎች በማይጥስ መልኩ የአባላትን የመምረጥና የመመረጥ መብትን ባከበረ ሁኔታ እንዲመሩ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከተቋቋሙበት ዓላማ አንፃር ግልፅ የኅብረት ሥራ ግንባር ቀደም መለያ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡የግንባር ቀደም መስፈርቱ የሚያተኩረው የእውቀት፣ የክህሎትና የአመለካከት (የትምህርት ዝግጅት)፣ የእሴቶች (ተማኝነት፣ ዲሞክራሲያዊነት፣ ግልፅነት፣አገልጋይነት)፣ ለመተዳደሪያ ደንባቸውና ለኅብረት ሥራ ሕጎች ተገዥ መሆን፣ በሥራ ዘመኑ የተሻለ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ያረጋገጡ፣ ማህበራዊ ሃላፊነት የመወጣት ብቃት፣የኅብረት ሥራ ማህበሩን በታማኝነትና ቁርጠኝነት ለመምራት ያለው ፍላጎት እና ሌሎች ተመሳሳይ መስፈርቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚለይ ይሆናሉ፡፡

ኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባር የራሱ የሆነ የፈጠራ ክህሎት የአመራር ጥበብ የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራር ከአባላት መካከል በትምህርት ዝግጅትታቸው የተሻሉ፣ በአካባቢው ህብረተሰብ በስነ ምግባራቸውና በስራ ተነሳሽነታቸው ተቀባይነት ባላቸው የኅብረት ሥራ ግንባር ደቀም መስፈርት መሰረት ተመርጠው እንዲመሩ ይደረጋል፡፡ይህ አሰራር ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው የአባላትን ዲሞክራሲዊ የመምረጥና የመመረጥ መብትን ሳይነካ እና የኅብረት ሥራ መርህን ሳይጥስ በአባላት ሙሉ ውሳኔ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በስነ ምግባርና ተግባራቸው ግንባር ቀደም የሆኑ አባላትን በመለየት የአመራርነት ክህሎታቸውን የሚያዳብር ተከታታይነት ያለው ስልጠና በመስጠት እና በማብቃት እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም አስፈላጊ የሆኑ የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት በአፈጻጸማቸው የተሻሉ አመራሮችን የማበረታታት ተጠናክሮ ይሰራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራር ልማት ፕሮግራም በመቅረፅ ወጣቶችና የሴቶች በአባልነትም ሆነ በአመራርነት እንዲሳተፉ ማበረታታት ይኖርበታል፡፡ ለዚህም አፈፃፀም ተግባረዊነት የሚያግዝ ተከታታይነት ያለው ሙያዊ ምክር፣ የድጋፍና ክትትል አቅጣጫን ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡

የኅብረት ሥራ አመራር አካላት ድርሻ የድርጅቱን ግብ እና ዓላማ ማስቀመጥ እና ዓላማውንም በሥራ መተርጎም ነው፡፡ እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ ለውጦችን በረጅም ጊዜ ዕቅዶች፣ ስልጣንና ሃላፊነትን በማውረድ እንዲተገበር ማድረግ፣ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ተግባራት ስልታዊ በሆነ መንገድ በየጊዜው መገምገም፣ በህብረተሰቡ፣ በአባሉ እና በቅጥር

ሠራተኞች መካከል ያለውን ግንኙነት ማስጠበቅ፣ በዚህም እንደ ድልድይ ሆኖ ማገልገል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የኅብረት ሥራ ማህበራት ቁልፍ የራሳቸውን የውስጥ ሥራ ፖሊሲ እና ፕሮግራሞችን መቅረጽ እና ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ አለባቸው፡፡

**መፍትሄ 6 ፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሮቻቸውን በሰለጠነ የሰው ኃይል መምራት**

የኅብረት ሥራ ማህበራትከደረሱበት የዕድገት ደረጃ እና ስራው ከሚጠይቀው ሙያ አንፃር ተወዳዳሪና ውጤታማ ሊያደርጓቸው የሚችሉ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ቀጥረው እንዲያሰሩ ይደረጋል፡፡ የተለየ ሙያን የሚጠይቁ መደቦችን በጥናት በመለየትና አስፈላጊውን መዋቅር በማዘጋጀት ባለሙያ ቀጥረው ማሰራት ይኖርባቸዋል፡፡ እንደ ስራቸው ባህሪና የዕድገት ደረጃ ሥራ አስኪያጅ፣ የግብይት ትስስር ባለሙያ የሂሣብ ሠራተኛ፣ የንብረት ክፍል ሠራተኛ፣ ቅጥር ገንዘብ ያዥ እና ጥበቃ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ከመሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በላይ ያሉት የኅብረት ሥራ ማህበራት እርከኖች የስራው ባህሪ በሚጠይቀው መስፈርት መሰረት የሰለጠነ ባለሙያ ቀጥረው ማሰራት ይኖርባቸዋል፡፡ አቅማቸው እየታየ ሁሉም የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያስፈልጓቸውን የሰለጠነ የሰው ሃይል ማሟላት ያለባቸው ሆኖ መንግስትን፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖችና ፌደሬሽኖች አቅም ለሌላቸው የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሩ በሚጠይቀው መስፈርት መሰረት አስፈላጊውን ባለሙያ በመቅጠር ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ ለዚህም የሚሆን ግልፅ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡ ለማንኛውም ቅጥር ሰራተኛ ግልፅ የሥራ መዘርዝር ወጥቶላችው በመስጠት የአፈጻጸም ግምገማ በማድረግ ደረጃ እየተሰጣቸው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሊመራ ይገባል፡፡

በመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት፣ ዩኒዬን እና ፌዴሬሽን ደረጃ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ውጤታማ እንዲሆኑ በአሰራር የሚቀመጠውን የሰው ኃይል ሳይሟላ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማግኘትም ሆነ ማደስ አይችሉም፡፡ በሚፈልጉት የስራ መስክ ባለሙያዎችን በአግባቡ ማግኘት እንዲችሉ ቀደም ብለው ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመነጋገር የሚያሟሉ ይሆናል፡፡

በኅብረት ሥራ ትምህርትና ተመሳሳይ መስክ የተመረቁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራ አስኪያጆች ተከታታይነት ባለው መልኩ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ አመራር አባላት ጋር በመገናኘት ለቀጣይ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ዕድገት አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ በአገልጋይነት ስሜታ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራ አስኪያጆች በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እና በአባላት ቅሬታ ላይ በትክክል መፍትሔ በመስጠት ላይ እንዲያተኩሩ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራ አስኪያጆች በሥራ አመራሩ እና በአባላት መካከል ያለውን ግንኙነት በጥሩ ሁኔታ ከማስጠበቅ ባለፈ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ዕቅድ በሚያዘጋጁበት ጊዜ የአሳታፊነትን ዘዴ መከተል እና የስራ አፈጻጸም

ሪፖርትን ለሥራ አመራር አባላት እና ለአባላት በየወሩ ማቅረብ እና ማስተዋወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲሁም ሥራ አስኪያጆች በቅጥር ሠራተኞች እና በእነሱ መካከል ጤናማ ግንኙነት ስለመኖሩ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ለዚህም ሥራቸው የተሻለና ሊቆያቸው የሚችል የኅብረት ሥራ ማህበሩን አቅምና የአከባቢውን ገበያ ሁኔታ ያገናዘበ የክፍያ ሁኔታ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ቅጥር ሠራተኞች ያሉባቸውን የክህሎት ክፍተት እየተጠና ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

የተማረ የሰው ሃይሉን በተግባርና በልምድ ልውውጥ በማብቃት፣ በየጊዜው በማሳደግ፣ ያሉትንም ባለሙያዎች የማብቃት እና የማበረታታት ስራ ይሰራል፡፡

## አምድ 6፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የአሰራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን ማጠናከር፣

### ሀ. ነባራዊ ሁኔታ

የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት ፍላጎት መሰረት ያደረገ አገልግሎት በማቅረብ የአባላትን ተጠቃሚነት መረጋገጥ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የተለያዩ ኅብረት ሥራ ማህበራት በየደረጃው ተደራጅተው የተለያዩ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ለዚህም የሚያገለግሉ አዋጆች፣ ደንቦች፣ የተለያዩ መመሪያዎች፣ የግብርና ኅብረት ሥራ ማህበራት ስትራቴጂ ተቀርፆ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም በርካታ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች ተፈተዋል፡፡

የተዘጋጁ በርካታ መመሪዎችና ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ፣ ቢዝነስ ፕላንና የተለያዩ ማኑዋሎች ቢኖሩም ለተጠቃሚው በማድረስ ስራ ላይ እንዲውል ከማድረግ አንፃር በርካታ የአፈፃፀም ጉድለቶች ታይተዋል፡፡ ከዚህም ውጭ አባላት የሚፈልጉትን አገልግሎቶችን ለይቶ በስፋት በማቅረብ ጥሩ ጅምር ያላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ቢኖሩም በአብዛኛው በርካታ ውስንነቶች ይታያሉ፡፡

በአገራችን በተለያዩ የሥራ ማስኮች የምረጥ ተሞክሮ ቅማራ ስትራቴጅ ተዘጋጅቶ እና ግንዛቤ ተፈጥሮበት እንዲሰፋ መንግስት አቅጣጫ በማስቀመጥ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ይህንን መሠረት በማድረግ በኅብረት ሥራ ሴክቴሩ ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመቀመር እንዲያስችል የምርጥ ተሞክሮ ቅመራ ሰነድ ተዘጋጅቶ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ አንጻር በተለያዩ የሥራ መስኮች በርካታ መሠረታዊ እና ዩኒዬን ኅብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው አባሎቻቸውን በተሸለ ሁኔታ በማገልገል እና ለአገር ኢኮኖሚ ግንባታ የድርሻቸውን በማበረትከት ላይ ይገኛሉ፡፡ ቁጥራቸው ውስን ቢሆንም ምርጥ ተሞክሮአቸው ተቀምሮ ለለሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት መስፋት የሚችል ኅብረት ሥራ ማህበራት አሉ፡፡ በሴክተሩ ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን ቀምሮ ለማስፋት ጅምር ሥራዎች ያሉ ቢሆንም ምርጥ ተሞክሮውን ቀምሮ በማስፋት በኩል በየደረጃው ያሉ የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት በኩል ሰፍ ውስንነት ይታያል፡፡

### ለ. የኅብረት ሥራ ማህበራት የአሰራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ለማጠናከር ያሉ ማነቆዎች:

**ማነቆ 1፦ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት የሚመጥን የአሰራር ስርዓት እና አገልግሎት አሰጣጥ አለመጠናከር**

የኅብረት ሥራ ማህበራት እድገት መሰረት ያደረገ የአሰራር ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ አለመዘርጋት፡፡ የአባላትን ችግር መሰረት ያደረገ ግልፅ የአገልግሎት አሰጣጥ የአሰራር ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ አለመዘርጋት፣ የአገልግሎት አሰጣጡን ጥራት ያለው፣ ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎችን አለመጠቀም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ አሰራርና አደረጃጀት አለማጠናከር፡፡ አሁን ያሉት መመሪያዎች እና አሰራሮች ላይ የሚታየውን ክፍተቶች በጥናት በመለየት የሚያሰራ አሰራር ስርዓት አለመዘርጋት፡፡ የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ አገልግሎቶች አለማስፋፋት፡፡ አባላት በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያላቸውን የእርካታ ደረጃ አለማጥናት፡፡ በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ያሉትን የውስጥና የውጭ ማነቆዎችን አለመለየት፡፡

**ማነቆ 2፦ በኅብረት ሥራ ማህበራት ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለይቶና ቀምሮ ማስፋት አለመቻል**

የኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎች ተለይተው አልተቀመሩም፣ ምርጥ ተሞክሮውን ለመቀመር የሚያስችል በቂ ግንዛቤ አልተፈጠረም፣ ለመቀመር የተሞከሩ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለማስፋፋት የተሰራው ሥራ በቂ አይደለም፡፡

### ሐ. ማነቆዎችን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች:

| |
|---|
| ካሉት የኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ 80 በመቶ የሚሆኑት ተጠናክረው በላቀ ደረጃ የሚፈለገውን አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ |

**መፍትሄ 1፦ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት የሚመጥን የአሰራር ስርዓት እና አገልግሎት አሰጣጥ መዘርጋት**

**የኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት የሚመጥን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣**

የኅብረት ሥራ ማህበራት የአበላት ችግር በዘላቂነት እንዲፈቱ ጠንካራ አሠራር ሥርዓት በመዘርጋት፣ የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በማሟላትና አስፈላጊውን ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

ለኅብረት ሥራ ማህበራትን ምቹ የሕግ ማዕቀፍና አሰራር ስርዓት በመዘርጋት ጠንካራና ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ፣ የኅብረት ሥራ መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ የአመራር ጥበብ፣ የፋይናንስ አስተዳደር፣ የግብይት ትስስር፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ እና ሌሎች በጥናት በመለየት ጠንካራ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በጥናት በመለየት ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት የኅብረት ሥራ ማህበራትን የመፈፀም አቅም በማሳደግ አገልግሎት አሰጣት ስርዓታቸው እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የማንጅመንት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስርዓት በማሻሻል ከአባላት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በማጠናከር ለአባሎቻቸው ጥራት ያለውና ቀልጣፋ አግልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የአገልግሎት አሰጣጥ በተሻለ ደረጃ ለማሳደግ እና የአደረጃጀትና የአሰራር ማነቆዎችን ለመፍታት የሚያስችል የዳሰሳ ጥናቶችን በየጊዜው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅተው እንዲያጠኑ በማድረግ ግኝቶቹ ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ ችግሮቻቸው እንዲፈቱ ይደራጋል፡፡

**የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ አገልግሎቶቸን ለአባላት ተደራሽ ማድረግ፡-**

ብዙ አባላት ያሏቸውና ለአባላት ተደራሽ አገልግሎት መስጠት ያልቻሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት ቅርንጫፎችን በመክፈት አባላትን በቅርበት እንዲያገለግሉ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም አስፈላጊነቱን በጥናት በመለየት የአገልግሎት አሰጣጣቸው ተደራሽ ለማድረግ እንዲቻል በአባላትን ፍላጎት መሰረት ተከፍለው በመደራጀት እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ ጠንካራ አቅም መፍጠር ያልቻሉና አባላት የሚፈለጉትን አግልግሎቶች በሚፈለገው ደረጃ ማቅረብ የማይችሉትን የአባላትን ፍላጎት መሰረት በማድረግ በማዋሃድ የማጠናከር ስራ በትኩረት ይሰራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አስፈላጊ ሎጅስትኮችን በማሟላት አሰራራቸው በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በማዘመን ጥራት ያለው፣ ቀልጣፋና ተደራሽ የሆነ የአገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት እርካታን ለማሳደግ የሚሰጡትን አግልንቶች በማስፋፋት ጥራት ያለው፣ ቀልጣፋና ውጤታማ አግልግሎት ለአባላት ማቅረብ እንዲችሉ የማጠናከር ስራ በትኩረት ይሰራል፡፡

***መፍትሄ 2፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን ምርጥ ተሞክሮዎችን ለይቶና ቀምሮ ማስፋፋት***

***ምርጥ ተሞክሮ መለየት፣ መቀመርና ማስፋት፡-***

DRAFT

በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የኅብረት ሥራ ማህበራት የተደራጁበት የሥራ መስኮች እና የሚያከናውኑዋቸው ተግባራት የተለያዩ በመሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራቱን ተጨባጭ የሥራ ሁኔታ እና ደረጃ የሚመጥን የምርጥ ተሞክሮ ቅመራ መስፈርት ይዘጋጃል፡፡

በምርጥ ተሞክሮ ቅመራ እና ማስፋት ላይ በየደረጃው የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት እንዲሁም ለኅብረት ሥራ ማህበራት አማራር አካላት የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

በሴክተሩ ያሉትን ምርጥ ተሞክሮዎች በየደረጃው የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት ተቀምሮ እንዲሰፋ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ በየደረጃው የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኑዬን እና ፌዴሬሽን በአባሎቻቸው መካከል ምርጥ ተሞክሮዎችን በመለየትና በመቀመር እንዲሁም ግንዛቤ በመፍጠር እንዲሰፋ በትኩረት ይሰራሉ፡፡

በየደረጃው በሚገኙ የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላትም ሆነ በኅብረት ሥራ ማህበራት በተለየ ትኩረት አድርጎ ከሚቀመሩና ከሚሰፉ ተግባራት ማከካል የአመራር ብቃት፣ የአሰራር ሂደት ጥንካሬ፣ የተግባራት አፈጻጸም ጥራት፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እና ተደራሽነት፣ የቴክኖሎጅ አጠቃቀም ብቃት፣ በእሴት መጨመር ያላቸው ተሞክሮ፣ የሰው ኃይል አስተዳደር እና አያያዝ ስርዓት፣ የፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር እና አጠቃቀም ስርዓት፣ በልዩ ፈጠራ የተከናወኑ ተግባራት እና ሌሎች ላይ ይሆናል፡፡

የሚቀመሩና የመሳፉ ምርጥ ተሞክሮዎች ተዓማንነት እንዲኖራቸው፣ ሊተገበሩ የሚችሉ፣ ለውጥ የሚያመጡ፣ ትክክለኛነታቸው የተረጋገጠ ሆኖ ኃላፊነትና ተጠያቅነትን መሠረት በማድረግ እንዲከናወን የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## አምድ 7፡- የኅብረት ሥራ ምርታማነት ማሳደግ ኤክስቴንሽን ስርፀትና የኢንዱስትሪ ግንኙነትን ማስፋፋት፣

### ሀ. ነባራዊ ሁኔታ

በአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማስፋፋት የሚሰሩ የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች በዋናነት የሚከናወኑት በመንግስት ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ምርትና ምርታማነትን ለማሰደግ የሚሰጡ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች በብዛት የሚከናወነው በመንግስት ነው፡፡ ከዚህም አንፃር አርሶ/አርብቶ አደሩ በመንግስት የሚሰጠውን ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለረዥም አመታት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በዚህም መሰረት ለአባላት ምርት የተሻለ ዋጋ እንዲያገኝ በሀገር ውስጥና በሀገር ውጭ የተሻለ የገበያ መዳረሻዎችን በማፈላለግ በኩል የኅብረት ሥራ ማህበራት በርካታ ጥረቶችን አድረገዋል፡፡



DRAFT

የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ምርት በአገር አቀፍና በአለም አቀፍ ገበያዎች ላይ ከሌሎች ጋር በጥራት፣ በብዛትና በወቅታዊነት ተወዳደሪ ሆነው ማቅረብ እንዲችሉ የተሻለ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም የተሻለ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት ላይ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡

በአሁን ጊዜ መንግስት ከሚሰጠው የአክስቴንሽን አገልግሎት ጎን ለጎን አንዳንድ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባሎቻቸው የኤክስቴንሽን ባለሙዎችን ቀጥረው የአክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ ሆኖም ለዚህ ስራ ተግባራዊነት የሚያግዝ ኅብረት ሥራ የኤክስቴንሽን አጠቃቀም የአሰራር ስርዓት አልተዘረጋም፡፡

የተወሰኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከኢንዱስትሪዎች፣ ከቄራዎች ድርጅት፣ ከአየር መንገድ፣ ከቢራ ፋብሪካዎች፣ ከዱቄት ፋብሪካዎች እና እሴት ከሚጨምሩ ከሌሎች ኢንዱስትሪዎች ጋር ትስስር በመፍጠር በርካታ ማነቆዎችን በመፍታት የአባላትን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ላይ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም የኅብረት ሥራ ማህበራት የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥና ከኢንዱስትሪዎች ጋር ያላቸው ትስስር በሚፈለገው ደረጃ የተጠናከረ አይደለም፡፡

## ሰንጠረዥ 4፡ ጨርጨር ኦዳ ቡልቱም ኃ.የተ ሁለገብ የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ዩኒዬን በሞደልነት የተወሰደ (bench mark)

1. **ጨርጨር ኦዳ ቡልቱም ኃ.የተ ሁለገብ የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ዩኒዬን**

**የአባላትና ካፒታል እድገት፡-** ዩኒየኑ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ሀረርጌ ዞን ውስጥ የሚገኝ ስሆን 2008 ዓ.ም መረጃ መሠረት የአባል መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ቁጥር 128፣ የተናጠል አባላት ቁጥር 43,576 (ሴት 11.6) ካፒታሉን ብር 51.7 ሚሊየን አድጓል፡፡

**የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት** ፡- የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች አቅርቦት፣ የፋጆታ ምርቶች አቅርቦት፣ የአገር ውስጥ እና የውጭ የግብርና ምርቶች ግብይት እና ሌሎች ናቸው፡፡

**ለአባላት የግብርና ምርታማነት ማስደግ የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፡-** ዩኒየኑ የአርሶ አደሩን የማምረት በህል እንዲዳብር በራሱ አቅም የተለያዩ ውጤታማ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን ባለሙያ በመቅጠር በማስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ መካከል የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል በምርጥ ዘር ብዜት፣ በቡና ምርት እና ጥራት ማሻሻል እና በቦሎቀ ምርት ማሻሻል ላይ ጥራት ያለው የኤክስቴንሽን አገልግሎት በማስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በእንስሳት ምርት እና ምርታማነትን ለማሻሻል የወተት ላሞችን ዝርያ ማሻሻል፣ በከብት ማድረልብ፣ በወተት ማምረትና ማቀነባበር እና በእንስሳት መኖ ማምረትና ማቀነባበር ላይ በቅርበት ለአርሶ አደሩ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

2. **መቂ ባቱ ኃ.የተ. የአትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር ዩኒየን፡**

**የአባላትና ካፒታል እድገት፡-** ዩኒየኑ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምስራቅ ሸዋ ዞን ዱግዳ ወረዳ የሚገኝ ስሆን በ2008 ዓ.ም መረጃ መሠረት የአባል መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ቁጥር 150፣ የተናጠል አባላት ቁጥር በድምሩ 7,994 (ሴቶች 17.69) ካፒታሉን ደግሞ ብር 60 ሚሊየን አድጓል፡፡

**የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት:-** የአባላት ምርቶች ቲማቲም፣ ሽንኩርት፣ ቃሪያ፣ ድንች፣ ጎመን፣ ፎሶሊያ፣ በሎቄ፣ ፓፓያ፣ የአትክልት ምርጥ ዘሮች፣ በቆሎ እና ሌሎች ምርቶችን በመረከብ በአገር ውስጥና በውጪ አገር ገበያ በማፈላለግ በተሻለ ዋጋ በመሻጥ አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

**የኤክስፖርት ግብይት ላይ መሳተፍ:-** በ2007 ዓ.ም ብቻ 1,794 ኩ/ል ፎሶሊያ ለውጭ ገበያ በማቅረብ አባላት ከምርቱ የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ችለዋል፡፡

**ለአባላት ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ:-** ለአባላት በተለይም በአትክልትና ፍራፍሬ ምረት ላይ የሙያ ድጋፍ በማስጠት አባላትን ውጤታማ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በአባላት ማሳ ላይ የበቆሎ እና የሽንኩርት ምርጥ ዘሮችን በማባዛት ለአባላት እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች በተመጣጣኝ ዋጋ በማሰራጨት የተክኖሎጅ ስርጸት ላይ ከፍተኛ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የተለያዩ ችግኞችን በማፍላትና በመትከል ለአረንጓዴ ልማት ዘርፍ የበኩሉን ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡ የእርሻ ሜካናይዜሽን ትራክተርና የበቆሎ መፈልፈያዎችን እና ሞተር ፓምፖ ከነጥገናው ለአባላት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

## ለ. የኅብረት ሥራ ምርታማነት ማሳደግ ኤክስቴንሽን ስርፀትና የኢንዱስትሪ ግንኙነትን ማስፋፋት ያሉ ማነቆዎች:-

### ማነቆ 1:- ጠንካራና ውጤታማ የኅብረት ሥራ ምርታማነት ማሳደግ ኤክስቴንሽን ስርፀትና የኢንዱስትሪ ግንኙነት ስርዓት አለመኖር

በኅበረተሰቡም ሆነ በአባለት ውስጥ የኅብረት ሥራ ጽንሰ-ሓሳብን ለማስረጽ በየደረጃው የሚሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ ውስን ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በራሳቸው የአክስቴንሽን አገልግሎት ለአባሎቻቸው ለመስጠት በቂ ገንዛቤ የላቸውም፡፡ ለዚህም የሚሆን ግልፅ የሆነ አሰራር አልተዘረጋም፡፡ እየሰጡት ያለውም የኤክስቴንሽን ስራ ደካማ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የሚዲያ ተቋማትም ሚናቸውን በሚገባ እንዲወጡ አልተደረገም፡፡

በኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን ላይ በቂ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች አይሰጡም፡፡ የቀበሌ የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በሚፈለገው ደረጃ የኅብረት ሥራ ማህበራትን እያጠናከሩ አይደለም፡፡ ለአባላት ቅድመ- ምርት እና ድህረ- ምርት ላይ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት ላይ ውስንነት ይታያል፡፡

የኢንዱስትሪና የኅብረት ሥራ ማህበራት ግንኙነት ግልፅ አይደለም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ኢንዱስትሪ የሚፈልጋቸውን ምርቶች ለይቶ ማቅረብ አለመቻል፡፡ ከኢንዱስትሪ ጋር እንዴት ተሳስረው መንቀሳቀስ እንዳለባቸው የሚያመላክት ግልፅ አሰራር አለመኖር፡፡

## ሐ. ማነቆዎችን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች:-

***በገጠር የሚገኙ የግብርና ኅብረት ሥራ ማህበራት የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን አገልግሎት 100 በመቶ***

*ለአባለት ይሰጣሉ፡፡*

**መፍትሄ 1፡- ጠንካራና ውጤታማ የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን ስርፀትና የኢንዱስትሪ ግንኙነት ስርዓት መፍጠር፤**

**ጠንካራና ውጤታማ የኅብረት ሥራ አክስቴንሽን መፍጠር፡-**

በየደረጃው የሚገኘው ሕብረተሰብ ስለኅብረት ሥራ ማህበራት ፋይዳ አውቆ ኢንዲደራጅ ለማድረግ ስለ ኅብረት ሥራ ጽንሰ-ሓሳብ ተከታታይነት ያለው ሁሉ አቀፍ የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘዴዎች በመጠቀም የማስገንዘብ ስራ ይሰራል፡፡ የኅብረት ሥራ ግንዛቤ ለማሳደግ ከፌደራል እስከ ቀበሌ የአስተዳደር በየደረጃው የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ ትላልቅ ዘመቻዎች (campaign)፣ የንቅናቄ መድረኮችን፣ ኮንፍራንሶችን የሚካሄድ ይሆናል፡፡

በሚዘጋጁ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮች ላይ ስኬታማ የሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተሞክሮዎች እንዲተላለፉ በማድረግ፣ የተለያዩ ግንዛቤ ማሳደጊ መሳሪያዎችን (toolkits’) በማዘጋጀት፣ የህትመትና ኤሌክትሮኒክስ የሚዲያ አመራጮችን እና ማህበራዊ ድህረ-ገፆችን በመጠቀም የማስተዋወቅ ስራዎች በስፋት ይሰራሉ፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ የሚቋቋመው የኅብረት ሥራ ሊግ የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን ስራን በስፋት ለመስራት ራሱን የቻለ የኅብረት ሥራ ልሳን የሚሆን ሚዲያ በማቋቋም የኅብረት ሥራ ግንዛቤ የማስረጽ ተግባር እንዲያከናውን ይደረጋል፡፡ የሚዲያ አመራጮችን በመጠቀም በሀገር ውስጥ ያሉ ስኬታማና ሞዴል የሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራትን በስፋት የማስተዋወቅ ሥራ ይሠራል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችል የኤክስቴንሽን አግልገሎቶችን በራሳቸው አቅም በጥራት እንዲሰጡ በትኩረት ይሰራል፡፡ በአገራችን በኅብረተሰቡ ውስጥ ሴቶች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው በመሆኑ ትርጉም ባለው መንገድ በልማት መሳተፍ ያስፈልጋል፡፡ ሴቶች በራሳቸው ወይም ከወንዶች ጋር በተመጣጠነ ስብጥር በኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲደራጁና የልማት ተሳትፎአቸውን እንዲያሳድጉ እና የአመራር ክህሎታቸውን በማዳበር በአመራሩ ውስጥ ድርሻቸውን እንዲያደግ ግንዛቤ ይፈጠራል፡፡

በአሁን ጊዜ በሀገራችን በገጠርም ሆነ በከተማ እያደገ የመጣውን አምራች የወጣቱን ኃይል ትኩረት በመስጠት በተለያዩ ሙያዎች በማሠልጠን የስራ ፈጣራ ክህሎታቸውን በማሳደግ እና በነባር ኅብረት ሥራ ማህበራት አባል እንዲሆኑ ወይም በአዲስ ተደራጅተው ስራ ውስጥ እንዲገቡ አስፈላጊ የሆኑ የብድር አቅርቦትና ምቹ የስራ ቦታ በመፍጠር ተጠቀሚነታቸውን እንዲያረጋግጡ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

አካል ጉዳተኞች በተለያዩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች በማደራጀት፣ ተከታታነት ያለው ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ በዚህ መሰረት አስፈላጊውን የብድር አቅርቦት እንዲያገኙ በማመቻቸት፣ የምርት ግብዓቶችን



DRAFT

በቀላሉ እንዲያገኙ እንዲሁም ለምርቶቻቸው የተሻለ የገበያ ዋጋ እንዲያገኙ በማድረግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ትኩረት በመስጠት እገዛ ይደረግላቸዋል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በከተሞች እየታየ ባለው መልኩ በተመሳሳይ መንገድ በገጠሩ ውስጥ በርካታ ቁጠባን በማሰባሰብና ወደ ኢንቨስትመንት ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ በዚህም መሰረት በገጠርም እና በከተማ የሚኖረውን ሰፊውን ነዋሪ ሕብረተሰብ ግንዛቤ በማሳደግ የቁጠባ ባህል እንዲዳብርና በዘለቄታው ራሳቸውን በራሳቸው በፋይናንስ እንዲተሳሰሩ የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራትን በሰፊው እንዲደራጁ እና ነባሮቹ እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡

በዕደ ጥበብና በአነስተኛ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ያለውን እምቅ ሀብት እና አገር በቀልና ተስማሚ ቴክኖሎጂ ከመጠቀም አኳያ በዘርፉ በገጠርም ሆነ በከተማ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበሩ የተለያዩ የኅብረት ሥራ ማኅበራት በዓላት እንደተጠበቁ ሆነው በአገራችን በየዓመቱ በሐምሌ ወር የመጀመሪያው ሳምንት ቅዳሜ "የኢትዮጵያ የኅብረት ሥራ ቀን" ተብሎ በሁሉም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዘንድ ይከበራል፡፡ በዚህም ላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጽንሰ-ሃሳብ፣ ዓላማ፣ መርሆ፣ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ለኅብረተሰቡ ትምህርት ይሰጣል፤ ቅስቀሳም በስፋት ይደረጋል፡፡ ይህም በሁሉም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዘንድ በንቃት የሚካሄድ ይሆናል፡፡ ለዚህም የሚሆን ፋይናንስ ከኅብረት ሥራ ማህበራት፣ ከኅብረት ሥራ ፈንድና በሌሎች ድጋፍ ሰጭ አካላት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

መንግስት ለኅብረት ሥራ ማህበራት ልማት ልዩ ትኩረት በመስጠት ለመደገፍ የሚያደረገውን የግንኙነት አግባብ በመወሰን ነፃነታቸውን በማይጋፋ መልኩ ራሳቸውን ችለው የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለአባሎቻቸው እንዲሰጡ ያበረታታል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ትምህርት የውስጥ አሰራርና አመራር ለኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት፤ የተለያዩ ኮሚቴዎች፤ ቅጥር ሰራተኞች፤ ለመንግስት አመራሮች፤ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅት መሪዎች፤ ለአካባቢው ተጽኖ ፈጣሪ ሰዎች እና ሌሎች አባል ላልሆኑ ስለ ኅብረት ሥራ በቂ የሆነ የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ ይደረጋል፡፡ በዚህም መሠረት ጠንካራና ሁሉን አቀፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻ (campaign) ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡

### የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን ስርፀትና የኢንዱስትሪ ግንኙነት ስርዓት ማጠናከር

የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ገበያን መሰረት ያደረገና ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆን ጥሬ ምርት እንዲያመርቱ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማሰደጊያና የኤክስቴንሽን ስራዎች አጠናክሮ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም ሲባል የኅብረት ሥራ ማህበራት በራሳቸው አቅም ለአባላት የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት አለባቸው፡፡



DRAFT

በገጠርም ሆነ በከተማ በተለያዩ የማምረትና አገልግሎት መስጠት ተግባር ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችን በኅብረት ሥራ ማህበራት በማደራጀት ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን ለማሳደግ የሚረዳ ግንዛቤ ለመፍጠር በቂ ጥረት አልተደረገም፡፡ ስለሆነም ለእነዚህ አካላት በቂ የክህሎትና የሙያ ስልጠና በመስጠት በኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲደራጁ ማበረታታት፣ በዚህም ተግባር ላይ የተሰማሩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በቅንጅት የሚሰሩበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

የአርብቶ አደሩን ማህበረሰብ ሕይወት ለማሻሻል በልማት ውስጥ በስፋት እንዲሳተፍና ለሚያመርቷቸው ምርቶች አስተማማኝ ገበያ እንዲያገኙ ስለኅብረት ሥራ ጠቀሜታና አስፈላጊነት ላይ ነባራዊ ሁኔታቸውን ባገናዘበ ሁኔታ በቂ ግንዛቤ በመፍጠር እንዲጠናከሩ ተቀናጅቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡ በተለይም የአካባቢውን ወጣቶች በማሰልጠን በእንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦ ኅብረት ሥራ ማህበር እንዲደራጁ በማድረግ በምርቶቻቸው ላይ እሴት በመጨመር ወይም ከኢንዱስትሪ ተቋማት ጋር በማስተሳሰር ለምርቶቻቸው የተሻለ የገበያ አማራጭና ዋጋ እንዲያገኙ በማድረግ በአካባቢው ሰፊ የሥራ እድል እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ በተለይም የአርብቶ አደሩን ነባራዊ ሁኔታ ልመጥኑ የሚችሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት አሰራር ስርኣት ተዘርግቶ እንዲተገበር በትኩረት ይሰራል፡፡

DRAFT

የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ገበያን መሰረት በማድረግ ለኢንዱስትሪ የሚሆኑ ጥሬ ምርቶችን እንዲያመርቱ ተከታታነት ያለው የግንዛቤ ማሰደጊያ የኤክስቴንሽን ስራዎች ተጠናክሮ ይሰራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ለአባል አርሶ አደሩ በአግሮኖሚክ ስራ (farming guidance) ላይ የአክስቴንሽን ድጋፍ ከማድረግ በተጨማሪ ለአባላት የሚጠቅሙ ዘመናዊና አዳዲስ አሰራሮችን እንዲሁም ቴክኖሎጂዎችን በማመንጨት፣ በማባዛትና በማሰራጨት፣ እሴት በመጨመር ተግባር እና የተለያዩ የቴክኒክ ድጋፎችን በማድረግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት ምርት መሰረት ያደረጉ በጥናት የተረጋገጡ የተለያዩ ኢንዱስትሪዎችን በራሳቸው በማቋቋም እና ለኢንዱስትሪው የሚሆኑ ጥሬ እቃዎችን ከአባላት ጋር በቀጥታ በማስተሳሰር ይሰራሉ፡፡ ለዚህም በቅድመ ምርት እና ድህር ምርት አያያዝ ላይ ተከታታይነት ያለው የኤክስቴንሽን አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን ኢንዱስትሪው በሚፈልገው የጥራት ደረጃ፣ ዓይነትና መጠን መሰረት አባላት ከኢንዱስትሪው ጋር እንዲተሳሰሩ ተገቢውን ሙያዊ ድጋፍ ሊያደርግ የሚችል ክፍል ሊኖራቸው ይችላል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ምርት በቀጥታ ተረከበው ከኢንዱስትሪዎችና ከአቀነባባሪዎች ጋር በሚያደርጉት ስምምነት መሰረት እንዲተሳሰሩ ይደረጋል፡፡ ይህ የሚሆነው የኅብረት ሥራ ማህበራት ኢንዱስትሪዎች ወይም አቀነባባሪዎች የሚፈልጉትን ምርት የጥራት ደረጃውን ጠብቆ፣ በሚፈለገው መጠንና በሚፈለግበት ጊዜና ቦታ ማቅረብ

ሲችሉ ነው፡፡ ይህንን ለማሳካት የሚቻለው አባላቱ ተገቢውን የአክስቴንሽን አገለግሎት ማግኘት ከቻሉ ነው፡፡ ስለዚህ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት በራሳቸው የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በሀገሪቱ በሚከፈቱ የተቀናጀ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ በመግባት የአባሎቻቸው ምርት ላይ እሴት ጨምረው ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ያቀርባሉ፡፡ እንዲሁም የሚያስፈልገውን የግብርና ምርቶች ጥራቱን ጠብቀው፣ እሴት ጨምርውና አደራጅተው ለኢንዱስትሪ ፓርኮች በጥሬ እቃነት በማቅረብ በማንኛውም ተግባራት ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ በዚህም መሰረት ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ለሚገቡት የኅብረት ሥራ ማህበራት መንግስት አስፈላጊውን ድጋፍና ማበረታቻዎችን ያደርጋል፡፡

## አምድ 8 ፡- የኅብረት ሥራ ሴክተር የትምህርት፣ የሥልጠና እና የጥናትና ምርምር ሥርዓት፣

### ሀ. ነባራዊ ሁኔታ

የኅብረት ሥራ ማህበራትን ጽንሰ-ሐሳብና አሰራርን ለማስረጽ መንግስት፣ አቅም ገንቢዎችና ራሳቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ የኅብረት ሥራ ትምህርትና ስልጠናዎችን በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም የሚሰጡ ስልጠናዎች ያልተቀናጁ፣ ወጥነት የሌላቸው እንዲሁም ተደጋጋሚ በመሆናቸው በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማ አልሆኑም፡፡ በክልል ደረጃም ስልጠናዎች በተመሳሳይ መልኩ ሳይቀናጁ የሚሰጡ ሲሆን ይህም ለበርካታ የሀብት ብክነት በር ከፍቷል፡፡ የትኛውን ስልጠና ማን፣ እንዴት፣ የትና ምን መስጠት እንዳለበት በግልፅ አልተቀመጠም፡፡ የስልጠና ማዕከል ባለመኖሩ በተቀናጀ ሁኔታ የኅብረት ሥራ ትምህርትና ስልጠና በአንድ ማዕከል መስጠት አልተቻለም፤ በተመሳሳይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጥናትና ምርምር በተቀናጀ መልኩ እየተጠና አይደለም፡፡ በዩኒቨርሲቲዎች የተጠኑ ጥናቶችን በማደራጀት የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲጠቀሙበት አልተደረገም፡፡

### ለ. የኅብረት ሥራ ሴክተር የትምህርት፣ የሥልጠና እና የጥናትና ምርምር ሥርዓት ያሉ ማነቆዎች

#### ማነቆ 1፡- ጠንካራ የኅብረት ሥራ የትምህርትና ሥልጠና ስርዓተ ትምህርት እና አሰራር አለመኖር፡፡

የኅብረት ሥራ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥባቸው ጠንካራ የኅብረት ሥራ የትምህርትና ሰልጠና ስርዓተ ትምህርት አለመኖር፡፡ ኅብረት ሥራ በሚያስተምሩ ዩኒቨርሲቲዎች ወጥነት ያለው ስርዓተ ትምህርት አለመኖር፡፡ የሚዘጋጀው የኅብረት ሥራ ስርዓተ ትምህርት በሚፈለገው ደረጃ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ፍላጎት መሰረት ያደረገ አለመሆን፡፡ የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ግልፅ የአሰራር አቅጣጫ አለመኖር፡፡ ስርዓተ ትምህርት በየወቅቱ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ፍላጎት መሰረት በማድረግ አለማሻሻል፡፡ ስርዓተ ትምህርትን መሰረት ያደረገ ችግር ፈቺ ስልጠና አለመስጠት፡፡

ክፍተቶችንና ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ስልጠና አለመዘጋጀት፤ የስልጠና የአሰራር መመሪያ አለመኖር፣ ተቀናጅቶ አለመስራት፣ ስልጠናዎች ወደ ታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል ተደራሽ አለመሆን፣ በኅብረት ሥራ ማህበራትና በዩኒቨርሲቲዎች መካከል ጠንካራ ግንኙነት አለመኖር፣ የተዘጋጁ የስልጠና ማኑዋሎች ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆን፣ ለስልጠና የሚሆን በቂ በጀት አለመኖር፣ የኅብረት ሥራ ጽንሰ-ሃሳብ ሳያውቁ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ቢዝነስ በልምድ የመምራት ችግር፣

### ማነቆ 2 - የተቀናጀ የኅብረት ሥራ የልህቀት ማዕከል አለመኖር

ስልጠናዎችን በተደራጀ መልኩ አለመሰጠት፣ ስልጠናውን ውጤታማ ለማድረግ አለመቻል፣ የስልጠና ቦታዎች አለመመቸት፣ አላስፈላጊ ወጭዎች መብዛት፣ የተረጋጋ ስልጠና መስጠት አለመቻል፡፡

### ማነቆ 3፡- የኅብረት ሥራ ሴክተር ግልፅ የጥናትና ምርምር አሰራር አለመኖር

ግልፅ የጥናትና ምርምር የአሰራር መመሪያ አለመኖር፣ ተቀናጅቶ አለመስራት፣ በኅብረት ሥራ ዙሪያ በተበታተነ መልኩ የተጠኑትን ጥናቶች ወደ ታች ተደራሽ አለማድረግ፣ በምርምር ተቋማት እና በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል ያለው ግንኙነት ዝቅተኛ መሆን፣ ለጥናትና ምርምር የሚሆን በቂ ፋይናንስ አለመኖር፡፡ ሴክተሩ ለኅብረት ሥራ ጥናት እና ምርምር ያለው ዝንባሌ አነስተኛ መሆን፣ በጥናትና ምርምር ስራ ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ በግልፅ አለመኖር ችግሮች ይታያሉ፡፡

### ማነቆ 4፡- የኅብረት ሥራ ሴክተር፣ የትምህርትና ስልጠና እና የጥናትና ምርምር ተቋማት ጠንካራ ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር፡-

የኅብረት ሥራ ጥናት እና ምርምር በተቀናጀ መልኩ እየተሠራ ባለመሆኑ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተመሳሳይ የሆኑ የጥናትና ምርምር ተግባራት ይካሄዳሉ፡፡ ይህ አሰራር ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዘነ ነው፡፡ በኅብረት ሥራ ሴክተሩ እና በትምህርት እና ምርምር ተቋማት መካከል ያለው ግንኙነት ደካማ ነው፡፡ ሴክተሩ በኅብረት ሥራ ላይ ለምርምር የሚያግዙ ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት በዘርፉ ጥናቶች እንዲደርጉ አያበረታቱም፡፡ በጋራ ተቀናጅቶ የምርምር ሃሳቦችን ለይቶ ለማጥናት እንዲቻል ግልፅ የሆነ የጋራ የግንኙነት አግባብ አለመኖር፣ ቀጣይነት ያለው የተቀናጀ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት አለመኖር፣

### ሐ. ማነቆዎችን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፡-

| |
|---|
| ***የኅብረት ሥራ ትምህርት፣ ስልጠና እና ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ 12 የልህቀት ማዕከላት ተገንብቶ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡*** |

**መፍትሄ 1፡ ጠንካራ የኅብረት ሥራ የትምህርትና ሥልጠና ስርዓተ ትምህርት እና አሰራር አለመኖር፡፡**

***የኅብረት ሥራ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ-ትምህርት፡-***

የኅብረት ሥራ ፅንሰ ሃሳብና ጠቀሜታ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጀምሮ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም በኅብረት ሥራ ሙያ በመደበኛነት ስልጠና ይሰጣል፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን በመስኩ በቂ የሰለጠነ የሰው ሃይል ለማፍራት እንዲቻል በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የስልጠናና የልምድ ልውውጥ ፕሮግራሞች ይዘጋጃሉ፡፡

የአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ወጥ እና ተስማሚ ዓለም አቀፋዊ ደረጃና ስታንዳርድ ያለው የኅብረት ሥራ ሥርዓተ ትምህርት በመገንባት የኅብረት ሥራ ማህበራትን በአሰራርና አመራር ውጤታማ ማድረግ ላይ ትኩረት ያደረገ ይሆናል፡፡ በየደረጃው ለሚገኙ ለማደራጃና ቁጥጥር አካለት አመራሮችና ባለሙያዎች፣ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት፣ አመራሮችና ቅጥር ሠራተኞች በየጊዜው በሚሻሻልና በተቀረፀ የኅብረት ሥራ ስርዓተ-ስልጠና መሰረት ወጥነትና ተያያዥነት ያላቸው ስልጠናዎች በቀጣይነት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

በኅብረት ሥራ የልህቀት ማዕከልም ሆነ በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ወጥ እና ተመሳሳይ የሆነ የኅብረት ሥራ የትምህርትና ስልጠና ሥርዓተ ትምህርት በሚዘጋጅበት ወቅት የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት፣ የኅብረት ሥራ ትምህርት የሚያስተምሩ ዩኒቨርሲቲዎችና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በሚገባ በማሳተፍ በቅንጅት ይቀረፃል፡፡ የኅብረት ሥራ ሴክተሩ ለኅብረት ሥራ ማህበራት እድገት እንዲያግዝ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የጋራ ፕሮጀክት በመቅረፅና በመተግበር፣ የማማካር ስራዎችን በጋራ በማካሄድ በጋራ ትብብር መሰራት ይኖርበታል፡፡

ማንኛውም የኅብረት ሥራ የልህቀት ማዕከል ወይም ዩኒቨርሲቲ ጥናት ላይ የተመሰረተ ከአገሪቱ ኅብረት ሥራ ማህበራት ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚሄድና የኅብረት ሥራ ማህበራትን መሰረታዊ ችግሮችን የሚፈታ ትምህርትና ስልጠና መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት በንድፈ ሃሳብ ላይ ያተኮረ የኅብረት ሥራ ትምህርትና ስልጠና የወሰዱ ተማሪዎችና ሰልጣኞች በተለያዩ ኅብረት ሥራ ማህበራት በመገኘት ከ50 በመቶ በላይ በመስክ በተግባር የተደገፈ ትምህርት የሚያገኙበት ሁኔታ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ መካታት ይኖርበታል፡፡ በዚህም መሰረት የሚሰጥ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት ትምህርት አገራችን የምትከተለውን ሶሽዮ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን መሠረት ማድረግ አለበት፡፡

በዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች የሚካሄዱ የተለያዩ የኅብረት ሥራ ስልጠናዎች፣ ዎርክሾፖች፣ ስምፖዚየሞችና ሴሚናሮች በጥናት ላይ የተመሰረቱና የኅብረት ሥራ ማህበራትን መሰረታዊ ችግሮችን በመፍታት ላይ ያተኮሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

**ጠንካራ የኅብረት ሥራ ትምህርትና ሥልጠና አሰራር በመዘርጋት ተደራሽ ማድረግ**

በገጠር የሚኖረውን ያልተማረውን የኅብረተሰብ ክፍል መደበኛ ያልሆነውን የጎልማሶች ትምህርትን ከኅብረት ሥራ ማህበራት ትምህርት ጋር አቀናጅቶ በመስጠት የስራ ፈጣራ፣ የአመራርነትና የቢዚነስ አሰራር ክህሎታቸውን በማሳደግ በስራዎቻቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ ለዚህም የሚመለከታቸው አካላት በጋራ ተቀናጅተው የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማትን በመጠቀም እንዲሰሩ ይደራጋል፡፡

በየደረጃው ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት እርከኖች የአባላትን ግንዛቤ ለማሳደግ በራሳቸው የስልጠና ማዕከል ወይም በአከባቢ ያሉትን ትምህርት ቤቶችን ወይም የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከልን በመጠቀም የአቅም ግንባታ ትምህርትና ስልጠናዎችን አቅደው መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት የአርሶ/ አርብቶ አደር የማሰልጠኛ ማዕከላት፣ ትምህርት ቤቶች እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ተቀናጅተው የሚሰሩበት አሰራር ይዘረጋል፡፡ የልህቀት ማዕከሉ ከገበሬ ማሰልጠኛ ተቋም ላይ የራሱን የኅብረት ሥራ ባለሙያ በመመደብ ስለ የኅብረት ሥራ ስልጠናና ትምህርት የሚሰጥበት አደረጃጀትና አሰራር ይዘረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ተማሪዎችና ሰልጣኞች ትምህርታቸውን ከማጠናቀቃቸው በፊት በኅብረት ሥራ ማህበራት ዘንድ በመገኘት ተሞክሮ የሚቀስሙበትና በተግባር የተደገፈ/ተግባር ተኮር/ ትምህርት የሚያገኙበት ሁኔታ መኖር አለበት፡፡ የሚሰጠው ትምህርትና ስልጠና ከኅብረት ሥራ ኢንዱስትሪ ጋር በቀጥታ የሚያገናኝ መሆን አለበት፡፡ ለዚህ ስራ ተብለው የሚዘጋጁ የስልጠና እና የትምህርት ማኑዋሎች፣ ሞጁሎችና መማሪያ መፅሃፍት የሚጠቀሙባቸው (case study and examples) የትምህርት መረጃዎችና ምሳሌዎች የገራችን ኅብረት ሥራ ማህበራትን ነባራዊ ሁኔታ ማዕከል የሚያደረጉና የሚጠቀሙ መሆን ይኖርበታል፡፡

የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳን መሰረት ያደረገ የትምህርትና ሥልጠና ለኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት፣ አመራር አካለት፣ ለቅጥር ሰራተኞች እና ባለሙያዎች በቋሚነት መስጠት ይኖርበታል፡፡

**መፍትሄ 2፡- ሁሉ አቀፍ የኅብረት ሥራ የልህቀት ማዕከላት በመገንባት አደረጃጀቱን ማጠናከር**

የኅብረት ሥራ የልህቀት ተቋም መኖር ህብረተሰቡ ስለ ኅብረት ሥራ ሙሉ እውቀትና ግንዛቤ ኖሮት ተጠቃሚ እንዲሆን ጥራት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ ትምህርትና ስልጠናዎችን ለመስጠትና ወደ ተጠቃሚ ለማውረድ ከማገዙም በላይ መንግሥት ለሥልጠና የሚያወጣውን ወጪ ይቀንሳል፡፡ ከአከባቢው ሳይርቅ በቅርበት አገልግሎት እንዲያገኝ ያግዛል፡፡

ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማህበራት የትምህርትና ስልጠና፣ ጥናትና ምርምር ስራዎች ላይ ተደራሽ የሆነ ድጋፍና አገልግሎት የሚሰጥ የራሱ ተግባርና ሃላፊነት ያለው የኅብረት ሥራ የልዕቀት ማዕል በፌደራልና በየክልሎች ደረጃ ይቋቋማሉ፡፡

የልህቀት ማዕከሉ ከዩኒቨርሲቲዎችና ከአቅም ገንቢዎች ጋር በጋራ በመሆን ኅብረት ሥራን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የጋራ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅና በመተግበር እንዲሁም የማማከር ስረዎችን በመተባበር እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

የልህቀት ማዕከሉ የሰለጠነ ባለሙያ በማፍራት፣ ደረጃውን የጠበቀ ስልጠና በመስጠት፣ ኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ አሰራራቸውን በብቃት እንዲመሩ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት፣ ተሞክሮዎችን በማስፋፋት፣ ጥራት ያላቸውና ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ወደ ተጠቃሚዎች በማውረድ አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ የባለቤትነት ስሜት እንድኖር መሰረት አድርጎ መሰራት አለበት፡፡

የልህቀት ማዕከል ከሁሉም በላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት እድገት አቅጣጫ በትክክል አሻግሮ አይቶ ለመተለምና ለማስቀጠል ብቻ ሳይሆን ወቅታዊ የዓለም የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና የአካባቢ የአየር ንብረት ለውጦችን ያገናዘበ እንዲሁም የዓለም ገበያን አስቀድሞ ያማተረ ሥራ እንዲሰሩ በየጊዜው አዳዲስና ከጊዜው ጋር የሚሄዱ የአሰራር ስርዓቶችን በጥናት በመለየት እንዲሰራበት ያደርጋል፡፡

የልህቀት ማዕከሉ የበጀት ምንጭ ከሚሰጠው አገልግሎት ከሚገኝና በራሱ የውስጥ ገቢ እንዲሁም በሚያገኛቸው ድጋፎች ይተዳደራል፡፡ ነገር ግን አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የኅብረት ሥራ ማህበራት ንቅናቄ እስኪረከብ ድረስ መንግስት በበጀት ይደግፋል፡፡ በቀጣይ ማዕከሉ በራሱ የውስጥ ገቢና ከኅብረት ሥራ ማህበራትና ከኅብረት ሥራ ፈንድ የበጀት ድጋፍ የሚያገኝበት አሰራር ይዘረጋል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት የልህቀት ማዕከል የስርዓተ ትምህርቱ አደረጃጀት የሚያተኩረው ለኅብረት ሥራ ማህበራት አመራር አካላት ለ5 ቀን የሚቆይ የአጭር ጊዜ ሥልጠና መስጠት፣ ለቅጥር ሠራተኞች እና ለባለሙያ ከ5-10 ቀን የሚቆይ የአጭር ጊዜ፣ ከ10-30 ቀን የሚቆይ የመካከለኛና ከ3 ወር በላይ የሚቆይ የረዥም ጊዜ የትምህርትና ሥልጠና መስጠት ላይ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም ግን አገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጡ ስልጠናዎች በዓይነትም ሆነ በይዘት በክልል በሚቋቋሙ የልህቀት ማዕከላት ከሚሰጡት ስልጠናዎች ይለያል፡፡ የልህቀት ማዕከሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናዎችን በደረጃ የሚሰጥ ሆኖ በሂደትም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጥበት አሰራር ይዘረጋል፡፡

ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ነባራዊ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ተጠሪነቱ ለክልሉ ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የሆነ የራሳቸው የኅብረት ሥራ የልህቀት ማዕከል በተመሳሳይ መልኩ ይቋቋማል፡፡ በክልሎች የሚቋቋመው የልህቀት ማዕከልም በአገር አቀፍ ደረጃ ከሚቋቋመው ጋር በጋራ ተቀናጅተው መስርት የሚስችላቸው የጋራ አሰራር ይኖራቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት በክልል ደረጃ ለሚገኙ መካከለኛ አመራሮች፣ ለማናጀሮች፣ ለኅብረት ሥራ ስራ አመራር አባላት፣ ቅጥር ሠራተኞች እና ለአባላት ከ1-3 ቀን የሚቆይ የአጭር ጊዜ ልዩ የክህሎት ስልጠናዎችን መስጠት አለበት፡፡ ይህም ሲሆን በአገር አቀፍም ሆነ በክልል ደረጃ በሚቋቋሙ የልህቀት ማዕከሎች የሚሰጠው ስልጠና የአሰልጣኞች ስልጠና ስልት ተጠቅሞ ተደራሽ ለማድረግ ይሰራል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደረግ የትምህርትና ስልጠና ስራ መቃኘት ያለበት የኅብረት ሥራ ግቦችን ለማሳካት፣ ክህሎታቸውን ለማሳደግ፣ ወቅታዊ ጥናቶችንና ምርምሮችን ለማጠናከር፣ ዕውቀት ላይ የተመሰረተ የአመራር ስርዓት እንዲኖር ለማድረግና በቂ የሰው ሃይል እንዲኖር ለማስቻል ነው፡፡ ለኅብረት ሥራ ማህበራትና ለማህበረሰብ ህልውና የሚያስፈልጉ ሀብቶችና ሂደቶችን በማልማትና በማጠናከር በፍጥነት የሚለዋወጠውን የዓለም ሁኔታ ለመቋቋም ሲባል ለኅብረት ሥራ ማህበራት ቀጣይነት የሚያግዙ በአጭርና በረዥም ጊዜ በሚከናወኑ፣ በጋራ መተማመን በተደረሰባቸው ግቦች ላይ፣ ያለውን ተለዋዋጭ ሁኔታ በመቋቋም፣ ከውጭ ካሉት ተቋማት ጋር ግንኙነት መፍጠር፣ ተቋማዊና ግላዊ ተግባራትን በማስፋት እና በየጊዜው አዳዲስና ከጊዜው ጋር የሚሄዱ የአሰራር ስርዓቶችን በጥናት በመለየት በትኩረት እንዲሰራበት ያደርጋል፡፡

**መፍትሄ 3፡- ግልፅና ጠንካራ የኅብረት ሥራ የጥናትና ምርምር አሰራር መዘርጋት፤**

የኅብረት ሥራ ማህበራት አሰራር ቀልጣፋና በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን በመስኩ የተለያዩ ጥናትና ምርምሮች ይካሄዳሉ፡፡ በዚህ መሰረት ለኅብረት ሥራ እድገት የሚበጁ የጥናትና ምርምር ስርዓት በመዘርጋት፣ የምርምር ሃሳቦችን ለይቶ በማጥናት የምርምር ውጤቶችን መተግበርና የተለያዩ የማማከር ስራዎች ይካሄዳሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ትምህርትና ስልጠና እና ጥናትና ምርምር ተግባር ላይ የተሰማሩ ዩኒቨርሲቲዎች፣ አቅም ገንቢዎች በአቅራቢያቸው የሚገኙ ኅብረት ሥራ ማህበራትን በቅርበት በሞዴልነት ይዞ በማጠናከር የተገኙ ተሞክሮዎችን ወደ ሌሎች አካባቢዎች እንዲስፋፉ በማድረግ ሂደት ቁልፍ ሚናቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

ለኅብረት ሥራ ጥናትና ምርምር የሚውል የበጀት ምንጭ ከኅብረት ሥራ ማህበራት፣ ከኅብረት ሥራ ፈንድ፣ ከመንግስትና በአቅም ገንቢዎች የሚገኝ ይሆናል፡፡

የኅብረት ሥራ ጥናትና ምርምር ስርዓት ግንባታን በተመለከተ የሀገሪቱን የእድገትና ልማት አቅጣጫ በተከተለ ሁኔታ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ንቅናቄ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ግብ ማዕከል አድርጎ መከናወን ይኖርበታል፡፡

የኅብረት ሥራ ጥናትና ምርምር የኅብረት ሥራ ሴክተርን ወቅታዊና ስትራቴጂካዊ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ጥናትና ምርምር እንዲያካሄዱ በተጨባጭ ከሚታዩ ችግሮች ማዕከል በማድረግ የኅብረት ስራ ሴክተሩን ችግር በማጥናት አማራጭ መፍትሄ አመላካች ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚያስችል የምርምር ውጤት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

**መፍትሄ 4፡- የኅብረት ሥራ ሴክተር፣ የትምህርትና ስልጠና እና የጥናትና ምርምር ተቋማት ጠንካራ ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሰራር መፍጠር፡-**

ለኅብረት ሥራ ማህበራት ትምህርትና ስልጠና እና ጥናት እና ምርምር ላይ የሚሳተፉ የኅብረት ሥራ ሴክተር፣ ሀገራዊ ኅብረት ሥራ ሊግ፣ ኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽኖች፣ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች፣ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በንድፊ ሀሣብ እና በትግበራ ሂደት በሚከናወኑ ተግባራት ድግግሞሽ ሳይፈጠር በጋራ ተቀናጅተው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት፣ አቅም ገንቢዎች፣ የምርምር ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች፣ ሌሎች ባለድርሻ አካላት አቅም ለመገንባትና የጥናትና ምርምር ስራዎችን ተቀናጅተው የሚሰሩበትና የምርምር ውጤቶችን በጋራ በመሆን ስራ ላይ የሚውልበት አሰራር ይፈጠራል፡፡

ለኅብረት ሥራ ማህበራት እድገት የሚያስፈልጉና በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ጥናት የሚደረግባቸውን ጉዳዮችን በመለየት ከኅብረት ሥራ ሴክተሩ ጋር በመሆን ጥናትና ምርምር እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

ከኅብረት ሥራ ሴክተሩ እና ከሌሎች አካለት ጋር የሚፈጠሩ የጋራ ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሰራሮች ዋና ትኩረታቸው በትምህርትና ስልጠና፣ በጥናትና ምርምር፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅና በማስረጽ፣ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችና ሰልቶችን በመቅረፅ እና ተሞክሮዎችን ማስተዋወቅና በማስፋት ስራዎች ላይ በጋራ ተቀናጅተው ይሠራሉ፡፡

ኅብረት ሥራ ማህበራት እና በሌሎች አቅም ገንቢዎችና ባለድርሻ አካላት የተውጣጣና በዕቅድ የሚመራ የጋራ የምክክርና ውይይት ፎረም እንዲኖር በማድረግ ለኅብረት ሥራ ማህበራት እድገት የሚያግዙ አዳዲስ ሃሳቦችን በማፍለቅ ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ የሚዘረጋበት አሰራር ይፈጠራል፡፡

የሴክተሩን ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት አቅም ከመገንባት አንጻር ጉድለቶችን ፈትሾ ችግር ፈቺ እና ድግግሞሽ የሌለበት ሥልጠና የመስጠትና እንዲሁም ለዘላቂ መፍትሄና ለፖሊሲ ማመንጨት አቅጣጫ ሠጪ የሆኑ ጥናትና ምርምር ሥራዎች በትኩረት የሚሠሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

በጥናትና ምርምር ላይ የሚኖረው ግንኙነትና ቅንጂታዊ አሰራር በትምህርትና ስልጠና፣ በጥናትና ምርመር፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅና በማስረጽ፣ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችና ሰልቶችን በመቅረፅ፣ ለትምህርት፣ ሥልጠና እና ምርምር የሚውል ፈንድ በማዘጋጀትና በመደገፍ፣ በየአመቱ የጥናት እና ምርምር ፕሮፖዛሎችን በማወዳደር የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ ባለሙያዎችንና ኅብረት ሥራ ማህበራትን በማበረታታት ሊሆን ይችላል፡፡

የኅብረት ሥራ ዙሪያ የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች ትኩረት የሚያደረጉት በአነስተኛ እና ከፍተኛ የምርምር ፕሮጀክቶች ላይ ይሆናል፡፡ የሚደረግ ጥናነትና ምርምር በኅብረት ሥራ አመሠራረት፣ አመራር እና አስተዳደር፣ በኅብረት ሥራ አባልነትና ተሳትፎ፣ በሴቶች እና ወጣቶች ተሳትፎ፣ ትኩረት የሚያደርግ ይሆናል፡፡ እንዲሁም ከሚያከናውኗቸው ተግባራት አንፃር በኅብረት ሥራ ግብይት፣ እሴት መጨመር፣ በኅብረት ሥራ ፋይናንስ (ባንክ ገንዘብ ቁጠባና ብድር፣

በኢንሹራንስ) እና በኦዲት ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በኅብረት ሥራ ማህበራት፣ በመንግስት እና በኅብረት ሥራ ማህበራት እና በኅብረት ሥራ ማህበራት እና ባለድርሻ አካላት መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ላይ እንዲያተኩር ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ፣ በምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፣ በገጠር ልማት፣ በአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በድህነት ቅነሳ ላይ ያላቸው ሚና በመለየት ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡

## አምድ 9፡- በኅብረት ሥራ አቅም ግንባታ የኅብረት ሥራ ማህበራት እና የሌሎች አካላት ሚና፡-

### ሀ. ነባራዊ ሁኔታ

**በአቅም ግንባታ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሚና**፡-

የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች፣ ፌዴሬሽኖች እና አንዳንድ የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በተወሰነ ደረጃ ለአባሎቻቸው የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም በአብዛኛው የሚሰጡት ስልጠናዎች ክፍተትን መሰረት ያደረጉ አይደለም፡፡ እንዲሁም የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን፣ የአመራር አካላትና የቅጥር ሰራተኞችን አቅም ለመገንባት ትኩረት ተሰጥቶ በተደራጀ አኳኋን ከመስራት አንፃር በየደረጃው ክፍተት ይታያል፡፡

**በአቅም ግንባታ የመንግሥት ሚና**፡-

መንግስት የኅብረት ሥራ ማህበራትን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ለማሳደግና የአደረጃጀት አሰራር ክፍተቶችን ለማሻሻል በርካታ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች አካላትን በማቀናጀት ለኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ የአቅም ግንባታ ድጋፎችን እንዲያደርጉ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ ሌሎችን በማስባበር የኅብረት ሥራ ማህበራት የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገራት የተለያዩ ተሞክሮዎችን እንዲያገኙ አድርጓል፡፡ በዚህም የሚጠበቀውን ያህል ባይሆንም በርካታ ለውጦች መጥተዋል፡፡

**በአቅም ግንባታ የአቅም ገንቢዎች ሚና፡-**

በሀገራችን አቅም ገንቢዎች የኅብረት ሥራ ማህበራትን አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ በርካታ የአቅም ግንባታ ድጋፎችን በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ አቅም ገንቢዎች የኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ፣ የሚሰጧቸው አገልግሎቶች እንዲስፋፉ እና የመፈጸምና የማስፈጸም አቅማቸው እንዲጠናከር የተለያዩ የአቅም ግንባታ ተግባራትን አከናውነዋል፡፡

በአቅም ገንቢዎች የሚደረጉ የአቅም ግንባታ ስራዎች በአብዛኛው በጥናት ላይ ያልተመሰረቱ፣ድግግሞሽ የሚበዛባቸው፣ውጤት መሰረት የማያደርግ፣ እርስ በርስ የማይናበብ እና ችግር ፈቺ አለመሆን ጉድለት ይታይበታል፡፡



DRAFT

በሀገራችን የኅብረት ሥራ ባለድርሻ አካላት የኅብረት ሥራ ማህበራትን አቅም ለማጠናከር አልፎ አልፎ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ በግብርና ምርት ግብይት ላይ ለተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት በሀገር ውስጥና በውጭ ግብይት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ ስልጠናዎችን ይሰጣሉ፡፡ በተለይም የኅብረት ሥራ ትምህርት የሚሰጡ ዩኒቨርሲቲዎች ለኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በፋይናንስ ዘርፍ ያሉ ባለድርሻ አካላትም የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የቁጠባ ባህል እንዲያሳድጉ አልፎ አልፎ ስልጠናዎች የሚሰጡበት አግባብ ይታያል፡፡ ሆኖም በባለድርሻ አካላት የሚሰጡ  የአቅም ግንባታ ተግባራት ስፋት የሌላቸውና ችግር ፈቺ አለመሆን ችግር ይታያል

**ለ. በአቅም ግንባታ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሚና ላይ ያሉ ማነቆዎች፤**

**ማነቆ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአቅም ግንባታ ትኩረት ሰጥቶ በአሰራር፣ በባለቤትነት እና በቅንጅት አለመስራት**

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሚሰጡት ስልጠና ትኩረት ስለማይሰጡ በእቅድ አይይዙም፡፡ የሚሰጡ ስልጠናዎች ያሉባቸውን መሰረታዊ የአቅም ክፍተቶችን የለየ እና በስልጠና መመሪያ የተደገፈ አይደለም፡፡ እርስ በርስ የማይናበብ፣ ችግር ፈቺ ያልሆነ ተደጋጋሚ ስልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡ ተግባራትን በመከፋፈል ማን ምን እንደሚሰራ በግልፅ ተለይቶ አለመሰጠት ችግሮች ይታያሉ፡፡ በአቅም ግንባታ ላይ የሚሳተፉ ሁሉም አካላት ተግባርና ሃለፊነት፣ መብትና ግዴታ በግልፅ አለመታወቅና በአፈፃፀም ላይ የመናበብ ችግር ይታያል፡፡

**ማነቆ 2፡- በመንግስት ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡ ስልጠናዎች አሰራር የተዘጋላቸው፣ ችግር ፈቺ እና ተደራሽ አለመሆን፣**

ለኅብረት ሥራ ባለሙያዎች፣ ለኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት፣ ለአመራር አካላት፣ ለቅጥር ሰራተኞች የሚሰጡ ስልጠናዎች በጥናት ላይ ተመስርቶ ክፈተቶችን በመለየት የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት አይደለም፡፡ የሚሰጡ ስልጠናዎችም ቀጣይነትና ተከታታይ የሌላቸውና ችግር ፈቺ አለመሆን ችግር ይታያል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ በቂ ዝግጅት ተደርጎበት አይሰጥም፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የስልጠና አሰጣጥ የሚመራበት ግልፅ  የስልጠና የአሰራር ስርዓት የለም፡፡ የኅብረት ሥራ የስልጠና ስትራቴጂና መመሪያ አለመኖር መሰረታዊ ችግሮች ናቸው፡፡ ራሱን የቻለ የኅብረት ሥራ የስልጠና ማዕከል አለመደራጀት ችግሮች ይታያሉ፡፡

**ማነቆ 3፡- ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚመሩባቸው የአቅም ግንባታ አሰራር ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ አለመዘርጋት፤**



DRAFT

ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚመሩበት ግልፅ የሆነ የስልጠና አሰራር የለም፡፡ ከዚህም የተነሳ የሚሰጡ ስልጠናዎች ምን ውጤት ለማምጣት እንደሆነ በግልፅ አለመቀመጥ እና የራሳቸው ስልጠና ስተሰራቴጂና የስልጠና መመሪያ ያለመኖር መሰረታዊ ችግሮች ናቸው፡፡

**ማነቆ 4፡- በአቅም ገንቢዎች ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡ ስልጠናዎች ቀጣይነት የሌላቸው፣ ራስን የማያስችሉ መሆን፤**

በአቅም ገንቢዎች የሚሰጡ ስልጠናዎች በአብዛኛው ችግሮችን በጥናት የለዩ አይደለም፤ ስልጠናዎቹም ቀጣነት የሌላቸው በመሆኑ ችግር ፈቺ አይደሉም፤ የኅብረት ሥራ ማህበራት ራሳቸውን እንዲችሉ ከማድረግ ይልቅ በተወሰኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ የጥገኝነት ስሜት ፈጥሯል፡፡

**ማነቆ 5 ፡- በባለድርሻ አካላት የሚደረጉ የአቅም ግንባታ ስራዎች የተቀናጀና ችግር ፈቺ አለመሆን**

ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ አለመስራት፣ የሚሰጡ ስልጠናዎች ተደጋጋሚ የመሆን ችግሮች ይታያሉ፡፡ በተጨማሪ የሚሰጡ ስልጠናዎች ቀጣይነትና ተደራሽ አለመሆን ችግር ይስተዋላል፡፡

**ሐ. ማነቆዎችን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች**

| |
|---|
| ***ከአጠቃላይ የአገሪቱ ከሚሰበሰበው የቁጠባ መጠን ውስጥ በፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ 40 በመቶ ይሆናል፡፡ የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባለት የሚየቀርቡት የብድር አገልግሎት ድርሻ 90 በመቶ ይሆናል፡፡*** |

**መፍትሄ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአቅም ግንባታ ትኩረት ሰጥቶ በአሰራር፣ በባለቤትነት እና በቅንጅት አለመስራት**

**የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአቅም ግንባታ ትኩረት መስጠት፣**

ኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ከተገኘው ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ ላይ ለአቅም ግንባታ የሚውል በጀት እንዲመድቡ ይደረጋል፡፡ ይህ በጀት በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የሚደነገግ ሆኖ በእቅድ የተያዘና በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ ይሆናል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በየአመቱ ከተጣራ ትርፍ ላይ ለስልጠና ከመመደብ በተጨማሪ ለስልጠና የሚሆን ፈንድ ከሌሎች አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት (መሰረታዊ፣ ዩኒዬኖችና ፌዴሬሽን) የአባላትን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የአቅም ክፍተታቸውን በመለየት የአባላት የፋይናንስና የአሰራር አቅም በመገንባት ተጠቃሚነታቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ እንዲሁም አንዱ ለሌላኛው ምርጥ ተሞክሮ በማካፈል ተከታታይነት በለው ሁኔታ የራሳቸውን አቅም እንዲገነቡ ይደረጋል፡፡

DRAFT

የሚሰጠው አቅም ግንባታ በይበልጥ የሚያተኩረው በሰው ሃብት ልማት፣ በመሰረተ ልማት ዝርጋታ፣ የቅድመ አዲት ዝግጅትና የህግ አገልግሎት፣ ባለሙያ መቅጠር፣ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣ የግብይት ዘርፋቸውን ማስፋፋት፣ በቢዝነስ ፕላን ዝግጅት እና በበጀት ዝግጅት፣ በቁሳቁሶች ድጋፍ፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በአየር ለውጥ መቋቋም፣ የፋይናንስ አቅማቸውን ማጠናከር፣ በተለይ በአረንጓዴ ልማት እና በተፈጥሮ ምርቶች ማምረት የአባላት ተሳትፎና ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ እና ሌሎች ላይ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በተሰማራበት የስራ መስክ ስለቆመለት ዓላማና ራዕይ ለአባላትና ለአመራሩ የአቅም ግንባታ አቅጣጫዎችን በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ጥልቅ የግንዛቤ ማሳደጊያ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት ይኖርበታል፡፡ በዚህም መሰረት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በሂሳብ አያያዝና ቁጠባ ላይ ያተኮረ ስልጠና ሲሰጥ በሌላ መልኩ የግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት ደግሞ በገበያና በግብይት ስርዓት ቅድሚያይሰጣል፡፡

## የኅብረት ሥራ ማህበራት በአቅም ግንባታ ስራ ላይ ተቀናጅቶ መስራት

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚያግዙ አቅም ገንቢዎች መሰረታዊ የሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ችግሮች በጥናት በመለየትና ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም ግን የሚደረጉት ድጋፎች ከችግራቸው የመውጫ አቅጣጫ ከመጠቆም እና ከማገዝ በዘለለ በተግባሮቻቸው ውስጥ በቀጥታ ጣልቃ በመግባት የተረጅነት ስሜት እንዲጠናወታቸው ማድረግ የለባቸውም፡፡ የአቅም ግንባታ ተግባርን ለማጠናከር የኅብረት ሥራ ማህበራት ከኅብረት ሥራ ባለሙያዎች፣ ከመንግስት አካልት፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ተቀናጅተው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

## ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የሚሰጡትን አቅም ግንባታ አሰራር መዘርጋት

የኅብረት ሥራ ማህበራት ያለባቸውን የአቅም ክፍተት በመለየት የውስጥ አቅማቸውን አሟጦ በመጠቀም እና አባላት በገንዘብና ማቴሪያል የሚሳተፉበት አሰራር መዘርጋት አቅማቸውን ለማጎልበት እንዲሰሩ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በራሳቸው የሚሳተፉባቸው የአቅም ግንባታ መስኮች በዋናነት የውስጥ መሠረተ ልማት ግንባታ፣ በማማከር ስራ፣ የልማት ፕሮግራሞችን በማቀናጀት፣ ለቦርድ አባላት እና ለአባላት ሥልጠና፣ትምህርት በመስጠት ላይ መሳተፍ አለባቸው፡፡

## መፍትሄ 2፡- በመንግስት አማካኝነት የሚሰጡ ስልጠናዎች ችግር ፈቺ እና ተደራሽ ማድረግ፣

## በአቅም ግንባታ የመንግሥት ሚና፡-

መንግስት የኅብረት ስራ ሴክተር የትምህርትና ስልጠና፣ የጥናትና ምርምር ተግባራትን የሚደግፍ ራሱን የቻለ የኅብረት ሥራ የልህቀት ማዕከል እንዲቋቋም አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡ የሚደረገው የቴክንክ፣ የፋይናንስ እና የማቴሪያል ድጋፍ በኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ የተረጅነት ወይም የጥገኝነት መንፈስ በማይፈጥር ሁኔታ ራስን በራስ የመርዳትና የመምራት እሴትና መርሆን ባከበረ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

በተጨማሪም መንግስት በአገር ውስጥና በውጭ ሀገር ያሉ የተሻሉ ተሞክሮ ያላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር የኅብረት ሥራ ፈጻሚውና አስፈጻሚ አካላት ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ማስፋት ተግባር በትኩረት ይሰራል፡፡

## የኅብረት ሥራ ማህበራት የአቅም ግንባታ አሰራር ስርዓት መዘርጋት፡-

መንግስት የኅብረት ሥራ ማህበራትን አቅም ለመገንባት የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ፣ በቂ የትምህርትና ስልጠና በጀት በመመደብ፣ ምቹ የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት የአቅም ግንባታ ተግባርን ይደግፋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የስራ አፈጻጸም በየጊዜው በመገምገም የሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲጠናከሩ ለማድረግ ጠንካራ ባለሙያዎችን በመቅጠር ድጋፍ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

በየደረጃው የሚገኙ የመንግሥት አመራር አካለት የኅብረት ሥራ ማህበራት የትራንስፎርሜሽን ማሳኪያ ዋነኛ መሳሪያ መሆናቸውን በመረዳት የኅብረት ሥራ ማህበራትን በተሻለ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ጠንካራ የአቅም ግንባታ የአሰራር ስርዓት እንዲዘረጋ ትኩረት ሰጥቶ ይደግፋል፡፡ እንዲሁም ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ፕሮጀክቶች በኅብረት ሥራ ማህበራት በኩል ለህብረተሰቡ እንዲደርሱ አቅጣጫ አስቀምጦ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

## መፍትሄ 3 ፡- በአቅም ገንቢዎች ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡ ስልጠናዎች ቀጣይነት ያላቸውና ኅብረት ሥራ ማህበራት ራስን የሚያስችሉ እንዲሆኑ ማድረግ፣

## በአቅም ግንባታ የአቅም ገንቢዎች ሚና፡-

አቅም ገንቢዎች ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት የሚያግዙ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የፋይናንስና የሎጂስቲክስ ድጋፍ እንዲያደርጉ በትኩረት ይሰራል፡፡ ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደረግ ማንኛውም የአቅም ግንባታ ድጋፍ የተረጅነት ስሜት እንዳይፈጥር ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ የሚደረገው ድጋፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት ችግሮቻቸውን በራሳቸው እንዲወጡ የሚያስችል ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር አዳዲስ ተሞክሮዎችን የማሰባሰብና በኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ተግባራዊ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡



DRAFT

አቅም ገንቢዎች ለኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት፣ ለስራ አመራር አካላት እና ለቅጥር ሰራተኞች የሚሰጧቸው ስልጠናዎች ክህሎታቸውን ለማሳደግና ግንዛቤ ለመፍጠር እንዲቻል በጥናት የተለዮ ችግሮችን መፍታት ላይ የሚያተኩሩ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የትምህርትና ስልጠና አቅም ግንባታ ድጋፍ እንደተጠበቀ ሆኖ በመሰረተ ልማት ግንባታ፣ በቴክኖሎጂ አቅርቦትና ሽግግር፣ አሰራራቸውን በማዘመን፣ ምርጥ ተሞክሮን በማስፋፋት፣ በተማረ የሰው ሃይል እንዲመሩ ማንኛውንም ድጋፍ በማድረግ ላይ ትኩረት በመስጠት የሚደግፉ ይሆናል፡፡

### መፍትሄ 4 :- በባለድርሻ አካላት የሚደረጉ የአቅም ግንባታ ስራዎች የተቀናጀና ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ማድረግ

#### በአቅም ግንባታ የባለድርሻ አካላት ሚና

በኅብረት ሥራ ማህበራትን አቅም ግንባታ ላይ የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኑት የአቅም ግንባታ ተግባር ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በጋራ ተወያይቶ እና አቅዶ በጥናት በተለዩ ችግሮችና ውጤት በሚያመጡ ተግባራት ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ እንዲሁም የሚደረገው የአቅም ግንባታ ድጋፍ የተቀናጀና የጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ፣ ቀጣይነት ያለው እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የተገኙ ውጤቶችን ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ጋር በጋራ የሚገመገም ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ግብይት ስርዓትን ማጠናከር

በአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት ምርትና ምርታማነት በማሻሻል ለአባላት ምርት የተሻለ የገበያ ዋጋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረጋቸውም በላይ ፍትሃዊ የገበያ ስርዓት እንዲገነባ የባኩላቸውን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡ የግብርና ምርትና ምርታማነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ቢሆንም አርሶ/አርብቶ አደሩን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ ሁኔታ ዘመናዊ የግብርና ምርቶች ስርዓት ባለመዘርጋቱ አምራቹ ላመረተው ምርት ተመጣጣኝ የገበያ ዋጋ እያገኛ አይደለም፡፡

አርሶ/አርብቶ አደሩ ምርቱ እንዲጨምር የተለያዩ የግብርና ቴክኖሎጅዎችን በመግዛት የሚጠቀም በመሆኑ የማምረቻ ዋጋ ይጨምራል፡፡ ለግብርና ሥራው መሠረት የሆነው ሰፊው አርሶ/አርብቶ አደር ላመረተው ምርት ተመጣጣኝ የገበያ ዋጋ የማያገኝ ከሆነ በኑሮው ላይ ጫና ከማሳደሩም በላይ የማምረት ፊላጎቱ ይቀንሳል፡፡ ከዚህም የተነሳ አገሪቱ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የነደፈችሁ ስትራቴጅ እና አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ልያስከትል ይችላል፡፡

ከግብይት ስርዓቱ አምራቹ እና ሻማቹ በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ ያልሆነበት ምክንያት የግብይት ተዋንኖች መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ባለመኖሩ እና በግብርና ምርቶች የግብት እሴት ሰንሰለት ውስጥ እሴት የማይጨምሩ አካላት በመግባት የግብይት እሴት ሰንሰለቱን በማንዛዛት አምራቹ እና ሸማቹ በቀጥታ እንዳይገናኙ በማድረግ በአቋራጭ ተጠቃሚ ሲሆኑ ይታያል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል አሰራር በሚፈለገው ደረጃ አልተዘርጋም፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ተጠናክሮ የአከባቢ፣ ማዕከላዊ እና የውጭ ገበያን በመጠቀም በአባላት ምርት ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ ማቅረብ እንዲሁም የፍጆታ ምርቶችን ምርት ከተመረተበት ቦታ ጥራቱን የጠበቀ ምርት በተመጣጣ ዋጋ በመግዛት ለተጠቃሚው የሚያደርሱበትን የአሰራር አቅጣጫ መከተል ያስፈልጋል፡፡ የአከባቢ ገበያ ለግብርና ምርቶች ግብይት ቅርብ በመሆኑ፤ በተለይም የተመረተውን የግብርና ምርት ከተመረተበት ማሣ ሳይበላሽ ለተጠቃሚው በቀጥታ ማድረስ ስለሚቻል እና ከሌሎች የገበያ አማራጮች አኳያ ሲታይ የትራንስፖርት ወጭው ተመጣጣኝ እና ተመራጭ በመሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ትኩረት ሰጥቶ እንዲጠቀሙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የአገራችን ማዕከላዊ ገበያ በባህሪው ብዙ ሻማቾች የሚገኙበት እና የተለያዩ ዓይነት ምርቶች የሚፈለግበት ስለሆነ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ተመራጭ የግብይት ቦታ ነው፡፡ ማዕከላዊ ገበያ በገጠር የሚገኘውን የአምራቹ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከከተማ ሸማች የኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የግብይት ትስስር በመፍጠር ጥራቱን የጠበቀ ምርት፣ በወቅቱና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ አምራቹንና ሸማቹን በቀጥታ ተጠቃሚ የሚያደርግ የግብይት ማዕከል ነው፡፡ የኢንዱስትሪ ምርት አቀነባባሪዎችን ከአምራቾች ጋር በቀጥታ በመገናኘት ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ የሚሆነውን ምርት እንዲለዋወጡ በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን በተሸለ ሁኔታ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ የሚመረተው ምርት አብዛኛው ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል በመሆኑ የገበያ ተኮር እና ሽጦ የማምረት አቅጣጫን በመከተል ምርቶቹን በስፋት ወደ ውጭ ገበያ በመላክ ከገበያው የተሸለ ዋጋ ተጠቃሚ በመሆኑና አርሶ/አርብቶ አደሩ የማምረት ሂደቱን እንዲያጠናክር ያግዛል፡፡

## ዓምድ 10፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብዓት ግብይትን ማጠናከር፣

### *ሀ. ነባራዊ ሁኔታ*

አርሶ/አርብቶ አደር የሕብረተሰብ ክፍል የግብርና ምርት እና ምርታመነትን ለማሳደግ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን መጠቀም የግድ ይላል፡፡ ሌሎች ከግብርና ውጭ ባሉት ተግባራት ላይ የተሰማሩ የሕብረተሰብ ክፍሎችም ቢሆኑ በተሰማሩባቸው የሥራ መስኮች ውጤታማ ለመሆን የሚያስፈልጉ የተለያዩ ግብዓቶችን መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ አባላት ለሥራቸው የሚያስፈልጓቸው ግብዓቶች በወቅቱ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ እና በሚፋልጉት መጠንና ቦታ በተናጠል ማግኘት አስቸጋር ነው፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ኅብረት ሥራ ማህበራት በአባላት የሚፈለጉ ግብዓቶችን በመለየት፣ በሚፈለገው መጠን፣ ጊዜ እና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ አባላትን ተጠቀሚ በማድረግ በኩል በዓለም ላይ ተከ የለሽ ተቋማት ሆኗል፡፡

በአገራችን የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት በገጠር የአባላት ፍላጎትን መሠረት በማድረግ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን ከመንግስት ጋር በመቀናጀት ለሕብረተሰቡ በማድረስ በኩል ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የፌደራል ኅብረት

ሥራ ኤጀንሲ መረጃ እንደሚያሳየው በአገርቱ በየዓመቱ በአማካይ ከሚሰራጩ የአፈር መዳበሪያ ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ 98 ከመቶ ደርሷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አባላት የሚፈልጓቸው ምርጥ ዘሮች በአማካይ 644,062 ኩ/ል፣ የተለያዩ ዓይነት ኬሚካሎች 766,416 ሊ/ር፣ የእርሻ ማሣሪያዎች እና ሌሎች ተፈላጊ ግብዓቶችን በጥራት፣ በወቅቱ እና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ አባላትን ተጠቃሚ ከማድረግ አልፎ በአገራችን በተከታታይነት ለተመዘገበው የኢኮኖሚ ድረገት ከፍተኛ ድርሻቸውን በመወጣት ላይ ይገኛሉ፡፡

## ለ. የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብዓት ግብይት ላይ ያሉ ማነቆዎች፤

### ማነቆ 1፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሚፈልጓቸውን ግብዓቶች በማቀድ በሚፈለገው መጠን፣ ጥራት፣ እና ጊዜ ማቅረብ አለመቻል፤

የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት እና ሕብረተሰቡ የተሰማሩባቸው የሥራ መስኮችን ሊመጥን የሚችል የተለያዩ ዓይነት ግብዓቶችን በተለይም የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን በራሳቸው አቅዶ በሚፈለገው ደረጃ መስራት አለመቻል፡፡ ከሌሎች አካላት ጋር በዕቅድ ላይ ተቀናጅተው ማስራት አለመቻል፡፡ ከዕቅድ ውጭ የሚቀርቡ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች በመጋዘን እያደሩ ለተለያዩ ብልሽት በመዳረግ የኅብረት ሥራ ማህበራት እያከሰሩ መሆናቸው፡፡ የግብዓት አቅርቦት እና ስርጭት በአግባቡ እየተመራ ባለመሆኑ ለኪራይ ሰብሳቢነት ድርጊት እና አመለካከት የተጋለጠ መሆኑ፤ የሚቀርቡ ግብዓቶች መጠናቸው እና ጥራታቸው የሚፈለገው ያህል አለመሆን ችግሮች ይታያሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሚፈልጓቸው ግብዓቶችን በወቅቱ ማድረስ ባለመቻሉ አባላትን በሚፈለገው ደረጃ ማርካት አልተቻለም፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚቀርቡ አንደንድ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች የመለዋወጫ እጥረት ችግር የሚታይ ማሆኑ እና በቂ ባለሙያ ባለመኖሩ ምክንያት በትናንሽ ብልሽት ቆሞ ከጥቅም ውጭ የሚሆኑበት ሁኔታ ይታያል፡፡ በግብዓት አቅርቦት እና ስርጭት ውስጥ ካሉ ተዋንያኖች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ፈጥሮ መስራት አለመቻል ችግሮችም ይስተዋላሉ፡፡ የጠራ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች አቅርቦትና ስርጭት መረጃ አለመኖር፡፡

## ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የምንከታላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤

### መፍትሔ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብዓት አቅርቦትና ስርጭትን ማጠናከር፡-

የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንዲያስችል የግብርና ምርት ማሳደጊያ ቴክኖሎጅዎችን፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎቶችን፣ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች አቅርቦትና ስርጭት ላይ ያላቸውን የማይተካ ሚናቸውን እንዲወጡ የተሸለ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች

በዋናነት በኅብረት ሥራ ማህበራት በኩል ቀርቦ እንዲሰራጭ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብአቶችን በሚቀመጠው አሰራር መሰረት በማድረግ ለአባላትና አባል ላልሆኑ አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በተለይም የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን የሚያቀርቡት እና የሚያሰራጩት ከተለያዩ አካላት ጋር በመቀናጀት ነው፡፡ አርሶ/አርብቶ አደር ማህበረሰብ የሚፈልገውን የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር የሚያቀርቡበት አሰራር ተዘርግቶ ይተገበራል፡፡ ከዕቅድ ውጭ የሚቀርቡ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች በመጋዘን እያደሩ በመበላሸት የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለኪሳራ በመዳረግ ላይ ይገኛል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያቀርቡት እና የሚያሰራጩትን ማንኛውንም ግብዓቶች የራሳቸው አቅደው እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያቀርቡት ምርጥ ዘር ከሚመለከታቸው የምርምር ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ በመስራት የዘር አቅርቦቱን በብዛትና በጥራት የሚያገኙበትን አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም የኅብረት ሥራ ማህበራት በራሳቸው አቅም ምርት ዘር አባዝቶ እንዲጠቀሙ እና አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ የግብዓት አቅርቦት እና ስርጭትን በአግባቡ በመምራት በኩል የአቅም ክፍተት ያለባቸው በመሆኑ ግብይቱ ለተለያዩ የኪራይ ሰብሳቢነት ድርጊት እና አመለካከት የተጋለጠ ነው፡፡ በመሆኑም የኅብረት ሥራ ማህበራት ለግብዓት ግብይት ጠንካራ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያቀርቧቸው ግብዓቶች ጥራታቸውን የጠበቁ፣ በወቅቱ እና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርቡ በማድረግ አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ የግብዓት ግብይቱ እንዲያሳልጥ ተጠናክሮ ይሰራል፡፡ በተለይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖች የአፈር ማዳበሪያ በራሳቸው አቅም በአገር ውስጥ ወይም በጆይንት ቨንቼር የማዳበሪያ ፋብሪካ አቋቁሞ በማምረት የአርሶ አደሩን ፍላጎት ከማሟላት በተጨማሪ በራሳቸው ከውጭ አገር በማስገባት አባላት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በትኩረት ይሠራል፡፡

በተጨማሪም የአፈር ማዳበሪያ የሚጠቀሙ አርሶ አደሮች የሚጠቀሙት ግብዓቶች ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች እና ፌዴሬሽኖች የአፈር መመርመሪያ መሳሪያዎችን በመገንባት እና በሙያው የሰለጠኑ ባለሙያዎችን በመቅጠር የአፈር ምርመራ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም የአፈር ለምነትን በማሻሻል ምርታመነትን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በማምረት እና በማቅረብ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

በግብዓት ግብይት ውስጥ የሚታየውን የፋይናንስ አያያዝ እና እጥረት ችግር ለመቅረፍ በግብዓት ግብይት ላይ የተሰማሩ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ተቀናጅተው የግብዓት የኩፖን አሰራርን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት እንደየተሰማሩባቸው የሥራ መስኮች ዓይነት

የሚያስፈልጉ የተለያዩ ግብዓቶች የሚቀርቡበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ለግብርና ግብዓት አቅርቦት ከፍተኛ ፋይናንስ የሚጠይቅ በመሆኑ ለፋይናንስ አቅርቦት መንግስት አስፈላጊውን አሰራር ዘርግቶ ይደግፋል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚቀርቡ አንደንድ የግብርና ምርት ማቀነባባሪያ ማሽነሪዎች፣ የድህረ ምርት ቴክኖሎጅዎች እና ሌሎች መሣሪያዎች ተገዝቶ ለአባላት ከተሰጡ በኋላ በመለዋወጫ እጥረት ምክንያት እና የሚጠግን ባለሙያ ባለመኖሩ ተበላሽቶ ለረጅም ጊዜ በመቆም የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለኪሣራ በመዳረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያሰራጩት መሣሪያ በቂ መለዋወጫ ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ እንዲገዙ ማድረግ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች፣ ፌዴሬሽኖች እና አቅም ያላቸው መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያስፈልጉ መለዋወጫዎችን በጥናት በመለያት በማቅረብ፣ በማሽን የጥገና ሙያ ያላቸው ባለሙያዎችን በመቅጠር እና በማሰልጠን የጥገና ወርክሾፖችን በመክፍት እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በራሳቸውና በአባላት የተለያዩ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች እና ቴክኖሎጅዎችን በማላመድ፣ በማባዛት እና በማሰራጨት ላይ በስፋት እንዲሳተፉ የሚያደርግ አሠራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የራሳቸው ፋብሪካ በማቋቋም አስፈላጊ የሆኑ የአፈር ማዳበሪያዎችን፣ የእንስሳት ማኖ እና ሌሎች ግብዓቶችን በሰፊው በማምረት ለተጠቃሚዎች እንዲያቀርቡ የተለያዩ ድጋፎች ይደረጋል፡፡

## ዓምድ 11፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሀገር ውስጥ ግብይትን ማጠናከር፣

### የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሀገር ውስጥ የግብርና ምርቶች ግብይትን በቀጣይነት ማሻሻል፡-

### ሀ. ነባራዊ ሁኔታ

የኅብረት ሥራ ማህበራት ውጤታማ ተግባራት ከሚያከናውኑባቸው የሥራ መስኮች አንዱ አባላት ያመረቱት የግብርና ምርቶች ገበያ በማፈላለግ በመሸጥ የአባላትን ተጠቃሚናት ማረጋጋጥ ነው፡፡ የግብርና ምርት ግብይት በባህሪው ጥንቃቄ የሚፈልግ የግብይት ዓይነት ነው፡፡ በአርሶ/አርብቶ አደር ደረጃ የሚመረቱ የግብርና ምርቶች የተለያዩ ቦታዎች ላይ ተበታትኖ መገኘቱ፣ የሚመረተው ምርት መጠን አነስተኛ መሆን፣ የምርቱ ባህሪ፣ የመሰረተ ልማት ችግሮች፣ የቦታ ሪቀት እና ሌሎች ምክንያቶች የግብርና ምርት ግብይቱ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በተበታተነ ቦታ ላይ የሚመረተውን የግብርና ምርቶችን አንድ ላይ በማሰባሰብ፣ በማከማቸት፣ የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት፣ የምርት ጥራትን በማስጠበቅ፣ እሴት በመጨመር ለአከባቢ እና

ማዕከላዊ ገበያዎች በማቅረብ አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ የግብርና ምርት እና ምርታመነት እንዲያድግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡

ለአብነት በግብርና ምርት ግብይት ጥሩ ተሞክሮ ካላቸው አገሮች መካካል ***ኬንያ*** ከአጠቃላይ ወተት ግብይት ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ 95 በመቶ፣ የቡና ግብይት 70 በመቶ እና የጥጥ ምርት ግብይት 95 በመቶው ደርሷል፡፡ ***በጃፓን*** 91 በመቶ የሚሆኑ የጃፓን ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ሲሆኑ በዓመት በአማካይ 96 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ዋጋ የሚያወጡ የግብርና ምርቶችን ሰብስበው በከተሞች ውስጥ በተሰጣቸው የገበያ ማዕከላት ምርታቸውን ለከተማ ሸማች ያቀርባሉ፡፡ ***በኒውዝላንድ*** ከአገሪቱ አጠቃላይ (GDP) ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ 22 በመቶ ሆኖ በግብርና ምርት ግብይት ውስጥ የወተትና ወተት ተዋጽኦ ምርት 95 በመቶ እና የሥጋ ምርት ግብይት ውስጥ 50 በመቶ ድርሻ አላቸው፡፡ **በፊንላንድ** የኅብረት ሥራ ማህበራት በወተት 96 በመቶ እና በስጋ ግብይት 82 በመቶ የግብይት ድርሻ አላቸው፡፡

በአገራችን ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት በግብርና ምርት ግብይቱ ውስጥ ያላቸው ድርሻ በአግባቡ ተጠንቶ የተቀመጠ ባይኖርም በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወደህ በግብርና ምርቶች ግብይት የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለገበያ የሚያቀርቡት ምርቶች በመጠንም በዓይነትም በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከግብርና ምርቶች ውጭ ያሉ ምርቶች ግብይትን በማከናወን አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ በኩል ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የተለያዩ የማዕድን፣ የደን ውጤቶች እና ሌሎች ተያያዥ ምርቶች የሚመረቱት በተበታተነ ሁኔታ በመሆኑ በቀላሉ በማሰባሰብ ለገበያ ማቅረብ አስቸጋር ነው፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተበታትኖ የሚመረተውን ምርት በማሰባሰብ እና እሴት በመጨመር ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ በማቅረብ አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ ለአገር ኢኮኖሚ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ተቋማት ናቸው፡፡ በዚህም በአነስተኛ ማዕድን ግንባታ አማካይነት ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ለብሔራዊ ባንክ በማቅረብ ሕገ ወጥ የማዕድን ምርት ግብይትን በመቀነስ ሚናቸውን ትልቅ የነበረ ከመሆኑም በተጨማሪ ለውጭ ገበያ የሚቀርበው የወርቅ ማዕድን ምርት በአብዛኛው በእነዚህ ኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት ነው፡፡

በተለያዩ አገሮች ውስጥ በዚህ ተግባር ውጤታማ የሆኑ በርካታ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደምገኙ የተለያዩ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በአገራችንም ቢሆን በተለይም በወርቅ ማምረት እና ግብይት፣ በደንና ሙጫ ውጤቶች ግብይት እና ሌሎች ተያያዥ ግብይቶች ላይ የተሰማሩ በርካታ ውጤታማ የኅብረት ሥራ ማህበራት ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ኅብረት ሥራ ማህበራት የተመረቱ ምርችን በማሰባሰብ፣ በማምረት፣ በምርት ላይ እሴት በመጨመር ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ በማቅረብ አባላትን ከገበያ ዋጋ የተሸለ ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በተለይም በማዕድን እና በደን ውጤቶች

DRAFT

ግብይት ውስጥ የሚታዩ የአሰራር መዝረክረኮችን በማስተካከል አገሪቷ ከዘርፍ ማግኘት ያለባትን የውጭ ምንዛሪ እንዲታገኝ በማድረግ በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት በየዕለቱ የሚያስፈልጋቸውን የፍጆታ ምርቶች በተናጠል ገዝቶ ለመጠቀም አመቺ አይደለም፡፡ የፍጃታ ምርቶች የዋጋ መወደድ፣ በቅርበት ያለማግኘት እና የጥራት ችግር የሚታይባቸው በመሆኑ አባላት በቀላሉ ለመሸመት አይችሉም፡፡ በዓለም ላይ ያሉ ተሞክሮዎች እንደምያሳዩት የኅብረት ሥራ ማህበራት ይህንን ችግር በመቅረፍ በኩል ሚናቸው የጎላ መሆኑን ነው፡፡ ለአብነት በተለያዩ አገሮች ውስጥ ያሉ ተሞክሮዎችን ስንመለከት በዓመት በአጠቃላይ ከሚቀርቡ የፍጆታ ምርቶች ውስጥ አማካይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ በዴንማርክ 36.4 በመቶ፣ በጃፓን አጠቃላይ የምግብ ገበያ ድርሻ ውስጥ 5.9 በመቶ እና በፊንላንድ 44 በመቶ እንደሚደርስ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በአገራችን በከተሞች አከባቢ ተደራጅቶ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን እና የሕብረተሰቡን የፍጆታ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በቅርበት በማቅረብ በርካታ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በገጠር የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራትም ቢሆኑ ለአባላት የሚያስፈልጉ የፍጆታ ምርቶችን በማቅረብ አገልግሎት በማስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በራሳቸው ከሚያቀርቧቸው በተጨማሪ በመንግስት የሚቀርቡ የፋጆታ ምርቶችን በመረከብ እና ለሕብረተሰቡ በማሰራጨት በርካታ ተግባራትን በማከናወን በመንግስት የተሰጣቸውን ኃላፊነት በመወጣት ላይ ይገኛሉ፡፡ የፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚያሳየው የኅብረት ሥራ ማህበራት በአማካይ የዓመቱ **6 ቢሊየን** ብር በላይ የሚያወጡ የፍጆታ ምርቶችን በማቅረብ ለአባላት እና ለሕብረተሰቡ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

## ሰንጠረዥ 7፡ አጋር የሸማቾች መሠረታዊ እና ምዕራብ የሸማቾች የኅብረት ሥራ ዩኒየን በሞደልነት የተወሰደ (bench mark)

1. **አጋር የሸማቾች የኅብረት ስራ ማህበር**

**የአባላትና ካፒታል እድገት፡-** በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ውስጥ የሚገኝ ስሆን በአሁኑ ጊዜ የአባላቱን ቁጥር በድምሩ 5,297 (77.57 ሴቶች) አባላት እና ካፒታሉን ብር 7.5 ሚሊዮን በላይ መድረስ ችለዋል፡፡ **የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት፡-** የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በአማካይ ከብር **50,000,000** ካፒታል በላይ በየዓመቱ በማንቀሳቀስ የድንግ፣ የኢንዱስትሪና የግብርና ምርቶችን ለአባላቱና ለአካባቢው ህብረተሰብ በሰፊው ማቅረብ ላይ ይገኛል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን ከገጠር አምራች ኅብረት ሥራ ማህበራት እና የኢንዱስትሪ ምርት ውጤቶችን ከአምራቾች ጋር ቀጥታ የግብይት ትስስር በማፍጠርና በማቅረብ አባላት እና የአካባቢው ማህበረሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

**የአባላትን ፍላጎት መሰረት አገልግሎትን በማስፋት መስራት፡-** የዳቦ መጋገሪያ ማሽን በመግዛትና በመትከል ለአባላቱና አካባቢው ህብረተሰቡ እስከ 4,400 ዳቦ በቀን በማቅረብ ላይ ይገኛል፡፡ ኅብረት ስራ ማህበሩ 60 ወላጅ አጥ ሕጻናትን በየአመቱ ብር 108,000 ወጭ በማድረግ የትምህረት ክፍያ እና የቁሳቁስ ድጋፍ እገዛ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪ ለአረጋውያን፣ ለአካባቢው የኮብል ስቶን ንጣፍ ፣አነስተኛ ድልድይ ግንባታ በመሳተፍ በመሳተፍ ማህበራዊ ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡

**ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፡-** በኅብረት ሥራ ማህበሩ የ2009 ዓ.ም መረጃ መሠረት 103 ቋሚ ሠራተኞች እና ለ15 ጊዜዊ ሰራተኞች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡

2. **ምዕራብ የሸማቾች ኃላ/የተ. የኅብረት ሥራ ዩኒየን ተሞክሮ፡**

**የአባላትና ካፒታል እድገት፡-** በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኝ ስሆን እስከ 2009 ዓ.ም መረጃ መሠረት የአባል መሠረታዊ ሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር 19፣ የተናጠል አባላትን ቁጥር 35 ሺህ በላይ በማድረስ እና ከፒታሉን 4.6 ሚሊዮን ብር በማሳደግ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

**በአባላትን ፍላጎት መሰረት አገልግሎት መስጠት፡-** በአሁኑ ወቅት ከ25 በላይ የሚሆኑ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርት ውጤቶች፡- ጤፍ፣ ሽንብራ ምስር፣ በቆሎ፣ ስንዴ፣ ሽንኩርት፣ ሻይቅጠል እና ሌሎች በጅምላ ለአባላቱ ተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ላይ ይገኛል፡፡

**የገበያ ሰንሰለቱን በማሳጠር ከገበያ ትስስሩ ተጠቃሚ ማድረግ፡-** በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች ከሚገኙ ኅብረት ሥራ ዩኒየኖች ጋር የገቢያ ትስስር በመፍጠር የገበያ ሰንሰለቱን በማሳጠር ለ**አብነት** በ2007 ዓ.ም በተለያዩ ግለሰብ ወፍጮ ቤቶች 1,750 ብር እና ከዚያ በላይ የሚሸጥ ጤፍ በ**1,420** ብር በማቅረብ 330 ብር የዋጋ ልዩነት ለአባላቱ በማቅረብ ተጠቃም አድርጓል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ በወቅቱ 12 ብር ኪሎ ይሸጥ የነበረ ሽንኩርት በዩኒዬናችን እና በአባላቱ ከ5 እስከ **7** ብር በኪሎ ማቅረብ ከብር 5 እስከ 7 ቅናሽ በማቅረብ አባሉን ተጠቃሚ ማድረግ ተችለዋል፡፡

**ለ. የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሀገር ውስጥ ግብይት ላይ ያሉ ማነቆዎች፤**

**ማነቆ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የሀገር ውስጥ የግብርና ምርት ግብይት የመጠን፣ የጥራት፣ ወቅታዊነት እና የአሰራር ችግር**

በግብርና ዘርፍ የተደራጁ ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር በርካታ ቢሆንም በግብርና ምርት ግብይት ላይ በሚፈለገው ሁኔታ እየተሳተፉ አይደለም፡፡ በግብይቱ ውስጥ የሚሳተፉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለገበያ የሚያቀርቡት ምርት ዓይነት እና መጠን አናሳ መሆኑ ሌላው ችግር ነው፡፡ ከአባላት የሚሰበሰቡ ምርቶች አባላት በምርት አያያዝ ላይ ያላቸው ክህሎት አናሳ መሆን እና የኅብረት ሥራ ማህበራት የምርት ጥራት ቁጥጥር ደካማ በመሆኑ ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶች የጥራት ችግር በስፋት ይታይባቸዋል፡፡

ምርቶችን በተለያዩ ምክንያቶች በወቅቱ ለገበያ ማቅረብ አለመቻል እና የሚመረቱ ምርቶች ወቅታዊ በመሆናቸው በግብይቱ ላይ አሉታዊ ተጽኢኖ በማድረስ ላይ ይገኛል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት ሥራን በሙያ ሊደግፍ የሚችል ባለሙያ አለመኖር፣ በግብይት ክህሎት አናሳ መሆን፣ የተደራጀ የገበያ መረጃ በአግባቡ ማግኘት አለመቻል እና በግብይቱ ውስጥ የኪራይ ሰብሳቢነት ድርጊት እና አመለካከት መኖር የሚጠቀሱ ዋና ዋና ማነቆ ናቸው፡፡

**ማነቆ 2፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የምርት ግብይት ተግባር የሚያሳልጥ መሰረተ ልማት አለመጠናከር፤**

ለግብርና ምርት ግብይት የመሰረተ ልማት አቅርቦት በሚፈለገው ደረጃ አለመኖር ዋናው ችግር ነው፡፡ ግብይቱን ለማሳለጥ የሚያስችል ጥራቱን የጠበቀ የምርትን በህሪ ያገናዘበ የማከማቻ እና የትራንስፖርት እጥረት፣ የምርት ጥራት መጠበቂያ መሳሪያዎች በሚፈለገው ደረጃ አለመደራጀት፣ የግብይት ማዕከላት አለመገንባት፣ የመረጃ ልውውጥ ሊያፋጥን የሚችል ቴክኖሎጅ አለመዘርጋት፣ በምርት ላይ እሴት ለመጨመር የሚያስችሉ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎች በሚፈለገው ደረጃ አለመስፋፋት እና ሌሎች ማነቆዎች ይታያል፡፡

**ማነቆ 3፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ከግብርና ምርቶች ውጭ ባሉት ምርቶች ግብይት ላይ ያላቸው ተሳትፎ አናሳ መሆን፤**

አገራችን በማዕድን፣ በደን እና ሙጫ ምርቶች እና በሌሎች ተያያዥ ምርቶች ላይ ያላት እምቅ ሃብት በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል የኅብረት ሥራ ማህበራት በግብይቱ ውስጥ በሚፈለገው ደረጃ እየተሳሰፉ አይደለም፡፡ ግብይቱን ሊያሳልጥ የሚችል አሰራር በሚፈለገው ደረጃ አልተዘረጋም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በግብይቱ ላይ ያላቸው ግንዛቤ አናሳ ነው፡፡

ከሚመለከታቸው አካላት ለዚህ ተግባር የተሰጠው ትኩረትና ድጋፍ አናሳ ነው፡፡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመስራት ውጤታማ ተግባራትን በመፈጸም በኩል ሰፊ ማነቆ ይታያል፡፡

**ማነቆ 4፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሚፈልጓቸውን የፍጆታ ምርቶችን በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት እና በጊዜ ማቅረብ አለመቻል**

የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የሚያስፈልጉ የፍጆታ ምርቶችን በዓይነት እና በብዛት ማቅረብ አለመቻል፡፡ የሚቀርቡ ምርቶች ወቅታዊ ባለመሆናቸው አባላት በሚፈለጉበት ጊዜ ማግኘት አለመቻል፡፡ የግብርና ምርቶችን ሸማቾች ከአምራች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ጠንካራ እና ቀጣይነት ያለው ትስስር በመፍጠር ማስራት አለመቻል፡፡ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ከአምራቾች ጋር የግብይት ትስስር በመፍጠር በፋብሪካ ዋጋ በመረከብ በተመጣጣኝ ዋጋ ለአባላት በማቅረብ በኩል ክፍተት የሚታይ መሆኑ፡፡ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡትን አገልግሎት ለአባላት የተለያ የአገልግሎት መስጫ አሰራር ዘርግቶ አለመተግበር፡፡

የሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁት የአባላት የፍጆታ ምርቶች ፋላጎት ለማሟላት ቢሆንም በአብዛኛው መንግስት የሚያቀርባቸው የድጎማ ምርቶችን ላይ ብቻ ትኩረት ከማድረግ ውጭ የሚያስፈልጉ ምርቶችን በስፋት ማቅረብ አለመቻል ችግር ይስተዋላል፡፡ መንግስት በሚያቀርባቸው የድጎማ ምርቶች ስርጭት ላይ የኪራይ ሰብሳቢነት ድርግት የሚታይ መሆኑ፡፡ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራዎቻቸውን በአግባቡ መምራት እንዲችሉ የሚያደርግ ጠንካራ የአሰራር ስርዓት አለመኖር፡፡ ከመንግስት የሚረከቡ የፍጆታ ምርቶችን ለማስተዳደር የሚያስችል ጠንካራ አሰራር ስርዓት አለመዘርጋት ችግሮች ይታያሉ፡፡

**ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤**

| |
|---|
| ***የኅብረት ሥራ ማህበራት የአገር ውስጥ የግብርና ምርቶች ግብይት ድርሻ 70 በመቶ ይሆናል፡፡ በአገርቱ ዋና ዋና ከተሞች 60 ትላልቅ የገበያ ማዕከላት ተገንብቶ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡*** |

**መፍትሔ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የሀገር ውስጥ የግብርና ምርት ግብይትን ማሻሻል፣**

በአገራችን በግብርና ዘርፍ ተደራጅቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር በርካታ ቢሆንም በግብርና ምርት ግብይት ውስጥ የሚሳተፉት አናሳ በመሆናቸው በዘርፍ የሚሰጡት አገልግሎት ችግር ፈች አይደለም፡፡ በመሆኑም የግብርና ምርት ግብይቱን በማጠናከር ጥራት ያለው ምርት የኅብረት ሥራ ማህበራት በተደራጁበት የአደረጃጀት እርከን በግብይቱ ውስጥ ሊኖራቸው የሚገባውን ድርሻ በአግባቡ እንዲያድግ የተጠናከረ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

በግብርና ምርት ግብይት የሚሳተፉ በየእርካኑ ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያደርጉት የግብይት ቅብብሎሽ ሰንሰለት በየደረጃው እሴት የሚጨምር፣ ወጭን የሚቀንስ፣ የተንዛዛ የግብይት ሰንሰለትን የሚያሳጥር እንዲሆን የሚያስፈልግ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪ በግብርና ምርት ግብይት ላይ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት በምርት ግብይቱ ውስጥ ገብተው በስፋት እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የመደራደር አቅማቸውን በማጠናከር አምራቹ ከምርቱ የተሻለ የዋጋ ተጠቃሚ እንዲሆን ዋጋ ተቀባይ ብቻ ሳይሆኑ የዋጋ ሰጭነት አቅማቸውን በማዳበር፣ የአገር ውስጥ የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋፋት በግብይቱ ላይ የሚታየውን ችግር ለመቅረፍ በስፋት እንዲንቀሳቀሱ የሚያደርግ አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በእንስሳት እና እንስሳት ተዋጽኦ ምርት ግብይት ላይ ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ ይደራጋል፡፡

በግብርና ምርት ግብይት ውስጥ ያሉ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ምርቶችን በብዛት እና በጥራት በማሰባሰብ፣ በማከማቸት፣ በማጓጓዝ፣ በማሸግ፣ ደረጃ በመስጠት እና እሴት በመጨመር የመደራደር አቅማቸውን በማጎልበት ከሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር ለምርቱ የተሸለ ገበያ በማፈላለግ እንዲሻጥ የማድረግ ተግባር ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ በሌላ በኩል አባለት የሚያመርቷቸው ምርቶች ገበያ ተኮር እንዲሆን ግንዛቤ የመፍጠር ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች በግብርና ምርት ግብይት ላይ የአባላትን የመደራደር አቅም በማጎልበት፣ የገበያ መረጃ አገልግሎት መስጠት፣ የገበያ ትስስርን በማመቻቸት፣ የመጋዘን አገልግሎት በመስጠት፣ እሴት በመጨመር እና የትራንስፖርት አገልግሎቶችን በማመቻቸት ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት እንዲሰሩ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖች አባላት ለሰበሰቡት ምርት ገበያ በማፈላለግ አገር አቀፍ የጅምላ ግብይት ሥራዎች ላይ በመሳተፍ፣ ትላልቅ የእሴት መጨመሪያ ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም፣ በአገር አቀፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመዘርጋትና በማለዋወጥ፣ ፋይናንስ ማመቻቸት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን በማስተባበር እና የመደገፍ ተግባራት ላይ እንዲያተኩሩ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰበስቧቸው የግብርና ምርቶች አባላት በምርት አያያዝ ላይ ያላቸው ክህሎት አናሳ በመሆን እና የኅብረት ሥራ ማህበራት የምርት ጥራት ቁጥጥር ደካማ በመሆኑ ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶች አልፎ አልፎ የጥራት ችግር ይታያል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የተመረተውን ምርት ዓይነት፣ ጥራትና መጠኑን በመለየት እና ለምርቱ ደረጃ በመስጠት፣ የምርት ዱካ በማመላከት እና ምርቱን ቀድሞ የማስታዋወቅ ሥራዎች ተጠናክሮ ይሰራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ከምርታቸው የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል እና የበለጠ ለማምረት እንዲነሳሱ ለማድረግ ለምርቶች ትክክለኛ የጥራት ደረጃ በማስቀመጥ የተሻለ ጥራት ያለው ምርት ያቀረቡ አባላት የተሻለ የገበያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ጥራትን መሠረት ያደረገ የክፍያ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ጥራትን ለማስጠበቅ እንዲቻል የምርት ጥራት ቁጥጥር ባለሙያዎችን በመቅጠር እንዲያሰሩ የሚያደርግ አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

በየጊዜው የሚያጋጥመውን የግብርና ምርቶች የዋጋ መዋዠቅ ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ከምርት አቀነባበሪዎች ጋር ቀድሞ የኮንትራት ውል በመግባት ሸጦ የማምረት አሰራርን ተግባራዊ እንድያደርጉ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች ተቋማት ጋር የኅብረት ሥራ ማህበራት መሪህን በማይጻረር መልኩ በጆይንት ቬንቼር የሚሰሩበት አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በተለይም ከውጭ አገር በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርቶች ለመተካት ራሳቸው ወይም አባሎቻቸው እንዲያመርቱ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰሩ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፡፡

### መፍትሄ 2፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የምርት ግብይት ተግባርን የሚያሳልጥ መሰረተ ልማትን ማጠናከር፤

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባሎቻቸው የሚሰበስቡትን የምርት ዓይነትና መጠን ለማከማቸት የሚያስፈልጉ ለደረቅ፣ ለፈሣሽ፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ፣ ለኬሚካል እና ሌሎች ዓይነት ምርቶች ማከማቻ የሚሆኑ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖች በኅብረት ሥራ ማህበራት፣ በመንግስት እና በሌሎች አቅም ገንቢ አካላት ዘመናዊ እና አስፈላጊ መሳሪያዎችን ያሟሉ መጋዘኖች የሚገነቡበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ መጋዘኖቹም ለአካባቢ፣ ለማዕከላዊ እና ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ የአባላትን ምርት ዓይነትና መጠን ባገናዘበ መልኩ በየደረጃው ተገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት ምርት ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ማድረስ እንዲችሉ በከተሞች፣ በኢንዱስትሪ አካባቢዎች እና በመንገድ ዳር ላይ የተለያየ ዓይነት ደረጃ ያላቸው የገበያ ማዕካላት ገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት ሂደት እንዲሳለጥ እንደየምርቱ ባህሪ የአባላት ምርቶችን በማሰባሰብ በአገር ውስጥ ለአከባቢ፣ ለማዕከላዊ፣ ለተቀናጀ የግብርና ኢንዲስትሪዎች፣ እሴት መጨመሪያ ቦታዎች እና ለውጭ ገበያ ለማድረስ እንዲሁም አባላት የሚፈልጉትን የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለማቅረብ የሚያስችል ፈጣን እና ምቹ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

ኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት የሚሰበስቡትን የምርት ዓይነትና መጠን፤ ለአባሎቻቸው የሚቀርቡ ግብዓቶችንና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለማጓጓዝ የሚያስችል የትራንስፖርት አገልግሎቶችን የሚሰጡ ጠንካራ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲቋቋሙ ይደረጋል፡፡ ሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራትም በራሳቸው ወይም ከሌሎች ድርጅቶች ጋር እንዳስፈላጊነቱ መርሆአቸውን በማይፃረርና ተጠቃሚነታቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ በጆይንት ቬንቸር በመቀናጀት አመቺ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ ኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ግብይት እንዲሳለጥ ለማድረግ ቀልጣፋ እና ወቅታዊ የገበያ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ቴክኖሎጅዎችን በመገንባትና በመዘርጋት አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በምርት ላይ እሴት በመጨመር የግብርና ምርት የተሸለ ዋጋ አግኝቶ አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ ለአገር ኢኮኖሚ ግንባታ የራሱን አስተዋጽኦ እዲያበረክት ለማስቻል ከቀላል እስከ ትላልቅ የምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ ለዚህም ተግባር መንግስት እና አቅም ገንቢ አካላት ለኅብረት ሥራ ማህበራት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

## መፍትሔ 3፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ከግብርና ምርቶች ውጭ ባሉት ምርቶች ግብይት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ

**ከግብርና ምርቶች ውጭ ያሉ ምርቶች ግብይትን በቀጣይነት ማሻሻል፡-** በወርቅ፣ በዱር ሙጫ፣ በካርቦን ሽያጭ፣ በጨው፣ በባህሪ ዛፍ ዘይትና መድሃንት ማምረት እና ግብይት እና ሌሎች ተያያዥ ተግባራት ላይ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ተጠናክሮ እንዲሰሩ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ግብይት ለማሳለጥ በሌሎች ተቋማት የተቀመጡ የሕግ ማዕቀፎች እና አሰራሮች እንዳይጣሱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

ግብይቱን በተሸለ ሁኔታ ለማጠናከር እንዲቻል ዘርፉን ሊያግዝ የሚችል ጠንካራ እና ወጥነት ያለው የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ይተገበራል፡፡ በሚዘረጋው የአሰራር ስርዓት ላይ በዘርፉ ያሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት እና ሌሎች ፈጻሚ እና አስፈጻሚዎች አካላት ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ የጋራ መስተጋብር በመፍጠር እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከግብርና ውጭ ባሉ ግብይቶች ላይ ያላቸው ግንዛቤ አናሳ በመሆኑ የግንዛቤ መፍጠር ሥራ በስፋት ይሰራል፡፡ ሥራው በባህሪው ጠንካራ ባለሙያ የሚፈልግ በመሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት በዚህ ዘርፍ ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎች ቀጥሮ እንዲያሰሩ የሚያስፈልጉ ድጋፎች ይደረጋል፡፡

በየደረጃው የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ በተጨማሪም ዘርፉ በርካታ የመንግስት ተቋማት የሚመለከት ተግባር በመሆኑ ሌሎች የሚመለከታቸው

አካላት በዚህ ተግባር ላይ ለተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ድጋፍ ማድረግ የሚያስችላቸው አሰራር ተዘርግቶ ይተገበራል፡፡

## መፍትሄ 4፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሚፈልጓቸውን የፍጆታ ምርቶችን አቅርቦት ማሻሻል፤

**የኅብረት ሥራ ማህበራት የፍጆታ ምርቶች ግብይትን ማጠናከር፡-** የሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት የፍጆታ ምርቶችን ለአባላት በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ አባላትን ተጠቃሚ ከማድረግ ባሻገር ሰው ሰራሽ የሆኑ የገበያ ዋጋ ንረቶችን በመከላለከል የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ በትኩረት ይሠራል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የሚያስፈልጉ የፍጆታ ምርቶችን በዓይነት እና በብዛት በማቅረብ የአባላትን ፋላጎት ማርካት እንዲችሉ አስፈላጊው ድጋፍ እና ክትትል ይደረጋል፡፡

በከተማ የሚገኙ ሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት ገጠር ከሚገኙ አምራች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ጠንካራ እና ቀጣይነት ያለው የግብይት ትስስር በመፍጠር የግብርና ምርቶችን በቀጥታ ከአምራቹ የሚያገኙበትን አሰራር በመዘርጋት ጥራቱን የጠበቀ ምርት፣ በወቅቱና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ አምራቹን እና ሸማቹን በቀጥታ በማገናኘት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተጠናክሮ ይሰራል፡፡ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት ከኢንዱስትሪ ምርት አምራቾች ጋር በቀጥታ የግብይት ትስስር በመፍጠር ምርቶችን በፋብሪካ ዋጋ በመረከብ በተመጣጣኝ ዋጋ ለአባላት እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡

የፍጆታ ምርቶች አቅርቦት እና ስርጭት ውስጥ በየደረጃው የሚገኙ መሰረታዊ፣ ዩኒዮን እና ፌዴሬሽን ኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻቸው ምን መሆን እንደለበት አሰራር በመዘርጋት የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ በማድረግ ተግባሮቻቸው ሳይደበላለቅ በመተጋገዝ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡዋቸው አገልግሎቶች በዋናነት ለአባላት የሚሰጡ ቢሆንም ከለው ነባራዊ ሁኔታ ከአባላት ውጭ አገልግሎት የሚሰጡበት አሰራር ይኖራል፡፡ በመሆኑም አባላት የተሸለ ተጠቃሚ ለማድረግ ለአባት የተለየ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት የግዥ ስርዓታቸው የተጠናከረ ባለመሆኑ ምክንያት አሰራራቸው ላይ መዝረክረክ ስለምታይ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ይተገበራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያቀርቧቸው የድጎማ የፍጆታ ምርቶች ወቅታዊ በመሆናቸው ተግባሮቻቸውን በዘላቅነት እንዲያከናውኑ የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የድጎማ ምርቶችን ለሕብረተሰቡ ከማድረስ ባሻገር አባላት የሚፈልጉትን የፍጆታ ምርቶችን ዓይነት፣ በብዛት እና በጥራት ማቅረብ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እዲሰሩ ይደረጋል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት በኩል የሚቀርቡ የድኅማ ምርቶች ለሕብረተሰቡ በአግባቡ እንዲደርስ ለማድረግ ጠንካራ አሰራር ስርዓት በመዘርጋት፣ በዕቅድ ላይ በመመስረት እና ቁጥጥር በማድረግ የሚታየውን የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት እና ድርግቶች እንዳይሮር ለማድረግ በትኩረት ይሰራል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት በኩል የሚቀርቡ የድኅማ ምርቶች አፈጻጸም ላይ የመንግስት እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ኃላፊነት እና ድርሻ በተገቢው መንገድ ተለይቶ በውል ላይ ተመስርቶ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

የሸማቶች ኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሮቻቸውን የሚደግፉ ባለሙያዎችን በመቅጠር አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት ያለቀላቸው የፍጆታ ምርቶችን ለአባለት ከማቅረብ ባሻገር አቅም በመፍጠር የሚቀርቡ ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር ለአባላት እንዲያቀርቡ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

## ዓምድ 12፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የውጭ ግብይት ማጠናከር

### *ሀ. ነባራዊ ሁኔታ*

ኢኮኖሚያችን ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ለማሸጋጋር በሚደረገው ርብርብ ውስጥ የውጭ ግብይት ያለው ድርሻ እጅግ የላቀ ነው፡፡ የግብርና ምርት ከጊዜ ወደ ጊዜ መጠኑና ጥራቱ ሲጨምር ወደ ውጭ አገር ገበያ የሚላክ ምርት በዚያው ልክ ካላደገ የኢኮኖሚ ሽግግሩን እውን ማድረግ ያዳግታል፡፡ የተለያዩ አገሮች ተሞክሮ እንደሚያሳየው የኅብረት ሥራ ማህበራት የውጭ ገበያ መዳረሻዎን በማስፋት፣ በውጭ ግብይቱ ላይ የሚታየውን የተንዛዛ የግብይት ህደትን በማሳጠር፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን ዓይነት፣ መጠን፣ ጥራት እና ወቅታዊነትን ጠብቆ በመላክ ውጤታማ ተቋማት ናቸው፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት የውጭ ግብይት የተሳካ ተሞክሮ ካላቸው አገሮች መካከል ኒውዝላንድ የወተትና የወተት ተዋጽኦ 95 በመቶ እና በሥጋ ምርት 50 በመቶ፣ በኡራጓይ የወተትና የወተት ተዋጽኦ 90 በመቶ እና የስንዴ ምርት 60 በመቶ፣ በፊንላንድ የወተትና የወተት ተዋጽኦ 96 በመቶ እና ስጋ 82 በመቶ እና በኬንያ የቡና ግብይት 70 በመቶ እና የጥጥ ምርት ግብይት 95 በመቶው፣ የሚደርሰውን የውጭ ግብይት ድርሻ የሚይዙት የኅብረት ሥራ ማህበራት መሆናቸውን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት በውጭ ግብይት ላይ ያላቸው ልምድ የዳበረ ባይሆን በተለይን ቡና፣ ሰልጥ፣ ማር እና የእንስሳት ውጤቶችን ወደ ውጭ በመላክ አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ ለአገርቱ የውጭ ምርዛር በማስገኘት በኩል ጥሩ ጅምሮች ይታያል፡፡ በተለይም በአገራችን በቡና ግብይት ሰንሰለት ውስጥ የነበረውን የተንዛዛ የግብይት አሰራር በማሳጠር ግብይቱ የተሳለጠ እንዲሆን ያደረጉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ለአብነት ባለፉት 5 ዓመታት 544,659,852 በላይ የውጭ ምንዛሪ በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ይህንን በጎ ጅምር በማስቀጠል

ኅብረት ሥራ ማህበራት ለውጭ ገበያ የሚያቀርቧቸው ምርቶች ዓይነት እና ብዛት በመጨመር በውጭ ግብይት ውስጥ በስፋት እንዲገቡ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት ይኖርበታል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከውጭ አገር በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርቶች ለመተካት ራሳቸው ወይም አባላት እንዲያመርቱ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ ማድረግ አስፈላጊ ቢሆንም በአገር ውስጥ ሊገኙ የማይችሉ ምርቶችን ከውጭ በማስገባት አባላትን ማገልገል ያስፈልጋል፡፡ የሌሎች አገሮች ተሞክሮ እንደምያሳየው ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የተለያዩ ግብዓቶችን እና የፍጆታ ምርቶችን ከውጭ አገር በተመጣጣኝ ዋጋ በማስገባት ለአባላት በማቅረብ ተጠቃሚ ስያደርጉ ይታያል፡፡ ለአብነት 50,470,000 ከ/ል የአፈር ማዳበሪያ በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት ተሰራጭቷል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከውጭ በቀጥታ የሚያስገቧቸው ምርቶች የግብይት ሰንሰለቱ ያጠረ ስለሚሆን ከሌሎች አቅራቢዎች በመግዛት ለአባላት ከሚቀርቡ ምርቶች ጋር ስነጻጸር በዋጋም በጥራትም የተሸለ ነው፡፡

በአገራችን የግብርና ምርት ማሰደጊያ ግብዓቶችን ለአባሎቻቸው በማቅረብ ላይ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራዎቻቸውን የሚያከናውኑት ከመንግስት ጋር በመቀናጀት ሲሆን በመንግስት የማይቀርቡ ሌሎች ግብዓቶችን በራሳቸው በማቀድ በማስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ በአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች የአፈር መዳበሪያን ከውጭ አገር ለተከታታይ 4 ዓመታት አገሪቱ የአፈር መዳበርያ ፍላጎት ውስጥ 82 ከመቶ የሚሆነውን በማስገባት አርሶ አደሩን በወቅቱ፣ በጥራት፣ በሚፈለገው ቦታ እና በተመጣጣኝ ዋጋ ተጠቃሚ ያደረጉበት ተሞክሮ እንደነበረ ማረጃዎች ያሳያሉ፡፡

አገራችን በየዓመቱ ለግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን ከውጭ አገር ለማስገባት በሚሊየን የሚቆጠር ዶላር ታወጣለች፡፡ አባላት የሚፈልጓቸው የፍጆታ ምርቶችንም በተመሳሳይ የተወሰኑት ከመንግስት ጋር በመቀናጀት የሚያቀርቡ ሆነው ቀሪው በራሳቸው አቅዶ ይተገበሩታል፡፡ ኅብረት ሥራ ማህበራት በአባላት የሚፈለጉ ግብዓቶች እና የፍጆታ ምርቶችን ከውጭ አገር በቀጥታ ለማስገባት የሚያስችል አሰራር ባለመኖሩ ምክንያት ተግባራዊ ማድረግ አልቻሉም፡፡

## ሰንጠረዥ 8፡ የኦሮሚያ የቡና አብቃይ እና የፀሐይ ኃላ.የተ ሁለገብ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ዩኒየን በሞደልነት የተወሰዱ (bench mark)

> 1. *የኦሮሚያ የቡና አብቃይ ኃ. የተ. ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒዬን*
>
> **የአባላትና ካፒታል እድገት፡-** በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በ2008 ዓ.ም መረጃ መሠረት የአባል መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ቁጥር 357፣ የተናጠል አባላት ቁጥር በድምሩ 332,393 ካፒታሉን ደግሞ ከብር ብር 452 ሚሊየን ማሳደግ ችለዋል፡፡
>
> **የኢትዮጵያን ኅብረት ሥራ ማስተዋወቅ፡-** በኢትዮጵያ የቡና ምርት ላይ በአውሮፓ የተሰራዉን ጥቁር ወርቅ የተሰኘ ዘጋቢ ፊልም (Black Gold documentary film) በማዘጋጀት ቡናችንን ለአለም በማስተዋወቅ እና በተጓዳኝ የአገር የገጽታ ግንባታ ሥራ ሰርቷል፡፡ በቡና ግብይት ውስጥ ትልቁ ድርሻ የሚያበረክተውን 26 በተፈጥሮ /Organic/፣ 42 ፌርትሬድ /Fair trade/፣ 4 ሬይን ፎሬስት /Rain Forest Alliance/፣ 3 ኡትዝ /UTZ/ እና 15 መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ካፌ ፕራክቲስ /Café Practice/ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ዩኒየኑ በ25 አገሮች ውስጥ ለ90 ደንበኞች ቡና መሸጥ መቻሉ እና የሚያስገኘው የውጭ ምንዛሪ እያደገ መሄዱ በአማካይ በአመት $ 43,385,828 የአሜርካን ዶላር በማስገኘት ችለዋል፡፡
>
> **የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራትና አባላት ተጠቃሚነት እድገት፡-** የዩኒየኑ የመደራደር አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተ መምጣቱ እና በየአመቱ የሚሸጠው ቡና እየጨመረ መጥቶ በነጥር በአማካይ $ 3.30 የአሜርካን ዶላር መሸጥ መቻሉና ከገበያ በላይ በ $1.30 አሜርካን ዶላር ነጥር በማግኘት ላይ ይገኛል፡፡ ከ2006 ዓ/ም ጀምሮ ቡናን በተሻለ ዋጋ በመሸጡ በአገሪቱ ካሉት የቡና ላኪዎች ውስጥ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡
>
> **ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፡-** ዩኒየኑ 155 ቋሚና 1,200 ጊዜያዊ ሰራኞችን እንዲሁም 1,302 ቋሚና 12,000 ጊዜያዊ ሰራተኞችን በአባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ደረጃ የሥራ እድል መስጠር ችሏል፡፡
>
> 2. *የፀሐይ ኃላ.የተ. ሁለገብ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ዩኒየን*
>
> **የአባላትና ካፒታል እድገት፡-** በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ጎንደር ዞን ውስጥ የሚገኝ ስሆን በኒዩኑ የ2009 ዓ.ም መረጃ መሠረት የአባል መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ቁጥር 135፣ የተናጠል አባላት ቁጥር በድምሩ 117,933 እና ካፒታሉን 52.6 ሚሊየን ብር ማሳደግ ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡
>
> **የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት፡-** ዩኒዬኑ የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት መካከል የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን ማቅረብ እና ማሰራጨት፣ የአገር ውስጥ እና የውጭ የምርት ግብይት፣ የዘር ብዜት፣ የመጋዘንና የትራንስፖርት አገልግሎት፣ የእሴት መጨመር (አግሮ ፕሮሰስንግ) እና ሌሎች ናቸው፡፡
>
> **የኤክስፖርት ግብይት ላይ መሳተፍ፡-** የኒዩኑ እስከ 2009 ዓ.ም ለውጭ ገበያ ያቀርባቸው ሰብሎች ኑግ እና ሰሊጥ ስሆኑ በቀጣይ መሾ፣ ሽምብራ እና ጥቁር አዝሙድ ለማቅረብ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት ዩኒዬኑ ከ2004 እስከ 2008 ዓ.ም በድምሩ 20,710 ኩንታል ሰሊጥ እና ኑግ ሰብሎችን ለውጭ ገበያ በመናቅረብ 3,738,956.80 የአሜሪካን ዶላር በመሸጥ አባላት ከምርታቸው ተጠቃሚ እንድሆኑ በማድረግ ለአገሪቱ ተጨማሪ የውጭ ሚንዛሪ አስገኝቷል፡፡

### ለ. በኅብረት ሥራ ማህበራት የውጭ ግብይት ላይ ያሉ ማነቆዎች፤

### ማነቆ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት በውጭ ገበያ የሚፈለጉ ምርቶችን በስፋት፣ በጥራትና በወቅቱ ማቅረብ አለመቻል

በአገራችን ተደራጅቶ አገልግሎት እየሰጡ ካሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል በውጭ ግብይት ላይ ለመሰማራት በቂ አቅም (potenetial) ካላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ በውጭ ግብይት ላይ የተሰማሩ ቁጥራቸው አነስተኛ ነው፡፡ ለውጭ ገበያ የሚላኩ ምርቶች በዓይነትም ሆነ በመጠን አነስተኛ ናቸው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የምርት ጥራትን ለመጠበቅ አቅማቸው ደካማ በመሆኑ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች የጥራት ችግር ያለባቸው በመሆኑ ተወዳዳር አይደሉም፡፡ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች በሚፈለግበት ወቅት በማድረስ በኩል ችግሮች ይታያሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በውጭ ግብይት ላይ ያላቸው ግንዛቤ አናሳ መሆን፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት በውጭ ገበያ ላይ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን እንዲያመርቱ በማድረግ በኩል እጥረቶች አሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በውጭ ግብይት ላይ ያላቸው ግንዛቤ አናሳ መሆን፡፡ የውጭ ግብይት ሥራ በባህሪው ብቁ ባለሙያ የሚፈልግ ቢሆንም የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚፈለገው ደረጃ ብቁ ባለሙያ ቀጥሮ እያሰሩ አለመሆን፡፡ የሚመለከታቸው አካለት በመቀናጀት ለውጭ ግብይት እየሰጡት ያለው ትኩረት አናሳ በመሆኑ የሚደረገውም ድጋፍ ዝቅተኛ ነው፡፡

**ማነቆ 2፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችንና የፍጆታ ምርቶችን ከውጭ በጅምላ ለማስገባት የሚያስችል ግልጽ አሰራር አለመኖር**

የኅብረት ሥራ ማህበራት በአባላት የሚፈለጉ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን በራሳቸው አቅም ከውጭ አገር ለማስገባት የሚያስችል ግልጽ አሰራር የለም፡፡ በተመሳሳይ አባላት የሚፈልጉትን የፍጆታ ምርቶች ከውጭ አገር በማስገባት የአባላትን ፍላጎት ማርካት አልተቻለም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከውጭ የሚያስፈልጉ ምርቶችን ለማስገባት ሰፊ የክህሎት ችግር ይታያል፡፡ በየደረጃው የሚገኙ አካላት የኅብረት ሥራ ማህበራት ተፈላጊ ምርቶችን ከውጭ አገር በማስፈገባት አባላትን ተጠቃሚ እዲያደርጉ የሚሰጥ ድጋፍ አናሳ ነው፡፡ ከውጭ የሚገቡ ምርቶች በአገር ውስጥ ለመተካት ትኩት ሰጥተው መስራት አለመቻል፡፡

**ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የምንከታላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤**

| |
|---|
| ***የውጭ ግብይት (ማለትም በቡና፣ በሰሊጥ፣ የቅባት እህሎች፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ እንስሳት እና እንስሳት ተዋጽኦ፣ ቅመማ ቅመም እና ሌሎች) ድርሻ 65 ከመቶ ይደርሳል፡፡*** |

**መፍትሔ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት በውጭ ገበያ ያላቸውን ድርሻ ማሰደግ፡-**

ኢኮኖሚያችን ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር እንዲሸጋገር በሚደረገው ርብርብ ውስጥ የውጭ ግብይት ያለው ድርሻ እጅግ የላቀ በመሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት በውጭ ግብይት ላይ ትኩረት ሰጥተው በስፋት እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የውጭ ግብይት ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ በውጭ ግብይት ድርሻ ያላቸው አካላት ትኩረት ሰጥቶ እና ተቀናጅቶ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ በአገራችን በውጭ ግብይት ላይ ለመሰማራት ፖቴንሸያል ካላቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ በውጭ ግብይት ላይ እየተሳሰፉ ያሉት ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ አቅም ፈጥሮ በውጭ ግብይት ላይ በስፋት እንዲሳተፉ ለማድረግ አስፈላጊው ድጋፍ እና ክትትል ይደረጋል፡፡



DRAFT

የኅብረት ሥራ ማህበራት ምርቶቻቸውን በቀጥታ ወደ ውጭ መላክ እንዲችሉ ለማድረግ የሚያስፈልጉ አሰራሮች ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የውጭ ገበያ መረጃ አያያዝን ለማዘመን የሚያስፈልጉ ሶፊት-ዌሮችንና ድህረ-ገጾችን በመገንባት እና ሌሎች ዘመናዊ አሰራሮችን በመዘርጋት ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

የግብርና ምርታችን ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጠንም ሆነ በጥራት እየጨመረ በሚሄድበት ወቅት ወደ ውጪ አገር የሚላኩ ምርቶች በዚያው ልክ በማሳደግ የኢኮኖሚ ሽግግሩን እውን ለማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራት የውጭ ገበያ መዳረሻዎችን ማስፋፋት፣ በውጭ ግብይቱ ላይ የሚታየውን የተንዛዛ የግብይት ሂደት በማሳጠር፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን ዓይነት፣ መጠን፣ ጥራት እና ወቅታዊነትን ጠብቆ መላክ ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን በጥሬ ከመላክ ይልቅ እሴት በመጨመር እና ለምርቱ ልዩ ምልክት በመስጠት መላክ የምርት ዱካ (traceablity) ስለሚያረጋግጥ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች ወቅታዊነት ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት አሰራሩን ሊያንዛዙ የሚችሉ ችግሮችን በመለየት እንዲስተካከል በማድረግ የሚፈለጉ ምርቶችን በሚፈለግበት ወቅት እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ወደ ውጭ የምልኳቸው የአባላት ምርቶች የዓለም ገበያ የሚፈልገውን የጥራት ደረጃ መስፈርት እንዲያሟላ የሚያግዙ የድጋፍ የአሰራር ስርዓቶች ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በውጭ ግብይት ላይ የሚሰማሩ ኅብረት ሥራ ማህበራት በየአደረጃጀት እርከናቸው የምርት ቅብብሎሹ ቀልጣፋ እና እሴት የሚጨምር እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በተለይም በከፍተኛው እርካን ላይ ያሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት በውጭ ግብይት በሙሉ አቅማቸው እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡

በውጭ ግብይት ላይ የሚሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት መንግስት ልዩ የማበረታቻ እና ድጋፍ የሚያገኙበትን አሰራር ይዘረጋል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት እና በውጭ አገር የምርት ገዥዎች መካካል የሚደረጉ ውሎች ዓለም አቀፋዊ ይዜት እንዲኖራቸው የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮች፣ አባላት እና ባለሙያዎች በውጭ ግብይት ላይ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ ችግሩን ለመቅረፍ ሰፋፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በሚመለከታቸው አካላት ትኩረት ተሰጥቶ ይሰጣል፡፡ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች ጥራት እንዲኖራቸው እና በገበያ ላይ ተወዳዳር እንዲሆን የኅብረት ሥራ ማህበራት ብቃት ያላቸው የግብይት ባለሙያዎችን እንዲቀጥሩ በማድረግ አባላት ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያቀርቡት ምርቶች መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎችን ተገንዝበ እንዲያቀርቡ ሙያው ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት በውጭ ገበያ ላይ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን እንዲያመርቱ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ በትኩረት እንዲሰራ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በውጭ ገበያ ላይ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ምርቱን ከሚፈልጉ የውጭ አካላት ጋር የሁለቱን ጥቅም በሚያስከብር ሁኔታ የኮንትራት ውል (contract farming) በመፈራረም ሽጦ የማምረት አሰራርን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት መርሆዎቻቸው በማይጻረርና ተጠቃሚነታቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ እንደአስፈላጊነቱ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በጆይንት ቬንቸር ሊሰሩ የሚችሉበት አሰራር ይፈጠራል፡፡

## መፍትሄ 2፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችንና የፍጆታ ምርቶችን ከውጭ በጅምላ ለማስገባት የሚያስችል ግልጽ አሰራር መዘርጋት፤

**የግብዓት እና የፍጆታ ምርቶችን ከውጭ አገር በጅምላ ማስገባት፡-** የኅብረት ሥራ ማህበራት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በማምረት በአገር ውስጥ ምርት ከመተካትም ባሻገር እንደአስፈላጊነቱ የፍጆታ፣ የኢንዱስትሪ እና የግብርና ምርቶችን ከውጭ አገር በጅምላ የሚያስገቡበት ስርዓት ተዘርግቶ ይተገበራል፡፡ ኅብረት ሥራ ማህበራት የአፈር መዳበሪያ፣ ፀረ-ተባይ መድሃንቶች፣ ጸረ-አረም፣ የእንስሳት መድሃንቶች እና ሌሎች አገር ውስጥ የማይገኙ የግብርና ምርት ማሰደጊያ ግብዓቶችን በብዛት በማቅረብ አባላት የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ ለዚህም የሚያግዝ የዕውቀት እና የቴክኖሎጅ ሽግግር ለማድረግ የሚታዩ ተሞክሮዎች በተጠናከረ መልኩ እንድሰፉ ትኩረት ተሰጥተው ይሰራል፡፡

የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግበዓቶች እና የፋጆታ ምርቶችን ከውጭ የሚያስገቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ወጭን በመቆጠብ አባላትን የተሸለ ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲቻል የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽኖች እና ዩኒዮኖች እንደአስፈላጊነቱ እንደ አስፈላጊነቱ አቅም ያላቸው ማሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊሰተፉ ስርዓት ተዘርግቶ ይተገበራል፡፡

ከውጭ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግበዓቶች እና የፋጆታ ምርቶችን በጅምላ ለማስገባት በኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮች እና ቅጥር ሰራተኞች የሚታየውን የክህሎት ችግር ለመቅረፍ የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው ግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና እንዲጡ ይደረጋል፡፡

## ዓምድ 13፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የገበያ ጥናት እና መረጃን ማጠናከር

### ሀ. ነባራዊ ሁኔታ

የኀብረት ሥራ ማህበራት ግብይት ውጤታማ የሚሆነው ጠንካራ የግብይት ጥናት በማካሄድ ውጤታማነቱን በመረጋገጥ ከተሰራ ነው፡፡ በግብይት ተግባር ላይ የተሰማሩ ውጤታማ ተቋማት ለውጤታማነታቸው አንዱ ምክንያት ጠንካራ የገበያ ጥናት በማድረግ የግብይት ሥራዎቻቸውን ስለሚመሩ ነው፡፡

በአገራችን መንግስት የግብርና ምርት ግብይትን ለማሳለጥ አስፈላጊ የሆኑ የገበያ ጥናቶችን በማድረግ ወቅታዊ የገበያ መረጃ ለአርሶ አደሩ እና ለተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ መዋቅር ዘርግቶ ስሰራ ቆይቷል፡፡ በግብይት ሥራ ላይ የተሰማሩ የኀብረት ሥራ ማህበራት በአከባቢ፣ ማዕከላዊ እና ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቧቸው ምርቶች ጭምር ሰፊ የገበያ ጥናት በማድረግ ተግባሮቻቸውን በመምራት በኩል ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ የገበያ ጥናት ሊያካሂድ የሚችል ብቁ የገበያ ባለሙያ በመቅጠር አስፈላጊ የሆኑ የገበያ ጥናቶችን እንዲያካሂድ በማድረግ ሥራዎቻቸውን መምራት አለመቻል ትልቅ ችግር ነው፡፡

### ለ. የኀብረት ሥራ ማህበራት የገበያ ጥናት ላይ ያሉ ማነቆዎች፣

### ማነቆ 1፡- የኀብረት ሥራ ማህበራት ጥናትን መሰረት ያደረገ ግብይት አለማካሄድ፤

የኀብረት ሥራ ማህበራት የሚያከናውኑት ግብይቶች በቂ ጥናት ሳይደረግ የሚካሄድ መሆኑ፡፡ የኀብረት ሥራ ማህበራት በገበያ ጥናት ላይ ያላቸው ግንዛቤ አናሳ ማሆን፡፡ ለገበያ ጥናት ትኩረት መስጠት አለመቻል፡፡ የገበያ ጥናት የሚያጠና ጠንካራ የገበያ ባለሙያ ቀጥሮ ማሰራት አለመቻል፡፡ በገበያ ጥናት ላይ ከሚመለከታቸው አካልት ለኀብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጥ ድጋፍ አነስተኛ መሆን፡፡ የገበያ ጥናት እንዲካሄድ የተዘረጋ የአሰራር ስርዓት አለመኖር ዋና ዋና ማነቆዎች ናቸው፡፡

### ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የምንከታላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤

### መፍትሄ 1፡- በጥናት ላይ የተመሰረተ የኀብረት ሥራ ማህበራት ግብይትን መገንባት፡-

የኀብረት ሥራ ማህበራት ግብይት ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ ከምርት ማሰባሰብ ጀምሮ እስከ መጨረሻው የገበያ መዳረሻ ድረስ ያሉ የገበያ ሰንሰለቶች በጥናት በመለየት አዋጭነቱ ተረጋግጦ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ በተለይ በአከባቢ እና በማዕከላዊ ገበያዎች ላይ የሚደረጉ የኀብረት ሥራ ማህበራት ግብይቶች አዋጭነታቸው ተረጋግጦ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡

በውጭ ግብይት ላይ የሚሳተፉ የኀብረት ሥራ ማህበራት የውጭ ግብይት ውስጥ ያሉ አጠቃላይ ሂደቶችን ጭምር በማጥናት ማነቆዎችን በመለያት እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ የኀብረት ሥራ ማህበራት ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ

ከመላካቸው በፊት የግብይት አቅማቸውን በማሳደግ ጥልቀት ያለው የውጭ ገበያ ሁኔታ ጥናት በማድረግ አዋጭነቱ ተረጋግጦ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡

ማንኛው የኅብረት ሥራ ማህበር የገበያ ጥናት ሳያጠና እና አዋጭነቱ ሳይረጋገጥ የሚደረግ የግብይት ተግባር የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለኪሳራ ስለሚዳርግ የገበያ ጥናት ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ የገበያ ጥናት ጠንካራ አደረጃጀት የሚፈልግ በመሆኑ በተለይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖችና ፌደሬሽኖች ለዚህ ሥራ ትኩረት በመስጠት ጥናቱን በማጥናት አባል ኅብረት ሥራ ማህበራትን መደገፍ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፡፡

የገበያ ጥናት ሥራ ውስብስብ በመሆኑ በቂ የገበያ ባለሙያ ያስፈልገዋል፡፡ በመሆኑም የኅብት ሥራ ማህበራት የገበያ ጥናት ሊያጠና የሚችል ብቁ ባለሙያ በመቅጠር እንዲሰራ የሚደርግ አሰራር ይዘረጋል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት ግብይት ላይ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማት ችግር ፈች ድጋፍ እንድያደርጉ የሚያስችል አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የአባላትን ፍላጎት የሚያሟላ ኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት ችግር የሚፈታ የግብይት ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በገበያ ጥናት አሰራር እና አጠቃቀም ላይ በየደረጃው ለሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተከታታይነት ያለው የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሠጣል፡፡

የኅብረት ሥራ ግብይት ውጤታማ እና ቀጣይነት እንዲኖረው ጥልቀት ያለው እና ችግር ፋች ጥናት በኅብረት ሥራ ትምህርት እና ስልጠና ተቋማት፣ በኅብረት ሥራ ምርምር ተቋማት እና ሌሎች ጥናትና ምርምር ተቋማት ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ተቀናጅተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡ በዚህ ሂደት የኅብረት ሥራ ሊግ በበላይነት እንዲያስተባብር ይደረጋል፡፡ የጥናት ውጤቶቹ ለተጠቃሚ ኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲደር ይደረጋል፡፡

## ዓምድ 14፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት ምርቶችና አገልግሎት ላይ ዕሴት መጨመር፤

### *ሀ. ነባራዊ ሁኔታ*

በአገራችን ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት በምርቶቻቸው ላይ እሴት በመጨማር ለገበያ ለማቅረብ የገንዘብ፣ የዕውቀት፣ ክህሎት እና ሌሎች ማነቆዎች አለባቸው፡፡ በዚህ ምክንያት አባላት ብዙውን ጊዜ ለገበያ የሚያቀርቧቸው ምርቶች እሴት የተጨመረበት ባለመሆኑ ለምርቻቸው አስፈላጊውን የገበያ ዋጋ በማግኘት በምፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ እየሆኑ አይደለም፡፡ በምርት ላይ እሴት የመጨመር ተግባር የሚከናወነው የሸማቹን ፍላጎት በመለየት የሚሰራ ተግባር ስለሆነ እሴት የተጨመረበት ምርት በሸማቹ ዘንድ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ በዋጋ የተሸለ ስለምሆን አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎችን በመገንባት በአባላት ምርት ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ በማቅረብ አባላት ከምርቶቻቸው የተሸለ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ያሉ ተቋማት ናቸው፡፡

በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ ከቅርብ ጊዜ ወድህ በእሴት መጨመር ተግባር ላይ እየተሰማሩ ያሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት በቁጥርም በምስጡት አገልግሎትም በመጨመር ላይ ይገኛሉ፡፡ የአባላትን ምርት በመረከብ በማጓጓዝ፣ በማከማቸት፣ ጥራቱን በማስጠበቅ፣ በማሸግ፣ በማቀነባባር እና ሌሎች እሴቶችን በመጨመር ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ በማቅረብ አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ የተጀመሩ ጅምር ተግባራት አበረታች ናቸው፡፡ ሆኖም የኅብረት ሥራ ማህበራት ለእሴት መጨመር ተግባራት ካላቸው አቅም አንጻር ሲታይ ብዙ መሰራት እንዳለበት ያሳያል፡፡

DRAFT

## ሰንጠረዥ 9፡ ወደራ እና ራያ ዋከና ኃ.የተ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበር ዩኒየን በሞደልነት የተወሰዱ (bench mark)

1. ወደራ ሁለገብ የገበሬዎች የህብረት ስራ ማህበር ዩኒዬን

የአባላትና ካፒታል እድገት፡- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን ደብረ-ብርሃን ከተማ ውስጥ የሚገኝ ስሆን በዩኒየኑ የ2008 ዓ.ም መረጃ መሰረት የአባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ቁጥር 86 እንዲሁም የተናጠል አባላት ቁጥር በድምሩ 70,418 (ሴቶች 17.83) ማድረስ መቻሉ እና ካፒታሉን ብር 44.4 ሚሊየን ማሳደግ ችለዋል፡፡ የሚሰጧቸው ዋና ዋና አገልግሎቶች፡- 14 የስንዴ መውቂያ መሣሪያዎችን በ3 ወረዳዎች በሚገኙ 14 መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በማቅረብ ለአርሶ አደሩ በማሰራጨት አንድ ክምር ስንዴ በባህላዊ መንገድ ለመውቃት ረድቷል፡፡ በዚህም እስከ 4 ቀናት ይፈጅ የነበረውን በ8፡00 ሰዓት ውስጥ በመውቃት የሰው፣ የእንስሳት ጉልበትና የሴቶች የስራ ጫና ቀንሷል፡፡ እንዲሁም እስከ ብር 3,200 ይወጣ የነበረውን ገንዘብ ወደ ብር 900 ዝቅ እንዲል በማድረግ ጥራት ያለው ምርት እንዲመረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡እሴት የመጨመር ተግባር ላይ መሳተፍ፡- ከ2003 ዓ/ም ጀምሮ የስንዴ ዱቄት ማምረቻ ፋብሪካ በመገንባት የአባላት ስንዴ ምርት በመፍጨት ለገበያ በማቅረብ አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ ላይ የሚገኙ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ የእንስሳትን ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ለማድረግ የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በመገንባት መኖ በማቀነባበርና ለአባላት በማሰራጨት አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ለአባላት ምርት አማራጭ ገበያ በማፈላለግ ትስስር ማድረግ፡- ለከተማው ሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርትን በተመጣጣኝ ዋጋ እና በጥራት በማቅረብ ፣ለመንግስት ሠራተኛው እስከ 3 ወር የሚደርስ የዱቤ ሽያጭ በቋሚነት መስጠት እንዲሁም ለከተማው ዳቦ ቤቶች ዱቄት በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የአከባቢውን የገበያ ዋጋ እንዲረጋጋ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

## ለ. በኅብረት ሥራ ማህበራት ምርቶችና አገልግሎት ላይ ዕሴት መጨመር ላይ ያሉ ማነቆዎች፤

**ማነቆ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የእሴት መጨመር ተግባራትን በጥናት በመለየት በስፋት መግባት አለመቻል፤**

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት ሰብስቦ ለአገር ውስጥ እና ለውጭ አገር ገበያ የሚያቀርቧቸው ምርቶች እሴት የተጨመረበት ምርት ባለመሆኑ ዋጋውም ሆነ ተቀባይነቱ አነስተኛ በመሆኑ፡፡ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች እሴት የተጨመረበት ባለመሆኑ ምክንያት ለአባላት የሚያስገኘው ጥቅም እና ለአገር የሚያስመጣው የውጭ ምንዛሪ ዝቅተኛ መሆን፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት እና አባላት በእሴት መጨመር ጽንሰ ሃሳብና ጠቀሜታ ላይ በቂ ግንዛቤ ባለመኖሩ ምክንያት የእሴት ማጨመር ተግባርን ከባድ እና ውስብስብ አድርጎ መመልከት፡፡ የሚመለከታቸው የመንግስት እና ሌሎች አቅም ገንቢ አካላት ለእሴት መጨመር ተግባራት በሚፈለገው ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ ለኅብረት ሥራ ማህበራት አስፈላጊውን ድጋፍ አለማድረግ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለእሴት መጨመር ተግባር የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶችን በአግባቡ በማጥናት ማስፋፋት አለመቻል፡፡ የመሰረተ ልማት ግንባታውን በሙያ የሚደግፉ ባለሙያዎች በበቂ ሁኔታ አለመገኘት፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት መሠረተ ልማቶችን ለማስፋፋት የሚጠይቋቸው መሬት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች በሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ምላሽ አለማግኘት፡፡ መሠረተ ልማት ለመዘርጋት የሚያስፈልግ ፋይናንስ ከፋይናንስ ተቋማት ብድር በወቅቱ እና በሚፈለገው መጠን ማግኘት አለመቻል፡፡ ከሌሎች አቅም ገንቢዎች የሚሰጥ ድጋፍ በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን፡፡

**ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤**

- ***በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት ለገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶ 100 በመቶ እሴት የተጨመረበት ይሆናል፡፡***
- ***እንዲሁም ከቀላል እስከ ከባድ የኢንዱስትሪ ግንባታ ካሉት የኅብረት ሥራ ማበህራት ውስጥ 60 በመቶ ገንብቶ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡***

**መፍትሄ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የእሴት መጨመር ተግባራትን በጥናት በመለየት ማስፋፋት፡-**

በአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት ሰብስቦ ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ የሚያቀርቧቸው ምርቶች እሴት የተጨመረበት ምርት ባለመሆኑ ምክንያት ዋጋውም ሆነ ተቀባይነቱ በሚፈለገው ደረጃ አይደለም፡፡ በመሆኑም የኅብረት ሥራ ማህበራት በአባላት ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር አባላት ከምርታቸው የተሻለ የገበያ ዋጋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያደርግ አሰራር እንዲከተሉ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ ዓይነት አግሮ ፕሮሰሲንግ እንዱስትሪዎችን በማቋቋም የአባላት ምርቶችን በማቀነባበር፣ በማሸግ እና ልዩ ምልክት በመስጠት ለገበያ እንዲያቀርቡ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራር አካላት እና አባላት በእሴት መጨመር ጽንሰ ሃሳብና ጠቀሜታ ላይ በቂ ግንዛቤ የሌላቸው በመሆኑ ምክንት የእሴት ማጨመር ተግባርን ከባድ፣ ውስብስብ እና ብዙ ወጭ የሚያስፈልገው ተግባር አድርጎ የመመልከት ችግር በስፋት ይታያል፡፡ ይህንን ችግር ለማቅረፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት የእሴት መጨመር ተግባራትን በሙያ የሚደግፉ በዘርፉ ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎችን በመቅጠር በየጊዜው አቅማቸውን በመገንባት እንዲጠቀሙበት ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በየደረጃው የሚደረገው የእሴት መጨመር ተግባር ዘርፉ ተለይቶ፣ በጥራት ደረጃ፣ በዋጋ ተወዳዳር እና አዋጭ መሆኑ፣ ተቀባይነት፣ ቀጣይነት እና የተጠቃሚነት ደረጃ በጥናት በማረጋገጥ በስፋት እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአጭር እና የረዥም ጊዜ እቅድ በማዘጋጀት አስፈላጊ በሆኑ የእሴት መጨመር ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ አስፈላጊው ድጋፍ እና ክትትል ይደረጋል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት የእሴት መጨመር ተግባራት የሚከናወነው የእሴት ሰንሰለትን ተከትሎ ከቀላል እስከ ከፍተኛ ዕሴት መጨመር ተግባራት ሆኖ በዋናነት በግብርና ምርቶች፣ በእንስሳት እና እንሰሳት ተዋጽኦ ምርቶች፣ በደን ውጤቶች፣ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በማዕድን ውጤቶች ግብይት እና ሌሎች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት እሴት እንዲጨመርበት ያማድረግ ተግባር ተጠናክሮ ይሰራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አምዳዊ እና ከላይ ወደታች አወቃቀር መካከል የሚደረግ የምርትና አገልግሎት አቅርቦት ቅብብሎሽ እሴት በመጨመር ላይ ያተኮረ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ዕሴት የመጨመር ተግባር በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና በፌዴሬሽኖች ድጋፍ ከአባል አርሶ/አርብቶ አደር ጀምሮ በየእርከኑ ያሉ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ደረጃ እንዲተገበር ድጋፍ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚደግፉ እና የሚከታተሉ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ አቅም ገንቢ አካላት ለእሴት መጨመር ተግባር ትኩረት በመስጠት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የእሴት መጨመር ተግባራትን ተጠናክሮ ለመስራት እንዲቻል ከሌሎች ትላልቅ የኢንዱስትሪ ፓርኮች እና አግሮ-ፕሮሰሰንግ ኢንዱስትሪ ተግባር ላይ ከተሰማሩ ተቋማት ጋር የኅብረት ሥራ ማህበራት መርህን በማይጻረር ሁኔታ ተጠቃሚነታቸውን ባረጋገጠ መልኩ በጆይንት ቬንቸር የሚሰሩበት አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለእሴት መጨመር ተግባር የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶችን በጥናት በመለየት እንዲያስፋፉ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ለእሴት መጨመር ተግባር የሚዘረጉ መሠረተ ልማቶች ጥናት በማድረግ አዋጭነታቸውን በማረጋጋጥ እንዲገነቡ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያስገነቧቸው ለእሴት መጨመር ተግባራት

የሚያስፈልጉ መሠረተ-ልማቶች የተለያዩ እና ውስብስብ ስለሆነ ጠንካራ ባለሙያ የሚያስፈልገው በመሆኑ ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች እንዲደገፍ ይደረጋል፡፡

የግብርና ምርቶችን የሚያቀነባብሩ ቀላል፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን በየደረጃው በመገንባት እሴት እንዲጨምሩ ተገቢው ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በእሴት መጨመር ተግባራት ላይ የተሰማሩ ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ምርት ዓይነት፣ መጠንና ወቅታዊነት መሰረት በማድረግ የሚያስፈላጉ የእሴት መጨመሪያ ኢንዱስትሪዎች እንዲገነቡ ይደረጋል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት ተገንብቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ የእሴት መጨማሪያ ኢንዱስትሪዎች በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለባቸውን ችግሮች በጥናት እንዲለዩ በማድረግ በማጠናከር የተሸለ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት መሠረተ ልማቶችን ለማስፋፋት የሚጠይቋቸው ኢጋዥ የሆኑ መሬት፣ መብራት፣ የገጠር መንገድ፣ ቴሌኮምኒኬሽን አውታሮችን እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ተቀናጅቶ በተቀመጠው የሕግ አግባብ ፈጣን ምላሽ እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለእሴት መጨመር ተግባራት የመሠረተ ልማቶችን ለመዘርጋት የሚያስፈልገውን ፋይናንስ ብድር/በስጦታ በወቅቱ እና በሚፈለገው መጠን ከፋይናንስ ተቋማት እና ከሌሎች ለጋሽ ድርጅቶች እንዲያገኙ የሚያስፈልጉ አሰራሮች ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ሌሎች አቅም ገንቢ አካላት ትኩረት ሰጥቶ እንዲደግፉ የሚስችል አቅጣጫ ተቀምጦ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

**ዓምድ 15፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት የሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥን ማጠናከር፡-**

## *ሀ) ነባራዊ ሁኔታ*

የኅብረት ሥራ ማህበራት አርሶ/አርብቶ አደር አባላት የግብርና ምርት እና ምርታማነት እንዲጨምር ለማድረግ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት መጠቀም አስፋለጊ ይሆናል፡፡ አባላት እነዚህን የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎቶችን በተናጠል ገዝቶ ለመጠቀም አመች እና ዋጋውም ተመጣጣኝ አይሆንም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ፍላጎት በማጥናት የሚያስፈልጉ የግብርና የሜካናይዜሽን መሣሪያዎችን በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ አባላትን ተጠቃሚ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

በአገራችን ተደራጅቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ አንደንድ ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦት እና አገልግሎትን በተመጣጣን ዋጋ በማቅረብ አባላት እና ሕብረተሰቡን

ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሜካናይዜሽን አገልግሎት ፍላጎት በርካታ ቢሆንም አብዛኞቹ ኅብረት ሥራ ማህበራት አገልግሎቱን በስፋት በመስጠት በኩል ውስንነት ይታይባቸዋል፡፡

## ሰንጠረዥ 9፡ የራያ ዋከና ኃ.የተ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበር ዩኒየን በሞዴልነት የተወሰዱ (bench mark)

1. ራያ ዋከና ኃ.የተ. የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበር ዩኒየን

**የአባላትና ካፒታል እድገት፡-** በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ አርሲ ዞን ዶዶላ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ስሆን በዩኒዩኑ የ2008 ዓ.ም መረጃ መሠረት የአባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር 73፣ የተናጠል አባላትን ቁጥር 21,373 አባወራ/እማወራዎችን ማሳደጉ እና ካፒታሉን ብር 25.3 ሚሊየን ማድረስ ችለዋል፡፡

**የሚያቀርቧቸው ዋና ዋና አገልግሎቶች፡-** የምርጥ ዘር ብዜት፣ ማበጠር፣ ማሸግ እና ለአባላት ማሰራጨት (seed cleaning) እና የኤክስቴንሽን አገልግሎት በጥራት ይሰጣል፡፡ የእንስሳት ህክምና፣ መድሀኒት እና መኖ በማቅረብ አባላትን በስፋት ያገለግላል፡፡ ዩኒየኑ በ2007 ዓ.ም በአባላት መዋጮ በብር 24,000,000 የዱቄት ፋብሪካ በመገንባት፣ በብር 6,000,000 ሁለት ኮምባይነሮችን እና በብር 2,341,000 ሁለት ገልባጭ መኪኖችን በመግዛት ለአባላት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

**አግሮ መካናይዜሽን አግልገሎት ለአባላት ተደራሽ ማደረጉ፡-** የኮምባይነር አገልግሎት ለአባላት በመስጠቱ ከአከባቢ ዋጋ የመውቂያ ወጪ በኩንታል ከብር 70 እስከ 100 ያስከፍል የነበረውን ወደ ብር 35 እስከ 50 ማውረዱ በመቻሉ አባላትንና የአካባቢው ሕብረተሰብ ከፍተኛ ተጠቃሚ ማድረግ ችለዋል፡፡ ዩኒዬኑ ባለፉት ስድስት ዓመት ወስጥ ለ12,442 አርሶ አደር አባላት የመውቅያ አገልግሎት በመስጠት195,828 ኩንታል ስንዴ ምርትን በመውቃት አባላትን ከብር 6,853,980 እስከ 9,791,400 ልዩነት ከተጨማሪ ወጪ ማዳን ችለዋል፡፡

### ለ. በኅብረት ሥራ ማህበራት ሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት ላይ ያሉ ማነቆዎች፤

### ማነቆ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት አለመስፋፋት፤

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሜካናይዜሽን አገልግሎት ትኩረት በመስጠት አቅዶ መስራት አለመቻል፡፡ የሚያስፈልጉ የሜካናይዜሽ መሣሪያዎችን በዓይነት እና በብዛት ማቅረብ አለመቻል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦት እና አገልግሎት ላይ ያላቸው ግንዛቤና አቅም ውስን መሆን፡፡ ለግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት አቅርቦት የሚሆን ገንዘብ እጥረት መኖር፡፡ ከሚመለከታቸው አካላት የሚሰጥ ድጋፍ አናሳ መሆን፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በሜካይዜሽን አቅርቦት እና አገልግሎትን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅተው አለመስራት፡፡

### ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የሚንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤

*በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጠው የግብርና ሜካናይዘሽን አቅርቦት እና አገልግሎት 50 በመቶ ይሆናል፡፡*

### መፍትሔ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎትን ማስፋፋት፤

የግብርና ሜካናይዜሽን የአርሶ/አርብቶ አደሩን ምርት እና ምርታማነት እንዲጨምር፣ የግብርና አሰራር እንዲዘምን በማድረግ የአምራቹን ጉልበት በመቆጠብ የተሸለ ምርት ጥራቱን ጠብቆ እንዲመረት የሚያግዝ በመሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለግብርና ሜካናይዜሽን መሳሪያዎች አቅርቦት እና አገልግሎት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት ላይ ትኩረት በመስጠት አቅዶ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖችና ፌዴሬሽኖች እንዲሁም አቅም ያላቸው መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለግብርና ሥራ የሚያስፈልጉ የቅድመ-ምርት እና ድህረ-ምርት ቴክኖሎጅዎች ማለትም የእርሻ ትራክቴሮች፣ ማጨጃና መውቅያ ኮምባይነሮች፣ ለመስኖ አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች (አነስተኛ የውሃ መሳቢ ሞተር፣ የውሃ ማጠጫ ወ.ዘ.ተ.)፣ የሳር መጨጃ እና ማሰሪያ፣ ቢቢኤም እና ሌሎች ተፈላጊ መሠሪያዎችን የአባላትን ፍላጎት እና መልካ ምድራዊ ተስማምነትን በማጥናት በብዛት እና በዓይነት በማቅረብ አገልግሎት በመስጠት ላይ ትኩረት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት ተግባራትን ለማከናወን የሚያስፈልጉ የፋይናንስ እጥረቶችን ለመቅረፍ በራሳቸው፣ መንግስት እና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ተቀናጅቶ ፋይናንስ እንዲያመቻቹ በትኩረት ይሰራል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖችና ፌዴሬሽኖች ለአባለት የረጅም ጊዜ ብድር በማፈላለግ የግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎትን ለአባላት በዱቤ ዋስትና ማቅረብ የሚስችል አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦት እና አገልግሎት ላይ ያላቸው ግንዛቤ ችግሮችን ለመፍታት የሚመለከታቸው አካላት በመቀናጀት ተከታታይነት ያለው ችግር ፈች ስልጠናዎችን እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ በተለይም የሚቀርቡ ቴክኖሎጅዎች አጠቃቀም እና ሲበላሹም የሚጠገኑበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በዚህ ረገድ የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ድጋፍ እና ክትትል እንዲያደርጉ የሚያስችል አሰራር ይኖራል፡፡

የግብርና ሜካናይዜሽን በባህሪው ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚሰራ ተግባር እንደመሆኑ መጠን የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር እንዲሰሩ የሚያደርግ አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎቶችን ከማቅረብ ባሻገር አስፈላጊውን ቴክኖሎጅ እንዲያፈልቁ እና በማላመድ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ አቅማቸውን የመገንባታ ተግባር ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡

## ዓምድ 16፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት ምርት እና አገልግሎት ግብይት የቅብብሎሽ ሰንሰለት ማሳጠር፤

### *ሀ. ነባራዊ ሁኔታ*

የሌሎች አገሮች ተሞክሮ እንደሚያሳየው የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት ምርት በተሻለ ዋጋ እንዲያገኝ ለማድረግ እና አባላት የሚፈልጓቸው የፍጆታ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ እንዲቻል በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ካሉ ተቋማት ጋር የግብይት ትስስር በመፍጠር በርካታ ውጤቶችን በማስመዝገብ ላይ ይገኛሉ፡፡ በአገራችን ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያደርጉት ግብይት ትስስር የተጠናከረ ባለመሆኑ በገጠር የሚገኙ አምራች አርሶ/አርብቶ አደር እና በከተማ የሚገኙ ሸማች እና የኢንዱስትሪ ምርት አምራች የሕብረተሰብ ክፍል/ተቋማት በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ ማድረግ በኩል ውስንነቶች ይታያሉ፡፡

ሆኖም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በገጠር እና ከተማ የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት በተወሰነ ደረጃ የሚያደርጓቸው የግብይት ትስስሮች አልፎ አልፎ ውጤት በማሳየት ላይ ይገኛል፡፡ በገጠር ተደራጅቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ አምራች የኅብረት ሥራ ማህበራት ከተማ ከሚገኙ ሸማች የኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ጠንካራ የግብይት ትስስር በመፍጠር በተለይም የግብርና ምርቶችን በማገበያየት ላይ ጥሩ ጅምሮች አሉ፡፡ በከተማ የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን የፍጆታ ምርቶች ፍላጎት ለማርካት በቀጥታ ከአምራች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በመተሳሰር የግብርና ምርቶችን በቀጥታ ከአምራቹ በማስመጣት ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ተጠቃሚ በማድረግ ላይ የተጀመሩ ጅምሮች አበረታች ናቸው፡፡ ሆኖም እነዚህ ጅምር ተግባራት በተለያዩ ምክንቶች እየተተገበሩ ባለመሆኑ የሚጠበቅበትን ውጤት በማስገኘት አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ ውስንነቶች ይታያሉ፡፡

የግብይት ሰንሰለቱ የተንዛዛ በመሆኑ አባላት ከምርታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያደርግ ባለመሆኑ በተሸለ እንዲያመርቱ የሚያነሳሳ አይደለም፡፡ ሸማቹ ከአምራቹ የሚቀርበው የማምረቻ ዋጋ ተጠቃሚ አልሆነም፡፡ እሴት የማይጨምሩ አከላት በማሃል ሻማቹን በመጉዳት አምራቹን የማምረት ፍላጎት እንዲቀንስ በማድረግ ያልተገባ ጥቅም የሚያገኙበት ሂደት ይታያል፡፡ ይህንን ሰንሰለት በማሳጠር ችግሩን በመፍታት ረገድ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጅምር ሥራዎችን በመስራት ላይ ቢሆኑም በተለያዩ ምክንያቶች (በሥራ ቦታ፣ በቂ ፋይናንስ፣ በመጋዘን፣ የሰው ክህሎት እና ሌሎች ችግሮች) የተነሳ የሚጠበቀውን ያህል እየሰሩ አይደለም፡፡



DRAFT

**ለ. በኅብረት ሥራ ማህበራት ምርት እና አገልግሎት ግብይት የቅብብሎሽ ሰንሰለት ማሳጠር ላይ ያሉ ማነቆዎች፤**

**ማነቆ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የምርትና አገልግሎት ግብይት ቅብብሎሽ እሴት የማይጨምርና የተንዛዛ መሆን፤**

የኅብረት ሥራ ማህበራት ስርስ በርስ የሚደርጉት የግብይት ትስስር እሴት የማይጨምር እና ወጭ የሚያበዘ መሆን፡፡ በግብይቱ ውስጥ በመሃል ያሉ ደላሎች መብዛት፡፡ የኮሚሽን ግብይት አሰራርን ተከትሎ በመሥራት አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ በኩል ችግር የሚታይ መሆኑ፡፡ ከሚመለከታቸው አካላት የሚደረጉ ድጋፎች የተጠናከረ አለመሆን፡፡ የምርት ቅብብሎሹን ለማሳጠር እና ግብይቱን ቀልጣፋ ሊያደርግ የሚችል አሰራር በሚፈለገው ደረጃ አለመኖር፡፡

የግብይት ትስስር በሚፈጽሙ ተዋንያኖች መካከል ጠንካራ ትስስር ለመፍጠር የፍላጎት፣ የቅንነትና የተአማኒነት ችግር መኖር፡፡ በተዋንያኖች መካከል ጠንካራ የግብይት ትስስር አሰራር አለመዘርጋት፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በግብይት ትስስር ላይ ያላቸው ግንዛቤና ክህሎት ውስን በመሆኑ ምክንያት የመደራደር አቅማቸው ዝቅተኛ መሆን፡፡

**ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የሚንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤**

**መፍትሄ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የምርትና አገልግሎት ግብይት ቅብብሎሽን ውጤታማ ማድረግ፡-**

የኅብረት ሥራ ማህበራት እርስ በርስ የሚያደርጉት የምርት ቅብብሎሽ እሴት የሚጨምር እና ወጭን የሚቀንስ እንዲሆን ለማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራት በየአደረጃጀት እርከናቸው በግብይት ቅብብሎሹ ውስጥ የሚኖራቸውን የሥራ ድርሻ በግልጽ በማስቀመጥ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ የአባላት ባለቤትነትና ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ የኮሚሽን ግብይት አሰራርን ተግባራዊ በማድረግ ተከታታይነት ያለው ምርት ከአባላት እንዲቀርብ በማድረግ የግብይት ልውውጡን ዘመናዊና ፈጣን እንዲሆን ይደረጋል፡፡

አምራች ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ምርቶች በቀጥታ በመረከብ ወደ ተጠቃሚ ሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት ማድረስ እንዲቻል ማነቆ የሆኑ የመጋዘን፣ የትራንስፖርት፣ የገበያ ማዕከላት እና ሌሎች የመሠረተ ልማት ችግሮችን ለመቅረፍ የሸማች እና ሁለገብ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት እነዚህን መሰረተ ልማቶችን እንዲያሟሉ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ በከተማና በገጠር የተሳለጠ ጠንካራና ውጤታማ የምርት ቅብብሎሽ ስርዓት በቀጣይነት እንዲኖር በትላልቅ ከተሞች የምርቶችን ባህሪ እና ዓይነት ያገናዘቤ የሚርት ማከማቻና የገበያ ማዕከላት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ገበያ ተኮር ምርቶችን በዘላቂነት ማምረት እንዲችሉ የሚያደርጉ ስልቶችን በመንደፍ እና በማገዝ ዘላቅነት ያላው የምርት ግብይት ቅብብሎሽ እንዲኖር ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት ቅብብሎሹን ለማሳለጥ እንዲቻል በአመራሩ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚታየውን የቅልጥፋና ችግር ለመፍታት ግንዛቤ የማሳደግ ሥራ በቀጣይነት ይሠራል፡፡ ውጤታማ የኅብረት ሥራ ግብይት ቅብብሎሽ እንዲኖር ለማድረግ ሥራውን በሙያ የሚደግፍ መዋቅር በማደራጀት የሚያስፈልገውን የሰው ሀይል በማሟላት እና አቅም በመገንባት እንዲደግፉ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚያደርጉት የግብይት ቅብብሎሽ ውስጥ በመካከላቸው አላስፈላጊ ውድድር እንዳይኖር ለማድረግ በግብይት አሰራሮች ላይ ግልጽነት በመፍጠር በሚከሰቱ ችግር ላይ የተጠያቂነት ስርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ግብይት የአባላት ምርቶችን ሲሸጡና የሚያስፈልጉ የፍጆታ ምርቶችን ሲገዙ በመሃል ግብይቱን የሚያንዛዙ አላስፈላጊ የገበያ ሰንሰለቶችን በማስወጣት የሚከሰቱ ምዝበራና ብክነት እንዳይኖር የሚያደርግ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ በመሆኑም የሚደረገው የግብይት ቅብብሎሽ ወጪን በመቀነስ፣ የተሻለ የግብይት አገልግሎት በመስጠት፣ የምርት ጥራትን በማሻሻል እና የገበያ አቅርቦት ፍለጎት መሠረት በማድረግ ለምርት ትክክለኛ የጥራት ደረጃ በመስጠት ይከናወናል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል ጠንካራ የግብይት ትስስር ለማድረግ የግብይት ተዋንያን ፍላጎት፣ የቅንነትና የተአማኒነት እንዲኖር የሚያደርግ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራት ተዘርግቶ ተግበራዊ ይደረጋል፡፡ የግብይት ትስስሩ የሁለቱንም ተዋንያን ጥቅም ሊያስከብር በሚችል ሁኔታ አዋጭነታቸው በጥናት በማረጋገጥ ይከናወናል፡፡

የአባላት የፍጆታ ምርቶች ፍላጎት በጥናት በመለየት የሚያስፈልጉ ምርቶችን ለማቅረብ የሚያስችል ወጥነት ያለው የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት፣ ምርቱን ከሚያቀርቡ ድርጅቶች ጋር በቀጥታ የግብይት ትስስር በመፍጠር ምርቶቹን በብዛት እና በዓይነት እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡ የኢንዱስትሪ ምርት አቀነባባሪዎችን ከአምራቾች ጋር በማገናኘት ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ የሚሆነውን ምርት በቀጥታ እንዲለዋወጡ በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን እንዲያረጋግጡ ይደርጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በእንሰሳት አርቢዎች እና የቁራ ኢንዱስትሪ ባለቤቶች መካከል የሚታዩ ምዛናዊ የግብይት ችግር ለመቅረፍ ዘላቂነት ያለው አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በተለይም ህገ ወጥ ግለሰቦች በኅብረት ሥራ ማህበራትና በእንስሳት ግብይት ላይ በተሰማሩ በባለሀብቶች መካከል በመግባት አርቢው እና ባለሃብቱ እንዳይገናኙ በማድረግ የሚፈጠሩ አላስፈላጊ የግብይት ችግሮች በዘላቂነት እንዲፈቱ በማድረግ ጠንካራ የግብይት ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ በኅብረት ሥራ ማህበራት እና በጨው አምራች አከሲዮኖች መካከል የሚታይ

የተንዛዛ አሰራሮችን በማስተካከል ግብይቱ የሚሳለጥበት ሂደት እንዲኖር በትኩረት ይሰራል፡፡ ኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም አባላት የሚያመርቱት ማዕድናት ቀጣይነት ያለው የግብይት ትስስር በመፍጠር በቀጥታ ለሸማቹ ሕብረተሰብ በማቅረብ የሕብረተሰቡን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያደርጉት ማንኛውም የግብይት ትስስር መሪሆዎቻቸውን በመጠበቅ የአባላት ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ እንዲሆን ለማድረግ ጠንካራ የግብይት ትስስር አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራር አካላት እና አባላት በግብይት ትስስር ላይ ያላቸው ግንዛቤ በማሳደግ የመደራደር አቅማቸው ለማጎልበት እንዲችሉ አስፋላጊው ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በሀገር ውስጥና በውጭ ያሉ የገበያ መዳረሻዎች በመለየት ምርቶቻቸውን ከሚፈልጉ አካላት ጋር የግብይት ትስስር ማድረግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

የግብይት ትስስር ሕጋዊ እና አስተማማኝ የሆነ የአቅራቢና ተረካቢ የውል አፈጻጸም እንዲኖር በማድረግ የምርት ጥራት ጉድለትን በማሻሻል፣ ገበያን አፈላልጎ የመሻጥና የመግዛት ልምዳቸው እንዲዳብር አቅማቸውን የማጎልበት ሥራ ይሠራል፡፡ ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በሚደረጉ የግብይት ትስስሮች አልፎ አልፎ በአስፈጻሚው እና ፈጻሚው አካላት ላይ የሚታየውን የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካካት እና ድርግቶችን ለማስወገድ እንዲቻል ጠንካራ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## አምድ 17፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን መሠረተ ልማት ማስፋፋት፣

### ሀ. የኅብረት ሥራ ማህበራትን መሠረተ ልማት ማስፋፋት ነባራዊ ሁኔታ፡-

በአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት አሁን ከደረሱበት የእድገት ደረጃ አንፃር ተግባሮቻቸውን ለማከናወን እንደ ጽ/ቤት፣ መጋዘን፣ የእሴት መጨመሪያ ኢንዱስትሪዎች፣ መንገድ፣ ድልድይ፣ ኤሌክትሪክ፣ የውሃ አውታሮች እና ሌሎች የመሳሰሉት መሰረተ ልማቶች ያስፈልጋቸዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ እነዚህን መሰረተ ልማቶች በራሳቸው፣ በመንግስትና በአቅም ገንቢዎች ድጋፍ በተወሰነ ደረጃ በማሟላት በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም እነዚህ መሰረተ ልማቶች የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባራት በሚፈልጉት ደረጃ እየተሟሉ አይደለም፡፡

### ለ. የኅብረት ሥራ ማህበራትን መሠረተ ልማት ለማስፋፋት ሂደት ያሉ ማነቆዎች

### ማነቆ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት መሰረተ ልማት አለመስፋፋት እና ጠንካራ የመረጃ ስርዓት አለመዘርጋት፣

የመሰረተ ልማት ለማስፋፋት በቂ ፋይናንስ እና የመሬት አቅርቦት አለመኖር፣ የመሰረተ ልማትን የሚደግፍ በቂ ፕሮጀክት አለመኖር፣ የመሰረተ ልማት የሚደግፉ አካላት ተቀናጅተው አለመስራት፣ የሚያስፈልጉ የመሰረተ ልማት አይነቶች ላይ ለመደገፍ የእውቀትና የክህሎት ውስንነት መኖር ናቸው፡፡ ጥራትና ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ለማሰባሰብና ለመተንተን የሚስችል ዘመናዊ የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋት፣ በመረጃ ላይ የሚመለከታቸው አካለት ተቀናጅተው በመስርት ትክክለኛ መረጃዎችን ተደራሽ አለማድረግ ናቸው፡፡

### ሐ. ማነቆዎችን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤

*የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚያስፈልጋቸው መሠረተ ልማቶች ውስጥ 90 በመቶ ይሟላል፡፡*

**መፍትሄ1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት መሰረተ ልማት ማስፋፋት እና ጠንካራ የመረጃ ስርዓት መዘርጋት፣**

**ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶችን መስፋፋት፡-**

ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያስፈልጉ የመሠረተ ልማት ፍላጎት ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ኮሌጆች፣ የጥናት እና ምርምር ተቋማት ጋር በመሆን በጥናት ይለያል፡፡ ለዚህም የሚሆን አሰራር እና ወጥ የሆነ የህግ ማዕቀፍ ይዘረጋል፡፡ ቀደም ብሎ ስለመሰረተ ልማት አስፈላጊነትና ጥቅም ላይ ለአባላት ግንዛቤ ይፈጠራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሚያከናውኗቸው ለኤክስፖርት መር፣ ለአግሮ ፕሮሰሲንግ እና ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ፣ ለእንሰሳት ማቆያ፣ ለሜካናይዜሽን ስራዎች የሚሆን የመስሪያ ቦታ አቅርቦትና ሌሎች የሚፈለጉ ግብዓቶች እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በኅብረት ሥራ ማህበራት፣ በመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ አቅም ገንቢዎች ድጋፍ የመሠረተ ልማትን ለማስፋፋት የሚደግፍ የተቀናጀ የልማት ፕሮጀክት ተቀርፆ ተግባራዊ ይደረጋል፤ ወጪን በመጋራት መሰረተ ልማት እንዲያስፋፉ በትኩረት ይሰራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባለት ለሰበሰቡት ምርት ደረጃ ምደባ የሚሰጡበት፣ የሚያከማቹበት መጋዘን፣ ወደ ገበያ የሚያጓጉዙበት ትራንስፖርት እና በየደረጃው ለምርት ማቀነባበሪያ የሚሆን የእሴት መጨመርያ የሚያገለግሉ ትናንሽ ኢንዳስትሪዎች በመፍጠር ወደ በማኑፋክቸሪን ኢንዱስትሪ ውስጥ እሴት ለመጨመር የሚያግዙ ሌሎች የመሰረተ ልማቶች በስፋት እንዲገነቡ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚያገኙት ትርፍ ለስራ ማስፋፊያ፣ ለመንገድ ግንባታ፣ ለመብራት፣ ለውሃ፣ ለትምህርትና ለሌሎች ስራዎች መመደብ ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ለመሰረተ ልማት ግንባታ የሚመደበው በጀት በመተዳደሪ ደንቡ ውስጥ የሚወሰን ሆኖ ከተገኘው ትርፍ ላይ ከ5-10 ከመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖችና ዩኒዬኖች ለአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚስፈልጉ መሰረተ ልማቶችን በጥናት በመለየት በእቅድ ይዘው በወጪ መጋራት አሰራር መሰረት እንዲደግፉ ይደረጋል፡፡

### በኅብረት ሥራ ማህበራት ጠንካራ የመረጃ ስርዓት መገንባት፡-

የኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ አሰራር ስርዓት በመዘርጋት ጠንካራ የመረጃ ስርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ለኅብረት ሥራ ማህበራት ቀልጠፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ የተለያየ ዓይነትና ምቹ ሶፍትዌሮችን በመገንባት እና አቅም በመፍጠር እንዲጠቀሙበት ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የገበያ መረጃ ስርዓት መገንባት በማጠናከር ለአቅራቢዎች እና ገዥዎች ወቅታዊና ተዓማኒነት ያለው ምርትና አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ ሁሉ አቀፍ የገበያ መረጃ አሰጣጥ ስርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ በዚህም መሰረት የኅብረት ሥራ ማህበራት የመረጃ ስርዓት የማደራጀት፣ የማጠናከር፣ የመተንተን፣ የማሰራጨት (የአየር ሁኔታ፣ የገበያ ዋጋ፣ የምርት፣ የማምረቻ መረጃዎችን አጠቃላይ መረጃ) ስራዎች ተጠናክረው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

አቅራቢ እና ገዥ አካላት የጋራ መድረኮች በየጊዜው በማዘጋጀት ሁሉንም ተጠቃሚ ያደረገ የዋጋ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም ጥራቱን የጠበቀ ምርት የማምረትና የአገልግሎት አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

## ዓምድ 18፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት የስራ እድል ፈጣራን ማጠናከር፣

### ሀ. ነባራዊ ሁኔታ

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለዜጎች ቋሚ እና ጊዜያዊ የሥራ እድሎችን በመፍጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበርክቱ ተቋማት ናቸው፡፡ በዓለም ላይ የህብረት ስራ ማህበራት ለ250 ሚልየን ዜጎች ቋሚ የሥራ እድል በመፍጠር ተጠቃሚ ማድረግ እንደቻሉ መረጃው ያሳያል (ICA press releases 10 oct 2014)፡፡ በአገራችን ያሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለዜጎች ቋሚ እና ጊዜያዊ የሥራ እድሎችን በመፍጠር በኩል የራሳቸውን አስተዋጽ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡ በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ መረጃ መሠረት የአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት 1,425,000 ሰዎች ቋሚ እና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ፈጥሯል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ እድል የሚፈጥሩት ለአባላት የብድር አገልግሎቶችን በማመቻቸት ሥራ እንዲፈጥሩ በማድረግ፣ የተለያዩ ግብዓቶችን በማቅረብ ተጨማሪ ተግባራትን እንዲያከናውኑ በማድረግ ሲሆን አባል ያልሆኑ ዜጎች አባላት እና የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚፈጥሩት የሥራ እድል በመቀጠር ነው፡፡ ሆኖም በአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት መፍጠር ከሚገባቸው የሥራ እድል አንጻር በርካታ ክፍተቶች የሚታይ በመሆኑ አስፈላጊውን ስትራቴጅ

በመንደፍ የተሸለ የሥራ እድል እንዲፈጥሩ ለማድረግ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት የተፈጠሩ የሥራ ዕድሎችን ሊያሳይ የሚችል መረጃ በሚፈለገው ደረጃ ተደራጅቶ አለመገኘት ችግር ይታያል፡፡

## ሰንጠረዥ 10፡ የነጻነት ፋና የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ ኅብረት ሥራ ዩኒየን በሞደልነት የተወሰዱ (bench mark)

**የነጻነት ፋና የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ. ኅብረት ሥራ ዩኒየን**

**የአባላትና ካፒታል እድገት፡-** በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጉራጌ ዞን ውስጥ የሚገኝ ስሆን በዩኒየኑ የ2008 ዓም መረጃ መሰረት አባል መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር 108 ሆኖ የተናጠል አባላት ቁጥር 15,710 እና ካፒታሉን 11,880,720 ብር ደርሷል፡፡

**የሚሰጡት የቁጠባ አይነት እና እድገት፡-** የሚሰጣቸው የፋይናንስ አገልግሎቶች የመደበኛ ቁጠባ፣ መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ፣ የልጆች ቁጠባ፣ የጊዜ ገደብ ቁጠባ፣ ብድር፣ የኢንሹራንስ፣ የተለያዩ የህትመት ውጤቶች፣ የቴክኒክ ድጋፍ፣ የትምህርትና ስልጠና፣ የክትትልና ድጋፍ አገልግሎቶች ናቸው፡፡

**የብድር አገልግሎት እና የአባላት ተሳትፎ እና አመላለስ መስፋፋት፡-** ብድር የሚሰጥባቸው የሥራ ዘርፎችን የአባላትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ለግብርና ዘርፍ ልዩ ትኩረት በማስጥ የሚሰጥ ሆኖ በተጨማርም ለቤት ግንባታ፣ ለንግድ ስራ፣ ለህክምና፣ ለትምህርት እና ለቤት ቁሳቁስ መግዣ በማውጣት በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ይሰጣል፡፡ ብድር አመላለስ በየዓመቱ በአማካይ ከ 98 በመቶ በላይ ነው፡፡

**የአባላት በተለይ የሴቶች ተጠቃሚነት ማደግ፡-** የሴቶች የአመራርነት ሚና በተመለከተ ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት መካከል 70 በመቶ፣ በመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮች ውስጥ 92 በመቶ እና ከዩኒየኑ አመራሮች መካከል 65 የሚሆኑት ሴቶች ናቸው፡፡ የቁጠባ ባህል አድጓል፡፡ የአንድ ግለሰብ በመቆጠብ አቅም ከብር 0.50 ወደ ብር 6,000 በወር ደርሶዋል፡፡ የቤተሰብ ገቢ ጨምሯል፡፡ ሴቶች ከኢኮኖሚም ጫና ተላቀዋል፡፡ በርካታ አባላት ወደ ተሻለ የስራ ዘርፍ መሻገራቸው፣ ለአብነት፡- የትራንስፖርት አገልግሎት (ሚኒባስ፣ ባጃጅ፣ አይሱዙ)፣ የሆቴል አገልግሎት፣ የተለያዩ ንግዶች ውስጥ መግባት ችለዋል፡፡

## ለ. በኅብረት ሥራ ማህበራት የስራ እድል ፈጣራ ላይ ያሉ ማነቆዎች፤

### ማነቆ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት በስራ እድል ፈጠራ ላይ ግልጽና በቂ ግንዛቤ አለመኖር፤

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ እድል በመፍጠር ላይ ድርሻ እንዳላቸው አለመገንዘብ፡፡ የሥራ እድል ሊያስፋፉ የሚችሉ ተግባራትን በሚፈለገው ደረጃ ማስፋፋት አለመቻል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚፈጠር የስራ ዕድል የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ችግር መኖር፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ እድል ፈጠራን እንዲያስፋፋ ከሚመለከታቸው አካላት የሚሰጥ ድጋፍ አናሳ መሆን እና ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር፡፡ የሚፈጥሩት የሥራ እድል በተለይም የሴቶች እና

DRAFT

ወጣቶች ተጠቃሚነትን እንዲያረጋግጥ ማድረግ አለመቻል፡፡ በሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ በየደረጃው ለሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት አስፈጻሚዎች እና ፈጻሚዎች በቂ ግንዛቤ አለመፈጠር፡፡ የሥራ ዕድል የሚፈጠርባቸው የሥራ መስኮች በጥናት አለመለየት፡፡

**ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤**

| |
|---|
| ***በሚቀጥሉት 15 ዓመታት ውስጥ በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት ለ20 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡*** |

**መፍትሄ 1፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት የስራ እድል ፈጠራ ማጠናከር፡-**

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት እና ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር አንዱ ማህበራዊ ግደታቸው መሆኑን እንዲገነዘቡ ይደረጋል፡፡ ለዜጎች ሰፊ የሥራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በማስፋፋት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰሩ ለማድረግ አስፈላጊው ድጋፍ እና ክትትል ይደረጋል፡፡

አዲስ በሚደራጁ ወይም ቀደም ሲል በተደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚፈጠሩ የተለያዩ የሥራ መስኮች በተለይም እሴት በመጨመር ተግባራት ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት ለዜጎች ሰፊ የሥራ እድል እንዲፈጥሩ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ የእሴት መጨመር ተግባራትን ስያስፋፉ ከተለያዩ ጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማት ጋር የግብይት ትስስር በመፍጠር ምርቶቻቸውን ለማሸግ፣ ምልክት ለማድረግ፣ ለማጓጓዝ እና ሌሎች ተግባራት በማከናወን ዜጎች ሰፊ የሥራ እንዷል እንዲያገኙ የሚያስችሉ አሰራሮች በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት በሚሰጡ ብድሮች ሰፋፊ የሥራ እድል በሚፈጥሩ ተግባራት ላይ ትኩረት እንዲሰጡ በማድረግ ተበዳሪው አባል ለራሱ ከሚፈጥረው የሥራ እድል በተጨማሩ በሚያስፋፋው ፕሮጀክቶች ውስጥ ሌሎች ዜጎችን በመቅጠር እንዲያሰራ የመደገፍ ተግባር በትኩረት ይሠራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴ ዘላቂነትና ውጤታማነት ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ሴቶች እና ወጣቶች ወሳኝ ሚና ስላላቸው ለእነዚህ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ልዩ ትኩረት ተደርጎ ይሠራል፡፡ ሴቶችንና ወጣቶችን በስፋት የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት እንዲሆኑ በማድረግ በቀጥታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ ባሻገር በቅጥር የሥራ ዕድል በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆንና የሥራ ባህልና ፍቅር እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሴቶችና ወጣቶች የሚመቹ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ሰፊ የሥራ እድል እንዲፈጠርላቸው ይሰራል፡፡



DRAFT

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአካል ጉዳተኞች የሚመቹ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ እና በኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲደራጁ በማድረግ በተጨማሪም የሥራ እድል የሚያገኙበት አሰራር ተነድፎ ይተገበራል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓላማቸውን ተከትለው በሚሰሩት ተግባር ሂደት ከአባላት አልፈው ለዜጎች በሚፈጥሩት የሥራ እድል በተሻለና በተደራጀ መልኩ ማስቀጠል በሚያስችል መልኩ መንግስት የድጋፍና መበረታቻ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለዜጎች የፈጠሩትን የስራ ዕድል የመረጃ አያያዝ ስርዓት በማዘመን በአግባቡ እንዲይዙ ይደረጋል፡፡

ለአባላት እና ለሕብረተሰቡ የአነስተኛ የሥራ ዕድል ፈጠራ ቢዝነሶችን የማስፋፋት አቅማቸውን በማሳደግ የተለያዩ የሥራ ፈጠራ ሥራዎችን በስፋት እንዲከናወኑ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ መስኮችን በጥናት በመለየት፣ በቂ ግንዛቤ በመፍጠር፣ የሚሰጡትን አገልግሎቶችን በማስፋፋት አዳዲስ የሥራ መስኮችን በመክፈት፣ ከሌሎች አካላት ጋር በመቀናጀት እና ተግባሮቻቸውን በተማረ የሰው ኃይል እንዲመሩ በማድረግ ለዜጎች በቂ የሥራ ዕድል እንድፈጥሩ በትኩረት ይሰራል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ ዕድል ፈጠራ አሰራር ላይ ትኩረት በመስጠት አቅደው እንዲሰሩ ከማድረግ ጎን ለጎን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የሚሰራ ይሆናል፡፡

# ክፍል ስድስት፡-የኅብረት ሥራ የመረጃ ስርዓትን የማጠናከር ስትራቴጅ

## ዓምድ 19፡- የኅብረት ሥራ የመረጃ ስርዓትን ማጠናከር

### ሀ. ነባራዊ ሁኔታ

በአገራችን የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት ከመንግስት ከተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት መካከል የአገርቱን የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ እንቅስቃሴ በመሰብሰብ፣ መተንተንና ማደራጀት ለሚመለከተው አካል ማቅረብና ማሰራጨት ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በተደራጁባቸው የሥራ መስኮች የሚያከናውኗቸው የተለያዩ የአገር ውስጥ እና የውጭ የምርት እና አገልግሎት እንዲሁም የፋይናንስ ግብይቶችን መረጃ በመጠናቀር፣ በማደራጀት እና በመተንተን ለመንግስት እና ሌሎች መረጃውን ለሚፈልጉ አካላት ዝግጁ የማድረግ ተግባር በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡

የኅብረት ሥር ማህበራት የተሰማሩባቸው የሥራ መስኮች የግብይት ተግባራት በመሆኑ እና የሚያስተዳድሩት ንብረትም የአባላት እንደመሆኑ መጠን ጠንካራ የመረጃ አያያዝ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የገበያ መረጃ ስርዓት እስካልተጠናከረ ድረስ የኅብረት ሥራ ማህበራት ግብይትን ማዘመን ፈጽሞ አይቻልም፡፡ የመረጃ አያያዛቸው ከማኑዋል ወጥቶ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ቴክኖሎጅዎችን በመዘርጋት የመረጃ አያያዝ እና ልውውጡን ቀልጣፋ ማድረግ ያስፈላጋል፡፡

በአገራችን በአሁኑ ጊዜ የመረጃ አያያዛቸውን በማዘመን ቀልጣፋ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል፡፡ የግብይት አሰራራቸውን ለማዘመን እና የተሸለ ውጤት ለማስመዝገብ የተለያዩ ጠቃሚ ቴክኖሎጅዎችን በመዘርጋት ምርቶቻቸውን ለተጠቃሚው ለማስተዋወቅ የተጀመሩ አበረታች ጅምር ሥራዎች አሉ፡፡ ሆኖም አብዛኞቹ የኅብረት ሥራ ማህበራት የመረጃ አያያዝ ዘመናዊ ባለመሆኑ እና በቴክኖሎጅ አጠቃቀም ላይ ውስንነቶች የሚታይ በመሆኑ የመረጃ አያያዛቸውን ለማጠናከር ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት ይኖርበታል፡፡

ሆኖም በአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር እና የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ እና የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ ዘመናዊ ባለመሆኑ ምክንያት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በወቅቱ፣ በጥራት፣ በሚፈለገው መጠን እና ቀጣይናት ባለው ሁኔታ አደራጅቶ፣ ተንትኖ በማቀናጀት በኩል ሰፊ ክፍተት ይታያል፡፡

## ለ. የኅብረት ሥራ የመረጃ ስርዓት ላይ ያሉ ማነቆዎች፤

### ማነቆ 1፡- የተቀናጀና ዘመናዊ የኅብረት ሥራ መረጃ ስርዓት አለመኖር፤

የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት የመረጃ አያያዝ ስርዓታቸው የተጠናከረ አለመሆን፡፡ የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ ዘመናዊ አለመሆን፡፡ የማረጃ አያያዙን ጠንካራ ለማድረግ የሚያስችል በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል አደረጃጀት በየእርከኑ በሚፈለገው ደረጃ አለመኖር፡፡ የመረጃ አያያዙን ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ክህሎት እና ፋይናንስ በሚፈለገው ደረጃ አለመኖር፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ንብረት እና የሥራ እንቅስቃሴያቸውን በአግባቡ መዝግቦ አለመያዝ ትልቁ ችግር ነው፡፡ ለመረጃ አያያዝ በቂ ትኩረት መስጠት አለመቻል እና የኅብረት ሥራ ማህበራት በንብረት አያያዝ ላይ ክፍተት በመኖሩ አልፎ አልፎ ለምዝበራ የሚጋለጥ መሆኑ፡፡ የመረጃ አያያዙ ልማዳዊ አሰራርን የተከተለ መሆን እና በቴክኖሎጅ መደጋፍ አለማቻል ችግሮች ይታያሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት መረጃዎችን በአግባቡ በማደራጀት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ አለመቻል፡፡

### ማነቆ 2፡- የተቀናጀ የኅብረት ሥራ ማህበራት የገበያ መረጃ ስርዓት አለመኖር፤

የኅብረት ሥራ ማህበራት ጠንካራ የገበያ መረጃ በመዘርጋት መስራት አለመቻል ዋናው ችግር ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የምርት፣ አገልግሎት እና ፋይናንስ ግብይት ሂደታቸውን በአግባቡ በመዘርጋ በመስራት ላይ ውስንነቶች ይታያል፡፡ የገበያ መረጃውን ቀልጣፋ እና ተደራሽ ሊያደርጉ የሚችሉ ቴክኖሎጅዎችን በመዘርጋት መጠቀም አለመቻል ችግሮች በስፋት ይታያል፡፡ የገበያ መረጃውን በሙያ ሊደግፍ የሚችል ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎችን በመቅጠር መጠቀም አለመቻል ችግሮች በስፋት ይስተዋላሉ፡፡

### ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤

*በ80 ከተሞች የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት መረጃ ማዕከላት ተቋቁሞ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡*

### *መፍትሄ 1፡- የተቀናጀና ዘመናዊ የኅብረት ሥራ መረጃ ስርዓት ማጠናከር፡-*

በየደረጃው የሚገኙትን የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት የመረጃ አያያዝ ስርዓትን ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ የተቀናጀ እና ተአማኒነት ያለው እንዲሆን አሰራሮችን ዘርግተው እንዲተገብሩ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትን አቅም እና የሚያከናውኗቸው ተግባራትን ያገናዘበ ተግባሮቻቸውን በተደራጀ መልኩ እንዲመዘግቡ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ሊያግዙ የሚችሉ አሰራሮችን በመዘርጋት እንዲጠቀሙበት ይደረጋል፡፡

የተቀናጀ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት በመዘርጋት የሚተላለፉ መረጃዎች ጥራት፣ ቀጣይነትና ተኣማንነት ያላቸው እንዲሆኑ አስፈላጊ የሆኑ ሶፊትዌሮችን እና ድህረ-ገጾችን በመዘርጋት አጠቃላይ የኅብረት ሥራ ሴክቴሩን የሥራ እንቅስቃሴ የማጠናቀር፣ የመተንተን እና የማሰራጨት ተግባራት ተጠናክሮ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚከናወኑ ተግባራት መረጃዎችን ከማደራጀት ባለፈ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚፈልጓቸው የአገር ውስጥ እና የውጭ የገበያ መረጃዎች፣ የአየር ሁኔታ እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን በጥራት እና በፍጥነት ማግኘት እንዲችሉ የሚያግዝ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ስርስ በርሳቸው እና ከሌሎች የግብይት ተዋንያኖች ጋር በመተሳሰር ለሥራቸው የሚያስፈልጉ መረጃዎች የሚለዋወጡበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በየደረጃው የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት ተቀናጅተው የአገሪቱን የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ እንቅስቃሴ መረጃ በማደራጀት ጥራት፣ ቀጣይነትና ተአማንነት ያለው የመረጃ አያያዝ ስርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡ የመረጃ አያያዙን ቀልጠፋና ዘመናዊ ለማድረግ ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችን መዘርጋት ብቻውን በቂ ስለማይሆን የተዘርጋው አሰራር ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል አደረጃጀት ከፌደራል እስከ ወረዳ በሚገኙ የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ ተቋማት ውስጥ እንዲዋቀር ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የየዕለት የገበያ መረጃዎችን ባሉበት ቦታ ሆነው እንዲያገኙ የሚያግዙ የተለያዩ ተክኖሎጅዎችን በመዘርጋት ተጠቃሚ የማድረግ ሥራ ይሰራል፡፡ የግብይት መረጃዎችን በቀላሉ እንዲያገኙ የሚያስችላቸውን የተለያዩ መረጃ ሰጭ ቴክኖሎጅዎች የኅብረት ሥራ ማህበራትን ምርቶች የሚጠቀሙ የሕብረተሰብ ክፍሎች በስፋት

በሚገኙባቸው በሁሉም ከተሞች እና እንደ አስፈላጊነቱ በጥናት በመለየት በሌሎች ቦታዎች ጭምር የመንገድ ዳር መረጃ ሰጭ ድስፐለዮች ተተክሎ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

በዘርፉ አቅም የሚገነቡ አካላት የተሸለ የመረጃ አያያዝ ተሞክሮ ያላቸው አገሮችን በመለየት ተሞክሮ እንዲለዋወጡ ማድረግ እና የለሙ ሶፍት-ዌሮችን፣ አሰራሮችን እና ሌሎች ውጠየታማ የሆኑ ቴክኖሎጅዎችን በማፈላለግ አገልግሎት እንዲሰጡ በሙያ፣ በቁሳቁስ እና በፋይናንስ የታገዘ ድጋፍ እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ የመረጃ አያያዙን ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ የፋይናንስ እና ክህሎቶች እጥረቶችን ለመቅረፍ መንግስት እና ሌሎች አቅም ገንቢ አካላት ተቀናጅቶ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

አስፈላጊነታቸው እና ጣቃሜታቸው በጥናት የተረጋገጡ የተለያዩ ዓይነት የመረጃ አያያዝ እና አጠቃቀም ስርዓቶችን በመዘርጋት እና በማጠናከር የመረጃ ቅብብሎሹም ኃላፊነት እና ተጠያቂነትን ባሰፈነ ሁኔታ ይተገበራል፡፡

**የኅብረት ሥራ ማህበራት የመረጃ ስርዓት መገንባት፡-** በአገራችን ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለመረጃ አያያዝ ትልቅ ትኩረት መስጠት የንብረት እና አጠቃላይ የመረጃ አያያዝ እና አጠቃቀም እንዲያሻሽሉ አስፈላጊ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡ የመረጃ አያያዛቸው ከማኑዋል አሰራር እንዲወጣ ለማድረግ ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችን በመዘርጋት ቀልጣፋ እና ወጥነት ያለው የመረጃ አያያዝ እንዲኖር በትኩረት ይሰራል፡፡ የመረጃ አያያዛቸውን ለማዘመን የሚያስፈልጉ ሶፊት-ዌሮችን በመገንባትና ዘመናዊ አሰራሮችን በመዘርጋት የመረጃ አያያዝ ስርዓቱን በቀጣይነት የማሻሻል ተግባር ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ የተደራጀውን መረጃ ከሚፈልጉ የተለያዩ አካላት ጋር ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የተደራጀና የተተነተነ የገበያ መረጃዎችን፣ የገበያ ዋጋ፣ የምርት መጠን፣ ዓይነት፣ ጥራት፣ የአየር ሁኔታ እና አጠቃላይ መረጃዎችን የተለያዩ የሚዲያ አይነቶችን በመጠቀም ለአባላት እና መረጃውን ለሚፈልጉ አካላት እንዲሰራጭ የሚያደርግ አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡ ለተግባራዊነቱ የሚመለከታቸው አከላት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የመረጃ አያያዝ ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት በመረጃ አያያዝ ላይ በቂ ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎችን በመቅጠር እና ከጊዜው ናባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ እንዲያሰሩ የሚያደርግ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን፣ ፌዴሬሽን እና የኅብረት ሥራ ሊግ ጠቃሚ የሆኑ የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር የገበያ መረጃዎችን በማደራጀት፣ በመተንተን ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን፣ ፌዴሬሽ እና ሊግ ቀልጣፋ የኅብረት ሥራ ማህበራት የመረጃ ቅብብሎሽ ስርዓት በመዘርጋት የተደራጀ እና የተተነተነ

ለውሳኔ የሚያግዙ መረጃዎችን በወቅቱ ለአባላት፣ ለመንግስት እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ መረጃዎችን ተደራሽ ለማድረግ የራሳቸው ድህረ-ገጾችን እና የመረጃ ማዕከላትን በመገንባት ጥቅም ላይ እንድውል ይደረጋል፡፡

***መፍትሄ 2፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የገበያ መረጃ ስርዓትን ማጠናከር፡-***

የኅብረት ሥራ ማህበራት ግብይት ውጤታማ እንዲሆን እና አባላትን የተሸለ ተጠቃሚ እንዲያደርግ ጠንካራ የገበያ መረጃ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ የምርት፣ አገልግሎት እና ፋይናንስ ግብይት የገበያ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀት እና በመተንተን ለአቅራቢዎች እና ለገዥዎች ወቅታዊና ተዓማኒነት ያለው ሁሉ አቀፍ የገበያ መረጃ አሰጣጥ ስርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ ይህንን ተግባር ለማሳካት የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ድጋፍ እና ክትትል እንዲያደርጉ የሚያደርግ አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የገበያ መረጃ አያያዝን ለማዘመን የሚያስፈልጉ ሶፊት-ዌሮችንና ድህረ-ገጾችን በመገንባት እና ሌሎች ዘመናዊ አሰራሮችን በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህን ቴክኖሎጅዎች በመጠቀም የተደራጀና የተተነተነ የገበያ መረጃዎችን፣ የገበያ ዋጋ፣ የምርት መጠን፣ ዓይነት፣ ጥራት፣ የአየር ሁኔታ እና አጠቃላይ መረጃዎችን የተለያዩ የሚዲያ አይነቶችን በመጠቀም ለተጠቃሚው እንዲሰራጭ ይደረጋል፡፡ ለተግባራዊነቱ የሚመለከታቸው አካላትም አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

የገበያ መረጃን ማደራጀት፣ መተንተንና ማሰራጨት በቂ ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎችን የሚፈልግ ተግባር በመሆኑ ሁሉም የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሮቻቸውን ሊመጥን የሚችል ባለሙያ ቀጥሮ እንዲያሰሩ የሚያደርግ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የባለሙያዎቹን አቅም በማጎልበት አስፈላጊ የሆኑ የገበያ መረጃዎችን በጥራት እና በወቅቱ ተደራሽ ለማድረግ በየጊዜው የገበያ ጥናት በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚደግፉ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ፋይናንስ ስርዓት እና ተደራሽነትን ማጠናከር

## የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት እና አስተዳደርን ማጠናከር፣

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ከፋይናንስ ግብይቱ ጋር ተያይዞ ከሚነሱ አንገብጋቢ ጉዳዮች መካከል አንዱ የፋይናንስ አካታችነትን (finacila inclution) ማሳደግ ነው፡፡ የፋይናንስ አካታችነት የሚባለው የፋይናንስ አገልግቶችን ማለትም የገንዘብ ልውውጥ፣ ክፍያ፣ ብድር እና የኢንሹራንስ አገልግሎቶችን ለሁሉም ዜጋ በሚፈልገው ቦታ እና ጊዜ ቀጣይነት እና ተአማኒነት ባለው ሁኔታ በተመጣጣኝ ዋጋ ማድረስ ማለት ነው፡፡

አገራችን የፋይናንስ አካታችነትን በማሳደግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ አሉ ከሚባሉ አገሮች ተርታ የሚትገኝ በመሆኑ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የተለያዩ አሰራሮችን በመንደፍ በመንቀሳቀስ ላይ ትገኛለች፡፡ በአገራችን የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራትን መጠናከር ፍትሃዊ እና ተመጣጣኝ እድገት እንዲኖር፣ በገጠርና በከተማ መካከል ጠንካራ የፋይናንስ ትስስር በመፍጠር በጋራ ተደጋግፎ እንዲያድጉ ለማድረግ እና ፍትሃዊ እና ጤናማ የፋይናንስ ዝውውር እንዲኖር በማድረግ የዜጎች የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ይኖርበታል፡፡

የአገራችን አርሶ/አርብቶ አደር እንዲሁም በከተማ መካካለኛ እና ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ የሕብረተሰብ ክፍል በተለያዩ ኢንቨስትሜንት ተግባራት ላይ በመሰማራት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቹን ለመቅረፍ የሚያስፈልገውን ብድር ከፋይናንስ ተቋማት ማግኘት አስቸጋር ነው፡፡ አርሶ/አርብቶ አደሩ ምርትና ምርታማነቱ እንዲጨምር የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችንና ሌሎች ቴክኖሎጅዎችን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ብድሮች በወቅቱና በሚፈልገውን መጠን እስካላገኘ ድረስ ምርቱን ማሳደግም ሆነ ኑሮውን ማሻሻል አዳጋች ይሆናል፡፡

በተጨማሪም አርሶ/አርብቶ አደሩ ላመረተው ምርት የተሸለ የገበያ ዋጋ ለማግኘት እንዲችል ምርቱን ከአባላት የሚሰበስብበት የፋይናንስ ምንጭ ሊኖረው ይገባል፡፡ በተመሳሳይ በከተማ የሚኖረው ሕብረተሰብ ክፍልም ቢሆን ያለበትን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመቅረፍ እና ሌሎች አማራጭ የኢንቨስትሜት ሥራ ማስኮች ላይ በመስራት ከድህነት ለመላቀቅ የሚያስፈልጉ ብድሮችን በወቅቱና በሚፈልገው መጠን ማግኘት አለበት፡፡ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በገጠርና በከተማ የሚኖረውን የሕብረተሰብ ክፍል ድረስ በመዝለቅ ቁጠባን በማሰበሰብና ለእንቨስትሜንት ብድር በማመቻቸት ተደራሽ በማድረግ በኩል ቁልፍ ሚና ይጨወታሉ፡፡ ይህንን ዓላማ እንዲያሳኩ በአገራችን በአሁኑ ወቅት ብዛት ያላቸው የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

ሆኖም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በነዚህ የሥራ መስኮች ላይ ለመሰማራት የሚየስፈሊጓቸው ብድር በአግባቡ የማይመቻች ከሆነ ከችግሮቻቸው ለመላቀቅ ስሉ ለመንደር አራጣ አበዳሪዎች ብዝበዛ በመጋለጥ ለባሰ ችግር መዳረጋቸው አይቀሬ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል በአገራችን ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያከናውኗቸው የምርት፣ የግብዓትና የአገልግሎት ግብይቶች የከፍያ አሰራር ያልዘመነ እና ቀርፋፋ በመሆኑ የግብይት አሰራሩን አስቸጋር አድርጎታል፡፡

ባደጉ አገሮችም ሆነ እንደ እኛ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ተሞክሮ እንደሚያሳየው በኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ሚታዩ የፋይናንስ እጥረት ለመቅረፍ፣ ለግብይቱ ዘመናዊ የክፍያ አሰራርን ለመዘርጋት እና የአገሪቱን ማይኪሮ-ኢኮኖሚን

ለማረጋጋት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት፣ የኅብረት ሥራ ባንኮች እና የኅብረት ሥራ ኢንሹራንሶችን በማደረጃትና በማጠናከር አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ችግሮቹን በመፍታት ላይ ይገኛሉ፡፡

የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዋነኛው ተግባራቸው የአባላትን የቁጠባ ባሕል በማሳደግ ቁጠባን አሟጦ ማሰባሰብ፣ የአባላትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የብድር እና የኢንሹራንስ አገልግሎቶችን መስጠት፣ የግብይት ሥራውን ለማሳለጥ ዘመናው አሠራሮችን በመዘርጋት የተለያዩ ክፍያዎችን መክፈል ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ኢኮኖሚያው እና ማህበራዊ ጠቃሜታ ያላቸው ተግባራትን ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡

## አምድ 20፡- የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትና አስተዳደር፣

### ሀ. ነባራዊ ሁኔታ

አገራችን ካላት መልካዓ-ምድራዊ አቀማመጥና የሕዝብ አሰፋፈር አኳያ ሲታይ በመደበኛ የፋይናንስ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ብቻ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ተደራሽ ማድረግ አይቻልም፡፡ የአገራችን የሕዝብ አሰፋፈር የተበታተነ እና ከ80 በመቶ በላይ በገጠር የሚኖር ከመሆኑ የተነሳ በመደበኛ ያፋይናንስ አገልግሎቶችን በቀላሉ ማዳረስ አስቸጋር ይሆናል፡፡ ይህንን ሥር የሰደደ ችግር ለመፍታት በአገራችን በተለያዩ ጊዜያቶች የተለያዩ አቅጣጫዎች ተነድፎ የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማስፋፋት ሥራ ቆይቷል፡፡

በአገራችን ተደራጅቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎቶች ውስን በመሆኑ የአባሎቻቸውን ፍላጎት በማርካት በኩል ችግሮች ይታያሉ፡፡ የአገራችን ኢኮኖሚ በተለይም የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ እየተሻሻለ በመሆኑ አርሶ/አርብቶ አደሩ የሕብረተሰብ ክፍል ገቢው ከጊዜ ወደ ጊዜ በመሻሻል ላይ ይገኛል፡፡ በከተማ የሚኖረው የሕብረተሰብ ክፍልም በተለያዩ የአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች በመደራጀት የሚያገኘው ገቢ በማሻሻል ላይ ይገኛል፡፡ ሆኖም የሕብረተሰቡ በፋይናንስ አጠቃቀም ላይ ያለው የግንዛቤ ያልዳበረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አጠቃላይ የቁጠባ መጠኑ ከሚያገኘው ገቢ ጋር ስነጻጸር ዝቅተኛ ነው፡፡ በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የተደራጁ የሕብረተሰብ ክፍሎችም ቢሆኑ በግለሰብ ደረጃም ሆነ በኅብረት ሥራ ማህበራት ደረጃ የተሰበሰበው የቁጠባ መጠን ከገቢአቸው ጋር ስነጻጸር ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በአባላት ሙሉ ፈቃደኝነት የሚቋቋሙ እና አባላት ዴሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ በበላይነት የሚመሩት የአባላትን የፋይናንስ ፍላጎት መሰረት በማድረግ የቁጠባ፣ የብድር፣ የኢንቨስትመንት፣ የምንዛሪና የኢንሹራንስ አገልግሎቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ የሚሰጥ የፋይናንስ ተቋማት ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት

የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎት ሞደሎች ከሌሎች የፋይናንስ ሞደሎች ቀላል እና ሁሉንም ዜጋ ተጠቃሚ የሚያደርግ በመሆኑ በዓለም ላይ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው የፋይናንስ አሰራር ነው፡፡

በአገራችን በተለይም ባለፉት ቅርብ ዓመታት ወድህ መንግስት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በከተማ እና በገጠር አከባቢዎች በብዛት ተደራጅቶ አገልግሎት በማስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የተደራጁበትን ዓላማ መሠረት በማድረግ የአባሎቻቸውን የፋይናንስ አገልግሎቶችን ተደራሽ ለማድረግ የቁጠባ ባህልን በሕብረተሰቡ ውስጥ በማስረጽ ቁጠባን በስፋት ማሰባሰብ፣ ለአባላት ብድር መስጠት፣ የተለያዩ ዓይነት የፍላጎት ቁጠባዎች ማሰባሰብ፣ የአነስተኛ መድን ዋስት እና ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ የፋይናንስ አገልሎቶችን ለአባሎቻቸው ከማመቻቸት ባሻገር በአገርቱ ውስጥ የሚታየውን የፋይናንስ አካታችነት ችግር ለመፍታትም በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ ለሕብረተሰቡ የተለያዩ የፋይናንስ ክህሎት ማሳደጊያ ስልጠናዎች በመስጠት የሕብረተሰቡን የፋይናንስ ክህሎት ችግር እንዲቀረፍ በማድረግ የመቆጠብ ባህላቸውን በማሳደግ፣ ሕብረተሰቡ በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ተግባራት ላይ በመሰማራት ከድህነት እንዲወጡ በማድረግ በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡

## ሰንጠረዥ 5፡ የወረርባ ኃ. የተ መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በሞደልነት የተወሰደ (bench mark)

**የአባላትና ካፒታል እድገት፡-** የኅብረት ስራ ማህበሩ በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አዶዋ ዞርያ ወረዳ ውስጥ የሚገኘው ስሆን እስከ 2008 ዓ.ም ባለው መረጃ የአባላቱ ቁጥር በድምሩ 1,420 (ሴቶች 32.54) አባላት በሥራ ክልሉ ውስጥ ከሚገኙ አባዋራና እማወራ 86.63% አባል በማድረግ እና ካፒታሉም 9,070,129 ብር በላይ ደርሷል፡፡ በማህበሩ የሚቆጥቡ ህፃናት ብዛት 259 ወንዶች እና 183 ሴቶች ድምር 442 የደረሱ ሲሆን በተጨማሪ 36 ወንዶችና ሴቶች 19 በድምሩ 55 ከህፃናቶች በማህበሩ እየቆጠቡ አሁን እድሜያቸው በመድረሱ በአባልነት ታቅፍው እየቆጠቡ ይገኛሉ፡፡

**የሚሰጡት የቁጠባ አይነት እና እድገት፡-** የኅብረት ስራ ማህበሩ መደበኛ ቁጠባ፣ መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ፣ የጊዜ ገደብ ቁጠባ፣ የልጆች ቁጠባ እና የተቋማት ቁጠባ አገልግሎት ለአባላትና ለአከባቢው የሕብረተሰብ ክፍል በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ የሚሰበሰበው ቁጠባ እያደገ በመምጣት በድምሩ ብር 9.07 ሚሊዮን በላይ ተሰብስቧል፡፡

**የብድር አገልግሎት እና የአባላት ተሳትፎ እና አመላለስ መስፋፋት፡-** የአባላትን ፍላጎት መሰረት በድምር 1,111 (በድግግሞሽ) (ሴቶች 20.88 ብር) 12,348,973 ብድር ተሰጥቷል፡፡ ብድሩ የተሰራጨበት የሥራ ማስኮች በግብርና ስራ ላይ ለተሰማሩ ብር 7,656,373 ለ በድምሩ 798 አባላት (ሴቶች 17.42)፣ ግብርና ነክ ላልሆኑ ብር 4,692,600 በድምሩ 313 አባላት (ሴቶች 29.71) ተጠቃሚ አድርገዋል፡፡ ብድር ወስደው ኑሮዋቸውን የለወጡ በርካታ የኅብረት ሥራ ማህበራቱ አባላት እንደሉ



DRAFT

| |
|---|
| መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ |

**ለ. በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትና አስተዳደር የሚታዩ ማነቆዎች**

**ማነቆ 1፡- የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ጠንካራና ወጥ አለመሆን፣**

ከመደራጀት በፊት የአዋጭነት ጥናት ተጠንቶ አዋጭነቱ ሳይረጋገጥ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ውጤታማ መሆን አለመቻል ችግር ይታያል፡፡ በተጨማሪም ውጤታማ ያልሆኑ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በአባላት ውሳኔ መሪሆዎቻቸውን በመጠበቅ እንዲወሃዱ ወይም እንዲከፈሉ በማድረግ የማጠናከር ሥራ በሚፈለገው ደረጃ እየተሰራ አይደለም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሲደራጁ አልፎ አልፎ የመንግስት፣ ባለድርሻ እና አቅም ገንቢ አካላት ጣልቃገቢነቶች ይታያል፡፡ የተቀመጠውን አሰራር በመጣስ በአንድ የሥራ ክልል ውስጥ ከአንድ በላይ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የማደራጀት ችግር ይታያል፡፡ በአባልነት የሴቶችና የወጣቶች ተሳትፎ በሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረስ ሌለው መፈታት ያለበት ችግር ነው፡፡

**ማነቆ 2፡- የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎት አለመስፋፋት፣**

ሕብረተሰቡ በፋይናንስ አገልግሎቶች ላይ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን ዋናው ማነቆ ነው፡፡ አባላት የሚቆጥቡት የነፍስ ወከፍ የቁጠባ መጠን አነስተኛ መሆን፣ የአባላትን የብድር ፍላጎት ማርካት አለመቻል፣ የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎቶች በተለይም የቁጠባና ብድር ዓይነቶች አለመስፋፋት ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡ እርስ በርሳቸው እንዲሁም ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራትና ከፋይናንስ ተቋማት ጋር የግብይት ትስስር በመፍጠር የሚሰራው ሥራ በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማ አለመሆን ችግሮች ይታያሉ፡፡ ለአባላት የሚሰጡትን የፋይናንስ አገልግሎቶች ማዘመን አለመቻል ችግሮች ይታያሉ፡፡ ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በመተሳሰር ዘመናዊ የክፍያ አሰራሮች በመንደፍ አገልግሎት በመስጠት ረገድም የሚታዩ ክፍተቶች ሰፊ ናቸው፡፡

**ማነቆ 3፡ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አስተዳደር የሚያግዙ ዘመናዊ አሰራር ስርዓቶች አለመዘርጋት፣ የክህሎትና የእውቀት ችግር መኖር፣**

የውስጥ አሰራራቸውን ያለማዘመን፣ የቁጠባ፣ የብድር፣ የወለድ አሰላል እና ሌሎች አገልግሎቶች ለመስጠት የሚያስችል ወጥነት ያላቸው የአሰራር ስርዓቶችን በማዘርጋት በኩል በርካታ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ አሰራራቸውን በዓለም አቀፍ ስታንደርዶች እየለኩ መሄድ አለመቻል ሌላው ማነቆ ነው፡፡ ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት እና ፋይናንስ ተቋማት ጋር

ተሳስሮ ለመስራት የሚያስችል የግብይት ትስስር አሰራር ዘርግቶ በመሄድ በኩል ችግሮች ይታያሉ፡፡ የፋይናንስ አገለልግሎቶች ለማስፋፋት የሚመለከታቸው አካላት የዕውቀትና የክህሎት ክፍተቶች ይታይባቸዋል፡፡

### ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የምንከታላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤

### መፍትሄ1፡- የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ጠንካራና ወጥ ማድረግ፤

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የተደራጁን ፍላጎት መሠረት በማድረግ አዋጭነታቸውን በማረጋገጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት እሴቶችንና መርሆዎቻን በመጠበቅ በጥራት እንዲደራጁ የማድረግ ተግባር ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ አዋጭነታቸው ሳይረጋገጥ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን የፋይናንስ አገልግሎትን ተደራሽ ለመድረግ አቅም መፍጠር ስለማይችሉ ጥቅም ከመስጠት ባሻጋር አባላትን ሃብት እየበሉ የሚኖሩ ተቋማት ስለምሆኑ ከጥቅማቸው ጉዳታቸው ስለምያመዝን በአገራችን የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት መስፋፋት አሉታዊ ተጽኢኖ አሰድሯል፡፡ በመሆኑም ችግሩን ለመፍታት የሚመለካታቸው አካላት ትኩረት ሰጥቶ በመቀናጀት እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አሁን ባሉበት ደረጃ ተደራሽነታቸው በሚፈለው ደረጃ ላይ ባለመድረሱ ሕብረሰተቡን በስፋት ተጠቃሚ የማድረግ ውስንነት ይታያል፡፡ አደረጃጀቱ የሕብረተሰቡን አኗኗር መሠረት በማድረግ በሚኖርበት አከባቢ ወይም በሚሰሩበት ተቋም ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ያልተደራጁ የሕብረተሰብ ክፍሎች የፋይናንስ ክህሎታቸውን በማዳበር ዕድሜያቸው ለመደራጀት የደረሱ ማንኛውም የአገርቱ ዜጎች በሙሉ በማደራጀት ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሃብት ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ በተለይም አገራችን ድህነትን የማስወገድ አቅጣጫን በመከተል በሚደራጁ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ የሴቶችን እና ወጣቶች የአባልነትም ሆነ አመራርነት ተሳትፎአቸውን በስፋት የማሳደግ ተግባር ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት እርስ በርሳቸው አላስፈላጊ ውድድር ውስጥ ገብቶ ተጠላልፈው እንዳይወድቁ ለማድረግ የመደራደር አቅማቸውን በማሳደግ የተቋቋሙለትን ዓላማ በአግባቡ እንዲያሳኩ ለማስቻል በአንድ የስራ ክልል ውስጥ አንድ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ብቻ የሚደራጅ ይሆናል፡፡ አደረጃጀቱ የአገርቱን የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ሕግን ተከትሎ መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት፣ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ይሆናል፡፡

መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በዋናነት የተደራጁን ፋላጎት መሠረት በማድረግ አዋጭነታቸው ተረጋግጦ እንደ አስፈላጊነቱ ከቀበሌ ጀምሮ ሊደራጁ ይችላሉ፡፡ የሚደራጁት በግለሰብ አባላት እንደመሆኑ መጠን ትኩረታቸው አባላት የሚፈልጉትን የፋይናንስ አገልግሎቶችን በብዛት፣ በጥራትና በወቅቱ በማቅረብ ላይ ይሆናል፡፡ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የአባላት ቁጥር ማሳደግ ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ አባላት በብዛት የማፍራት ተግባር ላይ ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩኖች የሚደራጁት በሚቀመጠው የሕግ ማእቀፍ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ሆኖ ከአባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት አቅም በላይ የሆኑ ተግባራት በማከናወን አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ይሆናል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች መሠረታዊ የሆኑ የፋይናንስ አቅርቦት ችግሮችን ለመቅረፍ የሚደራጁ እንደመሆናቸው መጠን ከመሠረታዊ ገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ውጭ ያሉ ሌሎች ዓይነት የኅብረት ሥራ ማህበራትም አባል ልሆኑ ይችላሉ፡፡

ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩንዬን የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ አቅም የሚያጎለብቱ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ አባላት ሥራ ላይ እንዲያውሉ ዕገዛ ያደርጋሉ፡፡ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩንዬን በቀጥታ በራሱ ወይም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን ወኪል በመሆን ብድርን ወይም ቁጠባ መሰረት ያደረገ ወይም ሌሎች አነስተኛ የመድን ዋስትና አገልግሎቶችን መስጠት ይችላሉ፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ፌዴሬሽኖች የሚደራጁት በሚቀመጠው የሕግ ማዕቀፍ መሠረት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩኖች ሆኖ ከአባላት አቅም በላይ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን የሚቋቋም ይሆናል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ከሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት መካከል አባላቱ ከተለያዩ ተቋማት ጋር የፋይናንስ ግብይት ትስስር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ ተግባሮቻቸውን በሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲመሩ ዕገዛ ማድረግ፣ የሂሳብ አያያዛቸው ዘመናዊ እና ወቅታዊ እንዲሆን እና ሂሳባቸው በወቅቱ ኦዲት እንዲደረግ ድጋፍ ማድረግ፡፡ በተጨማሪም ፌደሬሽኑ በራሱ ወይም የሌሎች የመድን ዋስትና ድርጅቶች ወኪል በመሆን አነስተኛ የብድር፣ የቁጠባ፤ የእንስሳት፣ የሰብል እና ሌሎች የመድን ዋስትና አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡ አባላትን በአገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ደረጃ በመወከል ለአባላት ጥቅም ሊያስገኙ የሚችሉ የሥራ ግንኙነቶችን ያደርጋል፡፡

ከገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ውጭ የሆኑ ማንኛው የኅብረት ሥራ ማህበራት ከገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ለመቀናጀት እና ለመመጋገብ አንዱ ከሌላው ጋር በመተሳሰር ፋይናንሳቸውን እንዲያንቀሳቅሱ የሚያስችል አሠራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

አዳዲስ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን ከማደራጀት ጎን ለጎን ቀደም ሲል ተደራጅተው የነበሩት የኅብረት ሥራ ማህበራት ተጠናክረው የፋይናንስ አገልግሎት እንዲሰጡ ችግሮቻቸውን በመለየት እንዲጠናከሩ ለማድረግ በአባላቱ ሙሉ ፋቃደኝነት እንዲከፈሉ ወይም እንዲዋሃዱ ይደረጋል፡፡ ሆኖም የመከፈልም ሆነ የመዋሃድ ውሳኔ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በነፃነት የመወሰን መብትን ሳይጋፋ፤ በድጋፍ ስም የሚደረግ አላስፈላጊ ተጽዕኖ በማይኖር መልኩ እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

### መፍትሄ 2፡- የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎት ማስፋፋት፤

የአገራችን ኢኮኖሚ በተለይም የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ እየተሻሻለ በመሆኑ አርሶ/አርብቶ አደሩ የሕብረተሰብ ክፍል ገቢው ከጊዜ ወደ ጊዜ በመሻሻል ላይ ይገኛል፡፡ በከተማ የሚኖረው የሕብረተሰብ ክፍልም በተለያዩ የአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች በመደራጀት የሚያገኘው ገቢ በማሻሻል ላይ ይገኛል፡፡ ሆኖም የሕብረተሰቡ በፋይናንስ አጠቃቀም ላይ ያለው የግንዛቤ ያልዳበረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አጠቃላይ የቁጠባ መጠኑ ከሚያገኘው ገቢ ጋር ስነጻጸር ዝቅተኛ ነው፡፡

ይህንን ችግር ለመቅረፍ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባሎቻቸውን እና የሕብረተሰቡን የፋይናንስ ክህሎት ለማሳደግ የተለያዩ የፋይናንስ ክህሎት ማሻሻያ ትምህርቶች በስፋት እንዲሰጡ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን መደበኛ ቁጠባ መጠን ለማሳደግ የተለያዩ አሰራሮችን በመንደፍ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከማድረግ ጎን ለጎን የሚመለከታቸው አካላትም ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከመደበኛ ቁጠባ በተጨማሪ አዋጭ የሆኑ የተለያዩ መደበኛ ያልሆኑ የቁጠባ ዓይነቶች ማለትም የግብዓት መግዣ ቁጠባ፣ የማህበረሰብ የጋራ ቁጠባ፣ ወለድ አልባ ቁጠባ፣ የጊዜ ገደብ ቁጠባ፣ የልጆች ቁጠባ፣ የህክምና ቁጠባ፣ የበዓላት ቁጠባ፣ የትምህርት ቤት ቁጠባ፣ የቀብር ማስፈጸሚያ ቁጠባ፣ የአደጋ ጊዜ ቁጠባ /Emergency/Hardship saving/፣ የቁርጠኝነት ቁጠባ እና ሌሎች አማራጭ የቁጠባ ዓይነቶችን በማጥናት የማስፋፋት አቅጣጫን እንዲከተሉ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የአካባቢውን ህብረተሰብ የፋይናንስ አገልግሎት ችግር ለመቅረፍ መደበኛ ያልሆኑ ቁጠባዎችን ከእምነት ተቋማት፣ ከዕድሮች፣ ከአርሶ አደር ማሰልጠኛ፣ ጤና ጣቢያዎች እና ከሌሎች ተቋማት ሊሰበስቡ ወይም በአደራ ሊያስቀምጡ ይችላሉ፡፡

አርሶ/አርብቶ አደር ማህበረሰብ አከባቢ የሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚያገኙት ገቢ ወቅታዊ ስለሚሆን ምርት በማይገኝበት ወቅት መደበኛ ቁጠባዎችን አልፍ አልፎ የማቆራረጥ ችግሮች ይታያል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የፍቃደኝነት ቁጠባን በማስፋፋት አባላት ትርፍ ምርት በሚያገኙበት ወቅት ገንዘባቸውን በፍቃደኝነት የቁጠባ አገልግሎት እንዲቆጥቡ በማድረግ ችግር በሚኖርበት ወቅት ከዚያ አውጥቶ መደበኛ ቁጠባቸውን የሚቆጥቡበት

አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የአርሶ/አርብቶ አደሩን ማሕበረሰብ ፍላጎት በማጥናት የዓይነት ቁጠባ አገልግሎት የሚስፋፋበት አሰራር በማስቀመጥ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አርሶ/አርብቶ አደሩ እና የከተማውን ነዋር የሕብረተሰብ ክፍሎችን የፋይናንስ እጥረት በመቅረፍ፣ ለግብይቱ ዘመናዊ የክፍያ አሰራርን በመዘርጋት እና የአገሪቱን ማክሮ-ኢኮኖሚ በማረጋጋት ወሰኝ ተቋማት ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት እስካልተጠናከሩ ድረስ ሕብረተሰቡ የብድር ፍላጎቱን ለማሟላት ለመንደር ሕገወጥ አራጣ አበዳሪዎች በመጋለጥ ለባሰ የኢኮኖሚ ቀውስ መዳረጉ የማይቀር ነው፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት እየሰጡ ያለው የብድር አገልግሎት ዓይነቶች ውስን በመሆናቸው ዓይነቶቹን በማስፋፋት አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ በተለይም የሴቶች እና የወጣቶችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ የብድር ዓይነቶች ላይ በማተኮር አገልግሎቱን የማስፋፋት ሥራ ይሰራል፡፡

በገጠር የግብርና ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ለአርሶ/አርብቶ አደሩ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች መግዣ የሚሆነውን ፋይናንስ በማመቻቸት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ የግብርና ምርትና ምርታማነት ከጨመረ አምራቹ ከምርቱ ተጠቃሚ እንዲሆንና በተሸለ ለማምረት እንዲነሳሳ እና ግብይቱ እንዲሳለጥ የፋይናንስ ችግሩ እንዲቀረፍ የሚፈለገው ፋይናንስ በወቅቱና መጠን በማመቻቸት ረገድ ሚናቸውን እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ የግብርና ምርት በዋጋ ተወዳዳር ሆኖ አምራቹ ከምርቱ የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆንና በአገር ኢኮኖሚ ግንባታ ላይ የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ለማድረግ በግብርና ምርት ላይ እሴት ለመጨመር ፋይናንስ የማመቻቸት ተግባር ውስጥ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ያላቸው ድርሻ ትልቅ በመሆኑ በአግባቡ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

በከተማ የሚኖረው የሕብረተሰብ ክፍልም የመኖሪያ ቤት እጥረት፣ የተለያዩ የእንቨስትሜን ዘርፎች ውስጥ ተሳትፎ ድህነትን ለማሸነፍ ፋይናንስ ማግኘት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የአባላትን ፍላጎቶችን መሠረት በማረድግ ለቤት ግንባታ፣ ለቁሳቁስ ማሟያ፣ ለተሽከርካሪ ግዥ እና ሌሎች ንግዶች የሚሆነውን ብድር ለማመቻቸት እንዲቻል የብድር አገልግሎቶችን የማስፋፋት ጉዳይ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ለሚሰጡት ብድር አስተማማኛ ዋስትና ይጠይቃሉ፡፡ ለዚህም የግለሰብ አባላትን ዋስ ከማድረግ በተጨማሪ ጥናትን መሠረት በማድረግ ብድር ጠያቅው አባል በሕግ የተመዘገበ እና ሕግዊ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ለብድር ዋስት የሚያቀርብበት አሰራር ተዘርግቶ ተግበራዊ ይደረጋል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በአሁኑ ጊዜ ለአባላት የሰጡትን ብድር በማስመለስ በኩል ያላቸው ተሞክሮ በጣም ጥሩ የሚባል ነው፡፡ በተጨማሪም የአገራችን አርሶ/አርብቶ አደር እና የከተማው ኅብረተሰብ ገንዘብ

ተበድሮ የመመለስ የቀድሞ ባህሉ እንዳይበረዝ ጠንካራ አሰራር በመንደፍ ብድር የመመለስ ታሪካቸው እንዳይበላሽ ትኩረት ተደረጎ ይሰራል፡፡ ለዚህም የሚያግዝ ዘመናዊ የብድር አስተዳደር አሰራር በማስረጽና ክህሎታቸውን በላቀ ደረጃ እንዲያድግ የሚረዳ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጠባን ከማሰባሰብና ብድርን ከመስጠት ባሻገር የተቋቋሙበትን ዓላማ እና የሕግ ማዕቀፍን ጠብቆ አገልግሎታቸውን በማስፋፋት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም በራሳቸው ወይም አባላትን በመወከል ብድርን እና ቁጠባን መሰረት ያደረገ ወይም ሌሎች አነስተኛ የመድን ዋስትና አገልግሎቶችን በራሳቸው ወይም ከሌሎች ኢንሹራንስ ሰጭ ተቋማት ጋር በመቀናጀት አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አገልግሎቶችን በራሳቸው አቅም የማስፋፋት ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ዘርፉን በተሸለ ለማጠናከር መንግስት፣ ባለድርሻ አካላት፣ አቅም ገንቢዎች እና ዓለም አቀፍ የልማት አጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር የመነሻ ካፒታል፣ ብድር እና ተዘዋዋሪ ፈንድ እንዲመቻች ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የአባላትን ችግር የሚፈቱና የፋይናንስ አቅም የሚያጎለብቱ የተለያዩ ፕሮጅክቶችን በመንደፍ ተጨማሪ ፋይናንስ በማግኘት አባላት ወደ ተሻለ ኢንቨስትሜንት ውስጥ እንዲገቡ የሚያደርጉ አሰራሮች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

**መፍትሄ 3፡- የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አስተዳደር የሚያግዙ ዘመናዊ አሰራር ስርዓት ለመዘርጋት፣ የክህሎትና የእውቀት ችግርን መፍታት፤**

በአገራችን ተደራጅቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ካለባቸው መሠረታዊ ውስንነቶች መካከል አንዱ የሚሰጡትን የፋይናንስ አገልግሎቶች የሚመጥን የአሰራር ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ አለመዘርጋት እና የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ነው፡፡ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እንደመሆናቸው መጠን አሰራራቸው ጠንካራ መሆን አለበት፡፡ የተለያዩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለማስፋፋት ከሚዘርጉት የአሰራር ስርዓት በተጨማሪ የውስጥ አሰራራቸውን በማጠናከር የመረጃ አያያዛቸውን በማዘመን አባላትን ከማርካትም አልፎ ሌሎች አባል ያልሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን አባል እንዲሆኑ ለመሳብ ስለሚያግዝ በትኩረት ይሰራል፡፡

በመሆኑም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ አሰራራቸውን ለማዘመን ከልማዳዊ አሰራር ወጥቶ በቴክኖሎጅ በመደገፍ ከቀላል እስከ ትላልቅ ሶፈትወሮችና ሰርቨሮችን በመገንባት ወይም በመዘርጋት የሚጠቀሙበት አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ አሰራር፣ የተሟላ የአባላትን መረጃ፣ የቁጠባ መጠን፣ የብድር አሰጣጥና አመላለስ፣ የወለድ አሰላል እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን መዝግቦ እንዲይዙ የሚያግዝ ዘመናዊ አሰራር በመዘርጋት እንዲጠቀሙ ይደረጋል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎት ተወዳዳር እንዲሆን ለማስቻል የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እና አጠቃላይ ደህንነታቸውን እያረጋገጡ ለመሄድ እንዲያስችላቸው ዘመናዊ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ አፈፃፀም መለኪያዎችን በአግባቡ በመዘርጋት አፈፃፀማቸውን በየጊዜው እየለኩ የማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ እንዲሄዱ ይደረጋል፡፡

ቁጠባን በስፋት ከአባላት ለማሰባሰብ እና የብድር አገልግሎቶችን ተደራሽ ለማድረግ የአባላትን ፍላጎት በማጥናት የሚያስፈልጉ አሰራሮች ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

የአባላትን ችግር መሠረት በማድረግ የአደጋ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ የተለያዩ የአነስተኛ መድህን ዋስትና አገልግሎቶችን ማስፋፋት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት አባላትን ተጠቃሚ የማድረግ ተግባር በስፋት ይሰራል፡፡

በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ በአሁኑ ወቅት አብዛኞቹ የኅብረት ሥራ ማህበራት ያላቸው ገንዘብ በሥራ ላይ ያለ በመሆኑ የማይንቀሳቀስ የተከማቸ ገንዘብ አይታይም፡፡ ሆኖም አልፎ አልፎ በአንዳንድ ኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ የሚታየውን የማይንቀሳቀስ ገንዘብ ሥራ ውስጥ ለማስገባት እና ለወደፊቱ የኅብረት ሥራ ማህበራቱ ተጠናክሮ ወደ ሥራ በሚገቡበት ወቅት ሊፈጠር የሚችለውን የማይንቀሳቀስ ገንዘብ ሥራ ላይ ማዋል እንዲቻል ጠንካራ የፋይናንስ ግብይት ትስስር አሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በተለይም በከተማ እና ገጠር የሚገኙ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት መርሆ በማይጻረር መልኩ ሁለቱንም ተጠቃሚ የሚያደርግ የፋይናንስ ግብይት ትስስር እንዲኖር ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት እርስ በራሳቸው ከሚያደርጉት የግብይት ትስስር በተጨማሪ ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት፣ ከፋይናንስ ተቋማት እና ሌሎች ሕጋዊ ተቋማት ጋር የፋይናንስ ግብይት ትስስር ፈጥሮ የሚሰሩበት አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

በአገራች የኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ከሚታዩ የአሰራር ችግሮች መካከል የክፍያ ስርዓታቸው ቀልጣፋ እና ዘመናዊ አለመሆን አንዱ ነው፡፡ በምርት ወይም በአገልግሎት ተግባር ላይ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡት አገልግሎቶ የክፍያ አሰራሩ ዘመናዊ ባለመሆኑ ለተለያዩ ምዝበራ የተጋለጠ ነው፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዘመናዊ የክፍያ አሰራሮችን በመዘርጋት ከሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በመቀናጀት የሚሰሩበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡



DRAFT

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዘመናዊ አሰራሮችን መገንባት ብቻውን ግብ አይሆንም፡፡ በመሆኑም የሚሰጡትን የፋይናንስ አገልግሎት በሙያ ሊደግፉ የሚችሉ በቂ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎች በመቅጠር አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ወሳኝ በመሆኑ ማንኛው የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የሚሰጠው የፋይናንስ አገልግሎት መሠረት ያደረገ ብቁ ባለሙያ ቀጥሮ እንዲያሰሩ ይደረጋል፡፡

## ዓምድ 21፦- ኅብረት ሥራ ባንክ እና ኢንሹራንስ አደረጃጀትና አስተዳደር ኅብረት ሥራ ባንክ አደረጃጀትና አስተዳደር፦-

### ሀ. ነባራዊ ሁኔታ

የዓለም ተሞክሮ እንደሚያሳየው የኅብረት ሥራ ባንኮች የሚደራጁት ከአገር አገር የተወሰኑ ልዩነቶች ቢኖረውም የኅብረት ሥራ አደረጃጃትን ተከትሎ ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ባንኮች በዋናነት የሚደራጁት የአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት እና አባላትን የፋይናንስ አገልግሎቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ፣ የሚታየውን የፋይናንስ እጥረት ችግር ፈጣን ምላሽ ለመስጠት፣ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ግብይት ዘመናዊ የክፍያ አሰራርን ለመዘርጋት እና የአገሪቱን ማክሮ-ኢኮኖሚ ለማረጋጋት ነው፡፡ በብዙ አገሮች ውስጥ የኅብረት ሥራ ባንኮች ከአባላት ውጭ ለሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች የፋይናንስ አገልግሎታቸውን በመስጠት ተጠቃሚ የሚያደርጉበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

ለአብነት በዓለም ላይ በአጠቃላይ ከሚሰጠው የፋይናንስ አገልግሎቶች ውስጥ የኅብረት ሥራ ባንኮች የተደራሽነት ሽፋን 8.3 በመቶ ደርሷል፡፡ የተሸለ የኅብረት ሥራ ባንክ አገልግሎት ተደራሽነት ሽፋን ካላቸው አገሮች መካከል ፍላንድ 35 ከመቶ፣ ሰሜን አሜሪካ 48.3 ከመቶ፣ አሜሪካ 8.3 ከመቶ ሲሆን ከአፍሪካ አህጉር ኬንያ 21.3 ከመቶ፣ ሴኔጋል 23 ከመቶ፣ ሩዋንዳ 22.8 ከመቶ፣ ቤኒን 22.6 ከመቶ፣ ቶጎ 28.2 ከመቶ እንደደረሰ መረጃዎች ያሳያሉ (WOCCU 2015 Statistical Report)፡፡ ይህ መረጃ የሚያሳየው የኅብረት ሥራ ባንኮች የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎት ሞደል ባደጉ አገሮችም ሆነ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆ ነው፡፡

የዓለም ተሞክሮ እንደምያሳየው የኅብረት ሥራ ባንኮች አደረጃጀት የኅብረት ሥራ መርሆ መሠረት ሆኖ የፋይናንስ አስተዳደሩን ለመቆጣጠር የሁለትዮሽ የምዝገባ ስርዓት ተከትሎ ይመዘገባል፡፡ አደረጃጀቱ እና የሥራ አመራሩን በኅብረት ሥራ መርሆ መሠረት መሆኑን ለመከታተል በኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ሲሆን የፋይናንስ ስርዓቱን ለመቆጣጠር መንግስት በሚወክለው አካል ይሆናል፡፡ በአገራችን የኅብረት ሥራ ባንኮችን ለማደራጀት የተቀመጠ የሕግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ እስከአሁን የኅብረት ሥራ መርሆን ተከትሎ አልተደራጀም፡፡ በዋናነት በርካታ የኅብረት ሥራ ማህበራትን እና

የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላትን ይዞ የተደራጁ (የኦሮሚያ የኅብረት ሥራ ባንክ፣ አዲስ እንተርናሽናል ባንክ) በመደበኛ የንግድ ባንክ ሕግ ተመዝግቦ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

የገጠር ትራንስፎርሜሽ ለማምጣት ፋይናንስ አንዱ እና ዋነኛው መሳሪያ ነው፡፡ ስለሆነም የገጠሩን አርሶ/አርብቶ አደሩን የከተማውን አነስተኛ እና መካከለኛ የሕብረተሰብ ክፍል ኑሮ መለወጥ አይቻልም፡፡ አርሶ/አርብቶ አደሩ እና የከተማው አነስተኛ እና መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘው የሕብረተሰብ ክፍል ከመደበኛ ባንኮች የሚጠይቁትን መስፈርት (ዋስትና) ማቅረብ ስለማይችሉ የሚፈልጉትን ብድር ማግኘት አይችሉም፡፡ የኅብረት ሥራ ባንኮች በተለይም በመደበኛ የፋይናንስ አገልግሎቶች ተደራሽ ሊሆኑ የማይችሉ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ በማድረግ በኩል ከፋተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ተቋማት መሆናቸውን ነው፡፡

የኅብረት ሥራ ባንክ የሚከተለው የፋይናንስ አገልግሎት አሰራር የመደበኛው የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ላልሆኑት አርሶ/አርብቶ አደሮች እና ሌሎች በመካካለኛ እና ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተመቻ በመሆኑ የተሸለ ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል፡፡ የአባላትን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች አካላትም እንደ አንድ የፋይናንስ አገልግሎት መስጫ ተቋም ሆኖ ስለሚያገለግል በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ አማራጭ እና ተመራጭ የፋይናንስ አገልግሎት ሰጭ ተቋም በመሆን ላይ ይገኛል፡፡

የኅብረት ሥራ ባንኮች አገልግሎቶቻቸውን የሚሰጡት ከገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ተጣምሮ ለአባላት ተደራሽ በመሆን አገልግሎታቸውን በቀላሉ መስጠት የሚችሉ ተቋማት በመሆናቸው የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጅን ለማሳካት ተመራጭ ናቸው፡፡ በመሆኑም በኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ የኅብረት ሥራ ባንክ የሚደራጅበት አሰራር በመፍጠር የሕብረተሰቡን የፋይናንስ ችግሮች እንዲቀርፉ እና ለአገራችን የኢኮኖሚ ግንባታ የራሳቸውን ድርሻ እንዲወጡ በማድረግ የፋይናንስ አካታችነትን ለማሳደግ በምደረገው ርብርብ ውስጥ ሚናቸውን እንዲወጡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በግብርና ተግባር ላይ የተደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባሎቻቸው የሚሰበስቡት ምርት እና በሚያቀርቡላቸው የፍጆታ ምርቶች እና አገልግሎቶች ላይ ለሚደርስ ማንኛውም የአደጋ ስጋት ለመቀነስ የእሹራንስ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ በተለይም ምርት በመጓጓዝ ላይ፣ በመጋዘን ውስጥ፣ እሴት በሚጨመርባቸው ቦታዎች፣ በተሰበሰበበት ቦታ፣ በማሳ ላይ እና በተለያዩ ቦታዎች ለተፈጥሮ እና ለሰው ሰራሽ የአደጋ ስጋቶች ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡ በአገልግሎት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራትም በተመሳሳይ ለአባላት በሚሰጡት አገልግሎት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ባርካታ የአደጋ ስጋቶች ይኖራሉ፡፡

እነዚህን የአደጋ ስጋቶች ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ባይቻልም ለመቀነስ የሚቻልባቸው የተለያዩ አሰራሮች አሉ፡፡ የሌሎች አገሮች ተሞክሮ እንደሚያሳየው የኅብረት ሥራ ማህበራት ባላቸው ልዩ ባህሪ የራሳቸውን የመድን ዋስትና ተቋም በማቋቋም የአደጋ ስጋቶችን የሚቀንሱበት አሰራር ይታያል፡፡ የኅብረት ሥራ ኢንሹራንስ  አንድ የኅብረት ሥራ አባል ወይም ኅብረት ሥራ ማህበራት በንብረቱ ወይም በህይወቱ ላይ ሊያጋጥም የሚችል ድንገተኛና ያልታሰበን አደጋ ወይም ጉዳትን ወደ ሌላ አካል የሚያስተላልፍበት ዘዴ ነው፡፡ ይህ አሰራር በዓለም ላይ በስፋት ተስፋፍቶ በኅብረት ሥራ ማህበራት እና አባላት ላይ ሊደርስ የሚችለውን የአደጋ ስጋት በመቀነስ ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ በኩል ትልቅ ድርሻ በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በአገራችን የኅብረት ሥራ መድን ዋስትና ለማቋቋም የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ ምክንያት ተቋቁሞ አገልግሎት መስጠት አልቻለም፡፡ እያደገ የማጠው የኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር እና እየተስፋፋ ባለው የአገልግሎት ዘርፍ ሊክ እየጨመረ የሚሄደውን የአደጋ ስጋት ለመቀነስ  የኅብረት ሥራ ኢንሹራንስ ተቋማትን በማቋቋም አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

በአገራችን ያሉ የኢንሹራንስ ተቋማት በገጠር ያለውን የአደጋ ስጋት ዓይነቶችን ለይቶ በስፋት ተገቢውን አገልግሎት በመስጠት በኩል በርካታ ውስንነቶች ይታያሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት የተወሰኑ ኢንሹራንስ ተቋማት በአርሶ/አርብቶ አደሩ በተመረጡ የእርሻ እና የእንስሳት ምርቶች ላይ ሊደርስ የሚችለውን የአደጋ ስጋት ለመቀነስ እንዲቻል የኢንሹራንሽ አገልግሎት ሽፋን እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

### ለ. በኅብረት ሥራ ባንክ እና ኢንሹራንስ አደረጃጀትና አስተዳደር ላያ ያሉ ማነቆዎች

### ማነቆ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ ችግር ሊፈታ የሚችል የኅብረት ሥራ ባንክ አለመደራጀት

የኅብረት ሥራ ባንክ ባለመደራጀቱ ምክንያት በተለይም የኅብረት ሥራ ማህበራት እና አባላት ትላልቅ ብድሮችን አግኝተው የተሸለ ኢንቨስትሜንት ውስጥ ሚፈለገው ደረጃ መግባት አልቻሉም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ የግብርና ምርቶች ላይ እሴት ለማጨመር የሚያስችሉ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎችን፣ የገበያ ማዕካላትን ለመገንባት፣ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ለማስፋፋት እንድሁም በከተሞች የሪል ስቴት ግንባታ እና ሌሎች ትላልቅ ተግባራትን ለማከናወን ትላልቅ ብድሮች የሚያስፈልግ ቢሆንም አማራጭ ባንክ ባለመኖሩ ችግሩን መቅረፍ አልተቻለም፡፡ በሌላ በኩል የኅብረት ሥራ ባንክ ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት በፋይናንስ አገልግሎት ላይ የቴክንክ ድጋፍ በመስጠት የተሸለ አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደግፍ የሚችል ቢሆንም ባለመደራጀቱ አገልግሎቱን ማግኘት አልቻሉም፡፡ በገንዘብ ቁጠባና

ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት የሚሰበሰቡ ቁጠባዎችን በቅርበት ሊያስተዳድር የሚችል የኅብረት ሥራ ባንክ አለመኖርም እንደ ችግር የሚታይ ሆኗል፡፡

በአገራችን የኅብረት ሥራ ባንክ ለማቋቋም ከሕብረተሰቡ ሰፊ ፍላጎት ቢኖርም የሚፈቅድ የሕግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ ምክንያት ሊቋቋም አልቻለም፡፡ የኅብረት ሥራ ባንክ የሚሰጣቸው የፋይናንስ አገልግሎቶችም በአሰራር ልተቀመጡ በመሆኑ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋር ሆኗል፡፡

**ማነቆ 2፡- የኅብረት ሥራ ኢንሹራንስ አለመደራጀት**

አርሶ/አርብቶ አደር እና በከተማ በመካከለኛ እና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚኖረው የሕብረተሰብ ክፍል ተደራሽ የሚያደርግ የኢንሹራንስ ተቋም አለመኖር፡፡ የኅብረት ሥራ ኢንሹራንስ ተደራጅቶ ባለመኖሩ ምክንያት በተለይም የኅብረት ሥራ ማህበራት እና አባላት በሚያከናውኑት ተግባራት ላይ ለሚደርስ የአደጋ ስጋቶችን መቀነስ የሚያስች አሰራር መፍጠር አልተቻለም፡፡ የኅብረት ሥራ ኢንሹራንስ ለማቋቋም ከሕብረተሰቡ ሰፊ ፍላጎት ቢኖርም የሚፈቅድ የሕግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ ምክንያት ሊቋቋም አልቻለም፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት የሚሰበስቡት ምርት በመጓጓዝ ላይ፣ በመጋዘን ውስጥ፣ እሴት በሚጨመርባቸው ቦታዎች፣ በተሰበሰበበት ቦታ፣ በማሣ ላይ እና በተለያዩ ቦታዎች ላይሊሚደርሰው የተፈጥሮ እና ሰውሰራሽ አደጋ ሊቀንስ የሚችል ልዩ በሕሪያቸውን መሰረት ያደረገ የኅብረት ሥራ ኢንሹራንስ አልተቋቋመም፡፡ በአገልግሎት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራትም በተመሳሳይ ለአባላት በሚሰጡት አገልግሎት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ባርካታ የአደጋ ስጋቶችን መቀነስ እንዲቻል የኅብረት ሥራ ኢንሹራንስ አለመኖር አንዱ ማነቆ ሆኗል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች ኢንሹራንስ ተቋማት ጋር ተቀናጅተው እንዲሰሩ የሚያደርግ አሰራር አልተዘረጋም፡፡

**ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የምንከታላቸው የመፍትሄ አቅጣቻዎች፡-**

**መፍትሄ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ ችግር ሊፈታ የሚችል የኅብረት ሥራ ባንክ ማደራጀት፣**

በአገራችን ተደራጅቶ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት እና ግለሰብ አባላት በተለያዩ የኢንቨስትሜንት ተግባራት ላይ ለመሰማራት የሚጠይቁት ፋይናንስ መጠኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ በማጨመር ላይ ይገኛል፡፡ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባሎቻቸው የሚያሰባስቡት ቁጠባ አባላት ለሚያቀርቡት አነስተኛ የብድር አገልግሎት

ከመዋል አልፎ ለትላልቅ ኢንቨስትሜንት ልውል የማይችል በመሆኑ ከአባላት ለሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎችን በሚፈለገው ሊክ መልስ መስጠት አልቻለም፡፡

በአገራችን የኅብረት ሥራ ባንክ ለማቋቋም ከሕብረተሰቡ ሰፊ ፍላጎቶች ቢኖርም ባንኩን ለማቋቋም የሚፈቅድ የሕግ ማዕቀፍ ባለመኖሩና ግልጽ የሆነ አሰራር ባለመዘርጋቱ ምክንያት ሊቋቋም አልቻለም፡፡ ለዚህም የአነስተኛውን አርሶ/አርብቶ አደር ልማት ሊደግፍ የሚችል የኅብረት ሥራ ባንክ ለማቋቋም የሚያስችለውን የሕግ ማዕቀፍ እና የአሰራር አቅጣቻ በማስቀመጥ ባንኩን የማቋቋም ተግባር ይሰራል፡፡

በዚህ መሠረት የኅብረት ሥራ ማህበራትን መርሆ ተከትሎ ለሁሉም የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጥ የኅብረት ሥራ ባንክ ይደረጃል፡፡ የኅብረት ሥራ ባንክን የማደራጀት ተግባር የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት ሚና ሆኖ ቁጥጥሩን በተመለከተ መንግስት በሚያስቀምጠው የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ በሚወሰነው መሠረት ኃላፊነት ለሚሰጠው ተቋም አማካኝነት የሚከናወን ይሆናል፡፡ የኅብረት ሥራ ባንክ የሚቋቋመው ለሁሉም የኅብረት ሥራ ማህበራት አገልግሎት እንዲሰጥ በመሆኑ አባላቱ ከሁሉም ዓይነት የኅብረት ሥራ ማህበራት የተውጣጡ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ መንግስትም የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማበረታታት እና የበለጠ ለመደገፍ እንዲቻል በሕግ የተወሰነውን ዕጣ በመግዛት አበል በማሆን በሂደት ለአባላት እየለቀቀ የሚሄድበት አሰራር ይኖራል፡፡

የባንኩ አደረጃጀት ልክ እንደ መንግስት እና ግል ባንኮች ዋና መስሪያ ቤት ኖሮት በተለያዩ ክልሎች ላይ ቅርንጫፍ በመክፈት የፋይናንሰ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እንደመሆናቸው በአሰራራቸው የተሸሉ ከባንኩ ጋር ተቀናጅተው በውክልና እንደ ቅርንጫፍ የሚያገለግሉበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ባንኩ እንደ ማንኛውም ባንክ ሁሉአቀፍ የባንክ አገልግሎት በመስጠት አባላት በሚያቀርቡት የቢዝነስ ፕላን መሠረት የሚጠይቁትን ብድር የሚያገኙበት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በተለይም ለግለሰብ አባላት የሚሰጡ ብድሮች በኅብረት ሥራ ማህበራት በኩል የሚሰጥበት ሁኔታ በማመቻቸት አባላት በቀጥታ ከኅብረት ሥራ ማህበራቸው የሚያገኙበት አሰራር እንዲፈጥር ይደረጋል፡፡ የአባል ግለሰቦችን የፋይናንስ ፍላጎት ለማሟላት ለብድር የሚጠያቀውን የዋስትና ችግር ለመቅረፍ ምቹ አሰራሮችን በመንደፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ ባንኩ የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጠው በዋናነት ለአባል የኅብረት ሥራ ማህበራት እና ለግለሰብ አባላት ሆኖ በሚቀመጠው አሰራር መሠረት በማድረግ አባል ላልሆኑ አካላትም አገልግሎት የሚሰጥበት አሰራር ይኖራል፡፡

### መፍትሄ 2፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የአደጋ ስጋት ለመቀነስ እንዲቻል የኅብረት ሥራ ኢንሹራንስ ማደራጀት

DRAFT

## ኅብረት ሥራ ኢንሹራንስ አደረጃጀትና አስተዳደር፡-

የኀብረት ሥራ ማህበራት በላቸው ልዩ በሕሪ በመነሳት የአባላት ፍላጎት መሠረት በማድረግ የኀብረት ሥራ ኢንሹራንስ እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡ የኀብረት ሥራ ኢንሹራንስ ለማቅቅም የሚረዱ ምቹ የሕግ ማዕቀፍና አሰራር እንዲኖር በማድረግ በገጠር የሚኖረው አርሶ/አርብቶ አደር እና በከተማ የሚኖረው ዝቅተኛ እና መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ የሕብረተሰብ ክፍል ፍላጎትን መሠረት በማድረግ ያሉባቸውን የአደጋ ስጋት ችግሮችን የሚቀንስ የኢንሹራንስ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

የኀብረት ሥራ ማህበራት እና አባላት በሚያከናውኑት ተግባራት ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የአደጋ ስጋቶችን ወይም ኪሳራን በመቀነስ ቁጠባን ለማበረታታት፣ የሰራተኞችን ደህንነት ለማረጋገጥ፣ በንብረት ላይ የሚደርስ የብልሽት ጉዳት እና የኪሳራ መጠንን በመቀነስ አባላትን በተሸለ ተጠቃሚ ለማድረግ ትኩረት በመስጠት ይሰራል፡፡

የኀብረት ሥራ ማህበራት ባላቸው ልዩ ባህሪይ በሌሎች የኢንሹራን ተቋማት ብቻ መገልገል ችግሮቻቸውን በሚፈለገው ደረጃ ሊፈታ ስለማይችል ራሱን የቻለ ለሁሉም ተደራሽ ሊሆን የሚችል የኀብረት ሥራ ኢንሹራንስ ተደራጅቶ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

የኀብረት ሥራ ኢንሹራንስ የሚቋቋመው ለሁሉም የኀብረት ሥራ ማህበራት አገልግሎት እንዲሰጥ በመሆኑ አባላቱ ከሁሉም ዓይነት የኀብረት ሥራ ማህበራት ለተውጣጡ አባላት ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ መንግስትም የተወሰነ የዕጣ ድርሻ ይኖረዋል፤ በሂደትም ለአባላት እየለቀቀ የሚወጣ ይሆናል፡፡ የኀብረት ሥራ ኢንሹራንስን የማደራጀት ተግባር የኀብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት ሆኖ ቁጥጥሩን በተመለከተ መንግስት በሚያስቀምጠው የሕግ ማዕቀፍ ኃላፊነት ለሚሰጠው ተቋም ይሆናል፡፡

የኀብረት ሥራ ኢንሹራንስ ለኅብረት ሥራ ማህበራት እና ለአባላት አጠቃላይ እና የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት አጣምሮ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ የኀብረት ሥራ ማህበራት ባላቸው ቋሚ ንብረቶች ማለትም ፋብሪካዎች፣ ተሸከሪካሪዎች፣ መጋዘኖች እና ሌሎች ንብረቶች ላይ ሊደርስ የሚችለውን የአደጋ ስጋት ለመቀነስ ሁሉም የኀብረት ሥራ ማህበራት የአጠቃላይ ኢንሹራንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አሰራሮች ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የአነስተኛ ኢንሹራንስ አገልግሎትን በተመለከተ የኀብረት ሥራ ማህበራት በራሳቸው የሚያከናውኑት ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ከአቅማቸው በላይ የሚሆኑ ተግበራትን ኢንሹራንሱ ከኀብረት ሥራ ማህበራቱ ጋር በመቀናጀት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት የሚያተኩረው በኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ላይ ሆኖ አባላትን ተመጣጣኝ አረቦን በማስከፈል ጉዳት ወይም ኪሳራ በሚያጋጥማቸው ጊዜ ተመጣጣኝ የካሣ ክፍያ በመፈጸም አገልግሎት የሚሰጥበት አሰራር ይፈጠራል፡፡ ኢንሹራንሱ የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጠው በዋናነት ለአባል የኅብረት ሥራ ማህበራት እና ለግለሰብ አባላት ሆኖ በሚቀመጠው አሰራር መሠረት በማድረግ ሌለሎች አባል ላልሆኑ አካላትም አገልግሎት የሚሰጥበት አሰራር ይኖራል፡፡  በዚህ መሠረት የሚቋቋመው የኅብረት ሥራ ኢንሹራንስ በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የራሱን ቅርንጫፎች በመክፋት ወይም የኅብረት ሥራ ፌዴሬሽኖች/ዩኒዬኖችን እንደ ቅርጫፍ በመጠቀም አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፡፡

## አምድ 22፡- የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የቁጥጥር እና አሰራር ስርዓት

### *ሀ. ነባራዊ ሁኔታ*

የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ማለትም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት፣ የኅብረት ሥራ ባንኮች እና የኅብረት ሥራ ኢንሹራንስ የፋይናንስ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት በመሆናቸው በባህሪያቸው ለችግር የተጋለጡ ስለሆኑ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት እና አሰራር በመዘርጋት መቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት በቁጠባ እና ካፒታል የተሰበሰበው የቁጠባ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቶ ከ13.4 ቢሊየን ብር በላይ  እንደደረሰ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህ ገንዘብ በአብዛኛው የተሰበሰበው ከአርሶ/አርብ አደር እና በመካከለኛ እና ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ከሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍል በመሆኑ ለአደጋ እና ምዝበራ እንዳይጋለጥ ጠንካራ የቁጥጥር አሰራር ተዘርግቶ መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

የተለያዩ አገሮች ተሞክሮ እንደሚያሳየው ኅብረት ሥራ ባንክ እና ኢንሹራንስ የሚቋቋሙት እና የሚተዳደሩት እንደየአገርቱ የኢኮኖሚ ዕድገት እና የሚከተሉት የፖለትካ ስርዓት መሠረት የተለያየ ነው፡፡ በአንዳንድ አገሮች (ለአብነት ኬንያ፣ አየርላንድ፣ ጀርመን እና ሌሎች) የኅብረት ሥራ ባንክ፣ ኢንሹራንስ እና የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን የማደራጀትና የመመዝገብ ሥራው በኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት ሲሆን የፋይናንስ ግብይቱን እና ደህንነቱ ብሔራዊ ባንክ የሚቆጣጠርበት አሰራር በማስቀመጥ ይሰራሉ፡፡

በሌሎች አገሮች (ለአብነት፡- ታይላንድ እና ዝምባቡዌ- ለግብርና ሚኒስቴር፣ ናይጀርያ- ለገንዘብ ሚኒስቴር  እና ሌሎች) ደግሞ የኅብረት ሥራ ባንክ እና ኢንሹራንስ የአገልግሎት አሰጣጣቸውን በማሻሻል ከኅብረት ሥራ ማህበራት ውጭ ሌለሎች አካላትም አገልግሎት እንዲሰጡ በመፍቀድ የቁጥጥር ሥራውን ለግብርና ሚኒስቴር ወይም ለገንዘብ ሚኒስቴር በመስጠት የማቋቋም ተግባሩን ለኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካል እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ እንዲሁም በጃፓን እና

በሕንድ የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ ግብይቱንና ደህንነቱ በበላይነት የሚቆጣጠር ራሱን የቻለ ብሔራዊ የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ተቋጣጣሪ አካል በማቋቋም ይሠራሉ፡፡

ይህ የሚያሳየው የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎት ለአገር ኢኮኖሚ እድገት ምን ያህል ወሳኝ መሆናቸውን በመረዳት ለአደረጃጀቱ እና ቁጥጥሩ ሀገራት ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ እንደሆነ ነው፡፡ የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎት እየተስፋፋ ስሄድ ለመቆጣጠር የተለያዩ ተቋማት በጋራ መስራት እንደለባቸው ያሳያል፡፡

በአገራችን የኅብረት ሥራ ባንክ እና ኢንሹራንስን ካላቸው ባሕሪ እና ጠቃሜታ አንጻር በተለየ መልኩ ለማቋቋም ሆነ ለመቆጣጠር የወጣ የሕግ ማዕቀፍ ባይኖርም፣ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚቋቋሙት እና የሚተዳደሩት በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ነው፡፡ ቀድሞ በሥራ ላይ የነበረም ሆነ በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ያለው የኅብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚያደራጅ እና የሚቆጣጠር በየደረጃው ያለው የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር መዋቅር እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡

የአገሮች ተሞክሮ እንደሚያሳየው የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን ጨምሮ የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎት ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም እንደ ሞባይል ባንክንግ፣ የSMS፣ credite card እና ሌሎች ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም ከሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ጭምር በመተሳሰር የገንዘብ ልውውጡን ቀልጣፋ በማድረግ የተሸለ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያከነውኑት ተግባር በዋናነት የፋይናንስ አገልግሎትን መስጠት በመሆኑ የአሰራር ስርዓታቸው የተሟላ እና የሚያሰራ መሆን አለበት፡፡ በአገራችን የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚመሩባቸው አዋጅ፣ ደንብ፣ የተለያዩ መመሪያዎች፣ የስልጠና ማኑዋሎች እና ሌሎች ጠቃሚ የአሰራር ስርዓቶች ተዘርግተው እንዲጠቀሙበት በማደረግ ላይ ይገኛል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የቁጠባ፣ የብድር፣ የአነስተኛ መድህን ዋስት እና ሌሎች አገልግሎቶች እንዲያስፋፉ የሚያገለግሉ የተለየዩ ማኑዋሎች ተዘጋጅቶ አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ የውስጥ አሰራራቸውን ለማጠናከር እንዲችሉ የሂሳብ አሰራራቸውን ለማዘመን የሚያግዙ ቀለል ያሉ ሶፍትዌሮችን በመዘርጋት እንድገለገሉበት ጥረት ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም በተወሰኑ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ዩኒየኖች **ለአብነት** በኦሮሚያ ብ/ክ/ማንግስት ቀለጣ እና አዋሽ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች፣ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክልል መንግሰት የነጻነት ፋና

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ራሴድ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ዘመናዊ ቴክኖሎጅ በመዘርጋት ቀልጣፋ እና ተደራሽ አገልግት በመስጥ ላይ ይገኛሉ፡፡

ሆኖም እነዚህ ውስን የአሰራር ስርዓቶች የተዘረጉ ቢሆንም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አገልግሎታቸው እየተስፋፋ በመሆኑ የአገልግሎት ስፋቱን ሊመጥን የሚችል የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ በርካታ ክፍተቶች በመታየት ላይ ይገኛሉ፡፡ የተዘረጉ የአሰራር ስርዓቶችን ተከትሎ አገልግሎት በመስጠት ላይም የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር፣ የሚደረግላቸው ድጋፍ የተሟላ አለመሆን፣ የተዘረጉ አሰራሮችን ወደታች በማውረድ በአሰራሩ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር እንዲጠቀሙበት በማድረግ እና አሰራሩን ተጠቅሞ በማይሰሩት ላይ የሚወሰድ እርምጃዎች አናሳ ከመሆኑ የተነሳ በአጠቃቀም ላይ ሰፊ ችግሮች ይታያሉ፡፡

## ለ. የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የቁጥጥር እና አሰራር ስርዓት ላይ ያሉ ማነቆዎች፡-

### ማነቆ 1፡-ጠንካራ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖር፣

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ አሰራራቸው የተጠናከረ አለመሆን፣ ተግባሮቻቸውን በባለሙያ መምራት አለመቻል፣ የዓለም አቀፍ የፋይናንስ መለኪያዎችን በመጠቀም ተግባሮቻቸውን እየመዘኑ መሄድ አለመቻል፡፡ የሚደረገው ቁጥጥር ጠንካራ ያለመሆን ችግሮ ጎልቶ ይታያል፡፡ ለቁጥጥሩ ትኩረት ሰጥቶ በበቂ ሁኔታ ባለሙያ መድቦ በቆጣጠር አለመቻል፡፡ የፋይናንስ አያያዝ፣ አስተዳደር እና ድጋፍ አሰጣጥ ላይ የአቅም፣ የዕውቀት እና የክህሎት ክፍተት መኖር፡፡  የቁጥጥር ሥራውን ለማጠናከር የሚያስችል በቂ የሆነ አሰራር መዘርጋት አለመቻል ችግሮች ይታያሉ፡፡

### ማነቆ 2፡- ጠንካራና ሊያሰራ የሚችል የፋይናንስ የአሠራር ሥርዓት አለመዘርጋት፣

በአገራችን ተደራጅቶ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የገንዘብ ቁጠባን ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥራቸው በርካታ ቢሆንም የውስጥ አሰራራቸውን ሊያጠናክር የሚችል የተደራጀ እና ሁሉ አቀፍ የሆነ የአሰራር ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ የተጠናከረ አይደለም፡፡ የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጣቸው ከማኑዋል አልፎ በቴክኖሎጅ የሚደፈግ ባለመሆኑ ቀልጣፋ እና ጠንካራ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የሚሰጡትን የፋይናንስ አገልግሎት ለማስፋፋት የሚያስችል አሰራር በስፋት ዘርግቶ ጥቅም ላይ በማዋል በኩል ሰፊ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ የተዘርጉ የአሰራር ስርዓቶችን ሥራ ላይ ለማዋል የሰለጠነ ባለሙያ ማግኘት ሌለው ማነቆ ነው፡፡ የተዘረጉ የአሰራር ስርዓቶችን ተግባራዊ ላመድረግ የዕውቀት፣ ክህሎት እና ፋይናንስ ችግር መኖሩ፡፡

### ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የምንከታላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤

### መፍትሄ 1፡- ጠንካራ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የቁጥጥር ሥርዓት መፍጠር

### የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የቁጥጥር

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን የማደራጀት እና መቆጣጠር ተግባር የሚከናወነው በየደረጃው በሚገኙ የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት አማካይነት ይሆናል፡፡ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በአሁን ወቅት ተደራጅቶ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ስነጻጸር በአገልግሎት አሰጣጣቸው ላይ ምዝበራ እና ብልሹ አሰራር ብዙም አይታይም፡፡ ይህ ማለት ለወደፊት የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎት እየተስፋፋ በሚሄድበት ወቅት የአገልግሎት አሰጣጣቸው በዚሁ ደረጃ አስተማማኝ ሆኖ የሚቀጥል መሆኑን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ በመሆኑም በአሁን ወቅት የሚታየውን የተሸለ የአገልግሎት አሰጣጥ እና አሰራራቸው ተጠናክሮ እና ተሸሻሎ እንዲሄድ ለማድረግ የቁጥጥር ሥራው ጥብቅ እንዲሆን የሚያስፈልጉ አሰራሮችን በመዘርጋት እና ቁጥጥሩን በማጠናከር በትኩረት ይሠራል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ለአጠቃላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ ምንጭ በመሆን የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላትን በተሸለ ተጠቃሚ እንዲያደርጉ እና ለአገሪቱ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጅ መሳካት የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማስቻል ጠንካራ የክትትል እና ቁጥጥር አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የአገሪቱን የፋይናንስ ግብይት አሰራርን ተከትሎ የፋይናንስ ግብይቱን ሳያናጉ እንዲሰሩ አስፈላጊው ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግበት አቅጣጫ ይቀመጣል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ አሰራራቸው የተጠናከረ እንዲሆን አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሰለጠነ ባለሙያ በመቅጠር ተግባሮቻቸውን እንድመሩ ይደረጋል፡፡ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ መለኪያዎችን በመጠቀም አፈጻጸማቸውን እየመዘኑ የሚታዩ ክፍተቶች ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ እንዲሄዱ የሚያስችል የክትትል እና የቁጥጥር አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ማንኛውም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የተቀመጠውን አሰራር ተከትሎ የፋይናንስ ሪፖርቱን በየጊዜው ለኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት እንዲያቀርቡ የሚያደርግ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ለአሰራሩ ተገዥ በማይሆኑት ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

በየደረጃው የሚገኘው የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት በተለይም ለወረዳ መዋቅር የተለያ ትኩረት በመስጠት እንዲጠናከር የማድረግ ተግባር ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡ የቁጥጥር ሥራውን የተሸለ ለማድረግ የኢንስፔክሽን

DRAFT

እና ኦዲት ባለሙያዎች በብዛት እና በጥራት በመመደብ ጠንካራ ቁጥጥር እንዲደረግ በትኩረት ይሠራል፡፡ የቁጥጥር ሥራውን ለማጠናከር የሚያስችል ጠንካራ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### መፍትሄ 2፡- ጠንካራና ሊያሰራ የሚችል የፋይናንስ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣

### ለፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ጠንካራ የፋይናንስ አሠራር ሥርዓት መዘርጋት፡-

የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያስተዳድሩት ገንዘብ ከአባል አርሶ/አርብቶ አደር እና ዝቅተኛ እና መካካለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ከሚገኙ የከተማ ሕብረተሰብ የተሰበሰበ ገንዘብ በመሆኑ የውስጥ የአሰራር ስርዓታቸው ጠንካራ፣ ጥብቅ እና ሊያሰራ የሚችል እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በመሆኑም አሰራራቸውን ሊያጠናከር የሚችል የተደራጀ እና ሁሉ አቀፍ የሆነ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ጉዳይ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ ጠንካራ እና ሊያሰራ የሚችል የአሰራር ስርዓት መኖር ለፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የህልውና ጉዳይ መሆን አለበት፡፡

የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የአሰራር ስርዓታቸው ሳይጠናከር ቀርቶ ለሚዝበራ እና ኪሳራ ከተጋለጡ የሕዝብ ገንዘብ ለብክነት ብቻ የሚጋለጥ ሳይሆን በኅብረት ሥራ ማህበራት ህልውና ላይ ትልቅ ጠባሳ የሚያሳድር በመሆኑ ጠንካራ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

የሂሳብና የመረጃ አያያዝ፣ የብድር እና የወለድ አሰላልን የሚያዘምኑ እና ሌሎች አሰራራቸውን የሚያሻሽሉ የአሰራር የመዘርጋት ተግባር በስፋት ይሰራል፡፡ እነዚህን አገልግሎቶች ተግባራዊ ለመድረግ የሚያግዙ አቅማቸውን የገናዘበ ትላልቅ ሰርቨሮችን በመገንባት እንዲጠቀሙ ይደረጋል፡፡ ይህን አሰራር ለሁሉም ለማዳረስ የሚጠይቀው ፋይናንስ በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አቅም ብቻ የሚሻፈን ስለማይሆን መንግስትና ሌሎች አቅም ገንቢ አካላትም እንዲደግፉ ይደረጋል፡፡

በአሁን ወቅት አብዛኞቹ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚሰሩበት ልማዳዊ አሰራር ወጥተው የተሸለ እና ዘመናዊ አሰራር ስርዓት በመዘርጋት እንዲጠቀሙበት ይደረጋል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባሎቻቸው የሰበሰቡት የቁጠባ መጠን ከአባላት የገቢ መጠን ጋር ስነጻጸር በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያቱ ሕብረተሰቡ በቁጠባ ላይ ያለው ግንዛቤ አናሳ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ችግሩ ከመሠረቱ ልያሻሽል የሚችል የፋይናንስ ክህሎት ማበልጽጊያ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በዚህ መሠረት ግንዛቤውን በቀላሉ ማስረጽ እንዲቻል የተለያዩ የማስተማሪያ ዜዴዎችን በማዘጋጀት አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ በዚያው ሊክ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ የቁጠባ ዓይነቶችን ለማስፋፋት የሚያስችል አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የተሻለ ቁጠባ የቆጠቡ እና በተለያዩ የቁጠባ ዓይነቶች ላይ በስፋት የተሳተፉ አባላት የተሸለ ጥቅም የሚያገኙበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ የቁጠባ መጠንን ለማስፋፋት ይሰራል፡፡ የተለያዩ ዓይነት የቁጠባ ስልቶችን **ለአብነት** የሴቶች፣ የሕጻናት፣ የግብዓት መግዣ፣ የጤና፣ የውዴታ፣ የበዓላት ቁጠባ እና ሌሎች አሰራሮች ተነድፎ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ሊያስተሳስር የሚችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የመጠባበቂያ ሂሳቦች፣ የኅብረት ሥራ ፈንዶችን፣ የእርጅና ተቀናሽ ሂሳቦች እና ሌሎች ፈንዶችን የሚየስተዳድሩበት አሰራር ይዘረጋል፡፡ በሌላ በኩል የፋይናንስ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአሰራራቸውን አውታር (networked) በማድረግ ሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባሎቻቸው ጋር የሚያደርጉት የግብይት ክፍያ ስርዓት በፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት በኩል እንዲሆን የሚያደርግ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

አባላት የሚፈልጉት ብድር እና የገንዘብ ቁጠባን ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሰበሰቡት ቁጠባ መጠን ስለማይጣጣም የአባላትን የብድር ፍላጎት ለማሟላት ለብድር የሚሆነውን ሰፊ ፋይናንስ ለማግኘት የሚያስችሉ ጠንካራ አሰራሮችን ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የኢንሹራንስ አገልግሎት ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ በመሆኑ የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት እና የአጠቃለይ የኢንሹራንስ አገልግሎቶች የሚስፋፉበትን በጥናት አሰራር በመዘርጋት መስራት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ማስፋፋት የሚቻልባቸው አሰራሮች ተነድፎ እንዲተገበሩ በትኩረት ይሰራል፡፡

የኅብረት ሥራ ባንክ እና ኢንሹራን የአገልግሎት አሰጣጥ የትኩረት መስኮች እና የአገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የተለያዩ አሰራሮች ተነድፎ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎቱ ዘመናዊ እና ቀልጣፋ እንዲሆን ለማስቻል እንደ ሞባይል ባንክንግ፣ የSMS፣ credite card እና ሌሎች ቴክኖሎጅዎችን ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

### የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ ችግሮችን ለመቅረፍ የምንከተላቸው አቅጣጫዎች፡-

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የሚሰጡት አገልግሎት በአግባቡ ተደራሽ ለማድረግ ከሚያጋጥማቸው ማነቆዎች ውስጥ ትልቁ የፋይናንስ እጥረት ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሰብል ግብይት፣ ለግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችና ቴክኖሎጂዎ ግዥ፣ የፍጆታ ዕቃዎችን ለአባላት ለማቅረብ፣ የግብርና ምርት ላይ እሴት ለማጨመር፣ የአግሮ-ፕሮሰስንግ ተግባራት ላይ ለመሳተፍ፣ መሰረተ ልማትን ለማስፋፋት እና ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን የፋይናንስ እጥረት ፈታኝ በመሆን ላይ ይገኛል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ አቅርቦት ለማሻሻል ውስጣዊ እና ውጫው የፋይናንስ ምንጮች ላይ ትኩረት ተደርጎ መሰራት ይኖርበታል፡፡ ዋነኛው የኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ የፋይናንስ ምንጭ የአባላት ዕጣ በመሆኑ የአባላትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ተጨማሪ ዕጣዎችን በመሻጥ የሚያስፈልጉ ካፒታሎችን ማሰባሰብ አስፈላጊ ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በየዓመቱ ከሚያገኙት ትርፍ ውስጥ በሕጋቸው መሠረት የተወሰነውን በመቀነስ ለሥራ መስፋፊያ የሚያስቀምጡበት አሰራር ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት እርስ በርሳቸው፣ ከመንግስት፣ ከባንኮች፣ ከአነስተኛ ብድር ተቋማት፣ ከአቅም ገንቢዎች እና ሌሎች ተቋማት ጋር ጠንካራ የፋይናንስ ግብይት ትስስር በመፍጠር ተጨማሪ ካፒታል ማሰባሰብ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ከሌሎች ተቋማት ጋር በጆይንት ቨንቼር የሚሰሩበት አሰራር በመዘርጋት ተጨማሪ ፋይናንስ ማሰባሰብ የስፈልጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራዎቻቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ሊያጋጥማቸው የሚችሉ ኪሳራዎችን ለመቋቋም እንዲችሉ ከሚያገኙት ትርፍ ላይ ለመጠባበቂያ ገንዘብ እንዲቀመጥ ይደረጋል፤ ስለአጠቃቀሙ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአቅም ግንባታ፣ ኦዲት እና ሌሎች ጉዳዮችን በጋራ ለማከናወን የሚያስችላቸውን ኅብረት ስራ ፈንድ በማቋቋም የሚያስፈልገውን በጀት በመመደብ አገልግሎት ላይ የሚውልበትን አሰራር ያስቀምጣሉ፣ የፈንዱን አጣቀምና አስተዳደርን በተመለከተ ሕግ እንዲወጣለት ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከአባላት ውጭ በሚያደርጉት ግብይት እና በተለያየ ምክንያቶች ተካባች ሂሳቦች ሲፈጠሩ ይታያል፡፡ በመሆኑም ተካባች ሂሳቦች ላልተፈለገ ምዝበራ እንዳይጋለጥ ሥራ ላይ የሚውልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

## ለኅብረት ሥራ ባንክና ኢንሹራንስ ጠንካራ የቁጥጥር አሰራር ስርዓት መዘርጋት፤

የኅብረት ሥራ ባንክ እና ኢንሹራንስ የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎት የቁጥጥር ስርዓቱ በአግባቡ የተጠናከረ ካልሆነ የሚደርሰው ችግር አባላትን ለኪሳራ ከመዳረግ አልፎ በአገሪቱ የፋይናንስ ግብይት አሰራር ላይ ተጽኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ስለሆነም የኅብረት ሥራ ባንክ እና ኢንሹራንስ ለሕብረተሰቡ ተደራሽ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ለመድረግ ራሱን የቻለ ጠንካራ ሕግ ወጥቶለት እንዲመራ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ባንክ እና ኢንሹራንስ ቁጥጥሩን በተመለከተ በተለያዩ ሀገሮች የተለያዩ የቁጥጥር ስርዓቶችን በመዘርጋት የምከታተሉበት እና የምቆጣጠሩበት ሂደት ይታያል፡፡

በመሆኑም በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሁለትዮሽ የቁጥጥር ዘዴን በመጠቀም አጠቃላይ አሰራሩን በተመለከተ የኅብረት ሥራ ማህበራት መርሆ ተከትሎ ስለሚደራጁ አፈጻጸሙን የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት

የሚቆጣጠሩት ሆኖ የፋይናንስ ግብይቱንና ደህንነቱን በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ ወይም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር እንዲቆጣጠር ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ባንክ እና ኢንሹራንስ የሚቋቋሙት የኅብረት ሥራ ማህበራት መርሆና እሴቶችን ተከትሎ በባለቤትነት በኅብረት ሥራ ማህበራት ስለሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት አሰራርን ተከትሎ እየሰሩ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ ሆኖ ብሔራዊ ባንክ እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር አገሪቱን ፋይናንስ ደህንነት በበላይነት የሚቆጣጠሩ እና የሚመሩ አካላት በመሆናቸው የኅብረት ሥራ ባንክ እና ኢንሹራንስ የአገሪቱን የፋይናንስ አሰራር ጠብቆ እየሰሩ ማሆናቸውን የሚያረጋግጡ እና የተቋማቱን የፋይናንስ ደህንነት ጭምር የሚቆጣጠሩ አካላት በመሆናቸው ነው፡፡

## አምድ 23፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አቅም ማጠናከር

### *ሀ. ነባራዊ ሁኔታ*

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለተግባሮቻቸው ማስፈጸሚያ የሚሆነውን ፋይናንስ ለማግኘት የውስጥ አቅማቸውን አሟጦ መጠቀም ወሳኝ ነው፡፡ ከውስጥ የሚሰበሰበው ፋይናንስ ከዋጋ አንጻር ሲታይ አነስተኛ ወጭን የሚያስከትል በመሆኑ ተመራጭ ያደርገዋል፡፡ በሌላ በኩል የፋይናንስ ምንጩ አባላት በመሆናቸው ፋይናንሱ በኅብረት ሥራ ማህበራቱ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ የሚችል በመሆኑ ትልቁ ፋይዳ አለው፡፡

ፋይናንሱን በኅብረት ሥራ ማህበሩ አሰራር መሠረት የሚያንቀሳቅሱ እና የሚያስተዳድሩት የኅብረት ሥራ ማህበሩ አመራሮች በመሆናቸው ለመጠቀም አሰራሩ የተንዛዛ ስለማይሆን ምቹ እና ቀልጠፋ አገልግሎት ለመስጥ አመች ነው፡፡ በመሆኑም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፋይናንስ ለማሰባሰብ የአባላት ዕጣ ላይ ትኩረት በመስጠት ሌሎች የውስጥ አቅሞችንም በስፋት አሟጦ ለመጠቀም መስራት ያስፈልጋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ የአገር ብልጽግና መለኪያ ከሆኑ መስፈርቶች መካከል የዳበረ የዜጎች የቁጠባ ባህል እና የቁጠባ መጠን እድገት አንዱ ነው፡፡ ያለ ቁጠባ እንቨስትሜንት ሊኖር እንደማይችል ሁሉ ያለእንቨስትሜን የአገር ኢኮኖሚ እድገት ሊታሰብ አይችልም፡፡ በአሁኑ ወቅት የዜጎችን የቁጠባ መጠን ማሳደግ የአገራችን አጀንዳ ብቻ ሳይሆን የዓለም አገራት አጀንዳ በመሆን ሰፊ ሥራ በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡ እንደ እኛ ገና በማደግ ላይ ላሉ አገሮች ደግሞ ቁጠባን በስፋት በማሰባሰብ እንቨስትሜንት ውስጥ እንዲገባ በማድረግ የአገር ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገት ውስጥ ድርሻውን እንዲወጣ ማስቻል የሁሉም አካላት ድርሻ እና ርብርብ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡

በአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ የሕብረተሰቡ የቁጠባ በህል ዝቅተኛ በመሆኑ የግለሰቦች የቁጠባ መጠን እጅግ አናሳ ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በአሁኑ ጊዜ እየሰበሰቡት ያለው የቁጠባ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ቢሆንም አባላቱ ከሚያገኙት ገቢ የቁጠባ መጠናቸው ስነጻጸር በጠም አነስተኛ ነው፡፡ የአባላት የቁጠባ መጠን አነስተኛ ከሚያደርጉት ጉዳዮች መካከል አንዱ የአባላትን የቁጠባ በመጠን ለማሳደግ የሚሰጡ የፋይናንስ ክህሎት ማበልጽጊያ ሥራዎች አነስተኛ በመሆኑ አባላት በቁጠባ ላይ ያላቸው ግንዛቤ አናሳ መሆኑ አንዱ ሲሆን የአባላት የአቅም ውስንነት ችግሮች አሉ፡፡

በመሆኑም የሕብረተሰቡን የቁጠባ ባህል ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ አሰራሮችን በመዘርጋት መስራት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የ2009 ዓ.ም መረጃ መሠረት በአገራችን የአንድ አባል አማካይ የቁጠባ መጠን 3410 ብር የደረሰ ሲሆን በከተማ 8,264 ብር እና በገጠር 917 ብር ነው፡፡

በአገራችን ተደራጅቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት ፍላጎት መሠረት በማድረግ የተለያዩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፡፡ በግብርናው ዘርፍ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከመንግስት ጋር በጋራ በመሆን የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን ለአባላት በዱቤ በመስጠት፣ ለምርት ግብይት የሚሆን ፋይናንስ በማመቻቸት እና ሌሎች የፋይናንስ አገልግሎቶችን ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

መንግስት እና ሌሎች አቅም ገንቢ አካላት የኅብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ እጥረቱን ለመቀነስ ተዘዋዋር ብድር በመመደብ፣ የሥራ ማስጀመሪያ ገንዘብ (seed moeny) በመስጠት እና ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ ሆኖም በአሁኑ ወቅት ተደራጅቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎት ውስን በመሆኑ የአባላት ፍላጎት በማርካት በኩል ችግሮች ይታያሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሮቻቸውን ለማስፋፋት የሚያስፈልጋቸውን ፋይናንስ ማግኘት አለመቻል ችግር ትልቅ ማነቆ ሆኗል፡፡ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ልማት የሚደግፍ በቂ የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም በሚፈለገው ደረጃ የለም፡፡ ለዚህ ትኩረት ባደረገ ሁኔታ የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽ ላመድረግ የማስፋፋት ሥራ በትኩረት አለበት፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደረገው የርስ በርስ የፋይናንስ ግብይት ትስስር የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥማቸው የአባላትን የብድር ፍላጎት ለማሟላት እንዲቻል ለማበደር ፍላጎትና የገንዘብ አቅም ካላቸው ሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የጋራ ጥቅም በሚያስገኝ መልኩ ውጤታማና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ የሚደረግ የፋይናንስ ግብይት ትስስር ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ካላቸው እሴቶች መካከል አንዱ እርስ በርስ መረዳዳት (cooperation amoung cooperative) የሚባል ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በባሕሪያቸው የአባሎቻቸውን ፍላጎት ለማሟላት እርስ በርሳቸው ተጋግዘው እና ተረዳድተው የመስራት ስልትን የሚከተሉ ተቋማት ናቸው፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚደጋገፉባቸው የሥራ መስኮች መካከል የግብይት ትስስር በመፍጠር የሁለትዮሽ ጥቅምን በሚያስከብር ሁኔታ የመስራት፣ ያላቸውን እውቀትና ክህሎት በመለዋወጥ ለተሻለ ውጤት መስራት ናቸው፡፡ እርስ በርስ የሚያደርጉት የፋይናንስ ግብይት ትስስር ከሌሎች ተቋማት ጋር ከሚደረጉ የፋይናንስ ግብይት ትስስር በተሻለ መልኩ ውጤታማ ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያከናውኑት ተግባራት በአብዛኛው የአባላትን ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ፣ ተግባሮቻቸው እና ያላቸው ልምድ ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ ከሌሎች ተቋማት ጋር እንደሚያደረጉት የግብይት ትስስር አንዱ ሌላውን የመጠራጠርና የመስጋት ችግር የሚታይበት አይደለም፡፡

በአገራችን ያሉ የፋይናንስ ተቋማት ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የሚያደርጉት የፋይናንስ ግብይት ትስስር የተጠናከረ ባለመሆኑ በገጠር እና በከተማ በአነስተኛ እና መካከለኛ ገቢ የሚተዳደሩት የሕብረተሰብ ክፍል የፋይናንስ ፍላጎት አቅርቦት ተደራሽ በማድረግ ረገድ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ በሌላ በኩል ለእነዚህ የሕብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋሙ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የገንዘብ ምንጫቸው የአባላት ቁጠባ በመሆኑ እና የቁጠባ መጠኑ አነስተኛ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሚጠይቁትን ብድር በማመቻቸት የኢንቨስትመንት ፍላጎታቸውን በማሟላት በኩል የአቅም ውስንነት በስፋት ይታያል፡፡

ይህንን ችግር ለመቅረፍ መንግስት ሌሎች አቅም ገንቢ አካላትን በማስተባበር ለኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያደርጉ የሚደረግበት አሰራር አልፎ አልፎ ይታያል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የብድር ፋላጎታቸውን ባይሻፍንም ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ጋር የግብይት ትስስር በመፍጠር ለሥራቸው መንቀሳቀሻ የሚሆን ብድር የሚያገኙበት አልፎ አልፎ ያገኛሉ፡፡ ሆኖም የፋይናንስ ተቋማት የፋይናንስ ግብይት ትስስሩን ለማድረግ ፍቃደኛ አለመሆን ችግሮች በስፋት ይታያል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ግብይት ተግባሮቻቸው ማስፈጸሚያ የሚያስፈልግ ፋይናንስ በአብዛኛው የሚያገኙት ከራሳቸው የውስጥ ካፒታል ምንጭ ነው፡፡ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ መንግስት ለግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች የሚሆነውን ብድር ለኅብረት ሥራ ማህበራት በማመቻቸት አባላት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ ለግብርና ምርት ግብይት እና አልፎ አልፎ በከተማ ውስጥ የሚገኙ ሸማች የኅብረት ሥራ ማህበራት ለግብይት የሚሆናቸውን ፋይናንስ በመንግስት ይመቻቻል፡፡ በሌላ በኩል መንግስት ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዋስትና በመግባት የሚያስፈልጋቸውን ፋይናንስ ከባንኮች እንዲያገኙ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡

አንዳንድ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከባንኮች ጋር በቀጥታ ትስስር በመፍጠር የብድር ፍላጎታቸውን ያሟላሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አስተዳደራቸው እየተሸሻለ በመምጣቱ በፋይናንስ ተቋማት ተአማንነታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ

እየጨመረ ይገኛል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት እነዚህ የብድር ምንጮችን ብጠቀሙም በአገር ውስጥ እና በውጭ ግብይት ውስጥ ለመሰማራት የፋይናንስ ማነቆ ሊፈታ አልቻለም፡፡

## ሰንጠረዥ 6፡ ሦሥር ኃ.የተወ. የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን በሞደልነት የተወሰደ (bench mark)

**የአባላትና ካፒታል እድገት፡-** የሚገኘው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ውስጥ ስሆን የ2009 ዓ.ም መረጃ መሰረት አባል መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር 111 ሆኖ የተናጠል አባላት ቁጥር 58,626 (ሴት19.46) እና ካፒታሉን 11,443,919.81 ብር ደርሷል፡፡

**የሚሰጡት የቁጠባ አይነት እና እድገት፡-** የሚሰጣቸው የፋይናንስ አገልግሎቶች የመደበኛ ቁጠባ፣ መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ፣ የልጆች ቁጠባ፣ የጊዜ ገደብ ቁጠባ፣ ብድር፣ የኢንሹራንስ፣ የተለያዩ የህትመት ውጤቶች፣ የቴክኒክ ድጋፍ፣ የትምህርትና ስልጠና፣ የክትትልና ድጋፍ አገልግሎቶች ናቸው፡፡

በ2009 ዓ.ም መረጃ መሠረት መደበኛ ቁጠባ መጠን 12,292,324.91 ብር የደረሰ ሲሆን መደበኛ ያልሆኑ የቁጠባ ዓይነቶች 105,501,275.31 ብር በድምሩ 117,793,600.22 ብር ቁጠባ ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡

**የብድር አገልግሎት እና የአባላት ተሳትፎ እና አመላለስ መስፋፋት፡-** ብድር የሚሰጥባቸው የሥራ ዘርፎችን የአባላትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ለግብርና ዘርፍ፣ ለአነስተኛና ጥቃቅን ንግድ ሥራዎች እና ለማህበራዊ ጉዳዮች ሆኖ በ2009 ዓ.ም ብቻ 22,533,768.78 ብር ብድር ለአባለላት ያሰራጨ ስሆን ዩኒየኑ ከ2001 ጀምሮ እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ በድምሩ 12,150 (ሴቶች፣*19.95)* አባላት 108,073,877.20 ብር በአባል መሠረታዊ ማህበራት በኩል ብድር ለአባላት በማቅረብ ተጠቃሚ አድርጓል፡፡ የብድር አመላለሱም 98.2 ከመቶ ነው፡፡

### ለ. የውስጥ የፋይናንስ አቅም አሟጦ በመጠቀም ላይ ያሉ ማነቆዎች፤

### ማነቆ 1፡- አማራጭ የውስጥ የፋይናንስ አቅም አሟጦ አለመጠቀም

የኅብረት ሥራ ማህበራት በርካታ የውስጥ የፋይናንስ አቅሞችን አሟጦ አለመጠቀም፣ የፋይናንስ አማራጮችን ማስፋፋት አለመቻል፣ የታወጅ ዕጣዎችን አባላት አሟጦ እንዲገዙ አለማድረግ፣ የውስጥ ፋይናንስ አቅም ለማሳደግ የሚያግዙ የተለያዩ አሰራሮችን አለመዘርጋት፡፡ አባላት ተጨማሪ ዕጣዎችን እንዲገዙ ግንዛቤ አለመፍጠር፣ በትርፍ ክፍፍል ወቅት ዕጣ ያለውን ድርሻ በማሳደግ አባላት የተሸለ ዕጣ እንዲገዙ የሚያበረታታ አሰራር ማመቻቸት አለመቻል ችግሮች ይታያሉ፡፡

### ማነቆ 2፡- የቁጠባ ባህልን ለማሳደግ ጠንካራ የፋይናንስ ክህሎት ማበልጸጊያ ሥርዓት አለመገንባት፣

በአገራችን የሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች በቁጠባ ላይ ያላቸው ግንዛቤ ደረጃ ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የሚሰሩ የፋይናንስ ክህሎት ማበልጽጊያ ተግባራትም ሰፊ አይደለም፡፡ የሕብረተሰቡን ንቃተ ህሊና መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ የፋይናንስ ክህሎት ማበልጸጊያ ሰነዶች በሚፈለገው ደረጃ አልተዘጋጁም፡፡ ችግሩን ለመቅረፍ ሰፋፊ የንቅናቄ መድረኮችን በመፍጠር እና የተለያዩ ሚዲያዎች በመጠቀም ግንዛቤን ለማስረጽ የሚደረግ ተግባራት የደበሩ እና ቀጣይናት ያለው አይደለም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የቁጠባ መጠን ከሚያገኙት ገቢ ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው፡፡ በሌላ በኩል በተለያዩ የፍላጎት ቁጠባ ዓይነቶች ላይ በመሳተፍ የቁጠባ መጠናቸውን ለማሳደግ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ጠንካራ አይደለም፡፡

## ማነቆ 3፡- የፋይናንስ አገልግሎቶች አለመስፋፋት፣

ኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አገልግሎት ለማስፋፋት የሚያደርጉት ጥረት አናሳ መሆን እና ሕብረተሰቡ በፋይናንስ አገልግሎት ላይ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ ነው፡፡ ለምርት እና ለአገልግሎት የሚያስፈልግ ፋይናንስ በመለየት በወቅቱና በሚፈለገው መጠን ማቅረብ አለመቻል፡፡ አባላት የሚቆጥቡት የተናጠል የቁጠባ መጠን አነስተኛ መሆን፣ የቁጠባና ብድር ዓይነቶች መስፋፋት አለመቻል፣ የአባላትን የብድር ፍላጎት ማርካት አለመቻል፣ የሚሰጡት የፋይናንስ አገልግሎት አለመስፋፋት፣ እርስ በርሳቸው እንዲሁም ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት እና ከፋይናንስ ተቋማት ጋር የግብይት ትስስር በመፍጠር መሥራት አለመቻል ዋና ዋና ማነቆዎች ናቸው፡፡

## ማነቆ 4፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የርስ በርስ የፋይናንስ ግብይት ትስስር አሠራር ሥርዓት አለመዘርጋት፣

የኅብረት ሥራ ማህበራት የርስ በርስ የግብይት ትስስር እንዲያደርጉ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ አልተዘረጋም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የርስ በርስ የሚደረግ የፋይናንስ ግብይት ትስስር የሚያስገኘውን ጥቅም በአግባቡ ባለመረዳት ለመተሳሰር ፍላጎት ማጣት ችግሮች ይታያል፡፡ የፋይናንስ ግብይቱ ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዲደረግ ከሚመለከታቸው አካላት የሚደረግ ድጋፍ ደካማ የመሆን ችግር ይታያል፡፡ አደራጅ ተቋማትም በተለይም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ተቀራርቦ ችግሩን ለማፍታት የሚደረጉት ጥረት ደካማ ነው፡፡

## ማነቆ 5፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚያደርጉት የፋይናንስ ግብይት ትስስርና ግንኙነት የተጠናከረ አለመሆን፣

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ጋር የፋይናንስ ግብይት ትስስር እንዲያደርጉ የሚያስፈልግ የአሰራር ስርዓት አልተዘረጋል፡፡ የፋይናንስ ግብይት ትስስር አስፈላጊነት እና ጥቅም ላይ ሁለቱም የግብይት ትስስር

የሚፈጥሩ አካላት ግንዛቤ አናሳ መሆን፡፡ የፋይናንስ ተቋማት የሚያስከፍሉት የወለድ መጠን ወጥነት የለሌው መሆን፣ ፋይናንሱም በሚፈለገው መጠን እና በወቅቱ አለማግኘት፡፡ በአርሶ/አርብቶ አደሩን ውስጥ ተደራጅቶ አገልግሎት እያሰጡ ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ያገናዘቡ የብድር ዓይነቶችን በመዘርጋት አገልግሎት መስጠጥ አለመቻል፡፡ የግብይት ትስስሩን ለመፈጸም የፋይናንስ ተቋማት ፈላጎት ማጣት ችግር ሌላው ማነቆ ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትም ለግብይት ትስስሩ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በአግባቡ ተረድቶ ለማሟላት የሚያደርጉት ጥረት ክፍተት ያለበት ነው፡፡ የግብይት ትስስሩ ውጤታማ እንዲሆን የሚደረገው ድጋፍ በቂ አይደለም፡፡

**ማነቆ 6፡- መንግስትና አቅም ገንቢ አካላት ለኅብረት ሥራ ማህበራት በቂ የፋይናንስ ድጋፍ አለማድረግ**

መንግስት እና አቅም ገንቢ አካላት ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያደርጉት የፋይናንስ ድጋፍ ችግር ፈች አለመሆን እና ክፍተቶች የለየ አለመሆን ችግር ይታያል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአቅም ገንቢ አካላት ብዙ ጊዜ የአመራሩን እና ባለሙያውን የማስፈጸሚ እና የመፈጸሚ አቅም ለመገንባት ትኩረት ከማድረግ ባሻገር የፋይናንስ ችግሩን ለመቅረፍ የሚሰሩት ሥራ ውስን ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አቅም ለመደጎም የሚመደብ ተዘዋዋር ብድር፣ የመነሻ ካፒታል እና መንግስት የሚሰጠው ድጎማ በጣም አነስተኛ ነው፡፡

**ማነቆ 7፡- ለኅብረት ሥራ ማህበራትን ግብይት የሚያግዝ የፋይናንስ አቅርቦት አለመኖር**

የኅብረት ሥራ ግብይት በባህሪው በርካታ ፋይናንስ የሚጠይቅ ግብይት ቢሆንም የሚያስፈልገውን ፋይናንስ በወቅቱ እና በሚፈለገው መጠን ለሚፈልገው ተግባር ማግኘት አለመቻል ችግር ይታያል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አቅም ደካማ መሆን፣ ለፋይናንስ ግብይት ትስስር አሰራር በሚፈለገው ደረጃ አለመኖር፣ የፋይናንስ ተቋማት ለኅብረት ሥራ ማህበራት ግብይት ብድር ለመስጠት ፋላጎት ማጣት እና ቅድሜ ሁኔታዎችን ለኅብረት ሥራ ማህበራት ምቹ አለመሆን፡፡

መንግስት ለግብርና ምርት ግብይቱ ትኩረት በመስጠት የሚያስፈልጉ ፋይናንሶች እንዲመቻች በማድረግ በኩልም እጥረቶች ይታያሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት ጋር በመነጋገር የኮሚሽን ግብይት አሰራርን ተግባራዊ በማድረግ ችግሩን ለመቅረፍ የሚያደርጉት ጥረት አናሳ ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ ችግሮቻቸውን ለመቅረፍ የመጋዘን ደረሰኝ አገልግሎት እንዲሰጡ ሊያደርግ የሚችል አሰራር ባለመኖሩ ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ግብይት መርህን ተከትሎ አለመስራት፡፡

**ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤**

ከአጠቃላይ የአገርቱ ከሚሰበሰበው የቁጠባ መጠን ውስጥ በፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ 25 በመቶ ይሆናል፡፡ የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባለት የሚየቀርቡት የብድር አገልግሎት ድርሻ 90 በመቶ ይሆናል፡፡

**መፍትሄ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት አማራጭ የውስጥ የፋይናንስ አቅማቸውን አሟጠው መጠቀም**

**የውስጥ አቅም አሟጦ መጠቀም እንደ ዋና የፋይናንስ አማራጭ፡-**

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ አቅርቦት ለማሻሻል በተለይም ውስጣዊ የፋይናንስ ምንጮች ላይ ትኩረት ተደርጎ መሰራት ይኖርበታል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ ችግርን ለመቅረፍ የአባላት ቁጥር መጨመር እና በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሸጥ ዕጣ መጠን መጨመር፣ የሚሸጠውን የዕጣ መጠን ከሚሰጠው የብድር መጠን እና ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የሽያጭ መጠን ጋር እንዲጣጣም ማድረግ፣ የሚሰበሰበውን የቁጠባ መጠን ለመጨመር የተለያዩ የቁጠባ ዓይነቶችን ተግባራዊ ማድረግ፣ ለአባላት ቁጠባ ተመጣጣኝ ወለድ የሚከፈልበትን እና ሌሎች ጠቃሚ የአሰራር ስርዓቶች ተዘርግቶ የሚተገበርበት አቅጣጫ ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ የፋይናንስ ምንጭ የአባላት ዕጣ እንደመሆኑ በጠቅላላ ጉባዔ የታወጁ ዕጣዎችን አባላት አሟጦ እንዲገዙ ይደረጋል፡፡ የካፒታል እጥረት ሲያጋጥም እንደ አስፈላጊነቱ ለጠቅላላ ጉባዔው በማቅረብ ተጨማሪ ዕጣዎችን በማወጅ እንዲሸጥ ይደረጋል፡፡

በተጨማሪም እንደ አስፈላጊነቱ በሕግ በሚቀመጠው አሰራር እና ጥናት ላይ በመመስረት የኅብረት ሥራ ማህበራትን መርሆ ሳይጻረር እና የኅብረት ሥራ ማህበራትን ህልውናና ጥቅም በማይነካ ሁኔታ የካፒታል እጥረት ስያጋጥመውና በጠቅላላ ጉባዔ ስወሰን አባል ላልሆኑት ግለሰቦች እና ተቋማት ዕጣ የሚሻጥበት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በየዓመቱ ከሚያገኙት ትርፍ ውስጥ የተወሰነውን በመቀነስ ለሥራ መስፋፊያ እንዲያስቀምጡ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ ችግሮቻቸውን በራሳቸው እንዲቀርፉ ለማድረግ ሁሉም የኅብረት ሥራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩንዬን አባል በመሆን መደበኛ ቁጠባ እንዲቆጥቡ እንዲሁም ሌሎች ሂሳቦቻቸውንም በዚያው የሚያንቀሳቅሱበት እና ብድር ሲያስፈልጋቸው የሚበደሩበት አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ ማስፋፊያ፣ ለማህበራዊ ልማት እና ለሌሎች ጉዳች የሚመደብ ገንዘብ ሥራ ላይ ሳይውል ለረጅም ጊዜ የቆዩ ተካባች ሂሳቦች ወደ አባላት ዕጣ ዞሮ ሥራ ላይ የሚውልበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ እጥረት

ከሚያጋጥማቸው ወቅቶች አንዱ በምርት ግብይት ላይ በመሆኑ የኮሚሽን ግብይት ሥርዓትን ተግባራዊ በማድረግ የውስጥ የፋይናንስ ችግሮችን ለመቅረፍ ይሠራል፡፡

**መፍትሄ 2፡- የቁጠባ ባህል ለማሳደግ ጠንካራ የፋይናንስ ክህሎት ማበልጸጊያ ሥርዓት መዘርጋት፤**

**የቁጠባ ባህልን ማሳደግ፡-** በአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ የሕብረተሰቡ የቁጠባ በህል ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የተናጠል የቁጠባ መጠን እጅግ አናሳ ነው፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የተለያዩ የግንዛቤ ማበልጽጊያ ተግባራትን በማዘጋጀት ሰፊው የሕብረተሰብ ክፍል ለመድረስ የተለያዩ አሰራሮች ተነድፎ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በቁጠባ ላይ ጥሩ ተሞክሮ ያላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት እና ግለሰቦች ተሞክሮ ተቀምሮ ወደ ሌሎች የሚስፋፋበት አሰራር ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራው የሚከናወነው የተለያዩ የንቅናቄ መድረኮችን፣ በአገርቱ ውስጥ ያሉ ኤለክትሮንክ እና ሕትመት ሚዲያዎችን በመጠቀም የሕብረተሰቡን በቁጠባ ላይ ያለውን ግንዛቤ የማሳደግ ሥራ ይሰራል፡፡ በዚህም በገጠር ያለው ሕብረተሰብ ከሚያገኘው ገቢ ጋር የሚመጣጠን የቁጠባ መጠን እንዲኖር በትኩረት ይሰራል፡፡

የሕብረተሰቡን የግንዛቤ ደረጃ ሊመጥን የሚችል የተለያዩ የፋይናንስ ክህሎት ማበልጽጊያ ሰነዶች ተዘጋጅቶ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ ሕብረተሰቡ ከታች ጀምሮ የቁጠባ ጠቃሜታ በማወቅ ተግባራዊ እንዲያደርግ ለማስቻል በሐይማኖት ተቋማት፣ በትምህርት ቤቶች የኅብረት ሥራ ክበባትን በማቋቋም፣ ባሕላዊ ህብረቶችን በመጠቀም ግንዛቤ እንዲያገኙ የሚያስችል አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

ሕብረተሰቡን ስለቁጠባ ባህል የሚያስተምሩ ጠንካራ ባለሙያዎች በየቀበሌው በመመደብ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ የሕብረተሰቡን የቁጠባ ባህል ለማሳደግ እንዲቻል በየደረጃው ከሚገኙት መንግስታዊ እና ማንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር በመቀናጀት የግንዛቤ መፍጠር ሥራው በስፋት ይሰራል፡፡

**መፍትሄ 3፡- የፋይናንስ አገልግሎቶች ለማስፋፋት የተቀመጡ አቅጣጫዎች፣**

**የፋይናንስ አገልግሎትን ማስፋፋት፡-** የኅብረት ሥራ ማህበራት አርሶ/አርብቶ አደሩ እና የከተማውን ነዋር የሕብረተሰብ ክፍሎችን የፋይናንስ እጥረት በመቅረፍ፣ ለግብይቱ ዘመናዊ የክፍያ አሰራርን በመዘርጋት በተለይም የሴቶች እና የወጣቶችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ የብድር ዓይነቶች ላይ በማተኮር አገልግሎቱን የማስፋፋት ሥራ ይሰራል፡፡

ኅብረት ሥራ ማህበራት በገጠር የግብርና ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ለአርሶ/አርብቶ አደሩ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች መግዣ የሚሆነውን ፋይናንስ በማመቻቸት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ አባላት

ከምርታቸው ተጠቃሚ እንዲሆንና በተሻለ ለማምረት እንዲነሳሱ ለማድረግ የግብርና ምርት ግብይቱ እንዲሳለጥ የፋይናንስ ችግርን ለመቅረፍ አስፈላጊውን ፋይናንስ በወቅቱና በሚፈለገው መጠን በማመቻቸት ረገድ ሚናቸውን እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

በተጨማሪም ግለሰብ አባላት ለሚያስፋፏቸው የሥራ መስኮች ለሚጠይቁት ፋይናንስ በመለየት እንዲያቀርቡ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የግብርና ምርት በዋጋ ተወዳዳር ሆኖ አምራቹ ከምርቱ የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆንና በአገር ኢኮኖሚ ግንባታ ላይ የራሱን ስተዋጽኦ እንዲያበረክት ለማድረግ ከአባላት የግብርና ምርት ለማሰባሰብ እና እሴት ለመጨመር የሚያስፈልገውን ፋይናንስ የማመቻቸት ተግባር ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት ያላቸው ድርሻ ትልቅ በመሆኑ በአግባቡ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

በከተማ የሚኖር የሕብረተሰብ የመኖሪያ ቤት እጥረት፣ በተለያዩ የኢንቨስትሜን ዘርፎች ውስጥ ተሳትፎ የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን ፋይናንስ ማግኘት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የአባላትን ፍላጎቶችን መሠረት በማድረግ ለቤት ግንባታ፣ ለቁሳቁስ ማሟያ፣ ለተሽከርካሪ ግዥ እና ለሌሎች ንግድ ሥራዎች የሚሆን ብድር ለማመቻቸት እንዲቻል የብድር አገልግሎቶችን ማስፋፋት ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡

በየደረጃው ያለውን ማስፋፊያ አካላት እና የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለማስፋፋት ያለባቸውን የክህሎት እና የግንዛቤ ችግሮችን በመለየት እንዲፈታ ይደረጋል፡፡ የተሻለ ልምድና ተሞክሮ ያላቸውን ኅብረት ሥራ ማህበራትን በመለየት የልምድ ልውውጥ እንዲያደረጉ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አገልግሎት በራሳቸው አቅም የማስፋፋት ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ዘርፉን በተሻለ ለማጠናከር መንግስት፣ ባለድርሻ አካላት፣ አቅም ገንቢዎች እና ዓለም አቀፍ የልማት አጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር የመነሻ ካፒታል፣ ብድር እና ተዘዋዋሪ ፈንድ እንዲመቻች ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈጠሩ የሚችሉ አደጋዎችን ለመቀነስ የአጠቃላይ መድን ኢንሹራንስ አገልግሎት እና አነስተኛ መድን ዋስትና አገልግሎት እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ በሌላ በኩል የኅብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ አቅም ለማዳበር የሚያስችሉ አሰራሮች በመንደፍ ከአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች፣ የመንደር ቁጠባዎች፣ ዕቁብ፣ ዕድር እና ሌሎች ማህበራዊ አደረጃጀቶች ጋር ተቀራርቦ በመስራት የፋይናንስ አቅማቸውን የሚያሳድጉበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

**መፍትሔ 4፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የርስ በርስ የፋይናንስ ግብይት ትስስር አሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣**

**ኅብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ ግብይት ትስስርን ማጠናከር፡-** በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የኅብረት ሥራ ማህበራት የማይንቀሳቀስ ገንዘብ ክምችት እና እጥረት ችግር የሚያጋጥመው እንደየአባላት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሁኔታ ነው፡፡ በመሆኑም የኅብረት ሥራ ማህበራት የገንዘብ እጥረት ወይም የማይንቀሳቀስ የገንዘብ ክምችት ሲያጋጥማቸው የሁለቱንም ጥቅም ሊያስከብር በሚችል መልኩ የርስ በርስ የግብይት ትስስር ፈጥረው ገንዘቡን የሚጠቀሙበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በከተማ የሚገኙ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የማይንቀሳቀስ የገንዘብ ክምችት ስለሚያጋጥማቸው የከተማ እና የገጠር የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ ግብይት ትስስር እንዲጠናከረ የሚያስችል አሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ በተለይም የግብርና ምርት ግብይት፣ የማዕድን ማምረት ተግባር ላይ የተሰማሩ ኅብረት ሥራ ማህበራት እና ሌሎችም የሚያንቀሳቅሱት ገንዘብ ወቅታዊ በመሆኑ ገንዘባቸው በማይንቀሳቀስበት ወቅት ሌሎች እጥረት ከሚገጥማቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የፋይናንስ ግብይት ትስስር ፋጥረው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

በአገራችን በመተግበር ላይ ያለው የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች አቅርቦትና ሥርጭት input voucher system በመጠቀም ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ጠንካራ የፋይናንስ ግብይት ትስስር በመፍጠር እንዲሰሩ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የኮሚሽን ግብይት አሰራርን ተከትሎ የሚሰሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ጠንካራ የፋይናንስ ግብይት ትስስር በመፍጠር የተሰበሰበው ምርት ተሸጦ ገንዘቡ ለአምራቹ እስከሚመለስ ድረስ ለአባላት የሚከፈለውን ቅድሚያ ክፍያ የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲያመቻቹ የሚያደርግ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖች እና ኅብረት ሥራ ሊግ ዓለም አቀፋ የፋይናንስ ተቋማት እና ከትላልቅ ለጋሽ ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር የፋይናንስ ድጋፍ (Grant loan) በማምጣት ኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ ችግር ለመቅረፍ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ዓለም አቀፋ የፋይናንስ ተቋማት ጋር በመቀናጀት በፋይናንስ ግብይት የማስተሳሰር ሥራ ይሰራሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የርስ በስር የሚያደርጉት የፋይናንስ ግብይት ትስስር ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የሚመለከታቸው የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡ በዚህ መሠረት የሚደረግ የፋይናንስ ግብይት ትስስር የሕብረተሰቡን የፋይናንስ ችግር ለመቅረፍ ያለው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን በመረዳት ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትም ድጋፍ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

**መፍትሔ 5፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚያደርጉት የፋይናንስ ግብይት ትስስርና ግንኙነት ማጠናከር፣**

የፋይናንስ ተቋማት እና ኅብረት ሥራ ማህበራት የሕብረተሰቡን የፋይናንስ ችግር ለመቅረፍ ጠንካራ ግንኙነት እና አብሮ የመስራት ባህልን ማዳበር አለባቸው፡፡ ጠንካራ እና ቀጣይነት ያለው የፋይናንስ ግብይት ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል ወጥነት ያለው የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ ሁለቱም ተቋማት የሚያደርጉት የግብይት ትስስር ዘለቄታ ያለው የጋራ ተጠቃሚነትን ሊያረጋግጥ በሚችል መልኩ በጠንካራ ውል ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ባንኮች እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ጠንካራ የፋይናንስ ግብይት ትስስር በመፍጠር ለአርሶ/አርብቶ አደሩ እና የከተማ ነዋሪውን የሕብረተሰብ የፋይናንስ እጥረት ለመቅረፍ ተቀራርቦ እና ተቀናጅተው እንዲሰሩ የሚያደርግ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት እና የፋይናንስ ተቋማትን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ የወለድ መጠን ጥናት ላይ በመመስረት እንድተገበር ይደረጋል፡፡ በተለይም የብድር ዋስትና ችግርን ለመፍታት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት የሚሰበስቡት የዕጣ ገንዘብ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ካፒታል ሆኖ የሚያገልግል በመሆኑ በባንኮች ውስጥ ለብቻ በማስቀመጥ ባንኩ ለብድር ዋስትና የሚጠቀምበት አሳራር ተዘርግተው እንዲተገበር ይደረጋል፡፡ የአነስተኛ የብድርና ቁጠባ ተቋማት ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የፋይናንስ ግብይት ትስስር በማድረግ የሁለቱንም አካላት የጋራ ጥቅም የሚያስጠብቅ አሰራር በማስቀመጥ አብሮ ተባብሮ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች ፋይናንስ ተቋማት ጋር የሚኖራቸው የፋይናንስ ግብይት ትስስር ግንኙነት በታማኝነት ላይ የተመሰረተ እና ብድር ወስዶ በወቅቱ ተጠቅሞ በመመለስ የመተቀም መሪህ መሠረት አድርጎ ዘላቅነት ያለው እንዲሆን ይሰራል፡፡ የግብይት ትስስር ሲፈጸም የሁለቱንም አካላት የውስጥ አሰራር ሳይጥስ በጥንቃቄ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

በፋይናንስ ተቋማት እና በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚደረገው የፋይናንስ ግብይት ትስስር ብድር ከማመቻቸት ባለፈ በአጠቃቀሙ ላይ የቴክኒክ ዕገዛ ማድረግ፣ ማማከር እና የመሳሰሉ ድጋፎችን ያካተተ ይሆናል፡፡ ኅብረት ሥራ ማህበራት እና የፋይናንስ ተቋማት የሚያደርጉት የፋይናንስ ግብይት ትስስር ዘላቅነት እንዲኖረው ለማድረግ የፋይናንስ ትስስር የጋራ መድረክ በመፍጠር እየተገናኙ የሚወያዩበት እና የጋራ አቅጣጫ በማስቀመጥ የሚሰሩበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### መፍትሔ 6፡- መንግስትና ሌሎች አቅም ገንቢ አካላት ለኅብረት ሥራ ማህበራት በቂ የፋይናንስ ድጋፍ ማድረግ



DRAFT

የኅብረት ሥራ ማህበራት አቅም ግንባታ ላይ የተሰማሩ አካላት የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራር አካላት እና ቅጥር ሰራተኞች የማስፈጸሚ እና የመፈጸም አቅም በመገንባት የሚያጋጥማቸውን የፋይናንስ ማነቆ መፍታት ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

መንግስት የኅብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ አቅም ለመደገፍና ለማጠናከር የፋይናንስ አቅም ሊያዳብሩ የሚችሉ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ እና የመነሻ ካፒታል የሚያገኙበትን ፈንድ በማቋቋም የተገኘውን ገንዘብ በረጅም ጊዜ ብድር ለኅብረት ሥራ ማህበራት በመስጠት ተጠቅሞ በወቅቱ እንዲመልሱ በማድረግ በሂደት ፕሮጀክቱን ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያሰረክቡበት አሰራር ይፈጠራል፡፡

መንግሥት ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያስፈልጉ የመሰረተ ልማቶችን በጥናት በመለያት መሠረታዊ የሆኑ መሰረተ ልማቶችን ገንብቶ በብድር መልክ ለኅብረት ሥራ ማህበራት በመስጠት በየዓመቱ በረጅም ጊዜ ገደብ ብድሩ የሚመልስበት አሠራር በመቅረጽ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ በሌላ በኩል መንግሥት ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያስፈልገውን ፋይናንስ ከፋይናንስ ተቋማት እንዲያገኙ ወሳኝ ለሆኑና የአባላትና የሕብረተሰቡን መሠረታዊ ችግሮች በዘላቅነት ለሚፈቱ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች የሚያስፈልገውን የብድር ዋስትና ከፋይናንስ ተቋማት እንዲያገኙ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

### መፍትሄ 7፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ግብይት የሚያግዝ የፋይናንስ አቅርቦት ማሻሻል

**የኅብረት ሥራ ማህበራት ግብይት የፋይናንስ አቅርቦት ማሻሻል፡-** የኅብረት ሥራ ግብይት በባህሪው በርካታ ፋይናንስ የሚጠይቅ በመሆኑ የውስጥ አቅማቸውን አሟጦ በመጠቀም የሚያስፈልጋቸውን ፋይናንስ እንዲያፈላልጉ ማድረግ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ያለባቸውን የውስጥ የፋይናንስ ችግር መፍታት እንዲቻል የአባላትን አቅም አሟጦ በመጠቀም እና ሌሎች አማራጮችን በመለየት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡ ለዚህም የአባላትን ግንዛቤ በማሳደግ የታወጁ ዕጣዎችን አሟጦ እንዲገዙ በማድረግ እና እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ዕጣዎችን በጠቅላላ ጉባዔ አቅርቦ በማሳወጅ እንዲሸጥ በማድረግ የውስጥ አቅምን የማጠናከር ሥራ በስፋት ይሰራል፡፡

በግብይት ላይ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት እና የኅብረት ሥራ ባንክ አባል በመሆን መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ቁጠባዎችን በመቆጠብ የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ አቅም በማሳደግ የሚያስፈላጋቸውን ፋይናንስ በብድር የሚያገኙበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከፋይናንስ ተቋማት ጋር የሁለቱንም ተቋማት ተጠቃሚ የሚደርግ እና የኅብረት ሥራ ማህበራትን መርህ በማይጻረር መልኩ የፋይናንስ ግብይት እንዲተሳሰሩ የሚያስፈልገውን ፋይናንስ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በግብይት ውስጥ ዋናኛው ሥራቸው ለአባላት ምርት የተሻለ ገበያ በማፈላለግ እንዲሸጥ በማድረግ የአባላት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም አባላትን በማሳመን የኅብረት ሥራ ማህበራት የኮሚሽን ግብይትን ተግባራዊ በማድረግ ለግብይት የሚያስፈልገውን ፋይናንስ በመቀነስ ምርቱን ከአባላት በመረከብ እና በመሸጥ ለአባላት የሚከፍሉበት አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ኅብረት ሥራ ማህበራት የኅብረት ሥራ ግብይት መርህን ተግባራዊ በማድረግ የነበሩ ልምዶችን እጠናክሮ በማስቀጠል የዱቤና የቅደመ ክፍያ አሰራርን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

የኅብራት ሥራ ማህበራት አባላት የግብርና ምርቶቻቸውን በማስያዣነት በመጠቀም የሚፈልጉትን ፋይናንስ ለማግኘትና የምርት ብክነትን ለመከላከል የሚያስችል ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖችን በመገንባት መጋዘኑን በሕጋዊ አካል በማስመዝገብ በሚዘረጋው የመጋዘን ደረሰኝ አሰራር መሰረት የመጋዘን ደረሰኝን እንደ ዋስትና በመጠቀም ከፋይናንስ ተቋማት የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በገበያ ላይ ተፈላጊ የሆኑ የአባላት ምርቶችን በቅዲሚያ በመለያት እና በማስተዋወቅ ምርቱን ከሚፈልጉ አካላት ጋር የኮንትራት ውል (contract farming) በመግባት ሽጦ የማምረት አሰራርን እንዲከተሉ ይደረጋል፡፡

## አምድ 24፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የሀብት አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል፣

### *ሀ. ነባራዊ ሁኔታ*

የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሮቻቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የሚያጋጥማቸውን ችግር መቋቋሚያ የመጠባበቂያ ገንዘብ እንዲያስቀምጡ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መጠባበቂያ ሂሣብ ውስጥ የተመዘገበ፣ በስጦታ ወይም በውርስ የተገኘ ንብረት እና በኅብረት ሥራ ማህበራት ፈንድ ሂሳብ ውስጥ ከተመዘገበው ገንዘብ ውጭ ያሉ የወል ንብረቶች የኅብረት ሥራ ማህበሩ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈርስ ከሆነ ለአባላት የሚከፋፈል እንደደሆነ ይታወቃል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሲቋቋሙ ወይም ለሚያከናውኗቸው ተግባራት የሚያግዙ የተለያዩ ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ሀብት በስጦታ፣ በውርስ፣ በሽልማት እና በልገሳ ያገኙዋቸውን የጋራ ንብረቶች በማንኛውም ጊዜ የማይከፋፈሉ እና በጋራ የሚተዳደሩ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል የኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራዎቻቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት በሚደረጉ ግብይቶች፣ በትርፍ ክፍፍል በወቅት ለአባላት ሳይከፋፈል የሚቀር ገንዘብ፣ ለመጠባበቂያ የሚቀነስ ገንዘብ በአግባቡ ማስቀመጥ ባለመቻል፣ ለማህበራዊ አገልግሎቶች የሚመደብ ገንዘብ በዋቅቱ ሥራ ላይ ማዋል ካለመቻል እና በተለያዩ ምክንያቶች በኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የሚከማች ገንዘብ ይታያል፡፡ ጥቅም ላይ ያልዋለውን ገንዘብ አሰራር በአግባቡ ባለመዘርጋቱ ምክንያት ለተለያዩ ምዝበራ እና ብክነት ከመዳረጉ በላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ የተስተካከለ እንዳይሆን አድርጎዋል፡፡

የሌሎች አገሮች ተሞክሮ እንደሚያሳየው የኅብረት ሥራ ማህበራት የጋራ ችሮቻቸውን በጋራ ለማፍታት የኅብረት ሥራ ፈንድ በማቋቋም ውጤታማ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ በአገራችን ፋንዱን ለማቋቋም የተሰራ ሥራ ባይኖርም የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ በመውሰድ የኅብረት ሥራ ፈንድ ለማቋቋም የሚፈቅድ የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ጠንካራ የኅብረት ሥራ ፈንድ በማቋቋም ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአቅም ግንባታ ተግባራት፣ ለኦዲት እና ሌሎች በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ለሚወስናቸው ተግባራት ላይ በማዋል ችግሮቻቸውን እንዲፈታ መደረግ ይኖርበታል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያከናውኑት ተግባር እየሰፋ ሲሄድ የሚያስተዳድሩት ንብረትም በዚያው ልክ እየበዛ መሄዱ አይቀርም፡፡ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በአገራችን ተደራጅቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያንቀሳቅሱት ንብረት ብዛት እና ዓይነት በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡ በእሴት መጨመር ተግባራት ላይ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ያላቸው ፋብሪካዎች እና ተያያዥ ንብረቶች እየበዛ ስለሆነ ጠንካራ አሰራር ካልተዘረጋ ለማስተዳደር አዳጋች ይሆናል፡፡ በአገር ውስጥ እና በውጭ ግብይት ላይ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለትራንስፖርት አገልግሎት የሚጠቀሙበት ተሽከርካሪ በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡

በአገልግሎት ዘርፍ የተደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት እና ለሕብረተሰቡ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል በርካታ ንብረቶችን በማስተዳደር ላይ ይገኛሉ፡፡ ንብረቶቹን በአግባቡ ማስተዳደር የሚያስችል ጠንካራ እና ወጥነት ያለው የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ማስተዳደር ካልተቻለ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለኪሣራ በመዳረግ ህልውናቸው ላይ አሉታዊ ተጽኢኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

### ለ. የኅብረት ሥራ ማህበራት የሀብት አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዓት ላይ ያሉ ማነቆዎች

**ማነቆ 1፡- ኅብረት ሥራ ማህበራት የመጠባበቂያ ሂሳብ፣ የማይከፋፈሉ የወል ንብረቶች እና ተካባች ሂሳቦች አጠቃቀምና አስተዳደር አሰራር አለመዘርጋት**

የኅብረት ሥራ ማህበራት የመጠባበቂያ ሂሳብ በየዓመቱ ከሚገኘው ትርፍ ላይ ተቀንሶ ለሚያጋጥሙ ችግሮች መቋቋሚያ እንዲውል የተቀመጠ አሰራር ቢኖርም ተግባራዊ እየተደረገ አይደለም፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የማይከፋፈሉ የዋል ንብረቶች አስተዳደርን በተመለከተ የተቀመጠ አሰራር ባለመኖሩ የተነሳ ለተለያዩ ችግሮች በመጋለጥ ላይ ይገኛል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሮቻቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት አለግባብ የሚከማቹ ሂሳቦች በመኖራቸው ምክንያት እና አጠቃቀማቸው ምን መሆን እንደለበት የተቀመጠ አሰራር ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ ለተለያዩ ብክነቶች እና ኪራይ ሰብሳቢነት ድርግቶች ጭምር በመጋለጥ ላይ ይገኛል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያከፋፍሉት ትርፍ ክፍፍል ግለሰብ አባላት ጋር በቀጥታ የሚደርስበት ግልጽ አሠራር አልተዘረጋል፡፡ የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ አናሳ ነው፡፡ የወል ንብረቶች የዕድሜ ቆይታቸውን ያገናዘቤ የእርጅና ተቀናሽ እና አገልግሎታቸውን የጨረሱ ንብረቶች ደግም አገልግሎት እንዲሰጡ ወይም እንዲወገዱ የሚያደርግ አሰራር ተግባራዊ አለማድረግ፡፡

## ማነቆ 2፡ የኅብረት ሥራ ፈንድ አደረጃጀት፣ አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዓት አለመዘርጋት

የኅብረት ሥራ ፈንድ አደረጃጃት፣ አጠቃቀምና አስተዳደር ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ የኅብረት ሥራ ፈንድ የሚፈታቸው ችግሮች ላይ ለሚመለከታቸው አካላት በቂ ግንዛቤ አልተፈጠረም፡፡ ፋንዱን በበላይነት የሚመራና የሚያስተዳድር ተቋም አለመደራጀት ሌላው ማነቆ ነው፡፡

## ማነቆ 3፡- ጠንካራ የኅብረት ሥራ ማህበራት የንብረት አያያዝ አስተዳደር ስርዓት አለመኖር

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ ዘርፍ እና ያሚያስተዳድሩትን የንብረት ዓይነት የሚመጥን ጠንካራ የንብረት አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ ንብረቱን ሊያስተዳድር የሚችል የሰለጠነ የሰው ኃይል አደረጃጀት አለመኖር ሌላው ማነቆ ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ንብረት ለኅብረት ሥራ ማህበራት ብቻ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያስገድድ ጠንካራ አሰራር አልተዘረጋም፡፡ የንብረት ቁጥጥሩ በሚፈለገው ደረጃ ጠንካራ አይደለም፡፡ አንዳንድ መሳሪያዎች እና ማሽነሪዎች በሚገዙበት ወቅት በኅብረት ሥራ ማህበራት ተጨባጭ ሁኔታ መስራት አለመስራቱ ሳይረጋገጥ የሚገዙ ስለሆነ በሥራ ላይ ችግር ስፍጥሩ ይታያል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለንብረታቸው ኢንሹራንስ እንዲገቡ የሚያስገድድ አሰራር አለመኖር ሌላው ችግር፡፡

## ማነቆ 4፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት የንብረት እና የሀብት ብክነት መኖር፤

የኅብረት ሥራ ማህበራት ንብረቶችን ከዓላማ ውጭ በማዋል ለብክነት የሚዳረጉበት ሁኔታ በስፋት ይታያል፡፡ ለተሽከሪካሪዎች አጠቃቀም የተዘረጋ አሰራር የለም፡፡ በልዩ በሕሪያቸው አጠቃቀማቸው በባለሙያ እንዲሆን የሚያስገድድ አሰራር ያላቸው ቢሆንም ሙያው በሌለው ሰው የሚንቀሳቀስ በመሆኑ ንብረቱ ብዙም አገልግሎት

ሳይሰጥ ለብልሽት ሲዳረግ ይታያል፡፡ ንብረቶች ስበላሹ በቀላሉ ተጠግኖ ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቢሆንም መለዋወጫ ባለመኖሩ፣ ጠግኖ ወደ ሥራ ሊያስገባ የሚችል የሰለጠ የሰው ኃይል በምፈለገው ደረጃ የለም፡፡ በመሆኑም በትናንሽ ብልሽት ምክንያት አገልግሎት ሳይሰጡ ለረጅም ጊዜ ስለሚቆዩ ከጥቅም ውጭ እየሆኑ ነው፡፡

**ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የምንከተላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤**

**መፍትሔ 1፡- ኅብረት ሥራ ማህበራት የመጠባበቂያ ሂሳብ፣ የማይከፋፈሉ የወል ንብረቶች እና ተካባች ሂሳቦች አጠቃቀምና አስተዳደር አሰራር መዘርጋት፣**

**መጠባበቂያ ሂሳብ፣ የማይከፋፈሉ የወል ንብረቶች እና ተካባች ሂሳቦች አጠቃቀምና አስተዳደር፡-**

የኅብረት ሥራ ማህበራት በየዓመቱ ኦዲት ተደርጎ ከሚገኘው ትርፍ ለመጠባበቂያ የሚቀመጠው ገንዘብ ተቀንሶ በአግባቡ ተለይቶ እንዲቀመጥ በማድረግ በሚቀመጠው የአሰራር መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ የመጠባበቂያ ሂሳብ አቀማመጥ በአሰራር ከተቀመጠው ጣሪያ በላይ እንዳይሄድ አስፈላጊው ቁጥጥር እና ክትትል ይደረጋል፡፡

ከተገኘው ትርፍ ላይ ለአባላት የሚከፋፈለው የትርፍ ክፍፍል አባላት የገዙት የዕጣ መጠን እና ያደረጉት ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ መሠረት በማድረግ በወቅቱ ሳይከማች እንዲከፋፈል ይደረጋል፡፡ ሆኖም አባሉ ካገኛው ትርፍ ክፍፍል ላይ የኅብረት ሥራ ማህበሩን አሠራር ተከትሎ ተጨማሪ ዕጣ ለመግዛት ፍላጎት ያለው ከሆነ ዕጣውን በመግዛት የነበረውን የዕጣ መጠን ማሳደግ ይችላል፡፡ ለዚህም የዕጣ ሰርቴፍከት ያገኛል፡፡

በመጠባበቂያ የሚቀመጠው ገንዘብ የኅብረት ሥራ ማህበሩ በሥራ ላይ እያለ ለሚያጋጥመው አደጋ ወይም ኪሳራ ማካካሻ ስለሆነ አንድ አባል በኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ እያለ ምንም ችግር ካልተከሰተ እና አባሉ መልቀቅ ከፈለገ ለመጠባበቂያ ከተቀመጠው ሂሳብ ውስጥ የድርሻው ተሰልቶ የሚሰጥበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

ከኅብረት ሥራ ማህበራት በስጦታ ወይም በውርስ ካገኘው ንብረቶች እና በኅብረት ሥራ ማህበራት ፈንድ ውስጥ ከተመዘገበው ገንዘብ ውጭ ያሉ የወል ንብረቶች የኅብረት ሥራ ማህበሩ በተለያዩ ምክንያቶች ከፈረሰ ለአባላት ንብረቱ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፋፈል ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ለወል ንብረቶች አስተዳደር እና አጠቃቀም ጠንካራ አሰራር በመዘርጋት በየትኛውም መንገድ የሚገኝ ንብረት የጠቅላላ ጉባዔ እውቅና እንዲኖር በማድረግ በአግባቡ ተመዝግቦ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

በትርፍ ክፍፍል በወቅት ሳይከፋፈል የሚቀር ገንዘብ፣ ለመጠባበቂያ የሚቀነስ  በአግባቡ ባለማስቀመጥ፣ ለማህበራዊ አገልግሎት የሚመደብ ገንዘብ በተለያየ ምክንያት በወቅቱ ሥራ ላይ ሳይውል በኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የተከማቸ ገንዘብ እንዳይኖሩ ለማድረግ ጠንካራ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ አገልግሎት ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ እንዲሁም የኅብረት ሥራ ማህበራት በየዓመቱ ከሚያገኙት ትርፍ ለግለሰብ አባላት በቀጥታ የሚደርስበት ወጥ የሆነ አሰራር ተዘርግቶ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

በተጨማሪም በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ የተፈጠሩ ተካባች ገንዘብ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ንብረት ስለሆነ ወደ ገንዘብ በመለወጥ እያንዳንዱ አባል በኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ ባላቸው ድርሻ እና ተሳትፎ መሠረት ወደ ዕጣ እንዲዞርላቸው በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ካፒታል ሆኖ እንዲያገለግል ይደረጋል፡፡

የወል ንብረቶች የዕድሜ ቆይታቸውን ያገናዘቤ የእርጅና ተቀናሽ እና አገልግሎታቸውን የጨረሱ ንብረቶች ደግም አገልግሎት እንዲሰጡ ወይም እንዲወገዱ የሚያደርግ አሰራር ተዘርግቶ ይተገበራል፡፡

### መፍሄ 2፡- የኅብረት ሥራ ፈንድ አደረጃጀት፣ አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት፤

**የኅብረት ሥራ ፈንድ አጠቃቀምና አስተዳደር ፡-** የኅብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት፣ የሕግ አገልግሎት፣ የአቅም ግንባታ፣ የጥናት እና ምርምር፣ ራሳቸውን የማስተዋወቅ እና የመሳሰሉትን ወጪዎችን ለመሸፈን የሚረዳ የኅብረት ሥራ ፈንድ እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ፈንዱ ተቋቁሞ አገልግሎት እንዲሰጥ ከተደረገ በአሁኑ ወቅት መንግስት የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማጠናከር የሚያወጣውን ወጭ በማስቀረት የኅብረት ሥራ ማህበራት ውጤታማ ስለሚያደርግ በትኩረት ይሰራል፡፡ ለኅብረት ሥራ ፋንድ አደረጃጀት፣ አጠቃቀምና አስተዳደር የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ፈንዱ የሚቋቋመው በአገርቱ ውስጥ ተደራጅቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ በሚገኙ በሁሉም የኅብረት ሥራ ማህበራት ተሳትፎ በመሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራቱን በማስተባበር እንዲቋቋም አስፈላጊ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የፈንዱ የፋይናንስ ምንጭ በየደረጃው ከተደራጁ የኅብረት ስራ ማህበራት ዓመታዊ ትርፍ፣ ከሚፈርሱ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከማይከፋፈል የጋራ ገንዘብና ንብረት፣ ህጋዊ ከሆኑ የገቢ ምንጮች ከሚገኝ፣ ከልማት አጋር አካላት በስጦታና በድጋፍ ከሚሰጥ ፋይናንስ ድጋፍ እና ከመሳሰሉት ምንጭ የገቢ ምንጮች በመሆኑ እንዲሰባሰብ ክትትል እና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የፈንዱ አስተዳደር በተመለከተ በሚቀመጠው የሕግ አግባብ መሠረት እንዲደራጅ በማድረግ ተቋሙ ጠንካራ እና ችግር ፈች ተቋም እንዲሆን አስፈላጊው ድጋፍ እና ክትትል ይደረጋል፡፡

### መፍትሄ 3፡- ጠንካራ የኅብረት ሥራ ማህበራት የንብረት አያያዝ አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት፣

**የኅብረት ሥራ ማህበራት የንብረት አያያዝና አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት፡-**

የኅብረት ሥራ ማህበራት ብዛት እና የሚሰጡት አገልግሎት ዓይነት ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያስተዳድሩት ንብረት ብዛት እና ዓይነት እየበዛ ስለሆነ የንብረት አስተዳደሩ ውስብስብ ይሆናል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የንብረት አያያዝ እና አስተዳደር ችግር ለመፍታት በቂ ጥናት በማድረግ የንብረቱን ዓይነት እና በህሪይ ሊመጥን የሚችል  የንብረት አያያዝ እና አስተዳደር የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚገለገሉባቸው ንብረት ዓይነት እና ብዛት እየጨመረ በሚሄድበት ወቅት የንብረት አስተዳደር ሥራ ውስብስብ ስሚሆን በሙያው የሰለጠ የሰው ኃይል የሚፈልግ በመሆኑ የሰለጠ የሰው ኃይል በመቅጠር እንዲጠቀሙ የማድረግ ሥራ በትኩረት ይሰራል፡፡ ለኅብረት ሥራ ማህበራት የንብረት ቁጥጥር ችግርን ለመቅረፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ የንብረት  ቁጥጥር እንዲጠናከር በማድረግ የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላትም ያላቸውን መዋቅር በማጠናከር ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

ኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያግዙ ንብረቶች ሲገዙ የሥራውን በህሪ በአግባቡ በማጥናት የዕቃውን ዓይነት ዝርዝር መስፈርቶችን በማዘጋጀት መስራቱ እና አለመስራቱን በባለሙያ በማረጋገጥ እንዲገዙ የሚያደርግ አሰራር ተዘርግቶ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በንብረት ላይ ሊደርስ የሚችል የአደጋ ስጋትን ለመቀነስ ለንብረቶቻቸው ኢንሹራንስ የሚገቡበት አሰራር በማስቀመጥ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የአገልግሎት ጊዜያቸውን የጨርሱ ቋሚ ንብረቶች የሚወገዱበት ግልጽ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እንዲደረግ በትኩት ይሰራል፡፡

**መፍትሄ 4፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት የንብረት እና የሃብት ብክነት ችግርን መፍታት፤**

የኅብረት ሥራ ማህበራት ንብረት ሲገዛ ዓላመው የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባራት በማከናወን ችግሮቻቸውን እንዲፈታ በመሆኑ ንብረቱ አገልግሎት መስጠት ያለበት ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ተግባር ብቻ እንዲሆን የሚያስገድዱ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

አንደንድ ማሽኖች እና የመገልገያ መሳሪያዎች በባህሪያቸው በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል የሚፈልጉ ቢሆንም ሙያው በሌላቸው ሰዎች እንዲሰሩ እየተደረገ ለረጅም ጊዜ ሊያገለግሉ የሚችሉ ዕቃዎች በቀላሉ ተበላሽቶ ከጥቅም ውጭ የሚሆንበት ሁኔታ እያጋጠመ በመሆኑ ልዩ ሙያ የሚያስፈልጋቸው መሣሪያዎች በሙያው በሰለጠኑ ባለሙያዎች ብቻ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

በተለይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽኖች፣ ዩኒዬኖች እና አቅም ያላቸው መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በማሽን ጥገና ላይ ሙያ ያላቸው ባለሙያዎችን በመቅጠር እና በማሰልጠን የማሽኖቹን በህሪ በማጥናት የሚያስፈልጉ መለዋወጫዎችን በማቅረብ የጥገና አገልግሎት የሚሰጡበት አሰራር ተዘርግቶ ይተገበራል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ንብረት ለመቆጣጠር፣ ንብረቱ ያለበት ደረጃ ለማወቅ እና መረጃውን ለማወቅ ንብረቱን ብክነት እና ምዝበራን ለመከላከል ዓመታዊ የቆጠራ ስርዓት (inventory) ተግባራዊ እንዲሆን በትኩረት ይሰራል፡፡

ክፍል ስምንት፡-የኅብረት ሥራ ማህበራት ደህንነትን ማረጋገጥ

የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት ዓለም አቀፍ ስታንዳርድን መነሻ በማድረግ በአገሪቱ የኦዲት አሰራር ስርዓት መሰረት በማድረግ የፋናንስ አፈፃፀምና የአጠቃላይ አሰራር ክንውን የሚረጋገጥበት ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት ሥራ በዋናነት የሚያተኩረው የፋይናንስ አስተዳደር፣ የዋና ዋና ተግባራት አፈጻጸም፣ የሥራ አመራር ስርዓት፣ ሃላፊነትን የመወጣት ብቃት፣ የጠቅላላ ጉባኤ የሥራ አፈጻጸም፣ የውክልና አሰጣጥ፣ የመረጃ አያያዝ፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት ባለቤትነት፣ ተቆጣጣሪነትና ተጠቃሚነት በህግ በሚወሰን መርሃ ግብር መሰረት ኦዲት እየተደረገ የሚረጋገጥበት ነው፡፡

የኦዲት ተግባር በየደረጃው ባሉ የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት እንዲሁም በኅብረት ሥራ ማህበራት በራሳቸው ተገቢ ትኩረት ተሰጥቶት አስፈላጊው የአሰራር ስርዓት፣ የሰው ኃይልና በጀት በማሟላት ጥራት ኖሮት ግልጽ እና ተጠያቂነት ባለው መልኩ መከናወን ያለበት ነው፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት እንደ አማራጭ የሚታይ ሳይሆን የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አቋም፣ የተግባራት አፈጻጸም፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት መሰረታዊ መርሆዎች መተግበራቸውን በማረጋገጥ የኦዲት ሪፖርቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ የሚጸድቅ እና በአባላትና በኅብረት ስራ ማህበራት ፣ በመንግስት፣ በባለድርሻ አካላት ዘንድ ያላቸው ተአማኒነትና ውጤታማነት የሚገለጽበት ስርዓት ነው፡፡

## ክፍል ስምንት፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ሬጉላቶር፣ ኦዲት እና ኢንስፔክሽን

### ዓምድ 25፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ሬጉላቶር ማጠናከር

#### *ሀ. ነባራዊ ሁኔታ*

የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲትን ተደራሽ ለማድረግ መንግስት ከፌደራል ጀምሮ በየደረጃው ባሉ የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት የኅብረት ሥራ ማህበራትን ኦዲት የሚያደርግ መዋቅር በመዘርጋት፣ የሰው ኃይልና በጀት በማሟላት፣ አስፈላጊውን የአቅም ግንባታ ተግባራትን በማከናወን የኦዲት ሽፋን ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም

የአፈጻጸም ልዩነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በየዓመቱ የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስና የዋና ዋና ተግባራት አፈጻጸም ኦዲት እየተደረገ ብቃትና ውጤታማነታቸውን በመረጋገጥ ላይ ይገኛል፡፡

በ2009 የፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ መረጃ መሰረት ሀገራዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት ሽፋን 25 ከመቶ ደርሷል፡፡ የኅብረት ሥራ ኦዲት የጥራት ደረጃን ለማሻሻል የተለያዩ የኦዲት አሰራር ማኑዋል፣ የኦዲት ስታንደርድ፣ የኦዲት የስልጠና ማኑዋሎችን በማጋጀት እና የኅብረት ሥራ ኦዲተሮች ግንዛቤ ለማስደግ ከሚመለከታቸው አካላት በመቀናጀት ሲሰራ ቆይቷል፡፡

ከዚህም በመነሳት አንዳንድ ኅብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት ሪፖርትን በመጠቀም ከተለያዩ አካላት ለስራ የሚያስፈልጓቸውን ብድር በማግኘት አገልግሎታቸውን በማስፋት የትርፍ ክፍፍልን ማድረግን ጨምሮ የአባላት ገቢ በማሳደግ እና ማህበራዊና ኢኮሚሚያዊ ችግራቸውን በመፍታት ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ ላይ ይገኛሉ፡፡

ሆኖም በየደረጃው ባሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ቁጥጥር አካላት በኅብረት ሥራ ኦዲት ላይ የአመለካከት፣ የዕውቀት፣ የክህሎት፣ የግንዛቤና የአደረጃጀት ችግሮች በመኖራቸው አገራዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት ሽፋንና ጥራት በሚፈለገው ደረጃ ላይ ማድረስ አልተቻለም፡፡

በሀገራችን መንግስት በየደረጃው የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚቆጣጠሩ አካላትን በማቋቋምና አቅም በመገንባት ኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባሮቻቸውን የተቀመጠውን አሰራርና የህግ ማዕቀፎችን ተከትሎ እንዲሰሩ ለማድረግ አስፈላጊወን ቁጥጥር በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት ተጠቃሚነትን በማሳደግ ለሀገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በተዘረገው መዋቅር መሰረት ባለሙያ በመመደብ የኅብረት ሥራ ማህበራት አፈጻጸምን ኢንስፔክት እያደረጉ ወቅታዊ ግብረ መልሶች በመስጠት እንዲታረሙ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የተቋቋሙበትን መሰረታዊ ዓላማ ከማሳካት አንጻር የመንግስት ዋና ተግባር መሆን ያለበት የኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥጥር ላይ ትኩረት መስጠት ቢሆንም ለማደራጀት የተደረገውን ጥረት ያህል መርሆዎችን ተከትሎ በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት ተግባሮቻቸውን እያከናወኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚደረገው ቁጥጥር ወቅታዊና ተከታታይ አለመሆን፣ በቁጥጥር ግኝቶች ላይ አፋጣኝ የእርምት እርምጃ አለመውሰድ፣ ለቁጥጥር ስራው ትኩረት አለመስጠት፣. የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚፈለገው ደረጃ አባላትን በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ ማድረግ አልቻሉም፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የአሰራር ስርዓት፣ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር፣ የተግባራት አፈጻጸም፣ የስራ አመራርና የቅጥር ሰራተኞች አስተዳደር፣ የአባላት ተሳትፎ፣ ባለቤትነት፣ ተቆጣጣሪነትና ተጠቃሚነትን እንዲሁም ተቋማዊ

መሰረተ ልማት አፈጻጸምን እየገመገሙ ኅብረት ሥራ ማህበራትን በአፈጻጸም ብቃታቸው በመለየት ጠንካራ ድጋፍና ክትትል መስጠት የሚያስችል የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ ስርዓት በመዘርጋትና በመተግበር የኅብረት ሥራ ማህበራትን ውጤታማ ያደረጉ አገሮች እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በአገራችን በዚህ ዘርፍ የተለያዩ ተሞክሮ ካላቸው ሀገራት ልምድ በመውሰድ የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ ስርዓት በመዘርጋት አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችና ደንቦችን በማዘጋጀት ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡

በዚህም አንዳንድ የሀገራችን ክልሎች ወደ ትግባራ በመግባት በክልላቸው የተደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በመመሪያውና በመስፈርቱ መሰረት እየመዘኑ የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በመስጠት ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላትን ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

### ለ. የኅብረት ስራ ማህበራት ሬጉላቶሪ ላያ ያሉ ማነቆዎች፤

#### ማነቆ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት ተደራሽ አለመሆን፤

በሀገራችን በኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት አስፈላጊነት፣ ጠቀሜታና ወሳኝነት ላይ በየደረጃው ያሉ አካላት የአመለካከት፣ የዕውቀትና የክህሎት ክፍተት ይታያል፡፡ ወጥ የሆነ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ አያያዝ አሰራር አለመዘርጋትና የሂሳብ ስራውን በሰለጠኑ ባለሙያ አለመስራት ሌለኛው ማነቆ ነው፡፡ የቅድመ ኦዲት ስራዎች በተገቢው መንገድ አለመከናወን፣ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓመታዊ አፈጻጸማቸውን የኦዲት መርሃ ግብሩን ተከትለው በባለቤትነት ኦዲት ማስደረግ አለመቻል ችግር ይታያል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አሁን ከደረሱበት የዕድገት ደረጃና ከቁጥራቸው ጋር የሚጣጣም ወጥ የሆነ የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት መዋቅር አደራጅቶ በሰው ኃይልና በሎጀስቲክ አለማሟላት፣ የኅብረት ሥራ ኦዲተሮች ደረጃና ደመወዝ ዝቅተኛ መሆን፣ በዘርፉ የሚያቆያቸው የሙያ ክፍያና ጥቅማ ጥቅሞች አለመኖርና ከፍተኛ የኦዲተሮች ፍልሰት መኖር የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት በሚፈለገው ደረጃ ተደራሽ እንዳይሆን አድርጓል፡፡

እንደየኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓይነትና ደረጃ የሚመጥን የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት የአፈጻጸም ስታንዳርድ አለመዘርጋት፣ ኦዲተሮችም ስታንዳርድን መሰረት አድርጎ በሙሉ አቅም ተግባራዊ አለማድረግ ችግሮች ይታሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት ተደረራሽ ለማድረግ እንዲቻል በውጪ ኦዲተሮች ኦዲት እንዲደረጉ የሚያስችል አሰራር አለመዘርጋት፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖችና ፌደሬሽኖች አባላትን ሂሳብ በወቅቱ ኦዲት እንዲደርግ በቂ ድጋፍ አለማድረግ፡፡

#### ማነቆ 2፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት ጥራት ችግር መኖር፤

DRAFT

በሀገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት በሚፈለገው የጥራት ደረጃ አለመከናወን፡፡ ለዚህ መሰረታዊ ምክንያቶች መካከል ወጥ የሆነ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ አያያዝና የኦዲት አሰራር ስርዓት አለመዘርጋት፣ ሂሳቡን በሰለጠኑ የሂሳብ ባለሙያዎች አለመሰራት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት የቅድመ ኦዲት ስራዎችን በተገቢው መንገድ አለመሰራት ይጠቃሰል፡፡

በተጨማሪም የኦዲት ሪፖርት መዘግየት፣ በጠቅላላ ጉባኤ በወቅቱ አለመጽደቅ እና በግኝነቱ መሰረት አፋጣኝ የእርምት እርምጃ አለመውሰድ፣ በየደረጃው ያሉ የዘርፉ አመራሮች የድጋፍና ክትትል ማነስ፣ የአባላት የቁጥጥር ውስንነት፣ የባለሙያዎች እውቀትና የክህሎት ችግር፣ በአንዳንድ ኦዲተሮች የሙያዊ ስነ ምግባር ጉድለት ምክንያት የኅብረት ሥራ ማህበራት ኃብትና ንብረት ለብክትና ምዝበራ መጋለጡ ለኦዲት ሥራ ጥራት መጓደል ከፍተኛ መንስኤ ሆኗል፡፡

### ማነቆ 3፡-የኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥጥር ደካማ መሆን፤

የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት ለኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥጥር በቂ ትኩረት አለመስጠት፡፡ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥጥር ጠንካራና ወጥነት ያለው ስርዓት አለመገንባት እና የኅብረት ሥራ ማህበራት የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ የሚመጥን የቁጥጥር መዋቅር አለመኖር ችግር ይታያል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የቁጥጥር አሰራር ስርዓት በበቂ ሁኔታ አለመዘርጋት፣ በየደረጃው ያሉ አስፈፃሚና ፈፃሚ አካላት ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥጥር በቂ ግንዛቤ ባለመፈጠሩ በአፈፃፀም ላይ ችግር ፈጥሯል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥጥር የኅብረት ሥራ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ የተግባራት አፈጻጸም ከመቆጣጠር አንጻር ውስንነት ይታይበታል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት መተዳደሪያ ደንባቸውን ተከትለው አለመስራት፣ የአፈጻጸማቸውን ሪፖርት በወቅቱ ለአባላት አለማቅረብ፣ ቅጥር ሰራተኞች የኅብረት ሥራ ማህበራት ደንብ፣ መመሪያና መርሆዎችን ተከትለው አገልግሎት ያለመስጠት ችግሮች ይታያሉ፡፡

### ማነቆ 4፡- በኅብረት ሥራ ማህበራት የሀብት ብክነት መኖር፤

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ አያያዛቸው ጥራቱን የጠበቀ አለመሆን፣ አባላት የተቆጣጣሪነት ሚናቸውን በተገቢው ሁኔታ አለመወጣት፣ የቁጥጥር ኮሚቴዎች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ አለመወጣት፣ የኅብረት ሥራ ህጎችን በተገቢው መንገድ አለመተግበር እና የባከኑ ሃብትና ንብረቶችን በወቅቱ ለህግ አቅርቦ አለማስወሰንና አለማስመለስ ችግሮች በስፋት ይታያሉ፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ያፈሩትን ሃብትና ንብረት ዕድገት ለማስቀጠልና ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚደረገው የቁጥጥር፣ የኦዲት፣ የህግ አገልግሎት ድጋፍ ደካማ ነው፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥጥር የሚገኙ ግኝነቶች ላይ አፋጣኝ የእርምት እርምጃ አለመውሰድ፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ገንዘብ፣ ሃብትና ንብረት አላግባብ በተለያየ መንገድ ለምዝበራ በመዳረጉ ምክንያት አባላት፣ መንግስትና አቅም ገንቢ አካላት በኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ እምነት እንዲያጡ አድርጓል፡፡

**ማነቆ 5፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ ተደራሽ አለመሆን፤**

በየደረጃው ያሉ የኅብረት ሥራ የማደራጃና ቁጥጥር አካላት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት፣ አቅም ገንቢዎች፣ ባለድርሻ አካላት በኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ ላይ የግንዛቤ፣ የዕውቀትና ክህሎት ክፍተት ይታያል፡፡ ጥራቱን የጠበቀ የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ አለመዘርጋት፣ የተጠናከረ፣ ወጥ እና ገለልተኛ የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ የአደረጃጀት መዋቅር አለመዘርጋት፡፡

የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ አገር አቀፍ ስታንደርድ በሚፈለገው ደረጃ አዘጋጅቶ ከኅብረት ሥራ ልህቀት ማዕከል ጋር አቀናጅቶ አለመምራት፣ በየደረጃው በሚገኙ የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት፣ ለኅብረት ስራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ ተገቢ ትኩረት አለመስጠት አሰራሩን በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማና ተደራሽ እንዳይሆን ማነቆ ሆኗል፡፡

**ሐ. ማነቆዎቹን ለመፍታት የምንከታላቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች፤**

| |
|---|
| ***የኅብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት ሽፋን፣ የኢንስፔክሽን አገልግሎት ሽፋን እና የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ማረጋገጫ እውቅና የአገልግሎት አሰጣጥ 100 በመቶ ይሆናል፡፡*** |

**መፍትሄ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት ተደራሽነትን ማሳደግ፡-**

**የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት ተደራሽነትና ጥራትን ማሳደግ፡-** በኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት ላይ ያለውን የአመለካከት፣ የክህሎትና ዕውቀት ጉድለቶችን መሙላት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የስልጠና ሰነዶችና የአሰራር ማኑዋሎች ተዘጋጅተው በተከታታይ የግንዛቤ ማሳደጊያና የአቅም ግንባታ ስልጠኛዎች በየደረጃው ለሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮች፣ ለኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት፣ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲተሮች ይሰጣል፡፡

በሀገራችን ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ዕድገት ደረጃ መሰረት ያደረገ ሳቢና ሰራተኞችን በዘርፉ ሊያቆይ የሚያስችል የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት መዋቅር በወጥነት በየደረጃው እንዲኖር በማድረግ መዋቅሩ በቂ ዕውቀትና ክህሎት ባላው የሰው ኃይል እንዲሟላ፣ ተግባሩን ማሳካት የሚያስችል የፋይናንስና ሎጀስቲክ አቅርቦት እንዲኖር በኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት ወጥ የሆነ የሂሳብ ዝርጋታ ስርዓት እንዲኖር ማስቻል የማጠናከር ስትራቴጂያችን አካል ተደርጎ ይከናወናል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ ስራ በሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲመራ በማድረግ ሁሉም የኅብረት ሥራ ማህበራት ወቅታዊ የሂሳብ መግለጫዎችን እያዘጋጁ በአመራሩ እንዲጸድቅ በማድረግ የቅድመ ኦዲት ስራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ ይደረጋል፡፡

የሂሳብ ዝርጋታ ማኑዋሎችን በማዘጋጀት፣ ዘመናዊ የሂሳብ አሰራር ስርዓት በመዘርጋት የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ በህግ በሚቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የሂሳብ መግለጫዎችን ለተቆጣጣሪ አካላት በየደረጃው እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት መርሀ ግብሩን ተከትለው ኦዲት ይደረጋሉ፡፡ ለተፈጻሚነቱ ቀጣይነት ያለው የክትትል ስርዓት ተዘርግቶ በማደራጃና ቁጥጥር አካላት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲተሮች ዋና ተግባራቸው ኦዲት ማድረግ ብቻ በመሆኑ በኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ ዝርጋታና ክትትል መዋቅር እንዲኖር በማድረግ ሂሳባቸው በአግባቡ ተስተካክሎ ለኦዲት ዝግጁ ስለመሆኑ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት እንዲጠናከር የውስጥ ኦዲት መዋቅር በየኅብረት ሥራ ማህበራቱ እንዲኖርና መዋቅሩ ቢያንስ በሩብ ዓመት አንድ ጊዜ የፋይናንስ አፈጻጸሙን እየገመገመ ጉድለቶች የሚታረሙበት ስርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት ዓለም አቀፍ ስታንዳርድን የተከተለና የፋይናንስና አጠቃላይ ክዋኔ ኦዲትን ያካተተ ሆኖ እንዲፈጸም እና የኦዲት ግኝቶችን ተግባራዊነት የሚያረጋግጥ የአሰራር መመሪያ ተዘጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በየደረጃው ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች የራሳቸውንና የአባላትን እንዲሁም የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የራሳቸውን ሂሳብ አስፈላጊውን በጀት በመመደብ ኦዲት ማስደረግ እንዲችሉ አሰራር ይተገበራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲተሮችና የሂሳብ ዝርጋታና ክትትል ባለሙያዎች ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ሙያዊ ስነ ምግባርን የተላበሰ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ ጤናማ ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚያስችል የኦዲተሮች ሙያዊ ስነ ምግባር መመሪያ በማዘጋጀት እንዲተገበር ይደረጋል፡፡ ተፈጻሚነቱም ክትትል ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት መርሃ ግብርን መሰረት አድርጎ በተከታታይ ኦዲት የማስደረግ፣ በኦዲት ወቅት ኦዲት ስህተት እንዳኖር፣ የኦዲት ግኝት ላይ የሚሰጡ ግብረ መልሶችን ፈጥኖ እንዲያርሙ ይደረጋል፡፡ ኦዲት የተደረጉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት አፈጻጸም የጥራት ደረጃ መሰረት በማድረግ እንደየአፈፃፀማቸው እውቅና ይሰጣል፡፡ ለዚህም ማስፈጸሚያ የሚያግዝ የአሰራር ስርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

DRAFT

የኅብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት ተደራሽነትን ለማስፋት በመንግስት አቅም ኦዲት ከሚደረገው በተጨማሪ የኅብረት ሥራ ኦዲት በውጭ አካላት የማስመርመር ስርዓት ተዘርግቶ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡ ለዚህም የኅብረት ሥራ ኦዲትና የኅብረት ሥራ ሂሳብ ተመራቂዎች በኅብረት ሥራ ኦዲት እና ሂሳብ ባለሙያነት በኅብረት ሥራ በማደራጀት የሂሳብና የኦዲት ስራ እንዲያከናወኑ የሚደረግ ሲሆን ለአፈጻጸሙም መመሪያ በማዘጋጀት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ኦዲት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ መንግስት ከሚያደርገው በተጨማሪ የኅብረት ሥራ የልህቀት ማዕከላት፣ የኅብረት ሥራ ሊግ እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ለኅብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት አገልግሎት የሚሰጡበት አሰራር ተዘርግቶ ይተገበራል፡፡ በነዚህ አካላት የተደረገውን ኦዲት የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት የሚያረጋግጡበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

**መፍትሄ 2፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት ጥራትን ማሻሻል፤**

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ ባለሙያዎችና ኦዲተሮችን የዕውቀትና ክህሎት ብቃት በማሳደግ የኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት ጥራት በተቀመጠው የኦዲት ስታንዳርድ መሰረት ደረጃውን ጠብቆ እንዲከናወን ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የስልጠና እና የአሰራር ማኑዋሎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት ወጥ የሆነ የሂሳብ ዝርጋታ ስርዓት እንዲኖር፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ ስራ በሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲመራ፣ ሁሉም የኅብረት ሥራ ማህበራት ወቅታዊ የሂሳብ መግለጫዎችን እያዘጋጁ በአመራሩ እንዲያጸድቁ የማድረግ እና አጠቃለይ የቅድመ ኦዲት ስራዎች በአግባቡ እንዲተገበር የማድረግ ተግባር አንዱ የማጠናከሪያ ስትራቴጂ አካል ተደርጎ ይከናወናል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት መሰረታዊ የሂሳብና ሌሎች ሰነዶች ለኦዲት ጥራት ወሳኝ ትርጉም ያላቸው በመሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሰነዶቹን አሟልተው እንዲጠቀሙ ይደረጋል፡፡

**መፍትሄ 3፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥጥርን ማጠናከር፤**

**የኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥጥር እና የህግ አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ፡-** መንግስት የኅብረት ሥራ ማህበራትን ደህንነት ለማረጋገጥ በጥናት ላይ በተመሰረተና የኅብረት ሥራ ማህበራት የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ የሚመጥን ወጥነት ያለው የቁጥጥር መዋቅር በየደረጃው በመዘርጋት በሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲሟላ በማድረግ ፋይናንስና ሎጀስቲክ በማቅረብ በትኩረት እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ኢንስፔክተሮች የቁጥጥር ስራውን በነጻነትና በገለልተኝነት እንዲያከናውኑ የሚያስችልና በግኝቱ መሰረት እርምጃ መውሰድ የሚያስችል የአፈጻጸም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥጥር ተግባር ላይ የሚሳተፉ አካላት የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት የሚዘረዝር ግልጽ የአሰራር መመሪያዎችና ማኑዋሎች በኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥጥር ላይ ያለውን የግንዛቤ፣ የዕውቀትና የክህሎት ጉድለቶችን መሙላት የሚያስችሉ በየደረጃው ለሚገኙ የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮች፣ አባላትና ቅጥር ሰራተኞች አስፈላጊ የሆኑ የስልጠና ሰነዶችና የአሰራር ማኑዋሎች በማዘጋጀት ተከታታይ የግንዛቤ ማሳደጊያና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ኢንስፔክተሮች በተቀመጠው አሰራር መሰረት የኅብረት ሥራ ማህበራትን ኢንስፔክት ካደረጉ በኋላ በተገኙ ግኝቶች መሰረት ጥሩ እየሰሩ ያሉ ተሞክሮዎችን ወደ ሌሎች የማስፋትና ክፍተት የሚታይባቸው ላይ በነፃነት አስፈላጊውን እርምጃ የሚወስዱበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት የኅብረት ሥራ ማህበራትን በአግባቡ መቆጣጠር የሚያስችል የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትና ምዝገባ፣ የሥራ አመራር፣ የውስጥ አሰራር፣ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ግብረ መልስ ተግባራዊነት፣ የአለመግባባት አፈታት ሂደታቸውንና ሌሎች ጉዳዮችን ያካተተ የኅብረት ሥራ ቁጥጥር መመሪያ በማዘጋጀትና ግንዛቤ በመፍጠር እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ ቁጥጥር እንዲጠናከር አስፈላጊ የሆኑ የስልጠና ማኑዋሎችን በማዘጋጀት የቁጥጥር ኮሚቴ አካላትን በተከታታይነት በማሰልጠን ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያከናውኗቸው ተግባራት በመተዳደሪያ ደንባቸው በጸደቀው መሰረት ብቻ እንዲሆን አስፈላጊው ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

### መፍትሄ 4፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የሃብት ብክነትን መከላከል፡-

የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የተቀጣጣሪነት ሚናቸውን በተገቢው መንገድ መወጣት እንዲችሉ ተከታታይ የአቅም ግንባታና የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠናዎች ለኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት እና አመራሮች በየደረጃው ይሰጣል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዘመናዊ የሂሳብ አሰራር ስርዓት በመዘርጋት፣ የሂሳብ ስራዎችን በወቅቱ በመመዝገብ እና በመዝጋት በማፀደቅ እንዲሰራ ተከታታይ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ እንቅስቃሴ በሙያ የሚደግፉ የሰለጠኑ የሂሳብ ባለሙያዎችን ቀጥረው እንዲያሰሩ የሚያስችል አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ እንቅስቃሴ አፈጻጸም ለቁጥጥር

እንዲያመች የሂሳብ መግለጫዎች በኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮች እየተረጋገጠ ለማደራጃና ቁጥጥር አካላት እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

በየደረጃው ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽኖች እና ዩኒየኖች ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ዘመናዊ የሂሳብ አሰራር መዘርጋትና የኅብረት ሥራ ማህበራትን ሃብትና ንብረት ደህንነት እንዲጠበቅ የማድረግ ኃላፊነት እንዲኖራቸውና ይህን በአግባቡ እንዲወጡ የሚያስችሉ የአፈጻጸም መመሪያዎች እየተዘጋጁ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ስራ ማህበራት ቁጥጥር ኮሚቴዎች ኅብረት ሥራ ማህበራትን እንዲቆጣጠሩ ለማስቻል የሚመረጡ የኮሚቴ አባላት በቂ ግንዛቤና የተሻለ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው እንዲሆን የሚያስችል ዝርዝር መስፈርት ተዘጋጅተው ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የቁጥጥር ኮሚቴዎች የኅብረት ሥራ ማህበራትን የአጭርና የረዥም ጊዜ እቅድ መነሻ በማድረግ ከሌሎች የውስጥ ቁጥጥር መዋቅር ጋር በመሆን በየጊዜው የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዕቅድ አፈጻጸም በመገምገም ሪፖርቱን በየጊዜው ለስራ አመራር ኮሚቴ እና ለጠቅላላ ጉባዔ በማቅረብ የሚታዩ ክፍተቶች የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የኅብረት ሥራ ህጎችንና መተዳደሪያ ደንባቸውን ላይ ያስቀመጡትን አሰራር እንዲከተሉ ለማድረግ በኅብረት ሥራ ህጎች ላይ ተከታታይ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ የኅብረት ሥራ ህጎች በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ እንዲገኙ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ህጎች ተፈጻሚነትን እየተከታተለ ጉድለቶችን የሚያርም ተከታታይ ቁጥጥር ስራዎች ይሰራሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የህብትና ንብረት ከብክነት ለመታደግና ለሚታየው ዕዳ መፍትሄ ለመስጠት፣ በተገቢው መንገድ መመለስ የሚገባቸውን ሀብትና ንብረት ለማስመለስና ችግሩን በዘላቂነት ለማስቀረት የተመዘበሩ፣ የጎደሉ ሀብትና ንብረት የት፣ እንዴትና መቼ እንደተመዘበሩ እና እንደጎደሉ በማረጋገጥ የማይመለሱትንና የሚመለሱትን ከህግ አንጻር በመለየት ባለቤት የመስጠት ስራ በየደረጃው እንዲሰራ የአፈጻጸም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በዚህ መሰረት ዝርዝር መረጃዎች ተደራጅተው ሊመለሱ የሚችሉና የማይችሉት ተለይተው ለኅብረት ሥራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ ለመንግስት ለውሳኔ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ እና በመንግስት ውሳኔ መሰረት ከህግ አንጻር መመለስ የማይችሉ ተብለው የተወሰኑ ዕዳዎች የሂሳብ አሰራርን ተከትለው ከኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ መዝገብ እንዲሰረዙ የሚደረግ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ መመለስ የሚገባቸውን የኅብረት ሥራ ማህበራት ዕዳዎች በህጋዊ አግባብ መመለስ እንዲቻል መንግስት የኅብረት ሥራ ማህበራት የችሎት ቀን ወይም የኅብረት ሥራ ችሎት እንዲቋቋም በማድረግ የባከኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሀብትና ንብረት በሕግ እንዲመለስ ይደርጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮችና

በየደረጃው ያለው የኅብረት ሥራ የህግ መዋቅር የኅብረት ሥራ አዋጅና አሰራሮች ላይ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

**መፍትሄ 5፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ ተደራሽ ማሳደግ፤**

**የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አገልግሎት ጥራትን ማጠናከር፡-** የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰራርን ተደራሽና ውጤታማ ለማድረግ በየደረጃው ላሉ ለኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት፣ ለኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮች፣ ለአቅም ገንቢዎች፣ ለባለድርሻ አካላት በኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ አሰራር ላይ የግንዛቤ፣ የዕውቀትና ክህሎት ክፍተት ሊሞላ የሚችል የስልጠና እና የግንዛቤ ማሳደጊያ ሰነዶች ተዘጋጅተው ተከታታይ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና በየደረጃው ባሉ የማደራጃና ቁጥጥር አካላት ይሰጣል፡፡

እንደየ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነትና ደረጃ ሁሉንም የኅብረት ሥራ ማህበራት መመዘን የሚያስችል የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ መመሪያ እና የመመዘኛ መስፈርት ሰነድ ተዘጋጅቶ ይተገበራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ ስርዓትን በኃላፊነትና በተጠያቂነት መተግበር የሚያስችል የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ መዋቅር በየደረጃው ወጥነት ባለው ሁኔታ እንዲኖር እና የሰለጠነ የሰው ኃይልና ሎጀስቲክ ተሟልቶ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ ጥራት ያለው የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ አሰጣጥ ስርዓት ተደራሽ ለማድረግ ከኅብረት ሥራ ልህቀት ማዕከላት ጋር ተቀናጅቶ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡

የልህቀት ማዕከላት በየደረጃው ላሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ መረጃ ለሚሰበስቡ፣ መረጃውን ለሚተነትኑ፣ ብቃት ደረጃ ለሚያረጋግጡ ባለሙያዎችና አመራሮች የመፈጸምና ማስፈጸም አቅም ግንባታ ስልጠና መስጫ ካሪኩለም ከማደራጃና ቁጥጥር አካላት ጋር በቅንጅት ተዘጋጅቶ ይተገበራል፡፡

በየደረጃው የሚገኙ በኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ ተግባር ላይ የተሰማሩ አመራርና ባለሙያዎች ወደ ተግባር ከመግባታቸው አስቀድሞ በኅብረት ሥራ ልህቀት ማዕከላት የሚሰጠውን የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ ስልጠና በማጠናቀቅ ተግባሩን ማከናወን የሚያስችል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ልህቅት ማዕከላት ከማደራጃና ቁጥጥር አካላት ጋር በብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ ያሉ የአፈጻጸም ማነቆዎችን በጋራ በጥናት እየለዩ ጉድለቶች የሚስተካከሉበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የኅብረት

ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ ስርዓት በሚፈለገው መንገድ ተደራሽና ውጤታማ እንዲሆን በማደራጃና ቁጥጥር አካላት ጠንካራ የድጋፍ፣ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ይተገበራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ አሰጣጥ ስርዓት ከአስፈላጊነትና ጠቀሜታው አንጻር ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሰራ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም ተግባሩን ሊደግፍ የሚችል ተጨማሪ ፕሮጀክቶች ተቀርጸው ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ የምዘና ውጤቱን መሰረት በማድረግ ለድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር የሚያገለግሉ አሰራሮችን ቀርጾ ተግባራዊ በማድረግ በምዘናው ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ ኅብረት ሥራ ማህበራት ደረጃቸውን የሚመጥንና ወደ ላቀ ደረጃ የሚደርሱበትድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

ከዝቅተኛ በታች ውጤት የሚያስመዘግቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ደግሞ የአፈጻጸም ደረጃዎች ውስጥ መግባት የሚያስችላቸው በጥናት ላይ የተመሰረተ የማጠናከርና የማብቃት ስራዎች በተከታታይ ይከናወናሉ፡፡ ከዝቅተኛ በታች ከነበረ አፈጻጸም ተላቀው ወደ ተሻለ አፈጻጸም ደረጃ የማይመጡ እና በግላቸው ውጤታማ የማይሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲዋሃዱ መጠናከር የማይችሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት ፈርሰው ከመዝገብ እንዲሰረዙ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት አመራሮች አሰራሩን በባለቤትነት እንዲመሩ ለማስቻል በየጊዜው የምክክር መድረኮችና ፎረሞች እየተዘጋጁ የሚተገበሩበት የአሰራር ስርዓቶች ተዘርግተው በቅርብ ድጋፍና ክትትል ይተገበራሉ፡፡

## ክፍል ዘጠኝ፡- የኅብረት ሥራ ሴክተር እና ሌሎች አካላት ድጋፍና ሚና፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ማህበራዊ አስታወጽዖ እና ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ተሳትፎ

መንግስት ያለውን ሃብት በአግባቡ አቀናጅቶ በመጠቀም በሀገራችን ድህነትን እና ኋላ ቀርነትን ለማስወገድ የተለያዩ ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀርጾ ተግባራዊ በማድረጉ የዜጎች ተጠቃሚነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትም እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ ለዚህ ውጤት የኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡

በመሆኑም የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትንና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት በማሳደግ በሀገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውስጥ ያላቸውን ከፍተኛ ሚና በአግባቡ እንዲወጡ መንግስት በየደረጃው የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚያደራጅና የሚያጠናክር፣ የማስፈጸም አቅማቸውን የሚገነባ፣ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ መዋቅር ዘርግቶ ተገቢውን የሰው ኃይልና በጀት በማሟላት እና የህግ ማዕቀፎችን በመቅረጽ ልዩ ልዩ ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በሀገራችን ኅብረት ሥራ ማህበራት አሁን ለደረሱበት ዕድገት የአቅም ገንቢዎች ድጋፍ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ ሆኖም የሚደረገው ድጋፍ በጋራ እቅድ ላይ ያልተመሰረተና በሚፈለገው ደረጃ ችግር ፈቺ አለመሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በመሆኑም ለቀጣይ አቅም ገንቢዎች የኅብረት ሥራ ልማትን በሚፈለገው ደረጃ መደገፍ እንዲችሉ በአቅም ገንቢዎችና በኅብረት ሥራ ሴክተሩ መካከል የሚታዩ ማነቆዎችን ለመፍታ ቅንጅታዊ አሰራር መዘርጋት ወሳኝ ነው፡፡

ለየትኛውም ተቋም ሁለንተናዊ ዕድገት ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚኖረው ግንኙነት ወሳኝ ነው፡፡ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት ዕውቀትና ሀብትን በተገቢው መጠቀም ስለሚያስችል አንዱ ለሌላው ተልዕኮ መሳካት እና ለርስ በርስ ጤናማ ግኙኑነት ከፍተኛ አስተዋጽ አለው፡፡

ሆኖም ባለድርሻ አካላት የሚያወጧቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ የሚወስናቸው ውሳኔዎች ሌሎች ባለድርሻ አካላትን የመጥቀማቸውን ያህል ቅንጅታዊ አሰራራቸው ካልተጠናከረ የጋራ ተጠቃሚነትና ጤናማ ግንኙነትን በከፍተኛ ደረጃ ሊጎዱ ይችላሉ፡፡

የተለያዩ ጥናቶችና አገራዊ ተሞክሮዎች እንደሚያስረዱት ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት የማይሰሩ ከሆነ የተቋቋሙበትን ዓላማና ዕቅዶች በተገቢው መንገድ ማሳካት ላይ ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ ስለሆነም የትኛው ተቋም ኃላፊነትና ተግባሩን ከግብ ለማድረስ ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ጉዳዮች ላይ አብሮ እያቀደ አፈጻጸምን በጋራ የሚገመግምበትን ስርዓት መከተል ውጤታማ ያደርገዋል፡፡

ኅብረት ሥራ ማህበራት ከመንግስትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የሚፈጥሩት ቅንጅታዊ አሰራርና የርስ በርስ መደጋገፍ ለአባላት ተጠቃሚነትና ለሀገር ማህበራዊና ኢኮኖሚዊ ዕድገት እያበረከቱ ያለው አስተዋጽኦ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡

የአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያሳድጉ ተግባራት ላይ በመሰማራት ውጤቶችን በማስመዝገብ ላይ ናቸው፡፡ የአገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት አሁን ለደረሱበት የዕድገት ደረጃም የባለድርሻ አካላት ድጋፍና ቅንጅታዊ አሰራር ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ ሆኖም ይህ ቅንጅታዊ አሰራር እና የርስ በርስ መደጋገፍ ከሚጠበቀውና መሆን ካለበት ጋር ሲነጻጸር ሰፊ ክፍተት ያለበትና በቀጣይ በትኩረት መሰራት ያለበት ጉዳይ መሆኑን የጥናት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ከኅብረት ሥራ ማህበራት መሰረታዊ መርሆዎች መካከል አንዱ ኅብረት ሥራ ማህበራት በመተዳደሪያ ደንባቸው ላይ በሚያጸድቁት ፖሊሲ ላይ ተመስርተው ለአካባቢያቸው ዘላቂ ልማት በሚያመጡና መሰረታዊ ችግር በሚፈቱ ተግባራት ላይ መሳተፍ ነው፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በማህበራዊ አገልግሎት ላይ መሳተፍ የአካባቢው ማህበረሰብ መሰረታዊ ችግር በመፍታት የዜጎችን ተጠቃሚነት ከማሳደጉ በላይ ኅብረት ሥራ ማህበራት በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እውቅናና ተቀባይነት እንዲኖራቸው፣ በአባላት ውስጥ የባለቤትነት ስሜት የሚያሳድግ፣ ዜጎች ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ጠቀሜታና ፋይዳ

በቂ ግንዛቤና የጠራ አመለካከት እንዲራቸው በማድረግ ዜጎች የኅብረት ሥራማህበራት አባልነት በንቃት እንዲሳተፉ ያስችላል፡፡

በመሆኑም በዓለማችን ላይ የሚገኙ ኅብረት ሥራ ማህበራት ይህን መርሆ ወደ ተግባር ለመለወጥ በሚያደርጉት መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ የበርካታ ዜጎችን ኑሮ ከማሻሻል አልፈው ሰፋፊ የአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ በመሳተፍ በሀገራት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ውስጥ ያላቸውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ በመወጣት ላይ ይገኛሉ፡፡ በሀገራችንም የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚያበረክቱት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች መካከል በማህበራዊ አገልግሎት ስራ ውስጥ የሚደርጉት እንቅስቃሴ በዋናነት ተጠቃሽ ነው፡፡

የሀገራችን ኅብረት ሥራ ማህበራት እንደ መርህ ከሚጠቀሟቸው እሴቶች ውስጥ በአባላት፣ እንዲሁም በአካባቢው ህብረተሰብና በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የመረዳዳት፣ የመተጋገዝ፣ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ መስራትን እንደ ተቋማዊ ዕሴቶች በመከተልና የርስ በርስ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን በመፍጠር ረገድ ተግባር በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

ከዚህ አንጻር የኅብረት ሥራ ማህበራት በየአመቱ ከሚያገኙት ትርፍ ላይ ለማህበራዊ አገልግሎት በመመደብ፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት በኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦቸው ረገድ በሚያደርጉት ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የገበያ ትስስር ከውጭ ሀገራት በሚያደርጉት ግብይት ለሃገራችን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘታቸው ባሻገር ምርቶቻቸውን በሚጠቀመው አካል ላይ በሚፈጥሩት መልካም ተፅዕኖ፣ የሚያገኙትንየፍትሃዊ ንግድ ጥቅም/ ፌር ትሬድ ፕሪምየም/ በቀጥታ ለማህበራዊ አገልግሎት በማዋል እንደየአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታ የአካባቢው መሰረታዊ ችግር በሆኑ በተለይም የትምህርት ቤቶች፣ የሰውና የእንሳስት ጤና ኬላዎች ግንባታና ውስጣዊ ቁሳቁስ ማሟላት፣ ቀበሌን ከቀበሌ ወይም ኅብረት ሥራ ማህበራትን ከኅብረት ሥራ ማህበራትየሚያገናኙ የውስጥ ለውስጥ መንገዶችና ድልድዮች ግንባታ፣ የመብራት ዝርጋታ፣ አቅመ ደካሞችንና አረጋውያንን፣ አካል ጉዳተኞችና በተለያየ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት እንክብካቤ፣ አቅም የሌላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ልጆችን እስከ ከፍተኛ ትምህር ደረጃ ድረስ የማስተማር፣ በሀገራዊ ትላልቅ ልማቶች ላይ የቦንድ ግዢና ተመሳሳይ የሆኑ ሀገራዊና አካባቢያዊ ማህበራዊ የልማት ተግባራት ላይ በመሳተፍ የድርሻቸውን በመወጣት ላይ ይገኛሉ፡፡

የሀገራችን ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ጥቅም ከማረጋገጥ ባሻገር በሀገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግንባታ ላይ ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ጎን ለጎን በዘርፈ ብዙ ተግባራት ላይ የሚያደርጉት ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ ሀገራዊ ዕድገትን ለማረጋገጥና የኅብረት ሥራን እንቅስቃሴን ውጤታማ ለማድረግ የሴቶችና ወጣቶች ሚና ወሳኝ በመሆኑ ሴቶችና ወጣቶችን በኅብረት ሥራ ማህበራት በማደራጀት፣ በአባልነትና አመራርነት በማሳተፍ፣ ለሴቶችና

ወጣቶች የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ ተግባራዊ በማድረግ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግራቸውን እንዲያቃልሉ ለማስቻልና የስራ ዕድል ከመፍጠር አንጻር የኅብረት ሥራ ማህበራት ተስፋ ሰጭ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

ኅብረት ሥራ ማህበራት በተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ፣ በተፋሰስ ልማትና ደን ልማት በመሳተፍ ደኖችን በመትከል፣ በመንከባከብና በአግባቡ በመጠቀም የደን ኅብረት ሥራ ማህበራት በማቋቋም አካባቢን ከመንከባከብ ባሻገር በካርቦን ንግድ እና በቱሪዝም መስክ ከመሳተፍ አንጻር ጥረቶችን በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ኅብረት ሥራ ማህበራት በየአካባቢያቸው ያሉ አረጋውያንን፣ አካል ጉዳተኞችና ወላጅ አጥ ህጻናትን ለመደገፍ ለነዚህ አካላት የሚሆኑ የስራ ዕድል በመፍጠርና በተለያየ መንገድ በመርዳት በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባሎቻቸው ለአካባቢው ህብረተሰብ ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ እና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ግንዛቤ በመስጠት እና በመደገፍ የሚጠበቅባቸውን ድርሻ በመወጣት ላይ ናቸው፡፡

## 9.1. የኅብረት ሥራ ሴክተር እና ሌሎች አካላት ድጋፍና ሚና፣

### 9.1.1. የመንግስት ድጋፍና ሚና

**የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር መዋቅራዊ አደረጃጀትን መጠናከር፡-**

የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ተጠቃሚነት ለማሳደግ፣ በገጠርና በከተማ በዝቅተኛ እና መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚኖረው ህብረተሰብ ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና በሀገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ላይ የሚያበረክቱትን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከግምት ውስጥ በማስገባት የኅብረት ሥራ ማህበራት ከደረሱበት የዕድገት ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ድጋፍ የሚሰጥ የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር ተቋም የማጠናከር ስራ በትኩረት ይሰራል፡፡

የኅብረት ሥራ ሴክተሩን ችግር በራሱ እየወሰነ የሚፈታና የዘርፉን ትራንስፎርሜሽን የሚያረጋግጥ፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት እያስመገቡ ያሉትን ውጤት የሚያልቅ፣ ተቋማዊ አሠራርና የአስተዳደር በዘላቂነት የሚያጠናክር አምዳዊ አደረጃጀት ያለው፣ በብቁ የሰው ሃይል እና ሎጀስቲክ የተሟላ ወጥ የኅብረት ሥራ መዋቅር ከፌዴራል እስከ ቀበሌ ድረስ በጥናት ላይ ተመስርቶ በየደረጃው በማዋቀር ለኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት፣ ለዜጎችና ለአገሪቱ ኢኮኖሚ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ በትኩረት ይደረጋል፡፡

ሴክተሩን ለማስተባበር የሚመደቡና በሴክተሩ ተቀጥረው የሚሰሩ አካላት ሴክተሩን ለመምራትና የሴክተሩን ተልዕኮ እና ራዕይ ለማስፈጸም የሚያስችል አመለካከት፣ በቂ እውቀትና ክህሎት እንዲኖራቸው በኅብረት ሥራ የልህቀት

ማዕከላት ውስጥ የስልጠና ስርዓት ተዘርግቶ ከአጭር እስከ መካከለኛ ጊዜ ተከታታይ የግንዛቤ ማሳደጊያ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ሴክተሩን የመፈጸም እና የማስፈጸም አቅም በዘላቂነት ለመገንባት የኅብረት ሥራ አቅም ግንባታ ስትራቴጂ ተቀርጾ በየደረጃው ያሉ የዘርፉ አካላት የትምህርት ዝግጅታቸውን እንዲያሻሽሉ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡

**መንግስት በኅብረት ሥራ ማህበራት መሰረተ ልማት ዝርጋታ ላይ የሚያደረገውን ድጋፍ ማጠናከር፡**

የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚያከናውኗቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ግብይቶች፣ እሴት የመጨመር ተግባራትና ሌሎች ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን ለማሳደግ የሚያስፈልጓቸውን የመሰረተ ልማት አቅርቦቶች በወቅቱ እና በተገቢው መንገድ እንዲያገኙ መንግስት ልዩ ትኩረት በመስጠት ይደግፋል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት ለሚካሄዱ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች የሚያስፈልጉ የፋይናንስ እጥረትን ለመቅረፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት ራሳቸው እና መንግስት ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የወጪ መጋራት መርህ እንዲከተሉ እና ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ጋር በማስተሳሰር እንዲሰሩ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የኅብረት ሥራ ማህበራት የራሳቸው የፋይናንስ ተቋማት እንዲመሰርቱ በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የፋይናንስ እጥረት ለመቅረፍ እና መሰረተ ልማት ዝርጋታቸው እንዲያድግ የሚያስችሉ ተግባራት በትኩረት ይከናወናሉ፡፡

**መንግስት ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የሚሰሩ አካላትን አቀናጅቶ መምራት፡-**

ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በጋራ የሚሰሩ አካላትን ዝርዝር መረጃ በመለየትና በቅንጅት የሚሰሩበትን አሰራር በማስቀመጥ ውጤታማነቱን የሚያረጋግጥበት የጋራ ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት ሁለቱንም ወገን አቀናጅቶ የሚመራበትን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል

### 9.1.2. የባለድርሻ እና አቅም ገንቢ አካላት ድጋፍና ሚና

**የባለድርሻ አካላት ድጋፍና ሚና፣**

ባለድርሻ አካላት የኅብረት ሥራ ማህበራትን በእውቀት ላይ ተመስርተው በተቀናጀ ሁኔታ እንዲደግፉ ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት አጠቃላይ ዓላማ፣ ተልዕኮ፣ መርህና ግብ፣ በሀገር ማህበራዊና ኢኮኖሚ ግንባታ ላይ ስለሚኖራቸው አስተዋጽኦ ተከታታይ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠናዎችና የምክክር መድረኮች በየደረጃው ባሉ የማደራጃና ቁጥጥር አካላት እየተዘጋጀ በትኩረት ይሰጣል፡፡

ባለድርሻ አካላት ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት የጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በባለድርሻ አካላትና በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚኖረው ግንኙነት አንዱ የሌላኛውን መርህ እና ተጠቃሚነት በማክበር እርስ በርስ መደጋገፍ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ኅብረት ሥራ ማህበራት እና ባለድርሻ አካላት በጋራ የሚያከናውኑትን ተግባር ለማሳካት በጥናት ላይ የተመሰረተ በተጨባጭ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ችግር የሚፈታ የተቀናጀ የጋራ የዕቅድ፣ የድጋፍ፣ የክትትልና የግምገማ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

መንግስት ኅብረት ሥራ ማህበራትን ለመደገፍ ካለው ቁርጠኛ አቋም በመነሳት የኅብረት ስራ ማህበራትን ለመደገፍ ያወጣቸውን እና የሚያወጣቸውን የህግ ማዕቀፎች በየደረጃው ያሉ ሴክተር መስሪያ ቤቶችና አመራሮች በአግባቡ ተረድተው እንዲተገብሩና ኅብረት ሥራ ማህበራትም የመብታቸው ሙሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

መንግስት የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለመደገፍ የሚያወጣቸውን የህግ ማዕቀፍ፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጽንሰ ሃሳብ፣ አስፈላጊነትና ጠቀሜታን በየደረጃው ያሉ ባለ ድርሻ አካላት በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው እንዲተገብሩ ተከታታይ የግንዛቤ ማስደጊያ መድረኮች በየደረጃው ባሉ የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት እና የኅብረት ሥራ ማህበራት በቅንጅት እየተዘጋጁ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

ባለድርሻ አካላት የሚያወጣቸው የህግ ማዕቀፎች፣ የሚወስኗቸው ውሳኔዎች ኅብረት ሥራ ማህበራትን የማይጎዱ እና ከኅብረት ሥራ ማህበራት ህጋዊ መብቶች ጋር የማይቃረኑ እንዲሆኑ ባለድርሻ አካላት በየደረጃው ካሉ የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት ጋር ተቀናጅተው እና ተናበው ይሰራሉ፡፡

ኅብረት ሥራ ማህበራትን በሚመለከት በተለያዩ ሴክተሮች የወጡ የህግ ማዕቀፎችና ከህጎቹ የመነጩ መብቶችን ወደ አንድ በማሰባሰብ ኅብረት ሥራ ማህበራትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በአግባቡ ተረድተው በስራ ሰነድነት እንዲጠቀሙት ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ህጋዊ መብቶች በአግባቡ መተግበራቸውን ለማረጋገጥና በአፈጻጸም ሂደት ያሉ ማነቆዎችን እየለዩ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመፍታት የጋራ የአፈጻጸም ግምገማ ስርዓትና የምክክር መድረኮች በየደረጃው ባሉ የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት እና ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በመቀናጀት እየተዘጋጀ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### አቅም ገንቢዎች ድጋፍና ሚና፡-

የኅብረት ሥራ ልማትን የሚደግፉ አቅም ገንቢዎች በቀጣይ የሚያደርጉት ድጋፍ ችግር ፈቺ እና የሚፈለገውን ውጤት እንዲያስመዘግብ አቅም ገንቢዎች የትኛውንም ድጋፍ ከማድረጋቸው አስቀድሞ በየደረጃው ከሚገኙ የኅብረት ሥራ

ማደራጃና ቁጥጥር አካላት፣ ድጋፍ ከሚደረግላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በቅንጅት መሰረታዊ ችግሮችን በጥናት እየለዩ የጋራ ስምምነት የተደረሰባቸው የጥናት ውጤቶች የሚተገበሩበት የአሰራር አቅጣጫ ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የሚደረገው የአቅም ግንባታ ድጋፍ ችግር ፈቺ እና ጠባቂነትን በማስወደግ የኅብረት ሥራ ማህበራት ቀጣይነት የሚያረጋግጥ እንዲሆን በጋራ የማቀድ፣ በጋራ የመተግበርና የመገምገም አሰራር ተዘርግቶ በትኩረት ይተገበራል፡፡

## 9.2. የኅብረት ሥራ ማህበራት ማህበራዊ አስታወጽዖ፣

**የኅብረት ሥራ ማህበራት ማህበራዊ አስተዋጽኦን ማሳደግ፡-** የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሳተፉባቸው ማህበራዊ አገልግሎት የአካባቢውን መሰረታዊ ችግር ያገናዘበ፣ በአባላት ሙሉ እውቅና የጸደቀና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ስምምነት የተደረሰበት ሆኖ በዋናነት በትምህርትና ጤና ተቋማት ግንባታና የውስጥ አደረጃጀት ማሟላት፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የሙብራት አቅርቦት፣ የመንገድና ድልድይ ስራ፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች እንክብካቤ፣ ወላጅ አጥ ህጻናትና የአባላት ልጆች በትምህርት ተግባራትን እንደመነሻ በመውሰድ እንደየአካባቢው ተጨባች ሁኔታ እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ አመራርና አባላት እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ማህበራዊ ተሳትፎ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት የስልጠና ሰነዶች ተዘጋጅተው ተከታታይ የግንዛቤ ማሳደጊያ እና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚከናወኑ የማህበራዊ ልማት ተግባራትን የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮች፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት፣ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች፣ ማህበራዊ አገልግሎቱን የሚያስፈጽሙ ሌሎች ባለድርሻ አካላት፣ የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት በቅድሚያ አውቀው መሳተፍና በቅንጅት እንዲመሩ ይደረጋል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት ለተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት በግዢ የሚቀርቡ ግብዓቶች አስፈላጊነታቸው ከተቋማቱ ጋር በጋራ ተለይተው ስምምነት የተደረሰባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

በመሆኑም በኅብረት ሥራ ማህበራት ለማህበራዊ አገልግሎት የሚመደብ በጀት ለታለመት ዓላማ ብቻ እንዲውል ለማስቻል፣ በየአቅጣጫው በኅብረት ሥራ ማህበራት የማህበራዊ ተሳትፎ ተግባራት ላይ የሚታዩ ጣልቃ ገብነትንና በማህበራዊ ልማት ስበብ የሚፈጠር ምዝበራና ብክነትን ለማስቀረት፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት ማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ ቀጣይነት ያለው የአባላት፣ የአመራር አካላት እና የመንግስት ድጋፍ፣ ክትትልናየቁጥጥር ስራዎች ተጠናክረው ይተገበራሉ፡፡

DRAFT

የኅብረት ሥራ ማህበራት የማህበራዊ አገልግሎት ስራዎች በተቀመጠላቸው የአሰራር ስርዓቶች መሰረት መተግበራቸውን ለማረጋገጥና በአሰራር ሂደት የሚያጋጥሙ የአሰራር ውስንነቶችን ለማረም የኅብረት ሥራ ማህበራት የአፈጻጸም ሪፖርት እየቀረበ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የሚገመገምበት የጋራ ምክክር መድረክ በየደረጃው ባሉ የኅብረት ስራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት እየተዘጋጀ ይተገበራል፡፡

## 9.3. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ተሳትፎ

የኅብረት ሥራ ማህበራት ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ የሚያደርጉትን ተሳትፎ ለማሻሻል፤ የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራርና አባላትን፣ የማደራጃና ቁጥጥር እና ባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ ለማሳደግ ኅብረት ሥራ ማህበራት በዘርፈ ብዙ ተግባራት ላይ ስልጠና ይሰጣል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን ከማህበራዊ ተሳትፎ ተግባሮቻቸው ጋር አስተሳስሮ የሚተገበሩበትና ለዘርፈ ብዙ ጉዳዮች እንቅስቃሴ ከማህበራዊ ተሳትፎ በጀታቸው እንደየአቅማቸው በመመደብ ሊያከናውኑ የሚችሉበት ግልጽ የአሰራር መመሪያ በማደራጃና ቁጥጥር አካላት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት የሴቶችና ወጣቶች የአባልነትና አመራርነት ተሳትፎ እና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት አሁን ያለበት ደረጃ በጥናት ይለያል፡፡ ሴቶችና ወጣቶች በኅብረት ሥራ ማህበራት በአባልነት እና አመራርነት በስፋት እንዲሳተፉና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ስለ ኅብረት ሥራ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ሴቶችና ወጣቶች ተኮር የስልጠና ሰነዶችና የአደረጃጀት ማኑዋሎች እየተዘጋጁ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫና የስራ ባህል ማሳደጊያ ስልጠናዎች በተከታታይ ይሰጣሉ፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራት የሴቶችና ወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚያግዙ ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች እየተቀረጹ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

ለኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት እና አመራሮች ስለ አካባቢ ጥበቃና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ጠቀሜታ እና አስፈላጊነት ላይ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎች በስፋት ይሰራሉ፡፡ የአካባቢ ጥበቃና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ተግባር የኅብረት ሥራ ማህበራት የዕቅድ አካል ሆኖ እንዲተገበር የሚያስችሉ አሰራሮች ተዘርግተው ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

በደን ልማትና ሌሎች የተፈጥሮ ሃብት ልማት ስራዎች ላይ ተደራጅተው በማልማት እና በመንከባከብ የሚጠቀሙ የኅብረት ሥራ ማህበራት አጠቃቀማቸው የአየር ንብረትን በማይበክል ሁኔታ ሆኖ መልሶ የመጠቀምና የመተካት ስትራቴጂን እንዲከተሉ በማድረግ በአካባቢ ጥበቃ ተግባራት ከሚገኘው ጥቅም ለአብነት እንደ ካርቦን ንግድ አይነት ጥቅሞችን እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

በየአካባቢው ያሉ አካል ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንና ወላጅ አጥ ህጻናት በኅብረት ሥራ ማህበራት ተጠቃሚ ሊሆኑባቸው የሚችሉ የስራ መስኮች በጥናት በመለየት የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮችና አባላት ተግባሩን በእቅድ ይዘው እንዲተገበሩ ይሰራል፡፡

ኅብረት ሥራ ማህበራትና አቅም ገንቢዎች በጋራ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ በኅብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው ሊሰሩ ለሚችሉ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን የመነሻ ካፒታልና ሌሎች የሙያ ስልጠናዎችን በማግኘት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፡፡ ለዚህም በየደረጃው ያሉ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው ቀጣይነት ያለው የድጋፍና ክትትል ስራዎችን ይሰራሉ፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት መደራጀት የማይችሉ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞችና ወላጅ አጥ ህጻናትን ኅብረት ሥራ ማህበራት ከማህበራዊ ፈንዳቸው በጀት በመመደብና የዕቅዳቸው አካል በማድረግ እንዲደግፉ ለኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮችና አባላት የግንዛቤ ማሰደጊያ ስራዎች ይሰራሉ፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚያካሄዷቸው የምክክር መድረኮች እና ልዩ ልዩ ጉባኤዎች ስለተላላፊ በሽታዎች ቅድመ መከላከል ስትራቴጂዎች እና ስለ ስነ ምግብ ጽንሰ ሃሳብና ጠቀሜታ ተከታታይ ትምህርትና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ይሰጣሉ፡፡ ለዚህም ተግባሩን በባለቤትነት የሚያስፈጽሙ መንግስታዊ አካላት እና በዘርፉ የተሰማሩ አቅም ገንቢዎች በየደረጃው ካሉ የኅብረት ሥራ ማደራጃና ቁጥጥር አካላት ጋር በመቀናጀት ተከታታይ የአቅም ግንባታ፣ የድጋፍ እና ክትትል ስራዎችን ይሰራሉ፡፡

## የስትራቴጂው የማስፈጸሚያ ስልቶች እና ክትትልና ግምገማ ስርዓት

### 1. የማስፈጸሚያ ስልቶች፡-

#### 1.1. የኅብረት ሥራ ሴክተር ኮሚዩኒኬሽን እና የሕዝብ ግንኙነት አሰራርን ማጠናከር

የኅብረት ሥራ ሴክተር የሕብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚሰራ ተቋም እንደመሆኑ በርካታ አካላት ከሴክተሩ የሚፈልጓቸው መረጃዎች አሉ፡፡ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች እና ተቋማት የኅብረት ሥራ ማህበራት ለገበያ የሚያቀርቧቸው የተለያዩ ምርቶችን ለመገበያየት፣ የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች ለመጠቀም፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚፈልጓቸውን የፍጆታ ምርቶች እና አገልግሎቶችን ለማቅረብ በርካታ ጠቃሚ መረጃዎችን ከሴክተሩ ይፈልጋሉ፡፡

ተጠቃሚዎች እነዚህን ምርቶች እና አገልግሎቶችን ትክክለኛ መረጃ አግኝቶ ለመገበያየት እና ለመለዋወጥ እንዲችሉ የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም መረጃዎችን ለሕብረተሰብ የማስተላለፍ ተግበራት በኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት

እና በኅብረት ሥራ ማህበራት በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡ በየደረጃው ያሉ የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ድህረ-ገጾችን በመዘርጋት፣ ማህበራዊ ሚዲያ በመክፈት፣ የኤለክትሮንክስ እና የሂትመት ሚዲያዎችን በመጠቀም የሴክቴሩን የሥራ እንቅስቃሴ ለተጠቃሚዎች በማቅረብ ላይ ይገኛሉ፡፡

በግብይታቸው ጠንካራ አቅም የፈጠሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት የራሳቸውን ዲህረ-ገጽ በማዘርጋት እና የተለያዩ የኤለክትሮንክስ እና ህትሜት ሚዲያዎችን በመጠቀም ምርት እና አገልግሎቶቻቸውን ለተጠቃሚው የማስተዋወቅ ተግባር ተጀምሯል፡፡ ሆኖም በኅብረት ሥራ ሴክተር ውስጥ እየተከናወኑ ያሉ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እና ጠቃሚ የሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት መረጃዎችን በተደራጀ እና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለተጠቃሚው እንዲደርስ ለማድረግ እየተሰራ ያለ ሥራ የተጠናከረ ባለመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት አለበት፡፡

በየደረጃው የሚገኘው ኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎችን ለማጠናከር ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡ በኅብረት ሥራ ሴክተሩ ውስጥ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን እና ጠቃሚ የሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት መረጃዎችን ጥራት እና ወቅታዊነት ጠብቆ ለሕብረተሰቡ እንዲደርስ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ምርትና አገልግሎት፣ የገበያ ዋጋ፣ የምርት ዓይነትና ጥራት፣ የአየር ሁኔታ እና አጠቃላይ መረጃዎችን በማደራጀት እና በመተንተን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመንግስት እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ይሰራጫል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት ምርትና አገልግሎቶቻቸውን ለተጠቃሚው እንዲያስተዋውቁ ለማድረግ ተከታታይነት ያለው የኅብረት ሥራ ማህበራት ኤግዚብሽን፣ ባዛርና ስምፖዚየሞች በራሳቸው እንዲዘጋጁ አስፈላጊው ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡ በኅብረት ሥራ ማህበራትና እና በሸማቾች መካከል ቀጣይነት ያለው ግብይት ትስስር እንዲኖር ለማድረግ የማስተዋወቅያ እና ግንዛቤ ማሳደጊያ መድረኮች እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡

የተለያዩ ዓይነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶችና ሚዲያዎችን በመጠቀም ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት አስፈላጊነት፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታ፣ የኅብረት ሥራ ፅንሰ-ሃሳቦች፣ ትርጉም፣ ዓላማ፣ እሴቶች እና መርሆዎችን ለሕብረተሰቡ፣ በየደረጃ ለሚገኙ አመራር አካላት እና ለሌሎች እንዲቀርብ በማድረግ ግንዛቤ የማሳደግ ሥራ ተጠናክሮ ይሰራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሕብረተሰቡ ያላቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ ከመሠረቱ ለማስረጽ በየትምህርት ቤቶች የኅብረት ሥራ ክበባትን በስፋት በማቋቋም ግንዛቤን የማሳደግ ተግባር በቀጣይነት ተጠናክሮ ይሰራል፡፡ የኅብረት ሥራ ሴክተሩ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ በማተኮር ለሕዝቡ መልዕክት የሚያስተላልፍ ራሱን የቻለ የሬዲዮና ቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ተከፍቶ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

በተጨመሪም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽኖች እና ዩኒዬኖች የራሳቸውን እና የአባላትን ምርቶች እና አገልግሎቶችን በማስተዋወቅ ላይ ተቀናጅተው እና ተጠናክሮ እንዲሰሩ የሚያደርግ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሕዝብ ግንኙነት ሥራቸው ትኩረት በመስጠት ብቁ ባለሙያዎችን በመቅጠር እንዲያሰሩ ይደረጋል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደየእድገት ደረጃቸው የራሳቸውን ሚዲያ እንዲኖራቸው የሚያደርግ አሰራር ይዘረጋል፡፡

የኅብረት ሥራ ሊግ አጠቃላይ የአገርቱን የኅብረት ሥራ ማህበራት የገጽታ ግንባታ ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት አገር አቀፋዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግንኙነቶችን እንዲያደርግ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የኅብረት ሥራ ሊግ የአገርቱን የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴ፣ የእድገት አቅጣጫ፣ የሉባቸውን ችግሮች በማደራጀት እና በመተንተን በአገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ የመገናኛ አውታሮችን (ኤለክትሮንክስና ህትመት ሚዲያ) በመጠቀም የገጽታ ግንባታ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት አቅም ገንቢ አካላት ለኅብረት ሥራ ሕዝብ ግንኙነት ሥራ ትኩረት በመስጠት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

## 1.2. የፈጻሚ እና አስፈጻሚ አካላትን ግንዛቤ ማሳደግ

ስትራቴጅውን ለማስፈጸም እንዲቻል በየደረጃው የሚገኙ ቁልፍ ፈጻሚ፣ አስፈጻሚ እና ባለድርሻ አካላት የሚኖራቸው ተግባር እና ኃላፊነት በዝርዝር ተቀምጧል፡፡ በስትራቴጅው የተለዩ ዋና ዋና የኅብረት ሥራ ሴክተር ማነቆዎችን ለመቅረፍ እና የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ እንዲቻል የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት፣ ባለድርሻ አካላት፣ አቅም ገንቢዎች እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ተቀናጅተው እና ትኩት ሰጥቶ ተግባርና ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ፡፡

የተቀመጡ ዝርዝር ስትራቴጅያዊ የመፍትሄ ሃሳቦች በአንድ ጊዜ የሚተገበሩ ሳይሆን በሚቀጥለው 15 ዓመታት ውስጥ በተቀመጠው መሰረት በየምዕራፉ ተከፋፍሎ የሚተገበር ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረት በየምዕራፎቹ የሚተገበሩ ዋና ዋና ተግባራት እርስ በርሳቸው የሚመጋገቡ በመሆናቸው ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት በየቅደም ተከተላቸው እንዲከናወኑ በማድረግ ይሆናል፡፡

በመሆኑም የኅብረት ሥራ ማህበራት በቁጥርም ሆነ በዓይነት በከፍተኛ ደረጃ እጨመሩ መምጣት፣ የአባላት ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ማደግ፣ የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ማለትም የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ግብይት ድርሻ እያደገ መምጣት ፣ እሴት መጨመር፣ አግሮ ፐሮሰሲንግ፣ ሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት መስፋፋት፣ የቁጠባ፣ የብድር እና የፍጆታ ምርቶች አቅርቦት በከፍተኛ ደረጃ በማደግ ላይ ይገኛል፡፡ ይህን ዕድገትና ለውጥ ሊመራ የሚችል ጠንካራ

አደረጃጀት፣ የሰው ኃይል፣ አሰራር እና ሌሎች አስፈላጊ ግብዓቶችን በማሟላት የሴክተሩን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም መገንባት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡

በዚህ መሠረት የማስፈጸሚያ ስልቶቹ መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

**የግንዛቤ መፍጠሪያ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት፡-** የውይይት መድረኩ በዋናነት የሚያተኩረው ከኅብረት ሥራ ማህበራት፣ ከኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት፣ በየደረጃ ካሉት የመንግስት አካላት፣ ዩኒቨርስቲዎች፣ ከተለያዩ ባለድርሻ እና አቅም ገንቢ አካላት እና ሌሎች ወሳኝ ከሆኑ ተቋማት ጋር የሚደረግ ይሆናል፡፡

**በስትራቴጅው ላይ ግንዛቤዎችን መስጠት፡-** የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራት የሚያተኩሩት በዋናነት ለኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት፣ አመራር አካላት፣ ቅጥር ሰራተኞች፣ በየደረጃው የሚገኙ አስፈጻሚ እና ፈጻሚ አካላት ተከታታይነት ያለው ስልጠናዎችን በመስጠት ይሆናል፡፡

**ለሥራው ስኬታማነት የሚያግዙ አሰራሮችን መዘርጋት፡-** ስትራቴጅውን ሳይንጠባጠብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ የሕግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት እና ማሻሻል፣ አስፈላጊ የሆኑ የአሰራር ስርዓቶችን በመዘርጋት፣ አደረጃጀቶችን በመዘርጋት እና በማጠናከር የሚሰራ ይሆናል፡፡

**ስትራቴጅውን የሚደግፉ ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን መንደፍ፡-** ለስትራቴጅው መሳለጥ አስፈላጊ የሆኑ የሕግ ማዕቀፎች፣ የተለያዩ አሰራሮች፣ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች እና ሌሎች የማስፈጸሚያ ስልቶች ተዘጋጅቶ ይተገበራሉ፡፡ በዚህ መሠረት ለአቅም ግንባታ ተግባራት፣ ለግብይት ማስፈጸሚያ፣ ለመሰረተ ልማት ግንባታ እና ዝርጋታ እና ኢንቨስትሜንትን የሚደግፉ የተለያዩ ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን በመንደፍ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

**የግንኙነት ስርዓትን በመዘርጋት፡-** የስትራቴጅ አፈጻጸም የሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው መረጃዎችን በመለዋወጥ፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት የሚተገበር ይሆናል፡፡ የስትራቴጅውን አፈጻጸም በተመለከተ መንግስት፣ ባድርሻ አካላት፣ አቅም ገንቢዎች እና ኅብረት ሥራ ማህበራት በየጊዜው ተገናኝተው አፈጻጸሙን እየገመገሙ የሚታዩ ችግሮች በወቅቱ እንዲፈቱ አቅጣጫ በማስቀመጥ የሚተገበር ይሆናል፡፡

## 2. ክትትልና ግምገማ ስርዓት፡-

በኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጅ አፈጻጸሚ የሚመለከታቸው መንግስት፣ የኅብረት ሥራ ማደራጃ እና ቁጥጥር አካላት እና የኅብረት ሥራ ሊግ አፈጻጸሙን በተመለከተ በየጊዜው ክትትል እና ግምገማ ያደርጋሉ፡፡ ለክትትል እና ግምገማ የሚያግዝ ስርዓት በመዘርጋት እንድገመገም ይደረጋል፡፡ በዚህም መሠረት በየምዕራፉ የኅብረት ሥራ ልማት ስትራቴጅውን አፈጻጸም የሚገመግም ቡድን በማደራጀት በአፈጻጸም ውስጥ የታዩ ክፍተቶችን በጥናት እንዲለይ

ይደረጋል፡፡ በተገኘው የጥናት ውጤት መሠረት ስትራቴጅው ለሚመለከተው አካል ቀርቦ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማድረግ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡

# ማጣቀሻዎች


1. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የገጠር እና የግብርና ፖሊሲዎች እና ስትራቴጅዎች (1994 ዓ.ም)
2. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጅ (1994 ዓ.ም)
3. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የማስፈጸም አቅም ግንባታ ስትራቴጅና ፕሮግራሞች (1994 ዓ.ም)
4. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የውጭ ጉዳይና አገራዊ ደህንነት ፖሊስና ስትራቴጅ (1995 ዓ.ም)
5. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የግብርና ኅብረት ሥራ ዘርፍ ልማት ስትራቴጅ (2004 ዓ.ም)
6. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት ግብርና ኤክስቴንሽን ስትራቴጅ (2010 ዓ.ም)
7. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚንስቴር ብሔራዊ የሆርትካልቸር ልማትና ግብይት ስራቴጅ (2010 ዓ.ም)
8. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚንስቴር የገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራ ስትራቴጅ (2009 ዓ.ም)
9. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት ብሔራዊ የሥራ ዕድል ፈጠራ ፖሊሲና ስትራቴጅ (2002 ዓ.ም)
10. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የሁለተኛ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2007 - 2012 ዓ.ም)
11. የኅብረት ሥራ ሴክተር የሁለተኛ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2007- 2012 ዓ.ም)
12. የኅብረት ሥራ ሴክተር የውጤት ተኮር ዕቅድ ከ2007 - 2012 ዓ.ም
13. የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ እንቅስቃሴ፣ ተሞክሮዎች፣ ማነቆዎችና የቀጣይ አቅጣጫዎች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አመራሮች የተዘጋጀ የኅብረት ሥራ የንቅናቄ ስልጠና ሰነድ (2008 ዓ.ም)
14. በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አገራዊ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሰነድ (2009 ዓ.ም)
15. በኢልኒኖ ምክንያት በአገሪቷ የተከሰተው ድርቅ ለመቋቋም የምግብ ሰብል ግብይት ትስስር ንቅናቄ በኅብረት ሥራ ማህበራት ለማካሄድ የተዘጋጀ የንቅናቄ ሰነድ (2008 ዓ.ም)
16. የፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የ2009 ዓ.ም ዓመታዊ ሪፖርት፣
17. ፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የአነስተኛ መድን ዋስትና የሥልጠና እና የትግበራ ማኑዋል (2009 ዓ.ም)
18. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የኅብረት ሥራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 274/94 ዓ.ም፣


DRAFT

19. የኤ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የኅብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 895/2009፣
20. ILO & ICA –Cooperative sustainable development goal (2015 G.C)
21. Guidline for cooperative legestilation (Hagen Henry)
22. Indial national policy of cooperative (2001 G.C)
23. The cooperative development policy for south Africa (2004 G.C)
24. The repubilic of Uganda national cooperative development policy (2009 G.C)
25. The united republic of Tanzania cooperative policy (1997 G.C)
26. https://ica.coop/en/co-operative-facts-figures/global-co-operative-statistics
27. http://www.woccu.org/impact/global_reach/statreport
28. http://www.ilo.org/global/lang--en/index.htm

DRAFT